የቤተክርስቲያን ማፈያዎች

በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ

ያልተነገሩ፣ አስፈሪና አስደንጋጭ እውነታዎች



ትርጉም
ሀኒም ኤልያስ

አርትኦት
ተክሉ ጥላሁን
(የጭን ቁስል መጽሐፍ ጸሐፊ)

@Amharicbookstore

የቤተክርስቲያን ማፈያዎች

ሄኖክ ሳህሉ
ተፋቲህ

ሀያሚ መጻሕፍት
መፈጸሚያ

... ከዚያ ተአምር ሰሪው መጥቶ ደበልደና ስቢተክርስቲያን አባላት እግዚአብሔር ይህ ምሽት የተቀደሰ ምሽት መሆኑን እንደነገረው ገልጾ "መልአኩ ሚካኤል መጥቶ ይባርከናል::" ደሳል:: የመልአኩ ሚካኤል ገበኝነ በሚባለው ጊዜ ያልተሰመዳ ተአምራት ደሰራስ፣ ምን አይነት ተአምራት ይሆን?

አታላዩ ዲያቢሎስ፣ ስአታላይ የኃይማኖተ አባቶች ገንዘብ በሚሰጠ ክርስቲያናች ተከበቦ፣ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን መሀል ሳይ በመቀም የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እያታለለ ነው...

ከመጽሐፉ የተወሰደ



ይህ መጽሐፍ በኃይማኖት ስምና ሽፋን የሚሰራውን ደብቅ ስራ በግልፅ የሚያሳይ ነው:: ጽሐፊው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እሱ እራሱ ሲሰራው የነበረውንና ሲሱችም የሚሰሩትን የወንብድና ስራዎች በግልፅ አውጥቶ ያሳየናል:: የተደበቁ፣ ያልተነገሩ አስደንጋጭ እውነታዎችን ይዘረገፋል:: ያስፈበትን፣ የሞከረውን፣ የናረበትን እውነት ይተርካል::

መጽሐፉን ካነበቡ በኋላ፣ ዛሬ በአንዳንድ ቤተ ክርስትያናት ውስጥ የሚካሄዱ አብዛኞች ነገሮች የሚስጥራዊ ማህበራት ተፅዕና ያስባቸው እንደሆኑ ይረዳሉ::

ይህ መጽሐፍ ዛሬ በቤተክርስትያን ውስጥ በሚደረግ የትናውም የህሰት ትምህርት ከመታለል እንዲድን አደንዎትን የሚከፍት ነው!!!

BOOK LAND
0922748282

ዋጋ 160.00 ብር ብቻ
ሙት ስልሳ ብር ብቻ

℗ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
© All Rights Reserved

© መብቱ ሙሉ በሙሉ የተከለሉ ጥላሁን ነው።
የመጀመሪያ ዕትም መጋቢት 2012 ዓ.ም.

CHURCH MAFIA
Makhado Sinthumule Ramabulana

የሀኒም ኤልያስ ሥራዎች

- የሕይወት መመሪያ
- የጣሪያ ስር እበቦች
- ኦሪጅን
- የዶሮ መረቅ ለነብሴ
- ባይብል ኮድ 1
- ባይብል ኮድ 2
- ባይብል ኮድ 3
- በጥበብ የመኖር ዕሴት

የተከለሉ ጥላሁን ቀደምት ሥራዎች

- የጭን ቁስል
- ጀንሆይን ማን ገደላቸው
- የቀን ጨለማ
- ከስኬት በስተጀርባ
- ያልሰከነ ዜማ
- የሎጥ መንገድ
- ያልተዘመረላቸው ጀግኖች
- ዲዚዲራታ
- የስኬት መንገዶች
- ትላንትን ሳስታውስ

ቡክ ላንድ አሳታሚና አከፋፋይ

0922 74 02 02 / 0930 08 33 08

ማስታወሻነቱ

ጊዜዋንና ገንዘቧን መስዋት አድርጋ የእንግሊዘኛ መፅሐፉን ከአሜሪካ ገዝታ ለላከችልንና ሁሌም የስራችን ደጋፊና ብርታት ለሆነችው፡-

ለሚስጥር ፍስሐ ጌራ

እንዲሁም መልካምነቷ በስራችን ሁሉ ላይ ለተገለጠውና ለዚህ መጽሐፍ መታተም ከፍተኛ ድጋፍ ላደረገችው፡-

ሰላማዊት ሙሉቀን መኪንንት

በተጨማሪም የእንግሊዘኛ መጽሐፉን ለጠቆመን ለወዳጃችን፡-

ምንዳ አባይነህ መካሻ

ከልብ የሆነው ይህ ስጦታችን ለእናንተ ማስታወሻ ይሁንልን።

@Amharicbookstore

ማውጫ

እንደ መንደርደሪያ 10

መግቢያ 11

ምዕራፍ አንድ

በልጅነቴ

ልደትና ዳራ 14

የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ስርዓት 16

የመሰቀሉ ምሽት የፀሎት አገልግሎት (የምሽት ንቃት) 19

መንፈሳዊ አጥበት 22

ምዕራፍ ሁለት

መንፈሳዊ ጉዞ

ዳራ 26

በልጅነት የክርስቲያን አሴቶችን መማር 27

የፓስተሩ ልጆች 30

እንደ ልጅ መሰየት 30

ምዕራፍ ሦስት

ህይወት ከመፀሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በኋላ

የመጀመሪያ ልምምድ 33

ከመፅ፡ፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በኋላ ቤተክርስቲያን ስለመትከል 36

ምዕራፍ አራት

ኃይላት

መጋቢነት በሾሻንጉቪ 40

በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሰ ገፊት 44

ስለ ኃይላት መጠየቅ 50

ምዕራፍ አምስት

ናይጄሪያ

ወደ ናይጄሪያ ስመሄድ መዘጋጀት 54

ናይጄሪያ መድረስ 56

ሴጉስ ውስጥ የነበረኝ ጊዜ 58

የካህናት አምልኮ 59

ፕቅፕቅ ወዳስው ጫካ ጉዞ 62

የጾኮምቦ ኃይል 63

የብረት፡ የነጉድጓድ፡ የመብረቅና የውሀ አማልክት 66

መንፈሳዊ አባት ወይም `አባቴ` 70

አባልነት 72

ሰዎችን መሳብ 73

ምዕራፍ ስድስት

ዚምባቡዌ ቺፒንግ

ምስጋናና አምልኮ በቴምቢሳ 79

ከዚምባቡዋያዊው ነቢይ ጋር የገል ንግግር 81

@Amharicbookstore

ቺፒንግ መድረስ 83

ምዕራፍ ሰባት

ሞዛምቢክ

በጠንቂይ የተቀደሰ ስፍራ 88
ሞዛምቢክ መድረስ 92
የአስራ ሁለት አመተ አድሚ ያሳት ሚስት 96
የስርዓቱ ክብረ በዓል 99
መናፍስቶችን መሰየም (አሳትና ጋይል) 101

ምዕራፍ ስምንት

ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጐ

ኮንጐ ውስጥ ባስ ደሴት ላይ 104
ቤተክርስቲያን ውስጥ ፕንቶላ ማካሄድ 106
ከባባ ፍራንሲስና ከጠንቂዮቹ ጋር መገናኘት 107
ከማምባውቱ ጋር ቀጠሮ 111
ተአምራዊ ገንዘብ 115

ምዕራፍ ዘጠኝ

አንዲት አንደተጀመረ

ከናይጄሪያ መመለስ 121
የአሀድ አገልግሎት 124
የመታወቂያ ቁጥርና የመኪና ታርጋ 126
የተአምራዊ ገንዘብ ክወናዎች 127
የአዳ ማማክር ክንውን 129
የስራ ቃሉ መጠይቅ ክንውን 130
የፅሁፍ መልዕክት፣ የዘመድ አዝማድ ግንኙነት ዝርዝርና ትንቢቶች 130
የህይወት አጋር የማገኝት ትንቢት 131
አባቦች፣ አሳና ሴሎች እንገዳ ነገርችን ማስመለስ 131
የራዕይ ዘይት 132
ከታሳላቅ ስብሰባዎችና ከመለጠት በፊት መስህብ ይዘጋጻል 133
የመጀመሪያው የመስክ ሰራተኛ 137
ሁለተኛው የመስክ ሰራተኛ 140
ሶስተኛው የመስክ ሰራተኛ 141

ምዕራፍ አስር

በዶክተር ያያ አይን ውንጌልን መሸቀጥ

የገንዘብ ወጥረት 142
የራዕይ ውሀ 152
የመስጥዕት ቅዳ 156
የሚናገር ክፉ መንፈስ 156
የሀሰት ገንዘብ ጋይል 156
የፈጠስ ትምህርት ቤት (ሂሲንገ ስኩል) 157
የሁሉም ሰዎች የተአምራት ማዕከል 159
የጋዜጠኝነትና መረጻ ሰጪነት ጋይል 160

@Amharicbookstore

ምዕራፍ አስራ አንድ
የሌች አይቪ ፈውስ ማታሰያ

የገበያ ፕርግራሞች 162

ምዕራፍ አስራ ሁለት
የመናፍስት አምልኮ ያለባችውን አብያተ ክርስቲያናትን መለየት

የምስጋና አምልኮ ሀሰተኛ መንገድ 168
በሀገራችን የሚታየው የአብያተ ክርስቲያናት ፈጣን እድገት 169
የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት 170
የቤተክርስቲያን ስሞች 171
በቤተክርስቲያን አባላት ላይ ያሉ ሙሉ የመቆጣጠር ኃይል 172
ሲሱች አብያተ ክርስቲያናት የመጎብኘት አደጋ 174
ከነቢየ ጋር አንድ ለአንድ 175
ከቤተክርስቲያን የመልቀቅ አደጋ 176
ሚስጥራዊነት 177
የቤተ ክርስቲያን አባላት እጩዎች እየመሰመሱ ይሰሰጥናሉ 178
በመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም ላይ የሚውሉ 180
አደገኛ መናፍስታዊ ዕቃዎች 180
መናፍስታዊ ቀለበቶች 180
ነጭ መሀረብና ፎጣ 181
ነጩ መሀረብ 181
የተአምር ውሀ 182
ቅዱስ ዘይት 183
ልብስ፣ ፎቶና ዶክመንቶችን ወደ ነቢያት ማምጣት 184
ቁሳዊነትን መለበክ 184
ፈዋሾች በቤተክርስቲያን 186
መንፈሳዊ ማታሰያ 188
ሶስተኛው አይን በመናፍስታዊ አምልኮ 189

ምዕራፍ አስራ ሶስት
ከማዕበል በኋላ የመመለስ ሂደት

በቁጥጥር ስር መዋል 195
ማረሚያ ቤት 200
ማገገም 202
የአካባቢ መቀየር 205
ከማዕበል በኋላ ህይወት 207
ማጠቃለያ 212

@Amharicbookstore

እንደ መንደርደሪያ

ይህ መፅሐፍ የትኛውንም ኃይማኖት ወይም ቤተ-እምነት ለመተቸት የቀረበ አይደለም። ሁሉም እምነቶች የየራሳቸው ስርዓት፣ መመሪያና ህግ ያላቸው ሆነው ሳለ፣ አንዳንድ ቤተ ክርስትያናትን ከሰላ ያደረጉ መንፈሳዊ አባቶች ግን የምዕመኖቻቸውን የዋህነት በመጠቀም የራሳቸውን ጥቅም ለማካሄድ እየሰሩት ያለውን የማፍያነት ተግባር የሚያጋልጥ ነው። በተጨማሪም ሚስጥራዊ ማህበራት በቤተክርስትያን ውስጥ በድብቅ የሚሰሩትን ነገር ለማሳየት የተዘጋጀ ነው።

ከምንም በላይ ዋና አላማው ሰዎች ባለማወቅና የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሆኑ በሚቆጥሯቸው መሪዎቻቸው ከመታለል ራሳቸውን መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ ነው። ስለ እምነቶቻቸው ስርአት በትክክል በመረዳት ራሳቸውን ከአጭበርባሪዎችና የበግ ሰምድ ከለበሱ ተኩላዎች እንዲጠብቁ ማስቻል ነው።

ከዚህ መፅሐፍ ታሪክ በመነሳት የእኛ እምነት መሪዎች ፍፁማን እንደሆኑ አድርገን በመቁጠር ሌሎች ቤተ እምነቶች ላይ ጣታችንን ብንጠቁም ችግሩን ልናጠፋው አንችልም። መልኩን ይቀይር እንጂ ችግሩ በሁሉም ቤተ እምነት እንዳለ የምናውቀው የአደባባይ ሀቅ ነውና። ስለዚህ ችግሩ በእኔ ቤተ እምነት ውስጥም ሊኖር ይችላል ብሎ በማሰብ፣ አይኖቻችንን ከፍተን በየቤተ እምነቶቻችን የሚከናወኑ ነገሮችን ከአምላክ ቃል አንፃር መመዘን እንድንችል የሚረዳ ነው።

መፅሐፉ ወደ አማርኛ የተመለሰው ‹‹CHURCH MAFIA›› ከሚለው የእንግሊዘኛ መፅሐፍ ላይ ሲሆን፣ ፀሀፊው የቤተክርስትያን አገልጋይ በመሆኑ በመፅሐፉ ውስጥ ያስቀመጣቸው ነገሮች ሁሉ እርሱ በግሉ ያለፈባቸውና የተለማመዳቸው ናቸው። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ አይን ከፋች የሆነ እውነተኛ ምስክር እንደሆነ እናምናለን።

አዘጋጁቹ

መግቢያ

በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰርጉ የገባ ሚስጥራዊ የሆነ ክፉ ኃይልና ስልጣን አለ። ይህ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ጥቂቶቹ እንዴት ወደ ሌቦች ዋሻነት እንደተለወጡ ለመግለፅ ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም አሁንም ግን ጥሩ አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸውን አይክድም። የዚህ መጽሐፍ ገፆች የያዙት ጥበብ ምን ማድረግ እንደሚገባን፣ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ እንዴት አስፈላጊ መሳሪያ በመሆን የወደቁትን ቅጥሮች እንደገና እንደምንገነባ ይመራናል። የዚህ መጽሐፍ አላማ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚከናወኑ ሁሉንም አይነት የጥንቆላ አሰራሮችና ማታለያዎች በዝርዝር ማጋለጥ ነው።

በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በአንድ ወቅት ልክ እኔ እደርገው እንደነበረው አይነት በትንቢት ሽፋን የሚካሄድ ሐሰተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አለ። ይህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚሰራው ከጥልቁ ባለ ኃይል ሲሆን የሚደረገውም ብዙ ሰዎችን ለመሳብ ነው። ይህ የሐሰት መንፈሳዊ አሰራር የምክር አገልግሎት ለመስጠት ክፍያዎችን የሚጠይቅ፣ ለሰዎች ተአምራዊ ገንዘብ የሚሰጥ፣ የሐሰት ትንቢቶችን የሚያሰራጭና የመድረክ ላይ የተቀናበረ ተአምራት የሚያደርግ ሲሆን የዚህ የሐሰተኛ አሰራር መሪዎችም ዘይቶች፣ ውሀ፣ መለኮታዊ ጥበቃ የሚያስገኙ የሚባሉ ስቲከሮችንና ሌሎች ነገሮችንም በሽያጭ ያቀርባሉ።

በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ብዙ የመድረክ ላይ የተቀናበረ ተአምራት ሲካሄድ በቴሌቭዥን፣ በሬዲዮና በማህበራዊ ሚዲያ እያየን

@Amharicbookstore

ነው። ይህ የተቀናበረ ተአምራት «ፎረንሲክ ፕሮፌሲ» ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህም ነቢያቶቹ ምዕመናኑን በመታወቂያ ቁጥራቸው፣ በቤት ቁጥራቸው፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ ቁጥራቸው፣ በመኪና ታርጋቸውና በሙሉ ስማቸው በትክክል የሚጠሩበት ረቂቅ ትንቢት ነው። ሰዎችም በዚህ ፊት ለፊታቸው በሚከሰተው ሚስጥራዊ አሰራር እርዳታ እንዲያገኙ ይደረጋሉ። ነገር ግን እነዚህ የምናያቸው ትንቢቶችና ተአምራቶች እውነት ቢሆኑ ናሮ ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን ለእግዚአብሔር ሲሰጡ እንመለከት ነበር። ነገር ግን በዚያ ፈንታ እኛ አሁን ያለን ተአምራት የሚያሳድድ ትውልድ ነው። ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እውነተኛ የፀሎት ቤቶች ቢሆኑ ናሮ ክፋት እስካሁን ይጠፋ ነበር። ከዚህ በኋላም ወንጀል፣ የትዳር ችግሮች፣ የስነ ምግባር ጉድለቶች፣ የእፅና አልኮል ሱሶች ወይም ሌተኛ አዳሪነት አይኖሩም ነበር።

ሰብዙ አመታት በጨለማው አገዛዝ ውስጥ ጄኔራል ሆኜ ሳገለግል ነበር። በኃይልና በዘና እጅግ ከፍ ብዬ የነበረ ሲሆን በዚህ ኃይል የማደጌ ምክንያት ደግሞ በክፉ መናፍስት መሰዊያዎች ላይ የማያቋርጥ የእንስሳት መስዋዕት በማቅረብ ነበር። ለዚህም በእያንዳንዱ ላምንት በስምንት የጣዖት መሰዊያዎች ላይ የእንስሳት መስዋዕት አቀርብ ነበር። በዚህ የአስማታዊ አለም ውስጥ የነበረኝ መንፈሳዊ ልምምድ ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚብራራ «ካታሊፓ» የሚል አስማታዊ ስም ተሰጥቶኝም ነበር። እኔ ያለፍኩበት አስማታዊ ተሞክሮ በአሁኑ ሰአት እጅግ ብዙ አብያተ ክርስትያናትን እየተቆጣጠሩ ስላሉት ሚስጥራዊ ኃይላት የሚገልጥ አይን ከፋች ሀያው ምስክር ነው።

ከሲኦልና እነዚህን ኃይላት ለመፈለግ ከተንገዘቡባቸው ቦታዎች ያገኟቸውን ሴራዎች በመግለጫ ብዙ የጠፉና የተታለሉ ሰዎች መረዳትና መጠንቀ እንደሚችሉ አምናለሁ። ይህንን መጽሐፍ ስታነቡ፣ መዳን፣ መፈወስና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በኩል የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት እንዲሆንላችሁ እፀልያለሁ።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ አንድ

በልጅነቴ

ልደትና ዳራ

የተወለድኩት ሊምፖፖ ውስጥ በሚገኘው አሁን ፖሎክዋኔ ፕሮቪንሻል ሆስፒታል ተብሎ በሚጠራው ፒተርስበርግ ሆስፒታል ውስጥ በሻኑዋሪ 13 ቀን 1982 ነበር። ሰዎች የአዲስ አመት እቅዳቸውን በማሰብ ስራ በዝቶባቸው በነበረበት ጊዜ ላይ በራማቡላና ቤተሰብ ውስጥ ወንድ ልጅ ተወለደ። ልጁ እንደ ማርቲን ሉተር ኪንግና ኤልዚስ ፕሪስሊ ያሉ ታላላቅ ሰዎች በተወለዱበት ወር ላይ የተወለደ በመሆኑ የሀሳኑ ወላጆች የሆኑት ወጣቶች ጥንዶች ከተጋቡ ከአንድ አመት በኋላ የመጀመሪያ ወንድ ልጃቸውን ወደ አለም መምጣት ሲቀበሉ በከፍተኛ ሀሴት ተሞልተው ነበር። በድርጊት የተሞላው የጃኑዋሪ 13፣ 1982 ማለዳ ሰሲንቱ መ·ሴና ለጆይስ ማሳላ ራማቡላና በይፋ የተከበረ የእናቶችና አባቶች ቀን ነበር። እናቴ የመጀመሪያ ልጄን ስመጀመሪያ ጊዜ በእቅፏ ስትይዝ መላው የማዋለጃ

ክፍል ሁኔታ በደስታና በደማቅ ክብረ በዓል ተሞላ። እናቴ ከምጥ የተነሳ በጣም ተዳክማ የነበረች ቢሆንም፣ የታቀፈችው የደስታዎቿ ሁሉ ጥቅል የሆነውን ትንሹ ልጇን አተኩራ እያየች በከፍተኛ ሀሴት ተሞልታ ነበር። እንግዲህ እናቴ እኔን የወለደችበትን ምትሀታዊ ቅፅበትና ስመጀመሪያ ጊዜ በክንዶቿ ስታቅፈኝ የነበረውን ስሜት ሁልጊዜ የምትገልፀው በዚህ መልክ ነበር።

ከተወለድኩበት ጊዜ ጀምሮ እናቴ ልትገልፀው የማትችለው የሆነ የተለየ ነገር እንዳለኝ ታምን ነበር። እስከዛሬም ድረስ በልቧ እኔ ተራ ህፃን ሳልሆን የእግዚአብሔር ሰጦታ እንደሆንኩ ታምናለች። ስለዚህም ገና እዚያ ማዋለጃ ክፍል ውስጥ እያለች ህይወቴን ሰጌታ ለመስጠት ወሰነች። እንደተወለድኩ ገና የለቅሶዬን ድምፅ ስትሰማ ፊቷ ምንም አይነት ቃላት ሊገልፁት በማይችሉት ደስታና ፍቅር ተሞልቶ ነበር። የእግዚአብሔር ጥበቃና ሞገስ በህይወቴና በዘመኔ ሁሉ እንዲሆን ስትፀልይ ፊቷ በደስታ አምላ ርሶ ነበር።

ወደ ደረታ አስጠግታ ባቀፈችኝ ጊዜም ለቅሶዬ እንዴት እየቀነሰ እንደመጣ ነግራኝ ነበር። እኔም በዚያ የማዋለጃ ክፍል ውስጥ የፀለየችው ትልቅ ፀሎት በሆነ መንገድ ከመንፈሴ ጋር እንደተገናኘ አስባለሁ።

የራማቡላናና የሴትየዋ ቤተሰቦች በአባቱ በኩል ባለችው አያቱ ማካዶ ተብሎ የተሰየመ ወንድ በመወለዱ በጣም ተደስተው ነበር። ይህ መልካም ዜና ልክ እንደ ሰደድ እሳት ወደ ቅርብ ዘመዶቻችን በፍጥነት በመድረሱ በ19ኛኛው ክፍለ ዘመን በሲኛ ስርወ መንግስት የቬንዳ ንጉሳ መሪ በነበሩት አለቃ ማካዶ ራማቡላና ስም የተሰየመውን

@Amharicbookstore

ሀፃን ለማየት መጠበቅ አልቻሉም። ይህ ስም ተራ ስም ሳይሆን በ1898 በነበረው ምፌፋ ቦር ጦርነት ወቅት የቬንዳን ጉሳ ለመጠበቅ የተዋጋ የታላቅ ጦረኛ ስም ነው። የተወለድኩት በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ በመሆኑና አባቴ ከክርስትና ጋር የሚዛመድ ስም እንዲኖረኝ ስለፈለገ ፍሪደም ሲል ሁለተኛ ስም አወጣልኝ። አባቴ ፍሪደም የሚለውን ስም የመረጠው በጣም የሚወደውን የዚምባብዌ ተወላጅ ሚሽነሪ፣ ሙዚቀኛና ፓስተር የነበረውን ፍሪደም ሴንግዋዮን ስለሚያስታውሰው ነበር። ሟቹ ፓስተር ፍሪደም ሴንግዋዮ በ1980ዎቹና በ1990ዎቹ በነበረው የሙዚቃ ተሰጥኦ በጣም የታወቀና ዝነኛ የነበረ ሰው ስለነበረ አባቴ ይህንን ስም የሰጠኝ ዝነኛ ሙዚቀኛ ወይም ልክ እንደ ፓስተር ፍሪደም ሴንግዋዮ ፓስተር እንድሆን ምኞት ስለነበረው ይሆናል ስል ለራሴ አስባለሁ።

እኔም በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ እንደሚያድግ እንደማንኛውም ልጅ ያደግኩት በክርስትና እሴቶችና መመሪያዎች መሰረት ነበር። ወላጆቼ ገና እንደተጋቡ አባቴ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ፓስተር ሆኖ ወደሚያገለግልበት እናቴ ደግሞ በአካባቢው በሚገኝ የጫማ ሱቅ ውስጥ ወደምትሰራበት ቬንዳ ውስጥ ወደምትገኘው ቶሆያንዱ መንደር ሄዱ።

የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ስርዓት

ወላጆቼ በቤተክርስቲያን ውስጥ በነበራቸው ፕሮግራምና በሌሎች ጉዳዮች በጣም ስራ ይበዛባቸው ስለነበር ለጥቂት ጊዜ ከአያቴና ከአክስቴ ጋር እንድቆይ ስሻጉ ወደምትባል ትንሽ ከተማ ሊልኩኝ ወሰኑ። አያቴ ኮኮ በዚያን ጊዜ የቅዱስ ዮሀንስ ቤተክርስቲያን

ነብይት ነበረች። በአያቴ ዙሪያ ማደጌ ትልቅ ከሆንኩ በኋላ በራሴ መንፈሳዊ ህይወት ላይ ሚና እንዳለው የተረዳሁበት መንፈሳዊ ልምምድ ነበር። ከአያቴ ጋር በነበርኩበት ጊዜ የተለያዩ የሙዚቃ ባንዶች፣ የቤተክርስቲያን ኳየር ዘማሪዎች፣ የአፍሪካዊ ዝማሬና የሚያማምሩ የቤተክርስቲያን አልባሳት ለብሰው ለመንፈሳዊ አጥበትና ምክር የሚመጡ ሰዎችን የማየት አጋጣሚ ነበረኝ። የአያቴ ቤተክርስቲያን ከመኖሻውም በትንቢት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ትንቢት፣ መዳንና ፈውስን ጨምሮ መንፈሳዊ ምክር ፍለጋ ወደ አያቴ የሚመጡ ሰዎችን እመለከት ነበር። አንድ ቀን ሁለተኛ ቤቴ ብሎ በምጠራው በአክስቴ ሪቼል ቤት ከአነዚህ የአፍሪካ ጅማሮ ቤተክርስቲያን እገልግሎቶች እንዱን ለመታደም አጋጣሚ ያገኘሁበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። በዚያ አርብ ምሽት ሰዎች ግቢው ውስጥ በተተከለችው በትንሿ ነጭና ሰማያዊ ድንኳን ውስጥ የሚደረገውን የመስቀሉ ምሽት የፀሎት አገልግሎትን ለመካፈል ቦርሳዎቻቸውንና ብርድልብሶቻቸውን ይዘው ሲመጡ አስታውሳለሁ። አንዳንዶቹ ሰዎች ደግሞ ከሌት አያቴ የምትሰጣቸውን ቅዱስ ውሀ እንደሆነ የሚያምኑትን ውሀ ይዘው ለመሄድ አምስትና ሁለት ሊትር ፈሳሽ መያዝ የሚችሉ ባዶ ኮዳዎችን ይዘው ነበር። ሌት አያቴ "ማምሴቤሌሲ" የሚል ስያሜ የተሰጣት ሲሆን ትርጉሙም መንፈሳዊ እናት ማለት ሲሆን ነብይ ስለሆነች፣ ሰዎች እንዲፈወሱ ለምትረዳና በማማከር ጊዜም የፀሎት ጥያቄዎቻቸውን ለምታዳምጥ ሌት የሚሰጥ ስያሜ ነበር።

አክስቴ ኮኮ ሲያም ዳግም ከመወለዷ በፊት በራሷ ቤተክርስቲያን ነብይት ነበረች። ቀድሞ በነበረችበት ቤተክርስቲያን

@Amharicbookstore

እንደ ነቢይ፣ ፈዋሽና መንፈሳዊ እናት (ማምሌቤሌሊ) የምትቆጠር ነበረች። በተጨማሪም መለኮታዊ የጥበብ ቃላት የምትናገርና አስፈላጊውን የቅስና ስራዎችን እንድትሰራ የምትጠበቅ ስትሆን የእርሷ የቅስና ስራዎች ሰዎችን ከህመም፣ ከችግርና ከመሀንነት ነፃ የማውጣት ኃይል ያላቸውና የወደፊቱን የሚተነብዩ እንደሆኑ ይታመን ነበር። እርሷ በነበረችበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ምዕመናኑ ወንዶችም ሆነ ሴቶች ነቢያቶቻቸው ግማሽ ሰውና ግማሽ አምላክ የሆኑ ከፍተኛ ስልጣን ያላቸውና የተከበሩ እንደሆኑ ይታመን ነበር።

በዚያ አርብ ከሰዓት በኋላ ሰዎች በታክሲዎችና በግል መኪኖች ወደ አክስቴ ቤት መምጣት ጀመሩ። ይህንን የመስቀሉ ምሽት የፀሎት አገልግሎት ለመካፈል ከሚመጡት ሰዎች አብዛኞቹ ሴቶች ሲሆኑ እነዚህ ሴቶች ወደ ግቢው ሲገቡ የሚያምር መዝሙር እየዘመሩ ነበር። እኔም ትንሽና ነገሮችን ለማወቅ የምጓጓ ልጅ እንደመሆኔ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ዛፍ ስር ተቀምጠው አክስቴ ያዘጋጀቻውን ብስኩት እየበሉና ሻይ እየጠጡ ሲዝናኑ እኔ ቤቱ ጥግ ላይ ሆኜ እነርሱን እመለከትና ውጪ የተደረደሩትን መኪኖች አቆጥር ነበር። አክስቴ እንዴት ጠንካራ ሰራተኛ እንደነበረችና ለነዚያ ሁሉ ሰዎች የሚሆን ብስኩት እንዴት ብቻዋን ትሰራ እንደነበር አስታውሳለሁ። አሁን ትንሿ ቤታችን ሰዎች በአመት አንድ ጊዜ ለመንፈሳዊ መነቃቃትና መንፃት ስርዓት የሚመጡባት መንፈሳዊ ቦታ ሆናለች።

የመስቀሉ ምሽት የፀሎት አገልግሎት (የምሽት ጉቃት)

የመስቀሉ የምሽት የፀሎት አገልግሎታቸውን የሚጀምሩበት ጊዜ ሲደርስ እንዲት ነጭ የቤተክርስቲያን ልብስ የለበሰች አሮጊት ሴት እየዘመረችና እያጨበጨበች ወደ ድንኳኑ ስትራመድ ሁሉም ሰዎች እሷን ተከትለው ወደ ድንኳኑ ያመራሉ። ምሽት በመሆኑ ሻማዎችና ኩራዞች ይበራሉ። በድንኳኑ ውስጥ ወንበሮችና ጠረጴዛዎችም አሉ። ከሌሎቹ ተሰብሳቢዎች በደረጃ ከፍ የሚሉ መሆናቸውን ለማሳየት የተለየ ልብስ ለሚለብሱ የቤተክርስቲያን መሪዎች የተዘጋጁ ሶስት ነጫጭ ሻማዎችና ሶስት ወንበሮች ማየቴንም አስታውሳለሁ። የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች የለበሱት ልብስ የተመረጡ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። እክስቴ እኔን፣ ታናሽ ወንድሜንና የአክስቴን ልጅ ወደ ድንኳኑ ጉተታ የምታስገባን ፊታችንን በእርጥብ ጨርቅ ጠረግ አድርጋ በርከት ያለ ቫዝሊን ፊታችንንና አጊራማ እግሮቻችንን ቀብታ እንዲሁም የሚሞቅ ልብስ አልብሳን ነበር። የቤተክርስቲያን ስርዓት በሚከናወንበት ወቅት ልጆች ለመጫወት ነፃነት ስለማይኖራቸው እኔ፣ ታናሽ ወንድሜና የአክስቴ ልጅ ወንበራችን ላይ እንደተቀመጥን መቆየት ነበረብን። ምሽቱን በሙሉ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ሲዘምሩ፣ ሲጨፍሩና ሌሎቹ ደግሞ በመስቀሉ ምሽት የፀሎት አገልግሎት ላይ በሚሰራ መንፈስ ተብሎ በሚጠራ ነገር ተፅዕኖ ሲወድቁ እያየን ነበር። ሰዎች በነፃነት እንግዳ የሆኑ ድምፆች ሲያሰሙና እንግዳ የሆኑ ድርጊቶች ሲያደርጉ ስንመለከት እነዚያ ድምፆችና ድርጊቶች ጨዋታ እንደሆኑ እናስብ ስለነበር ሴት አያቴ እኛም እንድንጫወት ነፃነት ስላልሰጠችን ተናደንባት እንደነበር አስታውሳለሁ። በመጨረሻ በድካምና በመሰልቸት እንቅልፍ ወሰደን።

@Amharicbookstore

አንቅልፍ ከወሰደን በኋላ ወደ ቤት ተወስደን ስለነበር በሚቀጥለው ማለዳ ስንነቃም የቤተክርስቲያኒቱ አባላት አሁንም በዚያች ትንሽ ድንኳን ውስጥ እየዘመሩና እየጨፈሩ ነበር። ሻያችንን ከጠጣን በኋላ እኔ፣ ታናሽ ወንድሜና የአክስቴ ልጅ ወደ ጉረቤት ሄደን ለመጫወት ወሰንን። ወደ ውጪ ለመውጣት ሙሉ ሴሊት ሲዘምሩ፣ ሲጨፍሩና የእግዚአብሔርን ቃል ሲያነቡ ባደሩ መንፈሳዊ ሰዎች በተሞላችው ድንኳን አጠገብ ስናልፍ ድንኳኑ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ሰዎች በተለይም ሴቶቹ ከእግር እስከራሳቸው በአሏራ ተሰውሰው ተመለከትኩ። ነጭ የነበረው ልብሳቸው በዚያ በድንኳን ውስጥ በነበረው መንፈስ ምክንያት መሬቱ ላይ ሲንከባለሉ የነበረ በመሆኑ ወደ ቡናማ ተቀይሯል። አሁንም ንፁህና የፀዳ ልብስ እንደለበሱ በተለዩ ወንበሮች ላይ የተቀመጡት የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ብቻ ነበሩ። ድንኳኑ ውስጥ የነበሩት አብዛኞቹ ሰዎች እስኪነጋ ድረስ የምሽቱን የመንቃት ስርዓት ሲካፈሉ የቆዩ በመሆናቸው ቆሽሸው፣ ደክመውና እርቧቸው ነበር። ሲያገለግሉ ቢታዩ እንደ አመፀኞና በአጋንንት ጥቃት ስር እንደሆኑ ስለሚነገራቸው ነቅተው መቆየት ይጠበቅባቸው ነበር።

ሌሎቹ ልጆች ለመጫወት ሲሮጡ እኔ ግን በድንኳኑ ውስጥ እየተከሰተ ያለው ነገር አጓጉቶኝ ስለነበር በዚያ ለጋ እድሜዬ እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ በአእምሮዬ መዝግቤው ነበር። መዝሙሮች ከዘመሩ በኋላ ጥቂት ሰዎች በፀሎቱ ወቅት ያጋጠማቸውን ለማብራራትና ምስክርነታቸውን እንዲያካፍሉ ጊዜ ተሰጥቷቸው ነበር።ምስክርነት ከሰጡት አብዛኞቹ መንፈሳዊ እንደሆኑ የሚቆጠሩና አሁንም ነብያት ለመሆን በስልጠና ሂደት ላይ ያሉ ሴቶች

ቢሆኑም ራሳቸውን የሚያውቁ አይመስሉም ነበር። ይህ መንፈሳዊ ራስን መሳት የሚመጣው የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ሲዘምሩ፣ ሲያዜሙ ወይም መዝሙር ሲዘምሩና መሳው ተሳታፊዎች በኃይል ሲያጨበጭቡ ነው። የሞገጨባቸው ድምፅ መንፈሳዊና የሚያስፈነጥዝ ሁኔታን ይፈጥራል። በዚያን ጊዜ እነዚያ ሰዎች የመንፈሱ መገኘት ስለሚሰማቸው ያ መንፈስ በእነርሱ ላይ እንዲሰራ ይፈቅዱለታል።

ይህ መንፈስ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰራ በመሆኑ በታዳሚዎቹ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይገለፃል። ይህ መንፈስ ሰዎች ላይ ሲያርፍ ሰዎቹ ይወድቃሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ ይህንን የሚያደርገው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሆነ እርግጠኞች ስለሆኑ የሰው መንፈስ በዚህ የተለየ መንፈስ ሲያዝ ያ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገናኝ ያምናሉ።

ልጅ ሆኜ ምን እየተካሄደ እንደነበር አይገባኝም ነበር። በመንፈሳዊ ጉዞዬ እያደግኩ ስመጣ ግን በሴት አያቴ ቤት ይደረጉ የነበሩት ነገሮች ስሜት ይሰጡኝ ጀመር። በኋላ በመንፈሳዊ ህይወቴ ሁሉንም ትናንሽ ነገሮች ስሜት በሚሰጥ መልክ ማገጣጠም ጀመርኩ። ከቤተክርስቲያን ፕሮግራም በኋላ አባላት ምስክርነታቸውን ያካፍላሉ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶች ያነባሉ። የቤተክርስቲያኒቱ አባላት መፀለይ ሲጀምሩ ፀሀይ ወደምትወጣበት ወደ ምስራቅ ዞረው ሲሆን ሁሉም ሰው ከፀለየ በኋላ ከቤተክርስቲያን መሪዎች አንዱ የጉባኤውን ፀሎቶች ከፍ ለማድረግና ልመናውን በባለስልጣንነት ለማረጋገጥ አላማ ፀሎቶቹን በሙሉ በአንድ ፀሎት ያሳርጋል። ሁላችንም አይኖቻችንን ጨፍነን የቤተክርስቲያን መሪውን ፀሎት

@Amharicbookstore

እያዳመጥን ድንገት በክፍድ ድምፅ ደስ የሚል ዜማ ያለው "ሆሳዕና" የሚለውን መዝሙር ይዘምራል። መዝሙሩን ረዘም እያደረገው ሲመጣ፣ ጉባኤው ሁሉ አብሮት መዘመር ይጀምራል።

ሲዘምሩ ማንም ሰምቹ እርሷቸዋል ወይም ደኮሟቸዋል ብሎ አያስብም። ሆሳዕና የሚለው መዝሙር ካለቀ በኋላ መሪው የቡራኬ ፀሎት ያደርጋል። ልክ "አሜን" ሲሉ ሻማዎቹ ይጠፉና ሰዎች ብርድ ልብሶቻቸውንና ቦርሳዎቻቸውን ድንኳኑ ውስጥ ትተው ወንበሮቻቸውን በመያዝ በቀስታ እየተራመዱ ሻይ ወደሚቀርብበት ዝር ይሄዳሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ መንፈሳዊ እናታቸውና ነብይ እንደሆነች ከሚቆጥሯት ሴት አያቴ ጋር ሰመነጋገር ወረፋ ይይዛሉ። እነዚህ ሰዎች ሌሊቱን ሙሉ ፀሎት ስነስርዓት ላይ የነበሩትና ጥቂቶቹ ደግሞ በመንፈሱ ተፅዕኖ መሬት ላይ ወድቀው የነበሩ ናቸው።

መንፈሳዊ እጥበት

በእድሜ የገፉት ሰዎች ከድንኳኑ ከወጡ በኋላ፣ ጥቂቶቹ ቁርስ ከመብላታቸው በፊት ጥቂት ሽለብ ለማድረግ ድንኳኑ ውስጥ ይቀራሉ። እኔም ፈጠን ብዬ ለቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ተዘጋጅተው ወደነበሩት ወንበሮች እሄድና ዋናው መሪ ሲለብክና ሲፀልይ የነበረበትን ሁኔታ በመከረጅ ደግሜ ለማለት እሞክራለሁ። ድንኳኑ ውስጥ የቀሩት ጥቂት ሰዎች በመሪው እየቀለድኩ መሆኔን ሲመለከቱና ማረፍ ስለምከለክላቸው ይቆጡኝ ነበር። ከዚያ መላው ግቢ ጥቂት የተጨነቁና በጣም መንፈሳዊ የሆኑ በሚመስሉ የቤተክርስቲያን ሰዎች የተሞላ በመሆኑ ከድንኳኑ ወጥቼ ወደ ቤት ውስጥ ገባሁ። ልክ ሰገባ ሴት አያቴ በእጃቸ ነጭ ዶሮ ይዛ ወደ

መታጠቢያ ቤት ስትሄድ አየሁ። ይቺን ምስኪን ዶሮ ምን ልታደርጋት እንደሆነ ለማጣራት ልከተላት ወሰንኩ። አያቴ ወደ መታጠቢያ ቤት ገብታ በሩን ዘጋችና በመታጠቢያው ላይ ውሀ ማፍሰስ ጀመረች። ዶሮዋ ስትጮህ የሚሆነውን ለመስማት ወደ በሩ ተጠጋሁ። ልጅ ስለነበርኩ በመታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ አልገባኝም። ወደ መታጠቢያ ቤቱ በር በጣም ስጠጋ አያቴ የማማክር ስራዋን በሚስጥር እየተከታተልኩና በስውር እያዳመጥኩ መሆኔን እንዳታውቅ በመፈለጌ ልቤ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

ምንም ድምፅ ሳላሰማ በጥንቃቄ እንደተራመድኩ እርግጠኛ ነበርኩ። በትንሿ መታጠቢያ ቤታችን የተለያዩ ሰዎች ተራ በተራ እየታጠቡ ስለነበረ ወለሉ ረጥቧል። እንደኛውን ጆሮዬን በሩ ላይ ለጥፌ አያቴ ድንገት በሩን ብትከፍት መሮጥ በምችልበት ሁኔታ ላይ መሆኔን አረጋገጥኩ።

በትኩረት ሳዳምጥ የነጯ ዶሮ ድምፅ እየጠፋ መምጣቱን አስተዋልኩ። "ዶሮዋ ምን ሆና ነው?" ስል ራሴን ጠየቅኩ ግን መልስ አልነበረኝም። አያቴ ስትፀልይና የምሚ ክርስቲና ንኩን መልእክ እየጠራች ነበር። (ምሚ ክርስቲና ንኩ ባየችው ራዕይ መሰረት በ1939 ጆሀንስበርግ አቅራቢያ አስራሁለት በሮች ያሉት ትልቅ ቤተክርስቲያን የከፈተች ሴት ነበረች)። ጆሮዬን በሩ ላይ እንደለጠፍኩና ድንገት አያቴ ብትከፍት ሮጬ ለማምለጥ እንደተሰናዳሁ ሳላስበው በሩ ተከፈተና እጅ ከፍንጅ ተያዝኩ። መያዜን ሳውቅ ወዲያውኑ ፈጣን ሰበብ መጣልኝና እንደታመመ ሰው ፊቴን ክስክስ አድርጌ ሆዴን እንዳመመኝ አስመሰልኩ። እንዳትመታኝ ስለፈራሁ ሆዴን ጭብጥ

@Amharicbookstore

አድርጌ ይገር እያቃሰትኩ "አያቴ ሆዴን አሞኛል።" አልኩ። ዘዴዬ በትክክል ሰርቷል። ምክንያቱም አያቴ አዘነችልኝ እንጂ አልመታችኝም ወይም አልጮኸችብኝም። በዐላነው ብስኩት ምክንያት ያመመኝ ስለመሰላት "አይዞህ የልጄ ልጅ አሁን ደህና ትሆናለህ" አለችኝና የሞተችውን ዶሮ በአንድ እጇ አንጠልጥላ ወደ ወጥ ቤት አመራች።

አልፋኝ ስትሄድ፣ በመታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ያለው ውሀ ምን አይነት እንደሆነ ለማየት ፈጠን ብዬ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄድኩ፤ ውሀው የዶሮ ደምና የሆነ ባለቀለም ዱቄት ያለበት ቆሻሻ ነበር። እጁን ውሀው ውስጥ ስነክረው ውሀው እጅግ ቀዝቃዛ ነበር። በመታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ሶስት ነጫጭ ሻማዎችም ነበሩ። አያቴ በዚያ ቆሻሻ በሚመስል ውሀ የምትታጠብ አንዲት ሴት አስክትላ ወደ መታጠቢያ ቤቱ እየመጣች መሆኑን ሳውቅ ፈጠን ብዬ ወጣሁ። ከዚያ አያቴ ሰዚያች ሴት እየተከተላት ያለውን "መጥፎ እድል" ለማባረር እንዴት መታጠብ እንዳለባት የተለየ ትዕዛዝ ስትሰጣት ሰማሁ። ይህቺን ሴት አተኩራ ስመለከት ድንኳኑ ውስጥ ሴሊቱን ሙሉ በነበረው ፀሎት ወቅት አቧራ ላይ ሲንከባለሉ ከነበሩት ሴቶች አንዷ መሆኗን አውቄ ነበርና አያቴ የምትናገረው ሴትዮዋ ስለሰበሰችው ቆሻሻና አቧራማ ልብስ እንደሆነ አያሰብኩ ነበር።

እሞኛል ማለቴን ረስቼው እየሮጥኩ ክቤት ወጣሁ። በምችለው ፍጥነት እየሮጥኩ ጎረቤት ድብብቆሽ እየተጫወቱ የነበሩትን ታናሽ ወንድሜንና የአክስቴን ልጅ ለማግኘት ሞከርኩ። እየሮጥኩ የነበረው ጫማዬን እንዳደረግኩ ስለነበር ይህን ጮማ የሆነ ዜና በፍጥነት ለወንድሜና ለአክስቴ ልጅ እንዳላድርስ ያደረገኝ ጫማው እንደሆነ

ስለተሰማኝ ጫማዬን አውልቄ በእጄ በመያዝ በባዶ እግሬ ሩጫዬን ቀጠልኩ። እነርሱ ውጪ ሲጫወቱ እኔ መታጠቢያ ቤት ውስጥ ያየሁትን ነገር በዝርዝር ልነግራቸው ጓጉቻለሁ። ስለ ነጯ ዶሮ እያሰብኩ ስለነበር፣ በጣም ልዩ የሆነውን የቀኑን ዜና ልነግራቸው ነው። ይህንን የነጯን ዶሮ ታሪክ ሰራሁ መያዝ ስላልቻልኩ የአክስቴ ልጅ ሊያና ወንድሜ ሬንዳኒ መሰማት እንዳለባቸው ተሰምቶኛል። ስለዚህ እነርሱን መፈለግ ቀጠልኩ። አግኝቼ ታሪኩን ስነግራቸው ሁለቱም እፈጠጡብኝ። እኔም ያቺ ምስኪን ዶሮ ምን እንዳጋጠማት ሁሉንም በዝርዝር መናገር ጀመርኩ።

ታሪኩን ስነግራቸው የአክስቴ ልጅና ወንድሜ ትናንሽ እጆቻቸውን ከጉፈሮቻቸው ላይ እድርገውና አፋቸውን ከፍተው የዜናውን እያንዳንዱን ዝርዝር እያዳመጡ ነበር። በመጨረሻ የአክስቴ ልጅ የነበራት ምላሽ ‹‹አምላኬ ሆይ!›› የሚል ሲሆን ወንድሜ ደግሞ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ በሀይወቱ ሁለተኛ ዶሮ እንደማይበላ ተናገረ። የልጅነት ታሪኬን ሳወራ ሰዎች ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነት ነገሮችን እንዴት እንደዚህ በዝርዝር እንደማስታውስ ይገርማቸዋል። እኔም ሁልጊዜ "ያንን የሚያውቀው ውስጣዊ መንፈሴ ብቻ ነው።" በማለት እመልስላቸዋለሁ።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ ሁለት

መንፈሳዊ ጉዞ

ዳራ

በ1990ዎቹ ወላጆቼ በድዛሲ ጉባኤ አፖስትሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያገለግሉ ነበር። በኋላ ላይ ግን አባቴ ለነበረው ጥሪ ምላሽ በመስጠት ሊምፖፖ ውስጥ ባለ የከተማይቱ ክፍል በሚገኝ ቤተክርስቲያን ለማገልገል መሄድ ነበረበት። በመሆኑም አዲስ ወደሚያገለግልበት ጉባኤ ቀረብ ለማለት የሚኖሩበትን ቤት ለቅቀው ሌላ ቤት መከራየት ነበረባቸው። አባቴ የአያቴ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ የእኔ ወላጆች ከሚያምኑት ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ከእንግዲህ እኔ ከአያቴ ጋር መሆን እንደሌለብኝ የወሰነውም በዚህ ጊዜ ነበር። ነገሮች የተባባሱት ደግሞ እኔ ለእናቴ አያቴ ጋ ብዙ ሰዎች ለመታጠብ እንደሚመጡና እሷም ሰምን መጥታ እንደማትታጠብ በየጠቅሏት ጊዜ ነበር። መታጠብ ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ስትጠይቀኝ ለአክስቴ ልጅና ለወንድሜ የነገርኳቸውን የነጯን ዶሮ

ታሪክ ነገርኳት። እናቴ ይህንን ዜና ለአባቴ ስትነግረው፣ አባቴ ከእንግዲህ ወዲያ እኔም ሆንኩ ታናሽ ወንድሜ አያቴ ጋ መኖር እንደማንችልና ትምህርት ቤት ሲዘጋና አልፎ አልፎ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ብቻ ልንጠይቃት እንደምንችል ወሰነ። ወላጆቼ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳያቋርጡ ለአያቴ መፀለይን ሰራቸው አደረጉት። ፀሎታቸውም ከብዙ አመታት በኋላ ምላሽ አግኝቶ አያቴ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኟ አድርጋ ተቀበለች። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከሞተችበት ጊዜ ድረስ የቀደመ ልምዷን ሁሉ አርግፍ አድርጋ ተወች።

በልጅነት የክርስቲያን እሴቶችን መማር

በዚያ ለጋ እድሜዬ ከወላጆቼ ጋር ማደጌ ንፁህ የክርስቲያን እሴቶችንና ስነምግባሮችን እንድማር ስላስቻለኝ፣ ለእኔም ሆነ ለወንድሞቼ በረከት ነበር። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ወደተማርንባቸው የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንድንሄድ እንገደድ ነበር። እኔ በጣም የምወደው የዳዊትና የጎልያድን ታሪክ ነበር። እንደ ዳዊት ያለ አንድ ተራ ልጅ ጉልያድን የሚያክል ግዙፍ ሰው ማሸነፉ ያስገርመኝ ነበር። የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪያችን ዳዊት ጉልያድን ያሸነፈው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ እንደሆነ ሁልጊዜ ትነግረኝ ነበር። ይህች አስተማሪያችን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ልጆች ሊረዷቸው በሚችሉበት መንገድ ማስተማር የምትችል ነበረች። ወላጆቻችን እኛን የሚጠብቅላቸው ሰው ስላልነበራቸው በሚሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ አብረን በመሄድ ብዙ የቤተክርስቲያን ፕሮግራሞችና ስብሰባዎች እንከታተል ነበር። አንድ ምሽት እናቴ እኔንና ወንድሜን ሬንዳኒን ወደ ምሽት የቤተክርስቲያን

©Amharicbookstore

ፕሮግራም እንደወሰደችን አስታውሳለሁ። እዚህ ያለው የምሽት ፕሮግራም አያቴ ጋር ከሚካሄደው የተለየ እንደሆነ ስለማውቅ ስመሄድ አላመነታሁም። እኔና ወንድሜ ከኪቦርዱ፣ ከድራሙና ከጊታሮቹ የሚወጣውን ጣፋጭ ሙዚቃ ለመስማት ጓጉተናል። የቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች ያሉበት ቦታ መሄድ የምንወደውም ለሙዚቃው ስንል ነበር። እዚያ ስንደርስ የአምልኮ ቡድኑና የድምፅ ኢንጂነሮቹ ዋናው ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት ድምፁን እየሞከሩ ነበር። የድምፅ ኢንጂነሩ ሌሎች ማይክሮፎኖችን ለመሞከር ሲሄድ መድረኩ ላይ ወዳስቀመጠው አንድ ማይክሮፎን እየሮጥኩ ሄድኩ። እናቴ ቀደም ብለው መጥተው ኋላ ካሉት መቀመጫዎች ላይ የተቀመጡትን የቤተክርስቲያኒቱን አባላት ሰላም በማለት ተጠምዳ ነበር። እኔም እንደደረስኩ ማይክሮፎኑን ላነሳ ወንድሜ ሬንዳኒ ደግሞ ወደ ኪቦርዱ ሄደ። ማይክሮፎኑን ስይዝ ክፍት እንደሆነ አላወቅኩም ነበር። ማይክሮፎኑን በእጄ እንደያዝኩ ከመድረኩ ፊት ሰፊት ወዳሉት ባዶ ወንበሮችና ከጥቂት ሰዎች ጋር እያወራች ወዳለችው እናቴ ተመለከትኩ።

ወዲያው "እሳት እሳት" እያልኩ መጮህ ጀመርኩ። ይህ እኔና ኪቦርዱን እየነካካ ያለውን ወንድሜን በጣም አስደሰተን። ከዚያ "ሬንዳኒ ተመልከት!" ስል ጠራሁት። ወደኔ ሲመለከት ብዙ ጋስትሮች ሲያደርጉ እንደሳየሁት እኔም የምለውና የማደርገው እንደሚለው በመተማመን አሁንም ከሰዎች ጋር እያወራች የነበረችውን እናቴን ጠራኋትና "እማ የምለውን ነገር እስክ ኋላ ድረስ የሚሰማ ከሆነ መጮህ አለብሽ።" አልኳት። እሷም አየት አድርጋኝ ወሬዋን ስትቀጥል "እሳት እሳት" እያልኩ መጮሄን ቀጠልኩ። ሁሉም ወደኔ ተመለከቱና

ፀመገረም ሳቁ። እኔም የጠበቅኩትን ውጤት ባለማየቴ እፍረትና ተሰፋ መቁረጥ ቢሰማኝም ይህ "እሳት" የሚለው ቃል ከኋላ ያለችውን እናቴን እንደሚያነቃት በመጠበቅ ደግሜ "እሳት፣ እሳት" እያልኩ መጮሄን ቀጠልኩ። የእኔ ምኞት እናቴ መሬት ላይ ስትንከባለል ማየት የነበረ ቢሆንም ምንም ነገር አልተከሰተም። ያገኘሁት ብቸኛ እሳት በድምፅ ኢንጂነሩ ጆሮዬን መቆንጠጥ ነበር። ይህንን መጽሐፍ ማንበባችሁን ስትቀጥሉ "እሳት" የሚለው ቃል በእኔ አገልግሎት ውስጥ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ታያላችሁ።

ስርዓቱ ሲጀመር እኔና ወንድሜ ከፊት ባሉት መቀመጫዎች ላይ ከእናታችን ጉን ተቀመጥን። የአምልኮ ቡድኑ መዘመር ሊጀምሩ እኛም ዘመርን፣ ጨፈርን። ከዚያ የፀሎት ጊዜ ሲመጣ እኛም በተግርነው መሰረት ፀለይን፣ ስባኪዎች አቋቋማቸውንና ድምፃቸውን ሲለዋውጡ እንዳየነው ሳይቀር አደረግን። እናታችን ወለሉ ላይ ተንበርክካ መፀለይ ስትጀምር እኔም ልክ እንደሷ ተንበረከኩና አይኖቼን ጨፍኜ መናገር ጀመርኩ። ጥቂት ከቆየሁ በኋላ ለእግዚአብሔር የምለው ነገር አለቀብኝና አይኖቼን ከፍቼ ስለመለከት እናቴ አሁንም እየፀለየች ነበር። እንደተንበረከክች እምባዋ ጉንጮቿን አጥርጦ ሲፈስ ስመለከትና ድምጿ የሚያስለቅስ ሲሆንብኝ ለእርሷ ተጨንቄ ነበር።

ከፀለይንና የምሽቱን ስብከት ከሰማን በኋላ አጭር መዝሙር ተዘመረና በቡራኬ ፀሎት ስርዓቱ ተፈፀመ። ካለቀ በኋላ ሁሉም የቤተክርስቲያን አባል እርስ በርስ ሰላምታ ተሰጣጠ፣ ተቃቀፈ። ይህም ስርዓት ነበር። እኔና ወንድሜም የምንናገረው የሬንዳ ቋንቋ ብቻ

@Amharicbookstore

ስለነበርና እዚያ ላሉት ሰዎችም ሆነ ቋንቋ እንግዳ ስለነበርን፣ እናታችን በሄደችበት ሁሉ አጠገቢ መሆን ነበረብን።

የፓስተሩ ልጆች

ወደ ቤት ስንመለስ እናታችን የሚጣፍጥ ምግብ ሰርታ ወደ ወጥ ቤቱ ጠራችን። እኛም ኤሌክትሪክ ስላልነበረን በሻማ ብርሃን እየተከታተልን ወደ ወጥ ቤት ሄድን። እኔና ወንድሜ በፍቅር የተሰጠንን ሰሀን ይዘን ጨለም ወዳለው ሳሎን ተመልሰን ተቀመጥን። ምግባችንን እየበላን ሳለ አባታችን አሮጌውን የካሴት ማጫወቻ በማምጣት የሚወደውን የፓስተር ጂሚ ስዋጋርት መዝሙር ከፈተ።

ከእራት በኋላ ሻማውን ለሚቀጥለው ቀን ለማስተረፍ እንድንተኛ እንገደድ ነበር። ወላጆቻችን ጠንቋዮችና አጋንንቶች ሌሊት እንዳይረብሹን ከመተኛታችን በፊት እንድንፀልይ ያበረታቱን ነበር። እኛም ክፍላችን እንደገባን ዘለን አልጋችን ላይ እንወጣና በብርድ ልብስ ተሸፍነን እንፀልይ ነበር። የቆርቆሮው ጣራ ቀን ከፀሀይ ካገኘው ሙቀት የተነሳ ምሽቱ ሲቀዘቅዝ የሚያስማው ድምፅ ስለሚያስፈራራን "እላት የእግዚአብሔር እሳት" እያልን እንጮህ ነበር። ልጆች ሆነን አጋንንቶች ወይም ጠንቋዮች ወደቆርቆሮው ላይ ይዘላሉ ብለን ስለምናስብ በብርድ ልብስ እንሸፈንና እንቅልፍ እስኪወስደን አይናቻችንን አጥብቀን እንጨፍን ነበር።

እንደ ልጅ መለየት

አንድ ማለዳ ከእንቅልፌ ስነቃ ሌሊት ባየሁት ህልም ግራ ተጋብቼ እንደነበር አስታውሳለሁ። ወዲያው በፍጥነት እየሮጥኩ ወደ

ወላጆቼ ክፍል ገባሁና ያየሁትን ህልም ነገርኋቸው። አባቴ ህልሞችንና ራዕዮችን መፍታት ላይ ጉብዝ ነበር። ገና ትንሽ ልጅ ሳለሁ ጀምሮ የተለያዩ አይነት ህልሞች አያለሁ። አንዳንዶቹ ህልሞች ግን ግራ ያጋቡኝ ነበር።

ልጆች በመሆናችን አጋንንትም ሆነ ክፉ መናፍስት ምን እንደሆኑ አንረዳም ነበር። ነገር ግን ሁሌ ማታ ማታ የእናታችን አክስት ኮኮ ሰሊና ያስተማረችንን፣ በምሽት ከሚመጡ ከሁሉም ክፉ መናፍስት የሚከላከል መሳሪያ እንደሆነ የተነገረንን "ጌታ ሆይ ኖና ትንሽ ነኝ ልቤ ውስጥ ከኢየሱስ በስተቀር ማንም እንዳይገባ ጠብቂኝ። አሜን" የሚለውን ፀሎት እንፀልይ ነበር። በዚያ ምሽት ግን በህልሜ ራሴን በተኛሁበት ክፍል ወስጥ ተቀምጬ ማየቴን አስታውሳለሁ። አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጬ አጠገቤ ባለው መስታወት ራሴን እያየሁ ነበር።

በእይኖቼ መስታወቱን እያየሁ ድንገት በስተግራዬ በመኝታ ቤቱ በር ስር ብሩህ አንፀባራቂ ብርሃን አየሁ። ፊቴን ወደ በሩ መልሼ አፌን ከፍቼ ከበሩ ስር የሚመጣውን አንፀባራቂና ወርቃማ ብርሃን እየተመለከትኩ ሳለ ነጭ የለበሰና በሚያንፀባርቅ ብርሃን የተከበበ ሰው አየሁ። ከፊቱ፣ ከእጆቹና ከእግሮቹ ብርሃን ይፈልቃል። መላው ሰውነቱ በብርሃን ውስጥ ያለ ይመስል ነበር።

ይህ ሰው በእጁ ወርቃማ ዕዋ ይዞ ወደኔ እየተጠጋ ነበር። በህልሜ በጣም ፈርቼ የነበረ ቢሆንም በውስጤ ግን በዚህ ምስል ፍቅርና ደስታ ተሰምቶኝ ነበር። የተሰማኝ ስሜት በቃላት ሊገለፅ የማይችል በጣም የተለየ ነበር። ድንገት እይኖቼን እንደጨፈንኩ ይህ

Amharicbookstore

ሰው ወርቃማ ፈሳሽ በሞንቅላቱ ላይ አፈሰሰብኝ። በህልሜ መሮሀ ጀመርኩ። ወዲያው ሞንቅላቴን ቀና ሳደርግ ያ ምስል ወደ ቡሩ ሲመለስና ክፍሉን የሞላው ብርሃን እየደበዘዘ ሄዶ ምስሉ ተሰወረ። ከዚህ ህልም ስነቃ ፊቴ በእምባ ተሸፍኖ ነበር። ህልሙ በጣም እውን የሚመስል ነበር።

ይህንን ህልም ለወላጆቼ ስነግራቸው አባቴ ያየሁት መንፈሳዊ ህልም እንደሆነና መለኮታዊ አካል ሊቀባኝ እንደመጣ ነገረኝ። አባቴን መቀባት ምን እንደሆነ ሰጠይቀው፣ በእግዚአብሔር መንግስት ለእግዚአብሔር ስራ መመረጥ እንደሆነ ነገረኝ። ያ የአባቴ ቃል በውስጤ የሚያድግ ትልቅ ዘር ሆነ። በህልሜ ሰምቾን ሳስተምር፣ ስሰብክ ባየሁ ቁጥር ለዚህ መልካም ስራ በእግዚአብሔር የተመረጥኩ መሆኔን ያረጋግጥልኛል። እያደግኩ ስመጣ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ጠንካራ ስሜት ማዳበር ጀመርኩ። እናቴ፣ እኔና ወንድሜን ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣ ሁልጊዜ ሱፍና ከረባት ስለምታስብሰን ሰዎች በቀልድ መልክ ትንንሽ ፓስተሮች ይሉን ነበር። እኔ ግን በአባቴ ቤተክርስቲያን ያሉ ሰዎች ትንሹ ፓስተር ብለው ሲጠሩኝ መሆኔን በማመን እነዚያን ቃላት በልቤ እጠብቃቸው ነበር። ለእኔ እነዚያ ቃላት ቀልድ ሳይሆኑ በውስጤ እያደጉ የመጡ ነበሩ።

ምዕራፍ ሦስት

ህይወት ከመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በኋላ

የመጀመሪያ ልምምድ

ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በተመረቅንበት አመት አንድ ላይ እንማር ከነበርነው ልጆች አብዛኞቹ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ስራ ቦሚገባ ተዘጋጅተው ነበር። ሁላችንም አገልግሎት የሚፈልገው የኃይማኖት ትምህርት ብቃት ብቻ እንደሆነ እናስብ ስለነበር አብዛኞቹ አብረውኝ የተማሩ ልጆች ስኬታማ ቤተክርስቲያን የመገንባት ራዕይ ሰንቀው ነበር። በስሜትና በእግዚአብሔር እሳት የተሞላን ወጣቶች ስለነበርን ምድር ላይ ባለችው የክርስቶስ አካል ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ተዘጋጅተን ነበር። አብዛኞቹ አብረውኝ የተማሩ ልጆች ስራላቸው እንደ ወንጌላዊ፣ ሀዋርያና ነቢይ አይነት ማዕረጎችን መስጠት ጀምረው ነበር። ኃይማኖታዊ ትምህርታችን በሌንጌቆስጤና

@Amharicbookstore

ሰው ወርቃማ ፈላሽ በጭንቅላቴ ላይ አፈሰሰብኝ። በህልሜ መጮህ ጀመርኩ። ወዲያው ጭንቅላቴን ቀና ሳደርግ ያ ምስል ወደ በሩ ሲመለስና ክፍሉን የሞላው ብርሃን እየደበዘዘ ሄዶ ምስሉ ተሰወረ። ከዚህ ህልም ስነቃ ፊቴ በእምባ ተሸፍኖ ነበር። ህልሙ በጣም እውን የሚመስል ነበር።

ይህንን ህልም ለወላጆቼ ስነግራቸው አባቴ ያየሁት መንፈሳዊ ህልም እንደሆነና መለኮታዊ አካል ሊቀባኝ እንደመጣ ነገረኝ። አባቴን መቀባት ምን እንደሆነ ስጠይቀው፣ በእግዚአብሔር መንግስት ለእግዚአብሔር ስራ መመረጥ እንደሆነ ነገረኝ። ያ የአባቴ ቃል በውስጤ የሚያድግ ትልቅ ዘር ሆነ። በህልሜ ሰዎችን ሳስተምር፣ ስሰብክ ባየሁ ቁጥር ለዚህ መልካም ስራ በእግዚአብሔር የተመረጥኩ መሆኔን ያረጋግጥልኛል። እያደግኩ ስመጣ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ጠንካራ ስሜት ማዳበር ጀመርኩ። እናቴ፣ እኔና ወንድሜን ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣ ሁልጊዜ ሱፍና ከረባት ስለምታለብሰን ሰዎች በቀልድ መልክ ትንንሽ ፓስተሮች ይሉን ነበር። እኔ ግን በአባቴ ቤተክርስቲያን ያሉ ሰዎች ትንሹ ፓስተር ብለው ሲጠሩኝ መሆኔን በማመን እነዚያን ቃላት በልቤ አጠብቃቸው ነበር። ለእኔ እነዚያ ቃላት ቀልድ ሳይሆኑ በውስጤ እያደጉ የመጡ ነበሩ።

ምዕራፍ ሦስት

ህይወት ከመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በኋላ

የመጀመሪያ ልምምድ

ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በተመረቅንበት አመት አንድ ላይ እንማር ከነበርነው ልጆች አብዛኞቹ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ስራ በሚገባ ተዘጋጅተው ነበር። ሁላችንም አገልግሎት የሚፈልገው የኃይማኖት ትምህርት ብቃት ብቻ እንደሆነ እናስብ ስለነበር አብረውኝ የተማሩ ልጆች ስኬታማ ቤተክርስቲያን የመገንባት ራዕይ ሰንቀው ነበር። በሰሜትና በእግዚአብሔር አሳት የተምላን ወጣቶች ስለነበርን ምድር ላይ ባለችው የክርስቶስ አካል ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ተዘጋጅተን ነበር። አብዛኞቹ አብረውኝ የተማሩ ልጆች ለራሳቸው እንደ ወንጌላዊ፣ ሀዋርያና ነቢይ አይነት ማዕረጎችን መስጠት ጀምረው ነበር። ኃይማኖታዊ ትምህርታችን በጴንጤቆስጤና

@Amharicbookstore

ካሪዝማቲክ አስተምህሮ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምንም አይነት ሚስጥራዊ የምትሀት ስያሜዎች ጥቅም ላይ አይውሉም ነበር። የክርስቶስን አካል ለመገንባትና ለማነቃቃት እግዚአብሔር በሚጠቀመው አምስት አጥፍ አገልግሎት የምናምን ነበርን።

እኔም መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ "ወንጌላዊ" ተብዬ እጠራ ነበር። ይህ በዘመናችን ከነበሩ ታላላቅ ወንጌላውያን ጋር የተዛመደ በመሆኑ እጅግ በጣም የምወደው ስያሜ ነበር። የመስቀሉ ወንጌል በእውነተኛ ስሜት ይሰበክ ስለነበር ሰዎች ሲየሱስን ሲያውቁ እንዴት እንደሚፈወሱ፣ እንደሚድኑና እንደሚተርፉ እናይ ነበር። በዚያን ጊዜ ለመፈወስና ለመዳን ጥቅም ላይ የሚውለው ሲየሱስ የሚለው ስም ብቻ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ የነበረውን ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ በፐሪቶሪያ ማዕከላዊ የንግድ ወረዳ ውስጥ ቤተክርስቲያን እንድመሰርት የተናገረኝን የእግዚአብሔርን ድምፅና እንዴት በከተማው መሀል ቤተክርስቲያን እንደመሰረትኩ የነበረኝን ድፍረት አስታውሳለሁ። የእግዚአብሔርን ድምፅ ስለማምን በዚያ የውጣትነት እድሜዬ ምንም ነገር አልፈራም ነበር።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተመረቅን በኋላ፣ አብዛኞቹ አብረውኝ የተማሩ ልጆች ወደ አገልግሎት ተሰማሩ። አንዳንዶቹ መጀመሪያ የነበሩበትን ቤተክርስቲያን ተቀላቀሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የራሳቸውን ቤተክርስቲያን መሰረቱና ተለያየን። የአንድ ኃይማኖት ወገን ከሆነ ቤተክርስቲያን ይልቅ የአንድ ኃይማኖት ወገን ያልሆነ ቤተክርስቲያን በጣም ፈጣን በሆነ ሁኔታ ያድጋል። በዚያ ላይም ብዙ የአንድ ኃይማኖት ወገን አብያተ ክርስቲያናት

ከአሮጌ ባህሎች ጋር የተዛመዱ በመሆናቸውና ውጣት ሰባኪያን እነዚያ አሮጌ ባህሎች ራዕዮቻቸውን እንደሚያግዱባቸው ወይም እንደሚያዘገዩባቸው ስለሚያስቡ፣ ቀድሞ የነበሩበትን የኃይማኖት ወገን ከማገልገል ይልቅ የራሳቸውን ቤተክርስቲያን መመሰረትን ይመርጡ ነበር። በእኛ ትውልድ መካከልም እነዚህ የግል አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደሚያድጉ አይተናል።

ዛሬ ይህንን መጽሐፍ ስፅፍ ጠላት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በቀላሉ የያዘበት ምክንያት መንፈሳዊ አባቶቻችን ይዘውት የቆዩትን አምላካዊ ስርአቶችን፣ ትክክለኛ ልማዶችንና መመሪያዎችን በአብያተ ክርስቲያኖቻችን መጠቀም ስለተውን እንደሆነ በግልፅ መናገር እችላለሁ። አንዳንድ ዘመናዊ አብያተ ክርስቲያናት ባህላዊ መንገዶች የማይረቡ ናቸው ብለው የሚያምኑ ቢሆንም በአገልግሎት እያደግኩ ስመጣ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በነበርንበት ጊዜ በጠላት ከመታለል ያዳኑን እንዳንድ አሮጌ የምንላቸው ባህሎቻችን መሆናቸውን ተረድቻለሁ።

የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ መቼ እንደተጀመረ የማወቅ አስፈላጊነትን ለማየት የቤተክርስቲያን ታሪክ እንማር ነበር። የቤተክርስቲያን የኃይማኖት ትምህርት ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የተለያዩ አስተምህሮዎች እንድናውቅ ረድቶናል። ልንማርበት የምንችልበት ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉ የሀሰት አስተምህሮዎችን የሚዘጋ ግድግዳ ለሆነው የቤተክርስቲያን ባህል ትኩረት እንሰጥ ነበር። ያ የቤተክርስቲያን ባህል ደግሞ የእምነታችን ስርዓት በትክክል ከየት እንደመነጨና አሁን በምናደርገው አይነት

@Amharicbookstore

የምንዘምረውና የምንፀልየው ለምን እንደሆነ የተሻለ መረዳት እንዲኖረን አግዞናል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በኋላ ቤተክርስቲያን ስለመትከል

በከተማ ውስጥ የመጀመሪያ ቤተክርስቲያኔን ሳቋቁም የቤተክርስቲያኒቱ አባል ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ረጅም ዝርዝር ነበረኝ። የነበረኝን ራዕይ ይደግፉሉ ብዬ ያሰብኳቸው ሰዎች በአእምሮዬ ውስጥ መኖራቸው ለመልካም ራዕይ መኖር መልካም ቢሆንም፣ በትክክል መልካም ራዕይ እንዲኖረን ለማድረግ ዋስትና ነው ማለት ግን አይደለም። ምክንያቱም ታላላቅ ራዕይ ትጋትና አቅም ኖሯቸው እየተነሱና እየወደቁ ያሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አይቻለሁ። እኔ የራሴን ቤተክርስቲያን በመሰረትኩ ጊዜም መጪው ጊዜ በጣም ብሩህና አስተማማኝ ይመስል ነበር። የማስበውም የፊት የፊቴን ብቻ ነበር። ራዕዬን መንፈሳዊ መረዳት ላላቸውና በመንፈሳዊነት ለበሰሉ ሰዎች ሳካፍል አብዛኞቹ በአገልግሎት ውስጥ የፀሎትን አስፈላጊነት መከረውኝ ስለነበር ለዚህ አገልግሎት መከፈት እያምና እፀልይ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ቤተክርስቲያን ለመመስረት ውጤታማ የሆኑ መንገዶችን ለማወቅ መፃህፍት ለማንበብ ጊዜ ወሰድኩ። ያነበብኳቸው አብዛኞቹ መጽሐፍት ግን የምዕራባዊው አለም ተፅዕኖ ያለባቸው ነበሩ።

በዚህ አገልግሎት ጉዞዬ ውስጥ የተረዳሁት ነገር ቢኖር አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ያንተ ልምድ ለራስህ ትምህርት ወይም

ለሌሎች እንደ ምርምር የሚያገለግል እንዲሆን እንደሚያደርግ ነው። ቤተክርስቲያኑ ከመከፈቱ ጥቂት ወራት በፊት እዚያው ኮተማ ላይ የነበረ ሌላ ቤተክርስቲያን የመክፈቻ ስነ ስርዓት ላይ ተገኝቼ ነበር። ቤተክርስቲያኑ ምርጥ በሆኑ ማስጌጫዎች አሸብርቋል፣ የአምልኮ ቡድን፣ ድምፅ፣ ትልልቅ ስፒከሮችና ምግብም ነበር። አንድ ፓስተር "ለመታመን ተፈትነህል።" የሚል ርዕስ ያለው ስብከት እንደለክ አስታውሳለሁ። አዲስ ቦታ፣ አዲስ የአምልኮ ቡድንና አዳዲስ አባላት ያሉት አዲስ ራዕይ በመሆኑ በጣም አስደስቶኝና አነሳስቶኝ ነበር። የማይረሳ የመክፈቻ ስነስርዓት ነበር። ይህንን የመክፈቻ ስነስርዓት ከታደምኩ በኋላ የእኔን ቤተክርስቲያን የመክፈቻ ስነስርዓት ማቀድ ጀመርኩ።

ከዚያ ቦታውን አስተማማኝ ለማድረግና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ለማድረግ ወደ ከተማ ተመለስኩ። ከተማ ሳለሁም ከዚህ በፊት ስታዲየም ውስጥ በተደረገ ፕሮግራም ላይ ተዋውቀው የነበረውን አንድ ሙዚቀኛ አገኘሁ። ራዕዬን ሳካፍለው ስለወደደው አብረን ፀለይንና የመክፈቻ ስነሥርዓቱን አንድ ላይ ሆነን ማቀድ ጀመርን። ከጂይ ምቢዛ ጋር የነበረን ቁርኝትና ወንድማዊ ፍቅር መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳሉት እንደ ዮናታንና ዳዊት ነበር።

ጂይ ምቢዛ ከመጀመሪያ ቤተክርስቲያን የመክፈት ሙከራዬ አንስቶ ከእኔ ጋር ነበር። ለአምልኮ ቡድኑና ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ለነበረው ሳውንድ ሲስተም ሀላፊ ነበር። የራሱን የሙዚቃ ሙያ ለመሞከር ብሎ ቤተክርስቲያኑን እስከለቀቀበት ጊዜ ድረስ ከእኔ ጋር እየሰራ ነበር። ጂይ ምቢዛ እኔ በእርሱ የሙዚቃ ተሰጥኦ የማምነውን

@Amharicbookstore

ያህል እርሱም በእኔ ራዕይና መንፈሳዊ ትምህርት ሰጥታ ያምን ስለነበር በእገልግሎቴ ውስጥ በዝቅታና በከፍታ ሁሉ ወዳጀ ነበር። እግዚአብሔር ከጥንቆላው አለም ባተረፈኝ ጊዜም ከእርሱ ጋር ቁጭ ብዬ በሙሉ ልቤ ምን ያህል በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ መስራት መቀጠል እንደምፈልግና ምን ያህል በሙሉ ኃይል ወደ አገልግሎት ሜዳ መመለስ እንደምፈልግ እንደነገርኩት አስታውሳለሁ። እርሱም "ጌታ በልብህ ባስቀመጠው ራዕይ አምናለሁ፣ ሁልጊዜም ምንም ነገር ቢሆን መመከት እንደምትችል አምናለሁ።" ሲል አበረታትቶኝ ነበር።

ወደ ቤተክርስቲያን ከተመለስኩና ከጥንቆላው አለም ከወጣሁ በኋላ ጂይ ምቢዛ እኔንና ባለቤቴን ፕሪቶሪያ በነበረው የቀጥታ የሙዚቃ ፕሮግራሙ ላይ በክብር እንግድነት ጋብዘን እንደነበር አስታውሳለሁ። ከጥንቆላ አሰራር ከዳንኩ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ስመለስ ብዙ ሰዎች ሊቀበሉኝ ተቸግረው የነበረ ቢሆንም እንደ ጂይ ምቢዛ ያሉ ሰዎች ዳግም በወንድማዊ ፍቅር እንኳን ደህና መጣህ ብለውኛል።

የመጀመሪያ ቤተክርስቲያን መክፈት

በመጨረሻ የመክፈቻው ቀን ደረሰ። የግብጣ ወረቀቶች ተላኩና ተቀባይነት አገኙ፣ ትላልቅ የገንዘብ አቅም ያላቸውን አባላት ለመላክም ሁሉም ቦታዎች ላይ ፖስተሮች ተሰጠፉ። ዝግጅቴ በቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያኒቱና በወዳጆች የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ነበር። ከፊት ለፊቴ ታላቅ ጊዜ የሚጠብቀው የአዲስ ቤተክርስቲያን መክፈቻ ስነስርዓት ነበር። ዝግጅቱ በጥሩ ሁኔታ የተካሄደበትና ብዙ

ታዳሚዎችም የነበሩበት ነበር። አንዳንድ ውጣት ሰባኪያን ራዕያቸው ለማህበረሰቡ ጥቅም አለው ወይም የለውም የሚለው የሚወሰነው በአባላቱ ቁጥር ነው ብለው ስለሚያምኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር መብዛት ወሳኝ ነገር እንደሆነ ያስባሉ። ስለዚህ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሚጨነቁት ስለ አዳራሾቻቸው ስፋት ነው። ፓስተሮች የሚከበሩት ባሏቸው ተከታዮች ብዛት ነው። በኋላ ግን የተረዳሁት እንድ ቤተክርስቲያን ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልገው አዳራሹ መሙላቱ ወይም ብዙ ሰው መገኘቱ ሳይሆን ነፍሳት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርገው ጌታን መቀበላቸው ነው።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ አራት

ኃይላት

መጋቢነት በሸሻንጉሼ

በፐሪቶሪያ ለአንድ አመት በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ በመጋቢት ካገለገልኩ በኋላ ሾሻንጉሼ ተብላ ወደምትጠራው የከተማይቱ ክፍል ስሄድ ወተትና ማር ወደሚፈስባት ምድር እንደመጣሁ አምኜ ነበር። ይህ ቦታ መቀየር ቤተክርስቲያናችንን እንደ የወንዶችና የሴቶች ህብረት፣ የወጣቶች እድገት፣ የሰንበት ትምህርት አገልግሎት፣ አዛውንቶችና ምስኪኖችን የመንከባከብና የመሳሰሉት የአገልግሎት ክፍል ያለው በሁሉም ነገር ያደገ እንደሚሆን አምኜ ነበር። በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያደግኩ በመሆኑና ወላጆቼ ቤተክርስቲያናቸውን እንዴት እንደሚመሩ እመለከት ስለነበረ ሁሉንም ነገር እንዳየሁትና እንደማውቀው ይሰማኝ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በምንማርበት ጊዜ አንድ ሰው ቤተክርስቲያን ለመመስረት ሲነሳ

ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ መሰረቱን እንደጣለና ሌላ መሰረት መጣል እንደማይገባ ይነግሩን ስለነበር እኔም ቤተክርስትያኔን የመሰረትኩት በእግዚአብሔር ቃል፣ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከመንፈስ ቅዱስ በበቀለ ትክክለኛ የክርስቲያን እምነት ላይ ነበር።

ስራዬን ስቀጥል ግን ትኩረቴ የፓስተሮች ሴሚናርና ስልጠና ከመከታተል ይልቅ የቤተክርስቲያኑ ህንፃ፣ አዳዲስ ጉባኤዎችና የቤተክርስቲያን አባላት በመመልመል ላይ በመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ የተቀበልኳቸው አንዳንድ መልካም ነገሮችና ምክሮች እየደበዘዙ መጡ። ከማንም ምንም አይነት ምክር ፈልጌ አላውቅም ነበር። ሁሉንም የምሰራው በራሴ በመሆኑና የራሴን ቤተክርስቲያን የማስተዳድር በመሆኔ ተጠያቂነት አልነበረብኝም። የራሴ አለቃ በመሆኔ የማደርገው ሁሉ በራሴ አይን ትክክል የመሰለኝን ብቻ ነበር። የአመራርና የስነ ምግባር ኮርሶችን በመውሰድ የፓስተርነት ሙያዬን በማሳደግ ላይ ገንዘብ ከማውጣት ይልቅ ራሴን የተቀባሁ ስመሆንና የበለጠ ኃይል ለማግኘት ወደ ሌሎች አፍሪካ ሀገራት ስመጓዝ ገንዘብ ሳሰባስብ አገኘዋለሁ።

ነቢያት ሆነው በሚያገለግሉ ሰዎች እንደሚቀና ወጣት ፓስተር እኔም ነቢይ ተብዬ መጠራት በመፈለጌ ኃይል ለማግኘት ልምድ ያላቸውን መንፈሳውያንን ለመገናኘት አፍሪካን የመሮር ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ሰው ሆንኩ።

በስነ መለኮት ትምህርት ከማያምኑ፣ ኃይማኖታዊ ስልጠና ከሌላቸውና በተአምራት ከሚያምኑ ሌሎች ነቢያት ጋር ትስስርና ግንኙነት መፍጠር ጀመርኩ። እነዚህ የነቢያት ቡድኖች ለማንም

@Amharicbookstore

የማይታዘዙ በመሆናቸው አብዛኞቹ ለየትኛውም የቤተክርስቲያን ባለስልጣናት አማኒ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። እኔን ወደ እነርሱ የሳበኝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ያገኘኋቸውን ኃይማኖታዊ ትምህርቶችና ንድፈ ሀሳቦች ሁሉ ተፈላጊነታቸው እንዲቀንስ የሚያደርገው እየፈካ የሚሄድ የሚመስለው የእነርሱ ተግባራዊ ልምምድ ነበር። ብዙዎቹ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ቢሆኑም፣ የሚመሩት ግን ማራኪና የቅንጦት የኑሮ ዘይቤ ነበር። ጥቂቶቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሆነው ሳለ የክብር ዶክትሬት ሳይቀር የተሰጣቸው ነበሩ። ከእነርሱ ጋር ያለኝ ግንኙነት የምመራት ትንሿ ቤተክርስቲያን እንደኔ ያለውን ደሀ ባለፀጋ የምታደርግና ህልሜን እንድናር የምታስችለኝ እንደሆነች አሳመነኝ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ያገኘኋቸውን እውቀቶች ተግባራዊ ለማድረግ ብሞክርም እነዚያ ነብያት በድሎት እየኖሩና በፈጣንና በውድ መኪኖች ሀገሪቱን ሲዞሩ የእኔ ቤተክርስቲያን ግን በጣም ቀርፋፋ በሆነ ሁኔታ እያደገች ያለች እንደሆነች ተሰማኝ። ስለዚህ ለራሴ ምናልባት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የትምህርት አሰጣጥ ጊዜ ያለፈበት ሊሆን እንደሚችልና ቤተ መፃህፍቱም ከአሁኑ ዘመን ጋር በማይሄዱ አሮጌ መፃህፍት የተሞሉ ስለሆኑ እንደሆነ አድርጌ ማሰብ ጀመርኩ። እግዚአብሔር ትዕግስት እንድለማመድ እንደሚፈልግና ለእኔ ባለው አቅድ እምነት ሊኖረኝ እንደሚገባ አልገባኝም ነበር። የነበረብኝ የገንዘብ ችግርም አገልግሎቴና ህይወቴ ስኬታማ እንዳይሆን አድርጎ ነበር።

በራስ በሚመራ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ የገንዘብ ችግር ብዙ ፓስተሮችን አስሮ የሚይዝና አንዳንዶቹንም አብያተ ክርስቲያናትን ትተው ሌሎች ነገሮችን እንዲከተሉ የሚያደርግ ነው። በእኔ ዙሪያ ያሉም አንዳንድ ፓስተሮች ይህንን የገንዘብ ችግር ለመቅረፍ ተራ ፓስተር ከመሆን ራሳቸውን እጅግ አስገራሚ ተአምራት ወደሚሰራ ነቢያት ሲቀይሩ መመልከት ችያለሁ። እኔም ምንም የእምነት ስልጠና በሌላቸው ጓደኞቼ ምክር ፓስተር ተብሎ መጠራት ጊዜ ያለፈበት መሆኑንና ራሴን ነቢይ ተብዬ ወደመጠራት ማሳደግ እንደሚገባኝ ተነግሮኝ በዚህ ውጥመድ ውስጥ መውደቅ ችያለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሳለን በአንድ ወቅት ብዙ የሰለጠኑና ብቃት ያላቸው ፓስተሮች ከአገልግሎት ወይም ከቤተክርስቲያን ጥለው ሲወጡ የምናየው ለምን እንደሆነ ተወያይተን እንደነበረ አስታውሳለሁ። አንድ ተማሪ አንዳንዶቹ መጀመሪውኑ "ጥሪ የሌላቸው" እንደሆኑ ሲናገር ሌሎቹ ደግሞ በአገልግሎት ላይ ልምድና ትዕግስት ስለሌላቸው ነው የሚል ሀሳብ ሰጥቶ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ከአመታት በኋላ እንደተረዳሁት እንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ ህይወት ከሌላኛው ቤተክርስቲያን የተለየ እንደሆነ፣ የገንዘብ ሁኔታና የቤተክርስቲያን አድገት ግን ብዙ ፓስተሮች የሚያጋጥሟቸው የተለመዱ ችግሮች እንደሆኑ ተገንዝቤያለሁ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ታላላቅ የማህበረሰብ መሪዎች እንድንሆን ያስለጠነን ቢሆንም ከተመረቅን በኋላ ግን ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት መሆን ያለብን መሆኑ ላይና የመ.ያ ስልጠናችንን የመቀጠል አስፈላጊነት ላይ አፅንዖት መስጠቱን ረስቶታል። አንድ

@Amharicbookstore

ሰው በአገልግሎት ውስጥ ችግሮች ቢያጋጥሙት እንኳን ሳይናወጥ መቆም የሚችልበትን ስልጠና ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው። ያ ባለመሆኑ ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ በሚያጋጥማቸው የገንዘብ እጥረት ግፊት ይሸነፋሉ።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ ግፊት

አንድ ቀን ነቢይ ሆኖ በሚያገለግል አንድ ጓደኛዬ መኪና ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ አንድ ሰው "ዶክተር" ብሎ ሲጠራው በመስማቴ በዚህ በተጨናነቀ ፕሮግራሙ መሀል መቼና የት ተምሮ ይህንን ማዕረግ ማግኘት እንደቻለ እያሰብኩ ነበር።

አንድ ነቢይ በነቢይነት አገልግሎቱ ተአምራት ስመሰራት አብዝቶ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚጓዝ በመሆኑ፣ ይህ ሰው "ዶክተር" የሚለውን ማዕረግ ለማግኘት ገዝቶት ወይም ጉቦ ከፍሎ ሊሆን እንደሚችል ባሰብም በሌላ ሰዎች ድብቅ አጀንዳ ራሴን ማስጨነቅ ስለሌለብኝ ችላ ብዬ አልፌው ነበር። በእርሱ መኪና ጋቢና ተቀምጬ እየተጓዝን እኔም ይህንን ፈጣን የህይወት ሰውጥ ሳገኝ፣ ውድ መኪና ስነዳና "ዶክተር" በሚለው ማዕረግ ስከብር አሰብኩ። የያዛትን ውብ መኪና ማየትና ማድነቁን ቀጠልኩ። ከመኪናዋ ውስጣዊ ውበት ላይ አይኔን ማንሳት አልቻልኩም። የመኪናዋ ጥራት ስዚህ ጓደኛዬ ያለኝን አድናቆት አባባብኝ። የመኪናዋ በቆዳ የተሰሩና የሚመቹ ወንበሮች እንዲሁም ሞቃት የክንድ መደገፊያዎች ከዚህ አለም ውጪ ያሉ ይመስሉ ነበር።

ወደ መኪናው የኋላ ወንበር ዞር ብዬ ስመለከት በጣም ውድ የሚባሉ ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ ሰአቶች፣ በዲዛይነር የተሰሩ ጃኬቶች፣ ሚማዎችና ውድ የሆኑ ላፕቶፖች አየሁ። ከዚያ ይህንን ጓደኛዬን እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከየት እንዳገኛቸው ጠየቅኩት። እርሱም እነዚህን ሁሉ ያገኘው ከቤተክርስቲያን አገልግሎት መሆኑን ሲነግረኝ ፖሊስ ድንገት መኪናውን ቢያስቆመው የመኪናዋ መስታወት ጥቁር ከመሆኑ የተነሳ የባንክ ዘራፊዎች የሚጠቀሙበትን ስለሚመስል እነዚህን ነገሮች ዘርፎ ሊመስላቸው ስለሚችል እንዳይታዩ አድርጎ እንዲያስቀምጣቸው ስነግረው፣ የመኪናው ኮፈን የሞላ በመሆኑ በኋላ መቀመጫ ላይ ያሉትን እነዚህን ዕቃዎች የሚደብቅበት ቦታ እንደሌለው ነገረኝ። ወዲያው የመኪናውን የፊት መሳቢያ እንድከፍት ነገረኝ። ስከፍተው ብዙ ገንዘቦችን የያዙ ወፋፍራም ነጫጭ ፖስታዎች ተመለከትኩ። እነዚህንም ያገኘው ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ነበር። እነዚህን ሁሉ ፖስታዎች ስመለከት፣ እግዚአብሔር ፅዋውን አትረፍርፎለታል ስል ሰራሁ አሰብኩ።

"ሰዎች የየራሳቸውን 'የይስሀቅ ዘሮች' እንዲሰጡ አዛለሁ እና እያንዳንዱ ሰው መስጠቱን አረጋግጣለሁ። ካስፈለገም በግድ አደርገዋለሁ። የማይሰጡትን ደግሞ ተበድረውም ቢሆን እንዲሰጡ አዛቸዋለሁ። ያደርጉታል።" ሲል ነገረኝና 2ኛ ነገስት 4፡3 ላይ የተፃፈውን ጠቀሰልኝ። እኔም "እውነትም አንተ በዚህ ሙያ ዋናው ዶክተር ነህ።" አልኩት። በአነጋገሩ የቀናሁ በመሆኔ ዝም ልበለው ወይስ ምንም የማያውቁ ሰዎችን እያታለለ በመሆኑ ልውቀሰው መወሰን አልቻልኩም።

@Amharicbookstore

ወዲያው ሮክ ብሎ ሳቀና ከዚያ አገልግሎት ያገኛቸውን ስልኮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ወደ ከተማ ወስዶ ሊሸጣቸው እንደሆነና እኔ ግን ከፈለግኩ አንድ ስልክ እንድወስድ ነገረኝ። ከዚያ ቤት ተቀምጬ በእግዚአብሔር ቃልና ተሰፋዎች ላይ ተመስጠ ከማድረግ ይልቅ የዚህ ነቢይ አገልግሎት በጣም ተስፋ የሚጣልበት ብሩህ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር። ይህ "ዶክተር ነቢይ" አሁንም አሁንም ከሚያትረመርሙ ወይም በሆነ ነገር ካልተደሰቱ ሰዎች የስልክ ጥሪ ይደርሰዋል። እርሱም አብዛኞቹን ደዋዮች እንደሚረግማቸውና ያን ካደረገ ደግሞ ሰላም የሌለው ህይወት ሲኖራቸው እንደሚችል እየነገረ ያስፈራራቸው ነበር። አብዛኞቹ ሰዎች መላ ህይወታችንን ሊያወሳስበው ይችላል ብለው ስለሚያምኑ የነቢይ እርግማን ይፈራሉ። ይህንን ስመለከት የእነዚህ ነቢያት ተከታዮች በፍርሃት የተያዙና እነዚህን እንደ ግማሽ ሰውና ግማሽ አምላክ እንደሆኑ የሚያስቧቸውን ነቢያት ለመታዘዝ እንደሚገደዱ ተረዳሁ። እነዚህ ነቢያትም የሚያታልሉት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተተከሉ ተራ ሰዎችን ነው።

መኖሪያዬ አካባቢ ደርሼ ከዚህ ሰው መኪና ስወርድ የሚቀጥለው አገልግሎቱ የት እንደሆነ የሚገልፀውን ፖስተር ሰጠኝ። የፖስተሩ ዲዛይን አይን የሚይዝና ለሚቀጥለው አገልግሎቱ ገቢያ የሚያመጣ ጥሩ መሳሪያ ነበር። ፖስተሩ ላይ ከዚህ በፊት በነበረው አገልግሎት ላይ የተፈወሱና የዳኑ ሰዎች የበፊትና የአሁን ፎቶዎች ያሉበት ሲሆን ፎቶዎቹም የምስክርነት ማስረጃዎች ሆነው የቀረቡ ነበሩ። በፊት ከሚሰው ስር ያለው ፎቶ ላይ በጣም አሰቃቂ ቁስል ያለበት ሰው የሚታይ ሲሆን አሁን የሚሰው ላይ ደግሞ ያ ቁስል ድኖና ተፈውሶ የሚያሳይ ነው። የፖስተሩ ንድፍና ይዘት ብዙ

ሰዎችን መሳብ የሚችል ነው። በዚያ ፖስተር ላይ በትልቅ ቤት አጠገብ ከልጆቿ ጋር የቆመች የአንዲት ሴት ፎቶግራፍም ያለ ሲሆን ይህቺን ሴት ከትንሽ ቤት አውጥቶ ለዚህ ያበቃት የነቢዩ ፀሎት እንደሆነ ገልፃ ማመስገኗ ተፅፏል። የሚቀጥለው ፎቶ ደግሞ በሚገፋ ወንበር ላይ ይቀመጥ የነበረ አሁን ግን በነቢዩ የተፈወሰ እንደሆነ የሚናገር ሰው ይታያል። የመጨረሻው ፎቶ ደግሞ ሶስት ህፃናት ያቀፈች ሴት ፎቶ ሲሆን ሜዲካል ዶክተር እንደሆነች የተገለፀችው ይቺ ሴት መሐን እንደነበረችና ከነቢዩ ፀሎት በኋላ ግን ሶስት ልጆችን በአንድ ጊዜ የመውለድ ተአምር እንደተፈፀመላት ስትናገር የሚያሳይ ነው።

የእነዚህን ተአምራት የሚባሉትን ትክክለኛነት ማንም ሰላልቀመሰው፣ በጥርጣሬ አይን ስላላየውና የተፈፀመው የእግዚአብሔር ነቢይ በተባለ ሰው በመሆኑ እያንዳንዱ ምስክርነት አሳማኝና እውነት ይመስላል። ከመኪናው ልወርድ በሩ ሲከፈት የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ የመኪናዋን ማማር እየተመለከቱ ነበር። ምክንያቱም በአካባቢው እንደሚታዩ መኪናዎች አይነት አልነበረችም። ያ ነቢይ 500 ራንድ የያዘ ፖስታ ሰጠኝና በገንዘቡ የምፈልገውን እንዳደርግ ነገረኝ። በሀሳቤ ለቤተሰቤና ለእኔ የሚበላ ነገር ስለመግዛት እያሰብኩ ነበር። ከዚያ ወደሴት ጓደኛው ለመሄድ እየተጣደፈ እንደሆነ ነገረኝ። የሴት ጓደኛዬ የሚላት ከጥቂት እመታት በፊት ከእርሱ ጋር አብሮ ሲያገለግል የነበረ ፓስተር ሚስት ነበረች። በጭንቅላቴ የሚመላለሱ ብዙ ጥያቄዎችን ይዤ ትኩር ብዬ ተመለከትኩት። ግን በአገልግሎት ከእኔ የሚቀድም በመሆኑ ምንም ማለት አልችልም። መኪናዋን አስነስቶ ሲሄድ እንኳን የመኪናዋን ማማር ከማድነቅ ማቆም አልቻልኩም ነበር።

©Amharicbookstore

በዚህ አጭር የነቢይነት አገልግሎቱ ይህንን ሁሉ ሀብት እንዴት ማግኘት እንደቻለ እያሰብኩ ፣ወዳለሁበት እውነታ ስመለስ ሁሉም ነገር ደብዛዛና ከባድ መስሎ ታየኝና ተስፋ መቁረጥ ስለተሰማኝ ስቦታዎንና ጥሪዬን ሳይቀር መጠራጠር ጀመርኩ። የመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳቃትና መመሪያዎችን ከሚጥሱ ሰዎች ይልቅ የእግዚአብሔርን መንገድ የሚከተሉና ሁሉንም ነገር በመፅሀፉ መመሪያ መሰረት የሚሰሩ ሰዎች ዝቅ ያሉ የሚመስሉት ለምን እንደሆነ አሰብኩ። ምሽቱ ሲቃረብ በዚያ ምሽት ልናደርገው የነበረው ስብሰባ እንደቀረ የሚገልፅ የይቅርታ መልዕክቶች መቀበል ጀመርኩ። አብዛኞቹ ሰዎች የማይመጡት ሌሎች የሚሰሯቸው ስራዎች ስላሏቸው እንደሆነ ባውቅም ስብሰባውን የምናደርገው ድንኳን ውስጥ ስለነበረ እየሩ ቀዝቃዛ በመሆኑ ምክንያት እንደቀሩ ለማሰብ ሞከርኩ። ወዲያው ተስፋ የሚያስቆርጡ ሀሳቦች ይመጡብኝ ጀመር።

"እኔ እዚህ ነኝ፣ የማቅዳቸው አገልግሎቶች ሁሉ ውጤታማ አይደሉም፣ የቤተክርስቲያኗ ዕድገት ዘገምተኛ ነው፣ የሚመጡት ወጣቶችና ልጆች ብቻ ናቸው። ይሄንን ከልብ የመነጨ ራዕይ የሚያግፍ የቤተክርስቲያን አመራር ብመርጥም እነዚያ የቤተክርስቲያን ምሰሶ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸውና የተማመንኩባቸው አመራሮች ፍላጎት አጥተው ሌሎች አገልግሎቶችን ለመቀላቀል ቤተክርስቲያን እየለቀቁ ነው።" እያልኩ ለራሴ ማሰብ ጀመርኩ። ከእኔ ጋር መሰራት ከጀመሩት ሰዎች ጋር በመራራቁ ስብራት ተሰማኝ። ከውጪ ለሚያዩኝ ሁሉን ነገር መቆጣጠር የቻልኩ ብመስልም ከተዘጋው በር ጀርባ ግን ቤተክርስቲያኒቱን እየለቀቁ በሚሄዱ ሰዎች ምክንያት ተስፋ መቁረጥ እየተሰማኝ ነበር።

ቤተክርስቲያኗን ለቀው ለወጡት ሰዎች ያለ እነርሱ መቆም እንደምችል ማረጋገጥ ስለፈለግኩ ሁኔታው ቤተክርስቲያኗንና አገልግሎቴን ለማላደግ ሌሎች መንገዶችን ማሰብ እንደሚኖርብኝ አስገደደኝ። ሰዎቹ አንድ በአንድ እየለቀቁ ሲሄዱ ቤተሰቤን እንዴት መደገፍና ማቆም እንደምችል ለራሴ ማሰብ ጀመርኩ። የነበሩብኝ እነዚህ ሁሉ ግፊቶች እኔ በአንዲት የስተማ ክፍል ውስጥ ተጣብቄ እየኖርኩ እያለ ውድ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩና ብልጭልጭ ህይወት ከሚኖሩ የነብያት ቡድን ጋር እንድቀራረብ አደረጉኝ። እነዚህ የነቢያት ቡድኖች ለመፀለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰላሰል ጊዜ አልነበራቸውም። አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ስለ ሀብታም ፓስተሮች፣ ነቢያትና ስላሏቸው ውድ መኪኖችና ንብረቶች በማውራት ነበር። እነዚያን አወዛጋቢ የሆኑ አለማቀፋዊ ሰባኪያንንና ነቢያትን የሚያመልኩ ነበሩ። በነዚህ ሰዎች ወዳጅነት ዙሪያ እየሆንኩ ስመጣ፣ ጌታ በውስጤ ስላስቀመጠው ስራ የነበረኝ ትኩረት ቀስ በቀስ እየጠፋ መጣ። አገልግሎት እንዴት መቆም እንደሚገባው የራሴን አይታ እንዲኖረኝ አደረግኩና በነዚህ ሰዎች የሚደረጉ ቅድስና የሌላቸውን አንዳንድ ድርጊቶች መውሰድ ጀመርኩ። ነገር ግን አሁንም ኃይል ለመቀበል መንፈሳዊ አባቶች ተብለው ወደሚጠሩት ሰዎች ስለሚሄዱበት አሰምአቀፋዊ ጉዞዎቻቸው የበለጠ ለማወቅ አፈልግ ነበር። አብዛኛው ወሬያቸው የሚያጠነጥነው በብልፅግና ዙሪያና እግዚአብሔር እንዴት በተትረፈረፈ ቁሳዊ ሀብት እንደባረካቸው በመናገር ነበር። ወንጌላቸው ትኩረት ያደረገው ቁሳዊ ነገሮችና ሀብት ላይ ነው። አንዳንዶቹ አስተምህሮዎቻቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባይሆኑም እያደጉ የሚመጡ

@Amharicbookstore

መሆናቸው ሊታይ ይህ ነገር ለእነርሱ እየሰራላቸው መሆኑ ግልፅ ነበር። ጤናማ ያልሆኑ አስተምህሮዎቻቸው የዘመኑ ስርዓት ባለመሆናቸው እንዲሁም በልሳናቻቸው ለመርገምና ተአምራት ለማድረግ ኃይል እንዳላቸው ስለሚናገሩ ብዙ ተከታዮች አሏቸው። ያሏቸው ነገሮች ሁሉ እኔ በቤተክርስቲያኔ ድንኳን ውስጥ ለረጅምና ቀዝቃዛ ምሽቶች በፀሎት የምጠይቃቸውን ነገሮች ይመስሉ ነበር።

በአገልግሎት ውስጥ እየታገለ እንዳለ አንድ ሰው እነዚህ ነቢያት ባላቸው ኃይል ስለቀናሁ እነርሱ የተለማመዱትን መለማመድ ፈለግኩ። "እቅጣጫውን ማወቅ ከፈለግክ ከአንተ በፊት በዚያ መንገድ የሄዱትን ጠይቅ።" እንደሚባለው ሁሉ ወዳጅነታችን እያደገና ከእነርሱ አንዱ ለመሆንና የእነርሱን የኃይል ምንጭ ለማወቅ አንዳንድ አስተምህሮዎቻቸውንና የህይወት ዘይቤያቸውን መኮረጅ ጀመርኩ።

ከዚያ ግን የእነርሱ ኃይል ከእግዚአብሔር እንዳልሆነና የሚያስተምሩትም ጤናማ አስተምህሮ እንዳልሆነ ብረዳም እነርሱ ወደሄዱባቸው ቦታዎች በመሄድ እነርሱ የሚመሰክሩላቸውን ኃይላት ይዤ መመለስ ፈለግኩ።

ስለ ኃይላት መጠየቅ

አንድ ቀን ከዚያ ዶክተር ነቢይ የቅርብ ጓደኞች አንዱ የሆነውንና "ሁለተኛ መክት" ብለው የሚጠሩትን ያገኘውን ሰው ይህ "ሁለተኛ መክት" የሚባለው ነገር እንዴት እንደሚገኝ ጠየቅኩት። እነርሱ እንደሚያምኑት የመጀመሪያው መክት የሚከሰተው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝና ጌታ ስትቀበል ሲሆን ሁለተኛ መክት

የሚከሰተው ደግሞ ከሆነ ሰው ወይም መንፈሳዊ አካል ኃይል ስታገኝ ነው። የዚያ ዶክተር ነቢይ የቅርብ ጓደኛ ሁለተኛ መክት ከተቀበለና ለአገልግሎት ከተሰየ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገልግሎትና በገንዘብ ትልቅ ውጤት እንዳየ በግልፅ ነገረኝ። ይህ ሰው ቤተክርስቲያን ውስጥ የሙዚቃ መሳሪያ የሚጫወት እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መደበኛ የሆነ ስልጠና የወሰደ አልነበረም። ነገር ግን ከነብይ ጓደኛዬ ጋር ለአገልግሎት ሲጓዝ ከዚህ ነገር ጋር እንደተዋወቀ ነገረኝ። ታሪካቸው አስደመመኝ።

አሁን ነቢይ ከሆነው ከዚህ ናይጄሪያዊ የሙዚቃ ተጫዋች ጋር ከነበረኝ ንግግር በኋላ ከናይጄሪያ ይህንን "ሁለተኛ መክት"ና መለየት ለማግኘት ገንዘብ ማግኘት እንዳለብኝ ለራሴ ነገርኩት። ይህ ወደ ነቢይነት የተለወጠው የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች እንደ ፕሬዚዳንቶች፣ ፖሊቲከኞች፣ ፓስተሮች፣ ዝነኛ ሰዎች፣ ሙዚቀኞች፣ የባህል ሀኪሞች ያሉ ብዙ ሰዎች ኃይል ለመቀበል ናይጄሪያ ውስጥ ወደሚገኝ እርሱ ወደሚያውቀው አንድ ቦታ እንደሚሄዱና ዝነኛ፣ ለትላልቅ ቦታዎች የሚመረጡ፣ ባለፀጋና ተአምር የመስራትና የነቢይነት ኃይል ኖሯቸው እንደሚመለሱ ነገረኝ። ይህንን ራስ ሰራሽ ነቢይ በትልቅ ጉጉትና ፍላጎት አዳመጥኩና እኔም በዚህ ሁለተኛ መክት የተባረኩ ለመሆን ወሰንኩ። ወደ ናይጄሪያ መሄድ ይህንን "መለየት" የማግኛ አጋጣሚ መሆኑን አየሁ። መላውን የአቅጣጫ ለውጥ እንደምትቃወም ስለማውቅ እቅዴን ለሚስቱ አንኳን አልነገርኳትም ነበር። ወደ ናይጄሪያ የመግቢያ ቪዛ ለማግኘት የሚያስፈልገውን ገንዘብ አገኘሁ። ቪዛው መጥቶ ነቢይ የሆነው ጓደኛዬ የት እንደምንሄድና ብዙ ነቢያትና ተዕእኖ ፈጣሪ ሰዎች

@Amharicbookstore

ኃይላቸውን ከየት እንደሚያገኙ ሲነግረኝ በጣም ተደሰትኩ። ይህ ወዳጄ ይህንን የአቅጣጫ ለውጥ አስመልክቶ ሁለት አማራጮችን ነገረኝ።

አንደኛው አማራጭ ናይጄሪያ ውስጥ ወደሚገኙ እጅግ ትልልቅ ቤተክርስቲያን ካላቸው አለማቀፋዊ ፓስተሮችና ነቢያት ጋር በመገናኘት ኃይል ለመቀበል እጃቸውን እንዲጭኑብኝ ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ብዙ ኃያል ነቢያት ወዲያውኑ ኃይል ወደሚያገኙበት ቦታ መጓዝ ነበር። ለሁለታችን የአውሮፕላን ቲኬት፣ የሆቴልና የምግብ የከፈልኩትን ገንዘብ የሆነ ሰው እጁን እንዲጭንብኝ በማድረግ ማባከን ስላልፈለግኩ ነቢያቶቹ በቀጥታ ኃይል ወደሚያገኙበት ቦታ መሄድ እንደሚገባን ሀሳብ አቀረብኩ። እነዚያን ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት የምገበኘው ኃይል የማግኘት ተልዕኮዬን ከጨረስኩ በኋላ እንደሆነ ነገርኩት። የፈራሁት ብቸኛ ነገር ልክ እነዚህ ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት የቤተክርስቲያን አገልግሎታቸውን በቲቪ እንደሚያሳዩት እንዳልታይ ብቻ ነበር። ጓደኛዬ አየት አድርጉኝ ከት ብሎ ሳቀ። ምን እንደሚያስቀው ስጠይቀው፦ "በነዚህ የቲቪ ጣቢያዎች የምታየው አብዛኛው ነገር እውንና እውነት እንደሆነ ታስባለህ?" አለኝ። "እምና ቲቪ እንዴት ይዋሻል?" አልኩት። ጓደኛዬም "አታስብ ወደነዚህ በቴሌቭዥን ተአምራት ወደሚያሳዩ አብያተ ክርስቲያናት ብንሄድም የዚያን ጊዜ እንተ 'ከእኛ አንዱ' ከሆንክ በኋላ ስለሚሆን ስለእንተ ተነግሮ በቴሌቭዥን እንድትታይ አይደረግም።" አለኝ። በተናገረው ነገር ግራ ብጋባም ምንም አልተናገርኩም።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሚያዙትና በቲቪ ላይ በአደባባይ ጠንቋይ ተብሰው ስለሚጠሩት ሰዎች እንዲነግረኝ ጠየቅኩት። ይህ ልምድ ያለው ወዳጄ እንደዚያ ያሉ ተአምራት ያ ነቢይ ምን ያህል ኃያል እንደሆነ ለማሳየት የሚቀናበር እንደሆነ ሲነግረኝ "ምን?" ስል ራሴን ጠየቅኩ። "እነዚህ የጥንቆላ ኃይላቸውን ለነቢዩ አስማርከው በመድረክ ላይ ምርር ብለው የሚያለቅሱት አሮጊቶች ሁሉ የውሸት ናቸው እያልከኝ እኮ ነው?" ስል ጠየቅኩት። "እም ቴሌቭዥን ስርጭት አላማ የተዘጋጀና ልምምድ ተደረገበት ሲሆን፣ እነዚያ ሁሉ ነገሮች 'የእግዚአብሔር ሰው ስራዎች' ተብሰው የሚጠሩ ናቸው።" አለኝ። በነዚህ ጊዜያቶች ሁሉ ሰዎች በትንቢትና ተአምራት ስም ድራማ እየተሰራባቸው ውሸት እየተመገቡ መሆናቸውን ያወቅኩት በዚህ ጊዜ ነበር።

ከዚያ ነቢይ ጓደኛዬ "እትጨነቅ፣ አንተ ፈቃደኛ ልብ ካለህና ለመማር የምትጓጓ ከሆንክ የዚህን ጨዋታ ዘዴዎች ሁሉ አስተምርሀለሁ።" አለኝ።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ አምስት

ናይጄሪያ

ወደ ናይጂሪያ ለመሄድ መዘጋጀት

ቪዛ ተሰጠኝና ለመጀመሪያ ጊዜ አለማቀፋዊ በረራ የምሳፈርበትን ቀን መጠበቅ ጀመርኩ። የመጀመሪያ የአውሮፕላን በረራዬ የተሳሳተ ምክንያት መሆኑ የሚያሳዝን ነበር። ለጉዞ ስዘጋጅ ለባለቤቴ ለፀሱትና ለአለማቀፋዊ የፓስተሮች ኮንፈረንስ ወደ ናይጂሪያ እንደምሄድ ስነግራት የጉዞዬ ብቸኛ ተልዕኮ የመናፍስት ኃይል ማግኘት እንደሆነ ስለማታውቅ ለእኔ የተሻሉ ነገሮች የምትመኝልኝ በመሆኗ ብቻ መልካም እድል እንዲገጥመኝ ተመኘችልኝ። በክርስትና ህይወቴ ሙሉ የህይወትን ግፊት በዚህ መንገድ ለማሸነፍ አፈተናለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር።

ከመሄዴ በፊት ላገኘው የምሄደው መንፈሳዊ ሰው ባባሱላ የሚባል ሲሆን እኔን በምክር ለማገልገል አስቀድሞ አንዳንድ ነገሮች

መገዛት ስላለባቸው ገንዘብ እንድልክ ጠየቀኝ። በገንዘቡም እኔ የተላለው ቦታ ከመድረሴ በፊት መንዳት ስላስብኝ ለዚያ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ለመግዛት እንደሆነ በመንገር ቃል ገባልኝ። ይህንን ስሰማ እኔን ለመርዳት የጉጓ እንደሆነ ስለተሰማኝ ገንዘቡን ቦሚቀጥለው ቀን እንደምልክለት ነገርኩት። ባባሱላ እንደሚያምነው ዋናው የጥንቆላ ስርዓት ከመደረጉ በፊት አንድ ሰው መንዳት ይገባዋል። ስለዚህም እኔ እዚያ ከመድረሴ በፊት ከአነርሱ አባላት አንዱ የሆነውና ጄነራል ቶም ተብሎ የሚጠራው ሰው የምታጠቡባቸውን ነገሮች እንደሚያመጣልኝ ተነገረኝ። የጥንቆላ ቡድኖች በቡድናቸው ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን እንደየደረጃቸው ስምና ማዕረግ ይሰጣሉ። እንዳንድ የጥንቆላ ቡድኖች ደግሞ እንደ ኮማንደር፣ ጄኔራል፣ ሜጀር የመሳሰሉ ወታደራዊ ማዕረጎችን ይሰጣሉ።

በአንተ ስር ብዙ ሰዎችን ካበቃህ፣ ደረጃህ በዚያው መጠን ያድጋል። እኔ እንደ ነቢይ በሰራሁባቸው ጊዜያት ጄኔራል የሚል ማዕረግ አግኝቼ ነበር። መንፈሳዊው ሰው የሚያደርግልኝ መንፈሳዊ እጥበት የሚከተሉኝ አሉታዊ መንፈሶች ሁሉ የሚያስወግድና እዲስ እንደተወለደ ሰው የሚያደርገኝ መሆኑን ነገረኝ። ጥንቆላ ድብቅ እውቀት ያለበት ሚስጥራዊ ኃይማኖት በመሆኑ ይህ ድብቅ እውቀት በሚስጥር መያዝ ይኖርበታል። ብዙ ሰዎች ጥንቆላን የሚቀላቀሉት የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነው ከሚል አይታ ነው። መንፈሳዊ እጥበቱ የእስማት መድኃኒትና ጥቁር ላሙና የያዘ ሲሆን፣ የእስማት ቅመማ ቅመሞቹ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ መጥፎ እድል የሚያመጡ ክፉ መናፍስትን የሚያስወግዱ እንደሆኑ ይታመናል። ስለዚህ ከራስ ፀጉርህ እስከ እግር ጥፍርህ እንድትታጠብ ይጠይቃል።

@Amharicbookstore

ሞንቅሳትን መታጠብ መድረሻህን የማንግት ምልክት ሲሆን በውሀ ከታጠብክ በኋላ ቆሻሻውን ውሃ አካባቢው ላይ ትረጫለህ። እኔም ያንን መንፈሳዊ እጥበት ለማድረግ ጊዜ ተሰጥቶኝ ነበር። ጥንቆላ ብዙ ሀግጋትና ትዕዛዛት ሲኖሩት ትዕዛዛቱን መከተል እንጂ አንተ እንደፈለግክ ማድረግ አትችልም። የጥንቆላው አሰም ከሚጠቀሙት ዘዴዎች አንዱ መንፈሳዊ እጥበት ማድረግ ወይም ወንዝ ውስጥ መጠመቅ ነው።

የጥንቆላው ቡድን አባል ከሆነው ከጀኔራል ቶም የመታጠቢያው እሽግ ሲደርሰኝ በቤተክርስቲያኔ ውስጥ ተቀምጬ ሰዎችን በማማከር ስራ በዝቶብኝ ነበር። ባባሉላ ደውሎ የመንፈሳዊ እጥበቱ እሽግና ትዕዛዛቱ ደርሰውኝ እንደሆነ የጠየቀኝ በዚህ ቀን ነበር። በጥንቃቄ የታሸገውን ሳጥን ተቀበልኩና ከሚስጥራዊ ማህበር የመጣ በመሆኑ ሚስቴን ጨምሮ ማንም እንዲያየው አልፈለግኩም። ስለዚህ እጥበቱን በዚያ ምሽት ቡሚስጥር አከናወንኩ። በጣም የሚያስጠላ እጥበት ከመሆኑ የተነሳ መላ ሰውነቴን ያላክከኝ ጀመር። ማሳከኩ ንፁህ ያልሆነው መንፈስ በመታጠብ እየተወገደ የመሆኑ ምልክት እንደሆነ ተነገረኝ። መታጠቤን እንደጨረስኩ ቆሻሻውን ውሀ ወዲያውኑ በጓሮው ዙሪያ ረጨሁና በረራዬንም በዚያው ምሽት ላይ አደረግኩ።

ናይጄሪያ መድረስ

ናይጄሪያ ስደርስ ሚዲያና የፊልሙ ኢንዱስትሪ ይህንን ሀገር በጣም ሰው የሚበዛበትና ጥቁር አሰማት የሚደረግበት ዋና ቦታ አድርገው እንዴት በመጥፎ እንደሳሉት ማሰብ ጀመርኩ። ሀገሪቱ

እንደ እፅ፣ ሀገወጥ ገንዘብ፣ ሀገ ወጥ የሰው ዝውውርና ጥንቆላ ባሉ መጥፎ ነገሮች የታወቀች ናት። ወደዚች ሀገር ስገባ እነዚህ ነገሮች እኔ ላይ ይከሰታሉ ብዬ አላሰብኩም ነበር። ይህንን ያላሰብኩበት ምክንያት ወደ ናይጄሪያ ከመምጣቴ ከጥቂት ሳምንታት በፊት አስቀድሞ በጥቁሩ ሳሙናና የተለየ ሽታ ባለው የአሰማት መድኃኒት በመታጠቤ ሲሆን ይችላል። ይህ ጥቁር ሳሙና ከናይጄሪያ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተላከልኝ ሲሆን የተቀበልኩትም በፖስታ ቤት በኩል ነበር። ጥቁሩ ሳሙና ከማይፈሰጉ ክፉ መናፍስት እንዲያፀዳኝ የተሰጠኝ ሲሆን የገረመኝ ነገር ይህንን ጥቁር ሳሙና መጠቀም ከጀመርኩ አንስቶ ከጨለማው መንግስት ጋር ያለተዋወቀኝ ዝቪይ ጓደኛዬ ላይ የነበረኝ ጥርጣሬ መቆሙ ነበር። እርሱ የሚናገረውን ሁሉ አልጠራጠርም ነበር። አብዛኞቹ ውሳኔዎቼ ሁሉ በጥቁሩ ሳሙና ላይ ባሉ ክፉ ኃይላት በግድ የሚሆኑ መሆናቸውን ግን አላውቅም ነበር።

ከሰምንት ሰዓታት በረራ በኋላ ሙርታላ ሞሀመድ አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ስደርስ በዚያ ጥቁር ሳሙና ከታጠብኩ ጀምሮ ፈቃዴ ሁሉ ስለተለወጠ የምናገረው በደመ ነፍስ እንደሚንቀሳቀስ ሰው ነበር። የዚያች ሀገር የአየር ጠባይ በጣም ሞቃት ከመሆኑ የተነሳ በወበቅና በውሀ ጥም የምሞት ስለመሰለኝ ቤቴ በጣም ናፈቀኝ። ሻንጣዎቻችን እስኪመጡ ከሌሎች ተጓዦች ጋር ሆነን ስንጠብቅ ከምንሰማው ወሬ ብዙዎች ወደ አብያተ ክርስቲያናት ለመሄድ የመጡ እንደነበሩ ተረዳሁ። ሻንጣዎቹ ላይመጡ ብዙ ስለቆዩ በጣም ደንግጬና ትዕግስት አጥቼ ነበር። ጓደኛዬም ሀገራቸው ላይ የተሰመደ ነገር በመሆኑ ዘና እንድል ነገረኝ።

@Amharicbookstore

ቆይቶ ሻንጣዎቻችን እንደመጡ ፈጠን ብዬ ሻንጣዬን ያዝኩና በእጄ የያዝኩትንም ጨምሮ የሚገፋው ተሽከርካሪ ላይ አደረግኩና ወደ በሩ አመራሁ። በሩ በራሱ ጊዜ የሚከፈት ነበር። ስወጣ ጮክ ብሎው የሚያወሩ ብዙ ሰዎች ሊያጋጥሙኝ ፀብ መስሎኝ ነበር። ገጽታዎቻቸውን ስመለከት ግን በሰላም እያወሩ መሆኑን ተረዳሁ። ጓደኛዬ የዚያ አገር ተወላጅ ስለሆነ ግራ መጋባቴን ችላ ብሎ ፈገግ አለና "እንኳን በሰላም ወደ ናይጀሪያ መጣህ ወንድሜ" አለኝ። መሸቶ ስለነበር ወዲያውኑ ታክሲ ይዘን ወደ ከተማ አመራን።

ሌጐስ ውስጥ የነበረኝ ጊዜ

ወክላ የበዛባት በአፍሪካ ውስጥ በጣም የተጨናነቀችው ከተማ ሌጎስ ስንደርስ በጣም ብዙ ጩኸት ተቀበለን። መኪኖች ያለማቋረጥ ጡሩንባ ያሰማሉ፣ እና በህይወቴ አይቼ የማላውቀው የመኪና ጭንቅንቅ ነበር። ወንዶችና ሴቶች በሳይክል ይጓዛሉ። ጀብሎዎች መንገድ ላይ ይሸጣሉ። ቦታው በሀገሬ ፕሪቶሪያ ውስጥ ያለውን ሰንሳይድ የሚባለውን ቦታ አስታወሰኝ።

ሌጐስ ከአቅሟ በላይ ሰዎች የበዙባት ከተማ ናት። አንዳንድ የመንገድ ላይ ቸርቻሪዎች እየሄደ ባለ አውቶቡስ ውስጥ ላሉ ሰዎች ዕቃዎች ለመሸጥ ይሞክራሉ። ትንንሽ ልጆች ከወንባቸው በላይ እርቃናቸውን ሆነውና ቡናማ ሱሪዎች ለብሰው እየተሯሯጡ "ንፁህ ውሀ ይሸጣል" እያሉ ይጮሀሉ።

"የእንግዳ ማረፊያ የሚል ፅሁፍ የተፃፈበት ቦታ ላይ ስንደርስ አይኖቼ በደስታ በሩ። ምክንያቱም ምሽቱን የምናሳልፍበት ቦታ

እንዳገኘን አውቄያለሁ። በጣም መሸቷል። እኛም ደክሞን ነበር። ለማረፊያችን አስቀድመን ክፍለን ስለነበር ያመጣን ሾፌር ሻንጣዎቻችንን ወደ እንግዳ ማረፊያው በማስገባት አገዘን። ጓደኛዬ የተወለደበት ከተማ በመሆኑና አንዳንድ ሰዎችን ስለሚያውቅ፣ ለሾፌሩ ሂሳቡን ከፈለውና የመጣነው በጣም አስፈላጊ ለሆነ ተልዕኮ ስለሆነ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት እንዲመጣና እንዲወስደን ነገረው። ሾፌሩ እንደገባው የሚያመለክት ፈገግታ አሳየንና በሚቀጥለው ቀን ወደ ተልዕኳችን ሊወስደን ተስማማ። ጓደኛዬ ፓስተር እንደሆንኩ ነግሮ ስላስተዋወቀን ሹፌሩ ለምን እዚህ እንደመጣን የጠረጠረ ይመስለኛል።

የካህናት አምልኮ

በሚቀጥለው ማለዳ የካህናት አምልኮ ተብሎ የሚጠራ አምልኮ አባል ወደሆነ አንድ ካህን ሄድን። የመጣነው ለሰዎች ኃይልና ገንዘብ የሚሰጡ ሚስጥራዊ ማህበራትን የማግኘት ተልእኮ ይዘን ነው። የዚህ አምልኮ ካህን ወደነበረው ወደዚህ ሽማግሌ ቤት ስንደርስ፣ በደስታ ተቀብሎን ልክ እንደቤታችን እንዲሰማን አደረገ። ወዲያው ይህንን ካህን ስለ አምልኪቸውና አንድ ሰው እንዴት የእነርሱ አባል ሊሆን እንደሚችል ጠየቅኩት። ካህኑ ኃይማኖታዊ እውነት ሰመፈለግ ያደረገውን የ20 ዓመታት ጉዞና ይህ ጉዞው ወደ ክርስትና ከዚያ ወደ እስልምና በመጨረሻም ወደዚህ አምልኮ እንደመራው ነገረን። ይህ አምልኮ የራሱ ካህናት ያሉት ኃይማኖት ነው። አንድ ሰው የዚህ አምልኮ አባል ለመሆን በመንፈሳዊ መዋረስ ውስጥ ማለፍ አለበት። ቀጥሎም ክርስቲያን ፓስተር ሆኖ የዚህ አምልኮ አባል መሆን ይቻል

@Amharicbookstore

እንደሆነ ጠየቅኩት። ሽማግሌውም ክርስቲያን ነቢያት ተብለው የሚጠሩ ብዙ ሰዎች በዚህ አምልኮ ውስጥ ካህናት ሆነው እያገለገሉ፣ በሀገራቸው ደግሞ አሁንም ክርስትናን የሚያካሂዱ እንደሆኑ ነገረኝ።

ሁለቱ ኃይላት ሊጋጩ ይችሉ እንደሆነም ስጠይቀውም፣ ሰውየው ወደኔ አየት አደረገና የእነርሱ አምልኮ በጣም ሀይለኛ ከመሆኑ የተነሳ፣ ብዙ ፓስተሮች፣ ነቢያትና ጳጳሳት ይህንን አምልኮ በሚስጥር እንደሚከተሉና ያንን በማድረጋቸውም ከዚህ አምልኮ ኃይል የተነሳ አብያተ ክርስቲያናቸው ፈጣን በሆነ ሁኔታ እንደሚያድጉ ነገረኝ። ፓስተር ማለት መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ የሚያውቅ ሲሆን የዚህ አምልኮ ካህናት ደግሞ የሁሉም ሚስጥራት አባቶች ወደመሆን የተለወጡ ናቸው ሲል ነገረኝ።

ይህ ሽማግሌ የአምልኪቸውን ምልክቶች እንዴት ማንበብ እንደሚቻል፣ ምን አይነት መስዋዕት ማድረግ እንደሚገባና መስህብና ድግምት እንዴት እንደሚዘጋጅ የሚያውቅ ነው። አንድ የክርስቲያን ፓስተር ጥያቄ የሚያስነሳ መስህብ መያዝ ካልፈለገ ተቀባይነት ማግኘት የሚያስችልና በጉባኤው ጥያቄ ውስጥ የማያስገባው ሌላ ድብቅ ዘዴ መጠቀም ይችላል ሲል ነገረኝ። አንዳንድ ፓስተሮች እንደ ላሙና፣ ጨው፣ ሻማ፣ የቀን መቁጠሪያ ካላንደር፣ ስቲከር፣ ዘይትና ሌሎች ኃይማኖታዊ ምርቶችን በመጠቀም ከእነርሱ አምልኮ፣ ኃይል እንደሚቀበሉ ጠቀሰልኝ። ይህንን ሰበር ዜና ስሰማ የምፈልገው ነገር አይኔ ስር እንደተቀመጠልኝ ተረዳሁ። ፓስተሮቹ ወደ እነርሱ ስሚመጡ ሰዎች ያለምንም ጥርጣሬ እነዚህን ነገሮች ለጉባኤያቸው እንደሚሸጡ ካህኑ ነገረኝ።

ቀጥሎ አንድ ነቢይ ስለ አንድ አይቶት ስለማያውቅ ሰው ጥልቅ የሆኑ ነገሮች ሳይቀሩ እንዴት በትክክል መተንበይ እንደሚችል ጠየቅኩት። በዚህ ጊዜ ያ ሽማግሌ በአምልኳቸው የሚጠቀሙበትን ሰሌዳ አነሳና በሩን ዘግቶ ያንን የጥንቆላ ሰሌዳ ተብሎ የሚጠራውን ሰሌዳ ጭኑ ላይ አስቀመጠ።

"እዚህ የምንጠቀመው ጥንቆላ እንጂ ትንቢት አይደለም እና ጥንቆላውን የምናደርገው በዚህ በምታየው ሰሌዳ ነው። ይህ የምታየው ሰሌዳ፣ በእግር ኳስ ጨዋታ የትኛው ቡድን እንደሚያሸንፍ፣ የሀገሪቱ ቀጣይ ፕሬዚዳንት ማን እንደሚሆን፣ የአንድን ሰው የግል ሁኔታዎች ዝርዝርና ብዙ ሌሎች ሚስጥራትን ሊነግርህ ይችላል።" አለኝ። ሽማግሌው ስለዚህ የጥንቆላ ሰሌዳ ሊያስረዳኝና ሊያብራራልኝ ሁሉም ነገር ፈጠራ እንጂ እውነት ሊሆን የሚችል ነው ብዬ አላሰብኩም። ምናልባት በአምልኳቸው ኃይል እንድተማመን እያታለለኝ ሊሆን እንደሚችል አስቤያለሁ። ከዚያ ያንን ከአንጨት የተሰራ ሰሌዳ እየተመለከተና ጥቂት መለመሮች በሰሌዳው ላይ እየሳለ ሙሉ ስሜ ማን እንደሆነ ጠየቀኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በቤተሰባችን ውስጥ የመጀመሪያ ልጅ እንደሆንኩ፣ አንድ ሴትና ሁለት ወንዶች የሆንን ሶስት ልጆች እንደሆንን ነገረኝ። ከተቀመጥኩበት ተነስቼ በእድናቆት አጨበጨብኩና ትንቢት ብዬ የምጠራው ይህንን እንደሆነና ብዙ የቤተክርስቲያን ሰዎች እንደሚወዱት ነገርኩት።

ይህ ሽማግሌ ባህላዊ ልብሱን ቀይሮ ውድ ሱፍና ሚማ ቢለብስና በእኛ ሀገር የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተአምራት አገልግሎት

@Amharicbookstore

ቢጀምር፣ በጣም ብዙ ገንዘብ እንደሚሰራ፣ የግል አውሮፕላንን ጨምሮ ብዙ ንብረቶችና የቅንጦት መኪናዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ ተረዳሁ። ይህ ሰው መጽሐፍ ቅዱስና ይህንን የእንጨት የጥንቆላ ሰሌዳ ይዞ እኛ ሀገር ቢመጣ በነፃ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ሳይቀር ይሰራሉትና በሀገሪቱ ውስጥ በጣም ትልቁ ቤተክርስቲያን ሊኖረው እንደሚችል ሰራሴ አሰብኩ። ይህንን የጥንቆላ ዘዴ እንዴት መማር እንደምችል ስጠይቀው የሆነ ሰው ሊያሰለጥነኝ እንደሚያስፈልግና የምማረውም በሂደት እንደሆነና ማንኛውም ሰው ሊሰራው የሚችለው ነገር እንደሆነ ነገረኝ። ከዚያ የጥንቆላውን ሰሌዳ በማየት ወደ እነርሱ ሀገር የመጣሁት በእርግጥም ኃይል ለማግኘት እንደሆነና ከእነርሱ ከተገናኘሁ በኋላ የምሄድበት ቦታም የምፈልገውን ኃይል ለማግኘት ትክክለኛው ቦታ መሆኑን አረጋገጠ። አይኖቼ ይህ ሾማሌ ካህን ምን ያህል እውቀት ያለው እንደሆነ ስለተመለከቱ ለእርሱ ጉብዝናና ጥረት እንዲሁም አይኖቼን ስለከፈተልኝ አድናቆቴን ለማሳየት ገንዘብ ሰጠሁት።

ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ ጉዞ

ከዚያ ከስተማ ውጪ ወደምትገኘው ራቅ ወዳለችው መንደር በመኪና እየሄድን ሳለ ጓደኛዬ ተደስቼ እንደሆነ በተደጋጋሚ ጠየቀኝ፣ እኔም ኃይል ስለመኖሩ መቶ በመቶ እርግጠኛ እንደሆንኩና ብዙ ፓስተሮች፣ ነቢዮችና ጳጳሳት በቲቪ በቀረቡ ቁጥር ትክክለኛ ትንቢቶችን የሚናገሩት የሆነ ነገር ተጠቅመው መሆኑን ማመኔን ነገርኩት። ይህ ፓስተር ወዳጄ "አሁን የምወስድህ ኃይሎች ሁሉ የሚገኙበት ቦታ በመሆኑ በምታደርገው ምርጫ ላይ በጣም ጥንቃቄ

ማድረግ ይኖርብሀል።" አለኝ የምፈልገውን የኃይል አይነት ስመርጥ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባኝ ደጋግሞ ሲነግረኝ ፊቱ ላይ ጠንከር ያለ ነገር አየሁ። ሌላ ጊዜ ነገሮች ላይ አጠንክሮ አይናገርም ነበር። በዚህ ጊዜ ግን በጣም ጠንከር አድርጎ እየነገረኝ ነው። "የምታገኛቸው ሰው ተራ ሰዎች ሳይሆኑ ጠንቋዮች ናቸው።" አለኝ።

"ጠንቋይ" የሚለውን ቃል ሲጠቅስ የፊራሁ ቢሆንም እንዳለመታደል ሆኖ አሁን አንድ ጊዜ ኃይል ለማግኘት ብዙ ጠልቄ ስለገባሁ ወደኋላ መመለሻ መንገድ አልነበረኝም። ተጨማሪ ነገሮች ሊነግረኝ እንደፈለገ ተሰምቶኖል። ግን ልክ የሆነ ሰው አቁም ያለው ይመስል ዝም አለ። ወደ መንደሩ እንደደረስን ሁለት ሞተር ሳይክሎችን ይዘን ወደ ትልቁ ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ መሄድ ነበረብን። በነዚያ ሞተር ሳይክሎች ለሰአታት ስንሄድ የምንሄድበት ይህ ሚስጥራዊ ቦታ በጣም ሩቅ መሆኑን ተገነዘብኩ። ከፊት ለፊታችን ወደ ሰማይ የሚወጣ ጭስ እስክምናይ ድረስ በሞተር ሳይክሎቹ ተጓዝን። ጭሱን በማየታችን ወደ መንደሩ መቃረባችንን ተረዳሁ። ከዚያ ጥቂት ውሾች ለየት ወዳለ አርሻ ወደ የሚያመራ ቀጭን የጠጠር መንገድ ላይ ቆመው ተመለከትን። በዚህ ጊዜ መድረሻችን በእርግጥም መቃረቡን በማወቄ ዘና ማለት ጀመርኩ።

የአኩምቦ ኃይል

የምንፈልገው ቤት ጋ ስንደርስ በደስታ ተቀበሉንና እየጠበቁን የነበሩ ሾማሌ ሰዎችን አስተዋውቀውን በረንዳ ላይ ተቀመጥን። አስቀድሞ በተነገረን መሰረት ምስጋናችንን ለማሳየት ለሾማሌዎቹ ደረቅ ጂን አቀረብን። ሾማሌዎቹ አንድ ሰው ተጣሩና ከቤቱ ጀርባ

© Amharicbookstore

እንዲወስደን ነገሩት። ከቤቱ ጀርባ በሚነድ የማገዶ እንጨት ላይ እየፈላ ያለ ውሀ ያለበት አንድ እጅግ ትልቅ ከበሮ አየሁ። ትልቁ ከበሮ ውስጥ ያለው ውሀ እየፈላ በመሆኑ እንፋሎቱ እኛ ከቆምንበት አንዲት ፍየል ከታሰረችበት ዛፍ ጋ ሆኖ ይታያል። የሽማግሌው ረዳት የመጀመሪያ ስራችን እኔን ከዘፋ መናፍስት መከላከል እንደሆነና "እኮ'ሮ" የሚባለው ኃይል እንዴት እንደሚሰራ ማሳየት እንደሆነ ነገረኝ። ወዲያው ከሆነ መያዣ ውስጥ ጥቂት የአስማት መድኃኒት አወጣና የታሰረችውን ፍየል ቀባት።

ያንን የአስማት መድኃኒት የፍየሏ ሙሉ ሰውነት ላይ ከቀባ በኋላ በትልቁ ከበሮ ውስጥ ያለውን የፈላ ውሀ እንድነካ ነገረኝ። ለመንካት ስሞክር እጀን በኃይል ስላቃጠለኝ "ቡጣም ያቃጥላል" አልኩት። ሁሉም ሳቁብኝ። ያ ረዳት ብዙ ቀዳዳዎች ያሉት ባልዲ ሰጠኝና ከጋለው ከበሮ ውስጥ የፈላውን ውሀ በባልዲው ወስጀ የታሰረችው ፍየል ላይ እንዳፈስ ነገረኝ። ባልዲው ብዙ ቀዳዳዎች ስላሉት ውሀውን ፍየሏ ጋ ማድረስ እንደማልችል ተናገርኩ። ከዚያ ያ ሰውዬ ባልዲውን ተቀብለኝና የፈላውን ውሀ ሞልቶበት መራት ላይ አንድ ጠብታ ሳይፈስ ፍየሏ ጋ አደረሰው። ወዲያው ያንን በባልዲ የሞላ የፈላ ውሀ ፍየሏ ላይ ሲያፈስባት በጣም የሚያስገርመው ነገር ፍየሏ ምንም የመቃጠል ሶሜትና ምልክት ሳታሳይ በእርታጋ መቆሟ ነበር። ፍየሏ የፈላው ውሀ የተመቻት ትመስል ነበር። ቀጥሎ ፍየሏን እንድነካት ተጠራሁና ስነካት የፈሰሰባት ውሀ እጅግ በጣም ቀዝቃዛ ነበር።

ይህንኑ ነገር ደግሜ እንድሞክር ተጠየቅኩ። ከከበሮው ውስጥ ውሀውን ቀዳሁና ባልዲው ብዙ ቀዳዳዎች እንዳሉት ስላየሁ ውሀው ወለሉ ላይ ጠብ እንዳይል በቀስታ እየተራመድኩ ወደ ፍየሏ ተጠጋሁ። ባልዲ ውስጥ ያለው ውሀ የፈላ መሆኑ በእንፋሎቱ ያስታውቃል። እኔም መጀመሪያ ስነካው እጀን ስላቃጠለኝ ሰሁለተኛ ጊዜ የፈላውን ውሀ ለመንካት አልሞከርኩም። ነገር ግን ያንን የፈላ ውሀ ፍየሏ ላይ ሳፈስባት ፍየሏ ምንም እንቅስቃሴ አላሳየችም። ውሃውን ከደፋሁባት በኋላ የፍየሏን ሰውነት ስነካው ግን ውሀው በጣም የቀዘቀዘ ነበር። ከዚያ ያ ሰው "ልብሶችህን አውልቅ፣ ልንቀቅልህ ነው።" አለኝ።

እንደታዘዝኩት አደረግኩ።

አይኖቼን በቀይ ጨርቅ ሸፈኑና ሌሎች የሚሸከሙኝ ሰዎች ተጠርተው ውሃ ያለበት ነገር ውስጥ ከተቱኝ። ሰውነቴ ውሀውን ሲነካ ውሀው እጅግ ይቀዘቅዝ ነበር። አይኖቼን የተሸፈነበትን ጨርቅ እንዳነሳው ተነገረኝና አይኖቼን ስገልጥ ራሴን ውሀ የቀዳሁበት እሳት ላይ የተጣደው ከበሮ ውስጥ አየሁት። ሰሶስት ሰአታት እንደምቀቀል ነገሩኝ። እኔም በዚያ ከበሮ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ቆየሁ። ባሰኛቸው ጊዜ ክዳኑን እየከፈቱ ይዘጉ ነበር። ከሶስት ሰአታት በኋላ ከዚያ ውጣሁና የታችኛውን የሰውነቴን ክፍል የምሸፍንበት ነጭ ልብስ ተሰጠኝና አሁን ወንድ ሆነህል አሉኝ። ያስገረመኝ ነገር ከከበሮው ውስጥ የሚወጣው እንፋሎት ብቻ መሆኑ ነበር። በኋላ ላይ ነጭ ዶሮ ታረደና ያንን መስዋዕት በሶስት የተለያየ መለዊያ ለሶስት ጣዖታት ማቅረብ ይጠበቅብኝ ነበር።

@Amharicbookstore

የብረት፣ የነጐድጓድ፣ የመብረቅና የውሀ አማልክት

የታችኛውን የሰውነቴን ክፍል የሸፈነውን ነጭ ጨርቅ ብቻ እንደለበስኩ ያለ ጫማ ወደ ጫካ ውስጥ ተራመድኩ። በአንድ እጄ የዶሮውን መስዋዕት በሌላ እጄ ደግሞ እነሰ ያለ የዛፍ ቅርንጫፍ ይዣለሁ። የማህበረሰቡ መሪ ወደ ብረት አምላክ ሊመራኝ ስለፈለገ ሌሎቹን ሰዎች ከኋላው እንዲከተሉት ትዕዛዝ ሰጠ። የብረት አምላክ ጋር ስንደርስ ይህ አምላክ ስላሰው ልዩ ኃይል ተነገረኝ። ከብረት አምላክ አጠገብ ለእርድ የተዘጋጀች እንዲት ፍየል ከዛፍ ጋር ታስራለች። ይህ የብረት አምላክ ከብረት የተሰራ ነው።

የቡድኑ መሪ "ይህ የብረት አምላክ ዲያብሎስ ነው፣ ሰዲያብሎስ መስዋዕት ካቀረብክ የምትፈልገውን ሁሉ ይሰጥሀል።" አለኝ። ዲያብሎስ ከተባለው አጠገብ እንደቆምኩ ሁለት ሰዎች አንድ ውሻ ይዘው መጡ። አንደኛው ሰው የውሻውን ጭንቅላት ሲይዝ ሌላኛው ሰው ደግሞ የኋላ እግሮቹን በመያዝ በብረት አምላክ ተቃራኒ እንዲቆም አደረጉ። ስለት የያዘ አንድ ሰው የውሻውን ጭንቅላት ሲቆርጠው የውሻው ጭንቅላት ልክ በማሜኔት እንደተሳበ ሁሉ በብረት አምላክ ላይ ወደቀ። ለብረት አምላክ የውሻ መስዋእት ከቀረበ በኋላ መሀላ እንድፈፅምና የብረት አምላክ ብለው ከሚጠሩት ዲያብሎስ የምፈልገውን እንድጠይቅ ተነገረኝ። የምፈልጋቸውን የትንቢት፣ ተአምራት፣ ገንዘብና የመሳሰሉትን ሁሉ ተናገርኩ። በመጨረሻ ስምምነቴን በቅል ውስጥ የያዝኩትን የዶሮ ደም እጄ ላይ በማፍሰስ ገለፅኩ። በውሻው ጭንቅላትና በብረት አምላክ ላይ የዶሮውን ደም

እያፈሰስኩ "የብረት አምላክ የምትፈልገውን ውሰድና የምፈልገውን ስጠኝ።" የሚሉትን ቃላት እንድናገር ተነገረኝ።

ከዚያ ወደሚቀጥለው የነጐድጓድና የመብረቅ አምላክ መሰዊያ ሄድኩ። ይህ አምላክ በእንጨት ቅርፆች የተሰራ ሲሆን በሰዎች ቤት ውስጥ በድንገት የሚነሳ እሳትና በተለያዩ ቦታዎች ሰዎችን የሚመታ መብረቅ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። በእንጨቱ ቅርፅ ላይ ደም ሳፈስ የክፉ ኃይል መገኘት ስለተሰማኝ ፀጉሬ ሲቆም ታወቀኝ። በዚህ የእንጨት ቅርፅ ላይም ደም እያፈሰስኩ ጥቂት መሀላዎችን ማድረግ ነበረብኝ።

የመጨረሻው መሰዊያ ትንሽ ወራጅ ወንዝ አጠገብ ሲሆን ወደ ትንሿ ወንዝ እንድገባና የቀረውን ዶሮ ደም ሰውነቴ ላይ እንዳፈስ ተነገረኝ። በዚያ የወንዝ ውሀ እየታጠብኩ የውሀውን መንፈስ እንድጠራ ታዘዝኩ። የውሀ መንፈስ በሌት ዖታ የምትጠራ ናት። የሁሉም እናት የሆነችና አኒታ ተብላ የምትጠራ ሲሆን፣ ስሟን ስጠራ ከእርሷ የምፈልገውን መጥቀስና ከዚያ የማማከሪያ ቤት የተሰጡኝን ህግጋት ሁሉ ለመከተል መሀላ አቀረብኩ። በመቀጠል በወንዙ ውስጥ መታጠቤን ጨርሼ ውጣሁና መሬቱ ላይ በደረቴ ሰጥ ብዬ እንድተኛ ተደረግኩ። እንደተጋደምኩ አንድ ሰው ግራ እጄን ሳብ አደረገና በምላጭ እጄን ከመዳፌ ስር ሶስት ቦታ ላይ በጣና ደሙን በሶስት ትናንሽ የባህር ሼሎች ላይ አንጠባጠበ። ደሙ በሼሉ ውስጥ እንደገባ ትናንሾቹን ሼሎች በነጭ ላባ በተሸፈነ ቅል ውስጥ እንዳደርግና ቅሉን ከድኜ ወንዝ ውስጥ እንዳስቀምጥ ታዘዝኩ፤ እንደታዘዝኩት አደረግኩ።

@Amharicbookstore

ቅሉ በውሀው ላይ እየተንሳፈፈ ሲሄድ ስመለከት ውስጡ የእኔ ደም እንዳለበት ስለማውቅ ወንዙ ደሜን ወዴት እየወሰደው ይሆን ስል አሰብኩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወንዙ ቅሉን እየገፋ ወደ ዳር ሰላወጣው ቅሉን እንዳመጣ ተነገረኝ። ካመጣሁት በኋላ እንድከፍተው ታዝዤ ቅሉን ስከፍት ደም የተደረገባቸው ሶስቱ ሼሎች የሉም።

ቅሉ እንደተከደነና ወንዙ ላይ ሲንሳፈፍ እንዳይፈስ በቀይና ነጭ ጨርቅ በደንብ ታስሮ የነበረ በመሆኑ ሼሎቹ አለመኖራቸውን ስመለከት በጣም ደነገጥኩ። ያንን ሚስጥራዊ ቅል ወንዙ ዳር ባለው አሸዋ እንድሞላው ተነገረኝ። ባዶ ጠርሙስ ሰጡኝና በወንዙ ውሀ እንድሞላው ተደረገ። ከዚያ በአሸዋው ላይ የዶሮው ደም ተረጨ። የሚያዋርሰኝ ሰው ግራ እጁን በመጠቀም ውሀውን መልሶ ወደ ወንዙ እየረጨ "አኒታ በእጄ ውሀ ጠራሁሽ በእጄ የዶሮ ደም መገብኩሽ ከዛሬ ጀምሮ "ሞካዶን" (እኔን) ታገለግይዋለሽ እርሱም ያገለግልሻል።" አለ።

ወዲያው ቅሉን ከደነና ሀገሬ ስገባ ይህንን ቅል በአካባቢው በሚገኝ ትልቅ ወንዝ አጠገብ ለአንድ ምሽት ሙሉ እንዳስቀምጠውና በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ቅሉን ሳንሳ የውሀ መንፈስ የሆነችውን የአኒታን ኃይል መግዛቴን ለማሳየት ጥቂት ሳንቲሞችን ወደ ወንዙ እንድጥል ታዘዝኩ። በመቀጠል የነጭ ዶሮ ደም በወንዙ ውስጥና በቅሉ ውስጥ እንዳደርግ ተነገረኝ። ከወንዙ ዳር ጥቂት ይቃቅ አሸዋ ወስጄ ቅሉ ውስጥ ካለው አሸዋ ጋር እንዳደባልቅና ቅሉ ውስጥ ካሉው አሸዋ ደግሞ በግራ እጄ ጥቂት ዘግኜ ወደ ወንዙ እንድበትን ተነገረኝ።

በጣም አስፈላጊ የሆነው ትዕዛዝ በቅሉ ውስጥ ያለው ኃይል መቀመጥ ያለበት ሀገሬ ላይ መሆኑን ነው። ከዚያ ቀይ፣ ሰማያዊና

ነጭ ቀለም ያላቸው ሶስት የተለያዩ ጨርቆች እንድገዛ ተነገረኝ። እነዚህ ጨርቆች በተለየ መንገድ መደርደር ነበረባቸው። ሰማያዊው ጨርቅ ወለሉ ላይ የሚቀመጠው የመጀመሪያው ጨርቅ ሲሆን የሚያመለክተውም አሁን እኔ ከባህሩ መንፈስ (የአኒታ ኃይል) አካል መሆኔን ነው። ቀዩ ጨርቅ በሰማያዊው ጨርቅ ላይ የሚደረብ ሲሆን ይህም የሚያሳየው ለአኒታ ኃይል መስዋዕት የሚያቀርበው ግራ እጄ መሆኑን ነው። በቀዩ ጨርቅ ላይ የተለያዩ ሀገራት የገንዘብ ኖቶች ማስቀመጥ ያለብኝ ሲሆን የነዚያ ሀገራት ሰዎች ወደኔ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ የማዘዣው መንገድ የነዚያ ሀገራት ትላልቅ የገንዘብ ኖቶችን በቀዩ ጨርቅ ላይ ማስቀመጥ ነው። ቅሉ በነጭ ጨርቅ የሚሸፈን ሲሆን ይህም ማንም የተለየ ኃይል እንደምጠቀም እንዳይጠረጥር ለማድረግ ሽፋንና ክልከላ የሚያደርግና በዚህ ምክንያት ሰዎች ንቁህና የፀዳሁ እንደሆንኩ እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው።

የሚያዋርሰኝ ሰው ሌሎቹን ነገሮች በራሴ የምማራቸውና የምረዳቸው መሆናቸውን ነገረኝ። በይፋ ለዚህ ቅል ውስጥ ላሰ ኃይል ተላልፌ ለመሰጠት ስዘጋጅ ቅሉን ከእኔ ተቀብሎ በሁለት እጆቹ በመያዝ ደረቱ ላይ ሶስት ጊዜ አጋጨና መልሶ ሰጠኝ። እኔም እንደታዘዝኩት ቅሉን በሁለት እጆቼ ይዤ ሶስት ጊዜ ከደረቴ ጋር አጋጨሁ። ቅሉን መሬት ላይ እንዳስቀምጥ አደረገኝና በግራ እጁ ግራ እጄን ጨበጠኝ። ግራ እጁ ከመዳፉ ስር ልክ እንደኔ ሶስት በምላጭ የተበጣ ምልክት አለው። በመጨረሻ እጄን ሶስት ጊዜ ሳመ እኔም እንደዚያው አደረግኩ። ምሽት ሲመጣ የመጀመሪያውን ሚስጥራዊ ተዋርሶ መጨረስ ችለን ነበር።

@Amharicbookstore

መንፈሳዊ አባት ወይም `አባቴ`

ከዚያ ወንዙን ሰቀን ወደ መሬት ስንመለስ ሹማምሌው የውሀው መናፍስት መሰዋዕቴን እንደተቀበሉና ስራዬን የሚባርኩልኝ እንደሆነ ያም ጥሩ ምልክት እንደሆነ ነገሩኝ። ወደ መንደሩ ስንመለስ ስለዚህ የተለየ ቦታ የሰማሁትን ሁሉ ማመን ጀምሬ ነበር። ያየሁት ሁሉ የማታለያ ዘዴ ሳይሆን ከሆኑ ኃይላት ጋር መናፍስታዊ ግንኙነት እንደነበረ አመንኩ። በሚስጥራዊ ማህበረሰቡ ተቀባይነት ስላገኘሁና ስለተዋረስኩ አሁን `ልጅ` እንደሆንኩና በአምልኮው `ካታ-ካታ` የሚል ስም እንደተሰጠኝና በዚህ አምልኮ የዘር ቆጠራ ውስጥ እንደገባሁ ተነገረኝ። ነቢይ ሆኜ በቤተክርስቲያን ሳገለግል የምታውቀው ነቢይ ካታካታ ተብዬ ይሆናል። የአምልኮ ቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች በመንፈሳዊ የዘር ቆጠራ ያምናሉ። ያስተዋውቃሉ። በአምልኮ ማህበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች በዚያ አምልኮ ቡድን ላዋረላቸው ሰው ልጅ ይሆናሉ። በዚህ መንፈሳዊ የዘር ቆጠራ ውስጥ አንድ ሰው መንፈሳዊ አባትን ሰመንፈሳዊ መፍትሄና ምሪት ሲያማክር በአምልኮው ውስጥ መንፈሳዊ ተዋርሶውን የሚያዘጋጀው ፓስተሩ ወይም ነብዩ ነው።

በአምልኮው ውስጥ የተዋረሰ ልጅ በተዋረሰበት ቅጽበት መንፈሳዊ አትብት ብለን የምንጠራው ነገር ያገኛል። በተፈጥሮ አንድ ህፃን የሆነ እድሜ ላይ ሲደርስ እትብቱ ተቆርጦ ይወድቃል። ይህ የማደግ ምልክት ነው። በመናፍስቱ አለም ውስጥም በቀጥታ ከመንፈሳዊ አባት ወይም እናት ጋር የሚያገናኘን መንፈሳዊ እትብት አለን። በመናፍስቱ ግዛት ማንም ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም።

አንድ ሰው ወይ ከእግዚአብሔር መንግስት አሰዚያም ከጨለማው መንግስት ጋር መሆን አለበት።

በጨለማው መንግስት ውስጥ በመንፈሳዊው ተዋርሶ አዲስ ልደት ያገኛል። በጥንቆላ ስራ ውስጥ ስትዋረስ አንተን ከሚያዋርስህ ሰው ውስጥ ካሉ አጋንንቶችና መናፍስቶች ጥቂቶቹ ወደ አንተ ውስጥ ይገቡና ሰውነትህ የነዚህ አዳዲስ የተወለዱ አጋንንት ማደሪያ ይሆናል። ይህ አጋንንት የመንፈሳዊ አባቱን ወይም እናቱን ድምፅ ሲሰማ ወይም ሲያያቸው በአክብሮት ዝቅ ይልላቸውና መንፈሳዊ መሪውን አባባ ወይም አማማ ብሎ ይጠራል። ይህ የሚሆነው ደካማው አጋንንት ከትልቁ አጋንንት ጋር በመንፈሳዊ ገመድ ስለሚገናኝ ነው።

የሚስጥራዊ ማህበረሰብ አባላትና የአምልኮ ቡድን ወይም ጥንቆላን የሚለማመዱ ፓስተሮች እነዚህን መንፈሳዊ ልጅ፣ መንፈሳዊ አባትና መንፈሳዊ እናት የሚሉትን ተመሳሳይ የጥንቆላ ማዕረጎች ይጠቀማሉ። ይህ አጋንንታዊ መንፈሳዊ ቤተሰብ ሲሆን ጊዜ እየገፋ ሲመጣ መንፈሳዊ ልጆች በመንፈሳዊ ባሎች ጥቃት ሊደርስባቸው ይችላል። በእነዚህ የጥንቆላ ስራ በሚካሄድባቸው አብያተ ክርስቲያናት፣ የፕሮግራሙ ስርዓት እንደ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አይነት ሲሆን እውነተኛ ማንነታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመደበቅ ልክ እንደ ክርስቲያን ይሰብካሉ። እኔም የዚህ እንቅስቃሴ አባል የነበርኩ በመሆኔ አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባላት በጥንቆላው መንግስት በዘይት፣ በውሀ፣ በማር፣ በሻማ፣ የተዋረሱ እንደሆኑና በአብዛኛው ያዋረላቸውን የዚያ የአምልኮ መንግስት አባል

@Amharicbookstore

ፎቶ ያለበትን የቤተ ክርስቲያን ልብስ እንደሚለብሱ አውቃለሁ። የነዚህን የተጠቀሱትን ነገሮች የሚጠቀሙ አባላት ነገሮችን በህልም ማየት ይጀምራሉ። ከእነዚህ መንፈሳዊ ህልሞች አብዛኞቹ በነዚህ የአስማት/የጥንቆላ ውጤቶች በኩል ነፍሳቸው መናፍስታዊ ተዋርሶ እንዳደረገች የሚያረጋግጥ ነው። አዳዲስ የተዋረሱ አባላት ያዋረሳቸው ፓስተር ወይም የቤተክርስቲያኗ ነቢይ ልጅ በሚያደርጋቸው መናፍስት ይያዛሉ። በቁጥጥር ስር ይሆናሉ። አንድ ሰው አንድ ጊዜ የእማማ ወይም አባባ መንፈሳዊ ልጅ ከሆነ ያ ሰው በድግምት ተፅዕኖና ቁጥጥር ስር ነው ማለት ነው።

አባልነት

ከዚያ ወደነበርንበት ቤት ስንመለስ ውጪ የተገደለውን ውሻ ስጋውን ከአስማት መድሀኒት ጋር በማቀላቀል ለእራት አዘጋጅተውት ነበር። ከበላን በኋላ ለሁለተኛው ክፍል ተዋርሶ እንድጠብቅ ነግረው ጨለማ ክፍል ውስጥ አስቀመጡኝ። ሚስጥራዊ ማህበረሰብ ውስጥ ከመናፍስት ስዋረስ የመጀመሪያ ጊዜዬ በመሆኑ ስርዓቱ ብዙ በእድሜ የገፉ ሰዎችን የሚስብ በመሆኑና እንዳንዶችም "ዛሬ በዚህች ሀገር ውስጥ ኃይል እንዳለ ታያለህ" ስለሚሉ መላው የተዋርሶ ሂደት ህጋዊ እንደሆነ አምኜ ነበር። በዚያ ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ነጫጭ የለበሱ በእድሜ የገፉ ሰዎች በምድጃ ዙሪያ ተሰብስበው ወደቆሙበት ቦታ ተወሰድኩ። እዚያ ስደርስ ከሽማግሌዎቹ ጋር አብሬ ሆንኩና ዘፈኑ ባይገባኝም ጭብጨባቸውን ተቀላቀልኩ።

እዚያ ያለሁት ፓስተርና አስተርጓሚዬ ከሆነው ጓደኛዬ ጋር ሲሆን በነዚያ 12 ሽማግሌዎች መሀል ወጣቶቹ እኛ ብቻ ነበርን።

ከሽማግሌዎች ጋር እንድተዋወቅ ተደረገና መሀከላቸው በመግባት ከአንዱ ሰው ወደ ሌሳው ሰው እንድንቀሳቀስ ተደረገ። እነዚህ ሰዎች ጥቂት የአስማት መድኃኒት እያኘኩና ደረቅ ጂን (አልኮል) ፉት ይሉና ያኘኩትን የአስማት መድሀኒትና የአልኮሉን ቅልቅል ፊቴ ላይ እየተፉ እጆቻቸውን እኔ ላይ አድርገው በህይወቴ ላይ በረከት እንዳገኝ መረቁኝ። ምርቃታቸውን ከጨረሱ በኋላ ወደ ቤቱ ውስጥ እስክጠራ ድረስ እዚያ እነርሱ መሀል እንድቆይ ተነገረኝ። ቀጥሎ እጅ ላይ የሚደረግ መቁጠሪያ ግራ እጄ ላይ አደረጉልኝና በምፀልይበት ወይም መስዋዕት በማቀርብበት ጊዜ ሁሉ ይህንን መቁጠሪያ እጄ ላይ ማድረግ እንዳለብኝ አዘዙኝ። ይህ መቁጠሪያ የዚህ ቡድን አባል ለመሆኔ ምልክት ነበር።

ሰዎችን መሳብ

በሚቀጥለው ጠዋት መንደሩን ለመልቀቅ ስንዘጋጅ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ጎጆዋ ውስጥ እንድገባ ተጠራሁ። ገብቼ የአምልኮውን መሪ ባባሎላን እየተመለከትኩ ተቀመጥኩ። ወዲያው ወደ ሀገሬ ስመለስ የቻልኩትን ያህል ብዙ መመልመል እችል እንደሆነ ጠየቁኝ። ይህ ለእኔ የሚሰጠኝ ሚስጥራዊ ተልእኮ ከሆነ ገና ጀማሪ በመሆኔና በሀገሬ የተከበርኩ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንኩ ተደርጐ ስለሚታወቅ ሌሎችን ለመመልመል እንደሚያስችግረኝ ነገርኩት። ሽማግሌው ሲመልስልኝ ፈጣን እድገት እንዲኖረኝና በኃይል ታላቅ ለመሆን ብቸኛው መንገድ ብዙ ሰዎችን ወደ እነርሱ ማምጣት መቻል እንደሆነ ነገረኝ።

@Amharicbookstore

ብዙ ሰዎች ባመጣሁ ቁጥር ብዙ ኃይል አገኛለሁ። በተጨማሪም የውሃዋ መንፈስ አኒታ ሌሎችን ወደሷ መንግስት በመላክ መብዛት እንደምትፈልግ አመለከተች። በሀገሬ ላይ ጋስተር በመሆኔ የማዋርሳቸውን ሰዎች መንፈሳዊ ልጆች ብዬ መጥራት ለእኔ ቀላል እንደሆነና ማንም ሊጠረጥረኝ እንደማይችል ነገረች። ከዚያ ሽማግሌው ሁለት የአስማት መድሀኒቶች ሰጠኝ። አንደኛው በግራ እጄ ያስያዘኝ "አሼ" በሚባል ጠንካራ የአስማት መድሀኒት የተሞላች አንዲት ትንሽ ጥቁር ቀንድ ስትሆን፣ በትንሹ ምላሴ ላይ ሳደርገው ሰዎች ሁሉ ብእኔ አገልግሎት ስር እንዲሆኑ ሰማድረግ የሚጠቅም ነበር። ሁለተኛው ስጦታ ደግሞ ሰዎችን ወደኔ ቤተክርስቲያን የሚስብ ከጠንካራ የአስማት መድሀኒት ጋር የተቀላቀለ የአሳማ ጭንቅላት ነበር። ሽማግሌው ከአስማት መድሀኒቱ ትንሽ ቆንጠር አድርጎ ሰጠኝና ጎጆዋ አጠገብ ያለ ዛፍ ላይ በመቀባት አንድሞክረው ነገረኝ።

እንደተነገረኝ አደረግኩና ተቀምጬ ያ ዛፍ ምን እንደሚሆን ሰማየት መጠበቅ ጀመርኩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንዲት ዳክዬ ወደ ዛፉ ስትራመድ አየሁ፣ ከእርሷ ተከትለው ሌሎች ዳክዬዎችም መጡና እዚያ ዛፍ አጠገብ ሲደርሱ ቆሙ። ውፍጪ የነበሩ ጥቂት ሰዎችም ወደዛፉ ሄደው ዛፉ ስር ቆመው ማውራት ጀመሩ። በአካባቢው የነበሩ ውሾች ሳይቀሩ በዚያ ዙሪያ ሆኑ። ሽማግሌው ይህንን የአስማት መድኃኒት ሀገሬ እንደደረስኩ ወዲያውኑ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ መቅበሬን እርግጠኛ መሆን እንዳለብኝ ነገረኝ። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ታሪኩ የተፃፈለት ኖህ እነዚያን ሁሉ እንሰሳት ወደ መርከቡ እንዲገቡ ያደረገው ይህንን የአስማት መድኃኒት ተጠቅሞ ነው አለ ሲል ቀለደ። ሁላችንም ሳቅን። ይህ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ የሚያውቅ በመሆኑ ምናልባት ከዚህ በፊት ጋስተር የነበረ ሊሆን እንደሚችል ጠረጠርኩ። ሽማግሌው ሲነግረኝ ይህ

ሰዎችን የሚስበው የአስማት መድኃኒት ጫካ ውስጥ አጋዘን ለመያዝ ለተቸገሩ የሰለጠኑ አዳኞች ከሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ አዳኞች ይህንን መድኃኒት ወስደው አንዱ ዛፍ ላይ ቀብተውት ከሄዱ በኋላ በሚቀጥለው ቀን ሲመለሱ ብዙ አጋዘኖች በዛፉ ዙሪያ ተሰብስበው እንደሚያገኙ ነገረኝ። በመጨረሻም ከሰጠኝ የአሳማ ጭንቅላት ጋር የሚመሳሰል እንደሆነ ነገረኝ።

በመጨረሻ ከፀለየ በኋላ መልካም መንገድ ተመኘልኝ። አርፈንበት ወደነበረው የእንግዳ ማረፊያ በንመለስ ከእነዚህ አምልኮዎች ጋር ያስተዋወቀኝ ጓደኛዬ ባገኘሁት ነገር ረክቼ እንደሆነ ጠየቀኝ። ያደረግኳቸው የተዋርሶ ስርዓቶች ሀገሬ ላይ በጣም ኃያል እንደሚያደርጉኝ እርግጠኛ ሆኗል። በዚያ እንግዳ ማረፊያ ጥቂት ቀናት እንደቆየን የአሳማው ጭንቅላት በስብሶ በጣም መሽተት ጀመረ። ሽታው የሚያስቀምጠን አልሆነም። የእንግዳ ማረፊያው አስተዳዳሪ ስለሽታው ማጉረምረም ሲጀምር ይህንን የሚሸት ነገር የአስማት መድኃኒት ይዤ ወደ አየር መንገድ መሄድ እንደማልችል አውቄያለሁ። ወዲያው ለጓደኛዬ የደህንነት ሰዎች ሊፈትሹን ስለሚችሉ ይህንን ነገር እንዴት አድርገን ወደ አየር መንገዱ ይዘን እንደምንሄድ ጠየቅኩት። ጓደኛዬም ደፋር መሆን እንዳለብኝና ሽታው የእኔ ስም ከናይጄሪያ እስከ ደቡብ አፍሪካ የሚታወቅ የመሆኑ ምልክት እንደሆነ ነገረኝ። ስላለንበት ሁኔታ የተጨነቀ ስላልመሰለኝ ኃይል የሌለኝ እንደሆንኩ ተሰማኝ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመመለስ ተዘጋጀን። አውሮፕላን ውስጥ ስንገባ ሽታው እጅግ አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም ስለዚህ ሽታ ማንም የጠየቀ አለመሆኑ አስገረመኝ። ወደ አእምሮዬ የመጣው ነገር ጓደኛዬ ለፊታሾቹ ጉቦ ከፍላቸው ይሆናል

@Amharicbookstore

የሚል ነበር። በመጨረሻም አብራሪው ታምቦ አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሰን ሲናገር እኔና ጓደኞዬ ያንን የሚሸት እሽግ እንደያዝን ትዕግስት በማጣት ተቀምጠን ነበር። ብዙ ሰዎች ስለ ሽታው እያጉረመረሙ ቢሆንም ማንም ወደኛ ለመጠጋት ወይም ለበረራ ባለሙያዎች ቀርቦ ለመናገር ድፍረት ስላልነበረው ምንም አልሆንንም። ምናልባት የብረቱ አምላክ በእኛ ላይ ምንም አይነት ወቀሳ ለማቅረብ ቃል እንዳይተነፍሱ አእምሯቸውን ዘግቶ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።

ከአውሮፕላኑ ስንወርድ የሚሸተውን እሽግ፣ ቅሱንና ጥቁሩን ቀንድ መያዝ ነበረብኝ። ጓደኞዬ ስለምንም ነገር እንዳልጨነቅና ይህንን አይነት ነገር የምይዘው እኔ ብቻ እንዳልሆንኩ እንዲሁም የአየር መንገዱ ሰዎችም ምንም ሊያደርጉኝ እንደማይችሉ በመተማመን ነገረኝ። የታምቦ አለምአቀፍ አየር መንገድ በጣም ጠንካራ ፍተሻ እንዳለው ስለማውቅ የገባሁበት አደጋ ከባድ እንደሆነ ገብቶኛል። ምንም አይነት ህገወጥ ነገር ያልያዝኩ ቢሆንም እንኳን የሚሸተው የአሳማ ጭንቅላት ሽታ አሳስፈላጊ ትኩረት እንደሚስብና ሊፈትሹ ቢያገኙት የምታወቀው ፓስተር በመሆኔ ስለሆነ በጣም ትልቅ ቅሌት ይሆናል። ጉዞዬ ጭንቀት የተሞላበት በመሆኑ እስከደርስ ድረስ እረፍት አልተሰማኝም ነበር።

ወደ መፈተሻው ስንገባ ሁለት ፖሊሶች አቆሙንና ጥያቄዎች ሊጠይቁን ሲጀምሩ፣ እኔ የጤና ችግር ስለነበረብኝ ባህላዊ ህክምና ለማግኘት ናይጄሪያ ሄደን እየተመለስን እንደሆነ ነገርናቸው። ወዲያው ጓደኞዬ ጥቂት የአሜሪካ ዶላሮች ከኪሱ አወጣና ጫማውን እንደሚያስር አይነት ተንበርክኮ ዶላሮቹን በጫማው ስር ሲያስቀምጥ አየሁት። ወደ ሁለቱ ፖሊሶች ተመለከተና ማድረግ የሚጠበቅበትን

እንዳደረገና ጫማው ስር ገንዘብ እንዳስቀመጠ ለማመልከት አንድ አይኑን በመጨፈን ጠቀሳቸው።

እኔ ግን በጣም የተረጋጋሁ ለማስመሰል ብሞክርም በህይወቴ እንደዚያ ፈርቼ አላውቅም። ኩተያዝኩ ዜናው የፓስተርነት ስራዬን ሙሉ በሙሉ ያጠፋዋል። ከዚያ ሁለቱ ፖሊሶች "ፓስፖርትህን ብንመረምር ችግር እንደምናገኝበት እናውቃለን።" እያሉ መቀለድ ጀመሩ። እኛም ገንዘቡን ወለሉ ላይ ትተን እየሳቅን አለፍን። ራቅ እንዳልን ዞሬ ስመለከት አንዱ ፖሊስ ወለሉ ላይ የተጣለውን ገንዘብ በጫማው ከቆመበት በኋላ በርከክ ብሎ ሲያነሳው አየሁ። ሁሉም ነገር በፍጥነት የተከናወነ ከመሆኑ የተነሳ ልክ የሁልጊዜ የስራው አንድ ክፍል የሆነ ይመስላል።

አየር መንገዱን ለቅቀን እየወጣን እያለም በጣም እንደተጨነቅኩ ነበር። ጓደኞዬ ግን ጀርባዬን መታ አደረገኝና "እትጨነቅ ፓስተር እነዚያን ፖሊሶች አውቃቸዋለሁ። መልካም ግንኙነት አለን።" አለኝ። ቶሎ ወጥቼ ወደ ቤተሰቤ ለመሄድ ስለቸኮልኩ ተጨማሪ ጥያቄ ልጠይቀው እንኳን አልፈለግኩም። በመጨረሻ አየር መንገዱን ለቀን ወጣንና ቀጥታ ወደ ቤት የሚወስደንን ታክሲ ያዝን። በዚያው ምሽት እኔ ወደማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የአሳማውን ጭንቅላት ቀበርን። ቀጥሎ ደግሞ ባዋረሰኝ ሰው እንደታዘዝኩት ቅሱን ወደ ወንዝ ወሰድኩ። በቤተክርስቲያን የጥንቆላ ስራ መጀመሪያዬ ይህ ነበር።

ከናይጄሪያ ከተመለስኩና የታዘዝኩትን ካደረግኩ በኋላ በነበረው የመጀመሪያ አሁድ ያየሁት ነገር ያስደንቀኝ ጀመር። ብዙ አባላት ያልነበራት ያቺ ትንሽ ቤተክርስትያን በአንድ ጊዜ በሰው ብዛት

@Amharicbookstore

ስትጨናነቅ ማየት የሚያስደንቅ ነበር። ከፕሮግራም መልስ ከባለቤቱ ጋር ወደቤት እያመራን ወደ ቤተክርስትያናችን ስለመጡ አዳዲስ ሰዎች ብዛት እያወራን እየተገረምንና እየተደነቅን ነበር። ባለቤቴ ምን እየተከናወነ እንዳለ ስላላወቀች ምንም አልጠረጠረችም። የአዳዲስ ምእመናን ባልተጠበቀ ሁኔታ የመምጣትን ሚስጥር የማውቀው እኔ ብቻ ነበርኩ።

አሁን የምናፍቀውን ታላቅ ነቢይ መሆን፣ ለምእመናኑ መተንበይ፣ በመንፈስ ሀይል እንዲወድቁ የማድረግ፣ ቅዱስ ውሀ፣ ዘይትና ሌሎች ነገሮችን በመሸጥ የመክበር ጥማቴ አውን የሚሆንበት ጊዜ እንደደረሰ አርግጠኛ ሆንኩ። ይህንን ፍላጎቴንና ተሰጥኦዬን ለማውጣትና ቤተክርስቲያኔን ለማሳደግ አፍሪካዊ ኃይል ለማግኘት ወደ ምስራቅ አፍሪካ ብዙ ማይሎች መንገዘ እንዳለብኝ ወሰንኩ። ይሁንና ባለቤቴ ግን እየቆየ በማሳያቸው እንግዳ ባህርያት እንዲሁም በምሄድባቸው ቦታዎች የማመጣቸውን የአስማት መድሀኒቶች የማስቀምጥበትና መሰዊያዎች የማዘጋጀበት ከእኔ በቀር ሌላ ማንም ሰው የማይገባበት ክፍል ማዘጋጀቴ ጥርጣሬ እንዲያድርባት በማድረጉ ጥብቃ ትጠይቀኝ ብሎም ነገሬ እንዳላማራት እያነሳች አረፍት ትነሳኝ ጀመር።

ምዕራፍ ስድስት

ዚምባቡዌ ቾፒንግ

ምስጋናና አምልኮ በቴምቢሳ

ሀገራችን ውስጥ በጣም ሰው ከሚበዛባቸው የከተማ ክፍሎች አንዱ በሆነው ቴምቢሳ ስላሰ አንድ ዚምባብዌያዊ ነቢይ ሰሰማ፣ ወደ ቴምቢሳ ሄጀ ይህንን ሰምች እባብ፣ አንሽላሊት፣ አሳና ሌሎች እንግዳ ነገሮች እንዲያስመልሱ የሚያደርገውን ሰው ለመገናኘት ወሰንኩ። ይህ አፍሪካዊ ነቢይ ወደየሚገኝበት ቤተክርስቲያን ስደርስ ነጭ የቤተክርስቲያን ልብስ ለብሶና ግንባሩ ላይ ነጭ መስቀል ያለበት ቀይ ጨርቅ አስሮ ነበር። ወደ እርሱ ስራመድ ልክ እንደሱ ነጭ ከለበሱ የቤተክርስቲያኑ አባላት ጋር እየተነጋገረ ነበር። ከእርሱ ጋር ይህንን ቀጠሮ ለመያዝ በስልክ ተገናኝተን ስለነበር ወደኔ ቀረበና ፓስተር ማክዶ መሆኔን ጠየቀኝ።

@Amharicbookstore

ቀጥሎ ፊቴን ወደ ፀሀይ አዙሬ እንድንበረከክና ውሀ ካለበት መያዣ ውስጥ እንዲት ትንሽ ለስላሳ ድንጋይ እንድወስድ አዘዘኝ። ከዚያ ጭንቅላቴን ነካና የተለየ ቋንቋ በመጠቀም መፀለይና መናፍስቶችን መጥራት ጀመረ። ምንም ያህል የማይመች ስሜት እንዲሰማኝ የሚያደርጉ ለየት ያሉ ድምፆችን ቢያሰማም፣ ኃያል መሆኑን ለማረጋገጥ ከእርግማን ሊያነፃኝ እንደሆነ ስለነገረኝ መፀለዩን እንዲቀጥል ወሰንኩ። ከዚያ ይህ ነቢይ እዚያው ያለንበት አደባባይ ላይ ሽሚዜን እንዳወልቅ አዘዘኝ። ያለሁት ከአካባቢዬ ርቄ በመሆኑና እዚህ ማንም ስለማያውቀኝ እንደታዘዝኩት አደረግኩ። ከዚያ ውሀ አምጥቶ ሶስት ጊዜ ሆዴ ላይ ረጨኝና ሆዴን በጥሬ መታኝ። ቀጥሎ "ሆድህ ውስጥ የሆነ ነገር አለ። ሚስትህ አንተን በቁጥጥሯ ስር ለማድረግ ከምግብ ጋር ቀላቅላ መድኃኒት ሰጥታሀለች።" አለኝ። ሚስቴ እግዚአብሔርን የምትፈራ ንፁህ ሴት እንደሆነች ስለማውቅ በትንቢቱ ሳቅኩ። ብዙ ቦታ እየሄድኩ ከጀርባዋ የአስማት መድኃኒት የምጠቀመው እኔ እንጂ እሷ ምንም አይነት የአፍሪካ የአስማት መድኃኒቶች እንደማትጠቀም አውቃለሁ። ቀጥሎም ይህ ነቢይ "ፓስተር ማካዶ፣ ባለቤትህ አደገኛ ሴት ናት።" አለኝ። ይህ ነቢይ በዚህ የፈጠራ ትንቢቱ ሚስቴን እያዋረዳት ነው ብዬ ስላሰብኩ ከእርሱ ጋር በነበረኝ ግንኙነት ላይ ፍላጎት አጣሁ። እውነተኛና ሀሰተኛ አስተምህሮዎችን መለየት የቻልኩበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን ይህ በአለባበሱ ቅዱስ ከሚመስለውና በሚያስፈራና በተለየ ቋንቋ ከሚናገረው ሰው ጋር መጣላት ስላልፈለግኩ ዝም አልኩ።

ትንቢት መናገሩን ከቀጠለ በኋላ ሆዴን ቆንጥጦ ይዞ በኃይል ሲጮትተኝ አንዲት ትንሽ እንሽላሊት እጁ ላይ ስትወድቅ አየሁ።

ይህቺ እንሽላሊት ሆዴ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየች እንደሆነችና በህይወቴ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ እንዳላገኝ የዘጋችብኝ ይህቺው እንሽላሊት እንደሆነች ነገረኝ። ይህ ነቢይ ዝም ብሎ ታሪኮችን እየፈጠረ መሆኑን አውቄያለሁ። ነገር ግን ወደ እርሱ የመጣሁት ኃይል እንዲሰጠኝ ወይም ሰዎች አባብና እንሽላሊት እንዲያስመልሱ የሚያደርገውን ዘዴ እንዲያስተምረኝ ስለሆነ ያመንኩት ሰመምሰል ምክርኩ።

እንዳመንኩት ስላሰበ የሚቀጥለው ደረጃ ወደኔ ቤት መሄድና በጠላቶቼ የተተከሱ የአስማት መድኃኒቶች ቆፍሮ ማውጣት እንደሆነ ነገረኝ። ይህ ነቢይ እኔ ላይ ሊጠቀም እየሞከረ ያለውን ዘዴ አስቀድሜ እንደተማርኩ አላወቀም። ዘዴው በማውቃቸው አንዳንድ ነቢያት ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን አንድ ተአምር ያሳዩና ከዚያ ሰዎች እንደ ዘይት፣ ውሀ፣ ጨው፣ የመታጠቢያ ዱቄት ወይም ሰሆኑ ስርዓቶች ጥቅም ላይ የሚውሱ ዕቃዎች ያሉ መንፈሳዊ ነገሮች ለመግዛት ብዙ ገንዘብ መክፈል ወደሚቀጥሉበት ሁለተኛ ደረጃ ይመራሉ። ይህ ሰው ሁሉንም ነገሮች ነግሮኝ ሲያበቃ ለብቻው ላነጋግረው እንደምፈልግ ነገርኩት።

ከዚምባቡዌያዊው ነቢይ ጋር የግል ንግግር

አንድን መናፍስታዊ አሰራር የሚከተል ሰው ለማነጋገር አንድ ጠርሙስ ደረቅ ጂን መግዛት እንደሚገባ ስለተማርኩ፣ ብደንብ ለመነጋገር በአቅራቢያ ወደሚገኘው የገበያ ማዕከል በመኪና ሄድንና አልኮሉን ገዛሁለት። ጠርሙሱን ከፍቶ መጠጡን ተጉነጨና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ተሞክሮ ተረከልኝ። እዚያው ላይ ሀሰተኛ ነቢይ ሆኖ

@Amharicbookstore

እንደሚሰራ አረጋገጥኩ። መጠኑ አልቆ ጠርሙሱ ባዶ ሲሆን አንድ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ ጉባኤውን ለመያዝና ለማስደነቅ ሊጠቀምባቸው ስለሚችላቸው የተለያዩ ኃይላት ተነጋገርን።

ከአንድ ጠርሙስ የጠጣን በመሆናችን ገንዘብ በማስከፈል ከሰዎች አካል ውስጥ እንሽላሊቶች፣ እባቦች፣ አሳምችና ሌሎች ነፍስ ያላቸው ፍጥረታትን ማውጣት የሚቻልበትን ኃይል እንዴት እንደማገኝ ሲረዳኝ እንደሚችል ነገረኝ። ይህ ኃይል በውጤታማነት እንዲሰራ ሰውነቱ ውስጥ በመርፌ መግባት እንዳለበት አወራኝ። ከሆዱ ውስጥ እንሽላሊት ሲያወጣ ስላየሁ ይህ ሰው ስለሚናገረው ነገር የሚያውቅ እንደሆነ አመንኩ። በዚሁ ኃይል ከሰዎች ግቢ የሆኑ ነገሮችን ቆፍሮ የማውጣት ዘዴ መካን እንደምችልም ነገረኝ። ይህንን ኃይል በጣም ማግኘት ስለፈለግኩ፣ ለማግኘት ምን እንደሚያስፈልግ ጠየቅኩት። ይህንን ኃይል ማግኘት የምችልበት ብቸኛ መንገድ፣ ድንበር አቋርጦ ዚምባቡዌ ውስጥ ሚኒካላንድ ወረዳ ውስጥ ወደምትገኝ ቺፒንግ ተብላ ወደምትጠራ ትንሽ ከተማ መንዝ እንደሆነ ነገረኝ።

ቀጥሎ ይህ ነቢይ "አጭሩ ሰው ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀኝ። ሳቅኩና "ቶኮሱሺን ማለትህ ነው?" ስል ጠየቅኩት። "አዎ ልክ ነህ።" አለኝ። ይህ አጭሩ ሰው ተብሎ የሚጠራው ክፉ መንፈስ የእንሽላሊትና የእባብ ተአምራት ይሰራ እንደሆነና ሰዎች ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲፀልዩና ኢየሱስ ወይም የመንፈስ ቅዱስ አሳት ብለው ሲጮሁ "አጭሩ ሰው አይሮጥም ወይም ኃይሉን አያጣም?" ስል ነቢዩን ጠየቅኩት። "ብዙ ፓስተሮች ለመፈወስና ተአምራት

ለመሰራት አጭሩ ሰው ተብሎ የሚጠራውን ክፉ መንፈስ ኃይል በሚጠቀሙበት ጊዜ ‹አሳት› ብለው ይጮሀሉ።" አለኝ። ወደ ዚምባብዌ አብረን ለመሄድ የወሰንነው ያን ጊዜ ነበር።

ቺፒንግ መድረስ

ዚምባብዌ እንደደረስን ቺፒንግ ወደተባለችው መንደር የሚያደርሰንን አውቶቡስ ያዝን። ሰሾፈሩ ወደ ቺፒንግ እየሄድን እንደሆነ ስንነግረው በዚያ አካባቢ የተለየ በሆነ ኃይሉ በጣም የታወቀና የተከበረ ስለሆነው ጠንካራ መናፍስታዊ ኃይል ያለው ሰው ነገረን። ይህ ሰው እኛ እሱ እያወራለት ወዳለው ሰው እየሄድን መሆኑን አላወቀም። ይህ መናፍስታዊ ኃይል ያለው ሰው በአካባቢው ያሉ ባህላዊ ሀኪሞችን ጨምሮ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈራ ነው። ወደዚህ ታላላቅ ኃይላት አሉት ተብሎ ወደሚታመነው ሰው ቤት ለመድረስ አንዲ ትንሽ ወንዝ ማቋረጥ ነበረብን።

ቤቱ ስንደርስ ግቢው የምክር አገልግሎት ከሰጣቸው ሰዎች በስጦታ ባገኛቸው መኪናዎች የተሞላ ነበር። ብዙ ሰዎች ለሰራላቸው ስራ ምስጋናቸውን ለማሳየት የመኪና ስጦታዎች ሳይቀር ይሰጡታል። የደረሰነው መጨረሻ ላይ ስለነበረ ረጅም ወረፋ መጠበቅ ነበረብን። ወረፋ ከያዙት አብዛኞቹ የሀገሬው ሰዎች አይደሉም። ስልፉ ውስጥ ያሉት ጥቂቶቹ የሀገሬው ሰዎችም ይህንን ኃይል ያለው ሰው ለማግኘት ተራቸው እስኪደርስ ለቀናት ሲጠብቁ የነበሩ ናቸው።

እኛም በደረስንበት የመጀመሪያ ምሽት ልናገኘው ስላልቻልን ብርድ ላይ ማደር ነበረብን። ወረፋ ከሚጠብቁ ሌሎች ሰዎች ጋር

@Amharicbookstore

እንደተቀመጥን ሰምቼ ሞዛምቢክ ውስጥ ስለሚገኝና እዚህ ቺፒንግ ውስጥ ላለው እኛ ለመጣንበት ሰው መንፈሳዊ አባት የሆነ ሌላ ኃይል ያለው ሰው ሊያወሩ ሰማሁ። ይህ መንፈሳዊ አባት በጣም ኃይለኛ መንፈስ እንዳለው፣ አእምሯቸው የታመሙ ሰዎችን እንደሚፈውስና ሌሎች ከአእምሮ በላይ የሆኑ ተአምራት እንደሚያደርግ በጥንቃቄ አዳመጥኩ። በውስጤ ይህንን ሞዛምቢክ ውስጥ የሚገኝ መንፈሳዊ አባት ለማግኘት ገንዘብ ማግኘት አለብኝ አልኩ።

ረጅም ጊዜ ስንጠብቀው የቆየነውን ይህንን የቺፒንግ መንፈሳዊ አባት ለመገናኘት ተራችን ደረሰና ወደ ቤት ውስጥ ስንገባ ሰውየው "ሰዎች ብዙ ቶኮሱሺ (ሰዎችን ለማስጨነቅና ለማስቸገር ብሎም ለመግደል የሚላክ ድንክ የሆነ የውሀ ውስጥ ክፉ መንፈስ) እንዳለኝ ቢያውሩም እኔ ግን ምንም አይነት ቶኮሱሺ እንደሌለኝ አውቄ።" አለኝ። ወዲያው ከሩቅ ቦታ የመጣሁ በመሆኔ ለእኔ አሪፍ ስራ እንደሚሰራልኝ ነገረኝና በዚያው ምሽት ወደ መቃብር ስፍራ ወስዶኝ አንድ መቃብር እያመለከተኝ "ይሄ አዲስ መቃብር ነው።" አለኝ። እዚያው ላይ ልብሶቼን አወላልቄ የአስማት መድኃኒት በተቀላቀለበት ቀዝቃዛ ውሀ እንድታጠብ አዘዘኝ። መቃብሩ ላይ ቆሜ ከታጠብኩ በኋላ ሰውነቴን ሙሉ እያሳከከኝ ቢሆንም ሰውየው መቃብሩ ላይ እንድጋደም ነገረኝ። መቃብሩ ላይ እንደተጋደምኩ ድንገት እንደመደንዘዝ ብዬ ወዲያው እንቅልፍ ወሰደኝና ስለ አንድ ህፃን ልጅ ህልም አየሁ።

ስነቃ ሰውየው ልብሶቼን በሙሉ መቃብሩ ላይ እንዳስቀምጥ ነገረኝ። ከዚያ ልብሶቼን መቃብሩ ላይ ጥዬ ሰውየውን እየተከተልኩ

እርቃኔን ወደ ሰውየው ቤት ስራመድ ሀገሬ ቢሆንና እንደዚህ በሌሊት እርቃኔን ስሄድ ጉረቤቶቼ ቢይዙን ምን እንደሚከሰት እያሰብኩ ነበር። ቤት ከገባን በኋላ ሰውየው መቃብሩ ላይ የተኛሁ ጊዜ ምን እንዳየሁ ጠየቀኝ። ህፃን ልጅ እንዳየሁ ስነግረው መቃብሩ ከሳምንት በፊት የተቀበረ የስድስት ወር ህፃን መቃብር እንደሆነ ነገረኝ። ቀጥሎም "አሁን የምሰጥህ የሞተውን ህፃን መንፈስ ነው። ምክንያቱም ህፃን ስለሆነ መንፈሱ ከአንተ ብዙ ነገር አይፈልግም አለኝ። እንደዚህ አይነት ነገር እንደሚከሰትና እንደሚሰራ አስቤ ስለማላውቅ በድንጋጤ አይናቼ ፈጠጡ።

የሞቱ ትልልቅ ሰዎችን መንፈስ የሚጠቀሙ ሰዎች መንፈሶቹ በጣም ሀይለኛና ለማላመድና ለመቆጣጠር የሚያስቸግሩ በመሆናቸው በጣም እንደሚቸገሩ ነገረኝ። በአስቸጋሪ መንፈስ ምክንያት ብዙ ሚስቶች እንዲያገባ የታዘዘ ሰው አንዳለም አስረዳኝ። አንዳንድ ጋስተሮችም ይህንን የሞተ ሰው መንፈስ ለማረጋጋት ብዙ ሚስቶች እንደሚያገቡ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ መንፈሱ ተቆረጡ አስኪላቸው ድረስ ፀጉራቸውን እንዳይቆረጡ የሚገደዱ መሆናቸውን ሰማሁ። "የትልቅ ሰው መንፈስ አብረኸው ለመሆን ይከብዳል፣ የህፃን ልጅ መንፈስ ግን በጣም ቀላል ነው። የምታደርግለት ነገር ቢኖር ጣፋጮችና አሻንጉሊቶች መግዛት ብቻ ነው።" አለኝ። ይህ መንፈስ ያለበት ሰው የሚናገረውን ሁሉ ማመን ይገባኝ እንደሆነ አላወቅኩም። ምክንያቱም የሚላቸው ነገሮች በድራማና በፊልም የሚሆኑ ብቻ የሚመመስሉ ናቸው። ስለዚህ በጥርጣሬና ባለማመን እየተመለከትኩት ነበር።

@Amharicbookstore

ከዚያ ወደ ክፍሉ ገባና የሆነ ነገር አዚጋጀልኝ። ያዘጋጀልኝ ላዩ ላይ በጥሩ ሁኔታ የተሰራ ንድፍ ያለበትና በውስጡ የሆነ ነገር የያዘ ትንሽ የቆዳ ቁራጭ ኪሴ ውስጥ ከተተልኝና እዚህ ቁራጭ ቆዳ አጠገብ ሁልጊዜ ከበቆሎ የሚሰራ ሚሌ ሚል የሚባለውን ምግብ እንዳስቀምጥ አዘዘኝ። በተጨማሪም ትንሽ ጥቁር ፈሳሽ የያዘ ብልቃጥ ሰጠኝና ትንሽ አበባ በመትከያ ውስጥ አድርጌ ቤት ውስጥ እንዳስቀምጠውና ብልቃጡ ውስጥ ያለውን ጥቁር ፈሳሽ በአበባው መትከያ ዕቃ ውስጥ እንድጨምርና ለአበባው ስም እንድሰጠው አዘዘኝ። ምክንያቱም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ የትንሹ ልጅ መንፈስ በዚያ አበባ ውስጥ እንደሚኖርና አበባው ሲያድግ መንፈሱም አብሮ እንደሚያድግ ነገረኝ። አበባው ከጠወለገ ደግሞ በዚያው አፈር ሌላ አበባ መትከል እንዳለብኝ ተነገረኝ። ለአበባው ትኩስ ውተት እንድሰጠውና በሳምንት አንድ ጊዜ ውሀ እንዳጠጣው እንዲሁም አጠገቡ ጣፋጮች እንዳስቀምጥለት ነገረኝ። ስለ ትኩስ ወተት ሲናገር ለአባቴ በየቀኑ ትኩስ ወተት የሚሸጥ አንድ ቤተክርስቲያን ትዝ አለኝ። ነገር ግን ይህ ሰው እየተናገራቸው ያሉት ነገሮች ከአእምሮዬ በላይ ስለሆኑ ሀሳቡን ወደ ጐን ገፋሁት።

የተሰጡኝን ብልቃጥና በቁራጭ ቆዳ ውስጥ ያሉ ሀይሎች ይዤ ከቺፒንግ ወደ ሀገሬ ስመለስ ከሌሎች ሀገራት ያገኘኋቸውን ኃይላት ለአዳዲሶች ማስተዋወቅ እንዳለብኝ እርግጠኛ ነበርኩ። ከዚያ ነጭ ሳህን ላይ ከበቆሎ የሚሰራውን ምግብ አደረግኩና ቁራጩን ቆዳ ሳህኑ አጠገብ አስቀመጥኩ። በዚያ ምሽት ብቻዬን ተቀምጬ ቴሌቭዥን እየተመለከትኩ የህፃን ልጅ ለቅሶ ይሰማኝ ጀመር። ህፃኗ ልጅ እያለቀሰች መስሎኝ ለማየት ስሄድ ልጄ ከእናቷ ጋር ተኝታለች።

እንቅልፍ ወስዷታል። የህፃን ለቅሶ እንደገና ሲሰማኝ ግራ ተጋባሁ፣ በኋላ ግን ከቺፒንግ ያመጣሁት የህፃን ልጅ መንፈስ መሆኑን አስታወስኩና በአበባ መትከያው ውስጥ በተከልኩት አበባ ላይ ትኩስ ወተት አፈሰስኩ። በሚቀጥለው ቀን ከበቆሎ የተሰራውን ምግብ ያስቀመጥኩበትን ሳህን ስመለከት ባዶ ነበር።

ራሴን ያስገባሁበት ህይወት በፍርሀት፣ በስጋትና በሚስጥራት የተሞላ ነበር። አንድ መናፍስታዊ አሰራር የሚጠቀም ሰው ፍርሃቴንና ስጋቴን ለማሸነፍ የአልኮል መጠጥ ማለትም ደረቅ ጂን እንድጠቀም ስለመከረኝ እኔም አልፎ አልፎ እንደዚያ ማድረግ ጀመርኩ።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ ሰባት

ሞዛምቢክ

በጠንቋይ የተቀደሰ ስፍራ

በእኔ ቤተክርስቲያን ውስጥ አልፎ አልፎ ሰምክር ይመጣ የነበረ ሚስተር ማቲቡላ የተባለ አንድ ሰው ነበር። ይህ ሰው ሮስተንበርግ አካባቢ ማዕድን ማውጫ ውስጥ ሲሰራ በነበረበት ጊዜ ያጋጠመውን ነገረኝ። የማዕድን አውጪ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት የቅርብ ጓደኛው ሞዛምቢክ ውስጥ በምትገኝ አንቾች በምትባል ትንሽ መንደር ውስጥ ስለሚኖር ሀይለኛ መንፈስ ስላለው ጠንቋይ እንደነገረው አጫወተኝ። ሚስተር ማቲቡላና ጓደኛው ይህንን ጠንቋይ ለማናገር ወደ ቦታው ሄደው ነበር። "ይህ ሸማግሌ ጠንቋይ ስለተለያዩ የአስማት መድኃኒቶች ከፍተኛ እውቀት ያለው ስለሆነ ብዙ ባህላዊ ሀኪሞች፣ የቢዝነስ ሰዎች፣ ፖለተሮችና ነዚያት ኃይል ለማግኘት ወደዚህ ጠንቋይ ይመጣሉ።" አለኝ።

"እንዴት ፖለተሮች እንደዚህ ያሉ ቦታዎች ሊሄዱ ይችላሉ?" ስል ጠየቅኩት።

ምንም እንኳን አሁን በአኔ ቤተክርስትያን ውስጥ በተለየ መንገድ መስራት ከጀመርኩ በኋላ በባህላዊ ሀኪሞች፣ በቢዝነስ ሰዎችና በፖለተሮች የሚጉብኝ ቢሆንም፣ የሚጎበኙኝን ሰዎች አብዛኛዎቹን ችግሮቻቸውን እንዴት እንደምፈታላቸው ስለማላውቅ ይህ ንግግራችን ጉጉት ይፈጥርብኝ ጀመር።

ሚስተር ማቲቡላ እንደነገረኝ እርሱና ጓደኛው ወደ ሞዛምቢክ የሄዱት ጓደኛው ሀብት እንዲያገኝ በመፈለጉ ነበር። ሽማግሌው ጠንቋይም ለሚፈልጉት ነገር የሚሆን ነገር እንደሚሰጣቸው፣ ይሁንና ግን ለአገልግሎቱ ወዲያው መክፈል እንደሌለባቸው ነገራቸው። ከፍያውን የሚፈፅሙት ከሚሰሩት ስራ ላይ ከሚያገኙት ትርፍ ላይ ብቻ ነው መሆን የሚችለው። ለዚህም ከሚያገኙት የመጀመሪያ ትርፍ ላይ የተወሰነውን ወራጅ ወንዝ ውስጥ እንዲወረውሩ አዘዛቸው። ይህንን ሀብታም የመሆን ኃይል ለማግኘት የሚያስፈልገው ነገር ሳንቲሞችን ወንዝ ውስጥ መወርወር ብቻ ስለሆነ ነገሩ ቀላል ይመስላል። ሚስተር ማቲቡላና ጓደኛው ይህንን "ሊናክዋጂ" የሚባለውን ኃይል ለመቀበል ወሰኑ። ነገር ግን ሚስተር ማቲቡላ እንደዚህ አይነት ነገሮች የቅርብ ቤተሰብ አባላትን ህይወት አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል ያውቅ ስለነበር እንደዚህ አይነት ኪዳን ውስጥ ለመግባት ጥርጣሬ አደረበት።

ሁለቱ የማዕድን ቁፋሮ ሰራተኞች ከሞዛምቢክ ከተመለሱ በኋላ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ለውጦች ማየት ጀመሩ። የሚስተር

@Amharicbookstore

ማቲቡላ ጓደኛ ህይወቱን ሙሉ ቁማር የሚጫወትና አሸንፎ የማውቅ ሰው የነበረ ቢሆንም ከኢንችቱፕ ከተመለሰ በኋላ ግን በቁማር ብዙ ገንዘብ ማግኘት ጀመረ። ያንን ጠንቋይ ካገኙ በኋላ እድል ወደ ጓደኛው በመዞሯ በውጤቱ ሁለቱም እጅግ ተደነቁ። ይህ ጓደኛው ማዕድን ቁፋሮውን በመተው የከበሩ ድንጋዮችን በህገ ወጥ መንገድ የማውጣት ስራ ጀመረና በዚህም ስራው በጣም ትርፋማ ሆነ። ሚስተር ማቲቡላ ማዕድን በመቆፈር መሬት ስር ሲሰፋ ይህ ጓደኛው ግን በውድ መኪናዎች የሚመላለስና የቅንጦት ኑሮ የሚኖር ሆነ። ሚስተር ማቲቡላ "ወደዚያ ጠንቋይ መሄዳችን የህይወታችን ትልቁ ስህተት ነበር።" ብሎ በነገረኝ ጊዜ በጣም አስደነገጠኝ። ከዚያ ግን ጓደኛው እንደተመለሰ በህይወቱ ደስታን ማጣጣም ችሎ ከነበረ እንዴት እንደዚህ ሊል እንደቻለ ግራ ስለገባኝ

"ምን ማለትህ ነው?" ብዬ ጠየቅኩት።

ሚስተር ማቲቡላ ወደኔ ጠጋ አለና በለስላሳ አነጋገር "ጓደኛዬ እነዚህን ሁሉ ሀብቶች ካገኘ በኋላ በህይወቱ በጣም አሳዛኝ ነገሮች ደረሱበት። በጣም አሰቃቂ የመኪና አደጋ ደርሶበት ሁለቱ ልጆቹ ወዲያውኑ ሲሞቱ እሱ ግን ጥቂት ሞሪቶች ብቻ አጋጥመውት ተረፈ።" አለኝ።

አንድ አባት ልጆቹን የማጣት ስቃይ እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል አስቤ እጅግ አዘንኩ። ቀጥሎ ሚስተር ማቲቡላ "ግን ፓስተር ልጆቹን ከቀበርን በኋላ የሆነውን አታምንም፣ ጓደኛዬ የበለጠ ሀብታም ሆነ፣ እስኪሞት ድረስ ህይወቱ ሁሉ በእድልና በጥሩ ነገር የተሞላ ሆኖ ነበር።" ሲል ነገረኝ።

ይህንን ታሪክ ከሰማሁ በኋላ ሚስተር ማቲቡላ የነገረኝ ሁሉ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ይህንን ጠንቋይ ለማግኘት ወሰንኩ። ብዙ የመናፍስታዊ አሰራር የሚሰሩ ሰዎች ጋር ሄጃለሁ፣ ነገር ግን አካባቢው ባሉ ሰዎች ጠንቋይ ተብሎ እንደሚጠራው የሞዛምቢክ ሰው ግን ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንዲኖሩኝ ያደረገ አልነበረም። አንድ ተራ ሰው እንዴት እንደዚህ አይነት ኃይል ሊኖረው እንደሚችል ለመረዳት ታገልኩ። ለምን እንደፈለግኩት እንዳይጠረጥር ሚስተር ማቲቡላን ለምሰራው ምርምርና ሙከራ ትረዳኛለህ ብዬ ወደዚያ ጠንቋይ እንዲወስደኝ ጠየቅኩት።

"ፓስተር ለእንተ ያለኝ ምክር አንድ ነው። ሽማግሌውን ኃይል እንዲሰጥህ የምትጠይቅ ከሆነ ቤተሰብህን የሚጨርስ ኪዳን ውስጥ እንዳትገባ።" ሲል አስጠነቀቀኝ።

"የሆነ ነገር ሳይ ሙከራ ለመስራት ስለፈለግኩ ብቻ ነው። ሽማግሌው ኃይል እንዲሰጠኝ የምጠይቅ ከሆነም፣ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳኝ እነስ ያለ ኃይል ነው የምጠይቀው።" አልኩት።

የመናፍስታዊ አሰራር አለም ችግር ወደ እኛ ለመማማከር የሚመጡ ሰዎችን ችግር ለመፍታት ሁልጊዜ ተጨማሪ መንገዶችና ዘዴዎች የሚያስፈልገን ስለሆነ በምንም መንገድ ባለን ሀይል ብቻ እርካታ አግኝተን መቀመጥ አንችልም። ሁልጊዜ ተጨማሪ ሀይል ያስፈልጋል። ሁል ጊዜ የተሻለ ጥበብ ያስፈልጋል። ሁልጊዜ ተዋርሶ ያስፈልጋል። ስለዚህ ከሚስተር ማቲቡላ ጋር ወደ ሞዛምቢክ ለመጓዝ ወሰንኩ። በምንሄድበት ቀን ከረዳቶቼ አንደኛውን በመኪና ሮተንበርግ

@Amharicbookstore

ድረስ አንዲያደርሰኝ ነገርኩትና ከሚስተር ማቲቡላ ጋ ሞዛምቢክ የሚያደርሰንን ታክሲ ያዝን።

ሞዛምቢክ መድረስ

ስንደርስ ማጉቶ ውስጥ ቆየንና በሚቀጥለው ጠዋት ወደ ቤይራ የሚሄድ አውቶቡስ ተሳፍረን በፍፁም የማልረሳው አንድ ትልቅ ድልድይ አቋረጥን። ቤይራ እንደደረስን ኢንችቶፐ ተብላ ወደምትጠራው ጠንቋዩ የሚገኝባት ትንሽ መንደር የሚያደርሰንን ሌላ መጓጓዣ ተጠቀምን።

ገና ወደ መንደሯ ስንደርስ አስገራሚ ነገር ነበር የጠበቀኝ። ጠንቋዩ ከሠያ በላይ ከሚሆኑት ሚስቶቹ ጋር በአንድ ትልቅ ግቢ ውስጥ የሚኖር መሆኑን ሳውቅ ማመን አቃተኝ። ሁሉም ሚስቶቹ የየራሳቸው ተመሳሳይ ባህላዊ ጎጆዎች ያሏቸው ሲሆን በውድ ድንጋይ የተገነባ የሚመስል አንድ ትልቅ ቤትም በግቢው ውስጥ አለ። ከሽማግሌው የልጅ ልጆች አንዱ ተቀበለንና ወደ እንግዳ ማረፊያው ወሰደን። ወደ እንግዳ ማረፊያው ስንራመድ፣ ውጪ የቆሙ ብዙ ውድ መኪናዎች አየሁ። አብዛኞቹ መኪኖች የእኔ ሀገር ሰሌዳ ቁጥር ያላቸው ነበሩ። እየወሰደን ያለው ወጣት "ብዙህ ሳምንት ብዙዎቹ እንግዶቻችን ከእናንተ ሀገር የመጡ ናቸው።" አለኝ። ይህንን ስሰማ ኃይል ፍለጋ ተሰላፊ የሆንኩት እኔ ብቻ ባለመሆኔ እፎይታ ተሰማኝ።

ወዲያው ሚስተር ማቲቡላ "ፓስተር እንደነገርኩህ ብዙ ሰዎች ኃይል ለማግኘት ወደዚህ ይመጣሉ፣ የእርሱ ኃይል ልክ እንደምትሀት እንደሚሰራ እኔ እራሴ በአይኔ አይቻለሁ።" አለኝ።

ሰፊውን ግቢ አቋርጠን ስናልፍ በሰንሰለት የታሰሩ ብዙ ወንዶችና ሴቶች አየሁና ወጣቱን ልጅ ምን ሆነው እንደሆነ ጠየቅኩት። "እነዚህ ሰዎች የአእምሮ ህመም ያለባቸው ሰዎች ሲሆኑ እዚህ የመጡት ለመንፃትና ለመፈወስ ነው። አያቴ የአእምሮ ህመም ያለባቸውን ሰዎች መፈወስ ይችላል።" አለኝ።

ይህ ሽማግሌ ተራ ሰዎችን ሀብታም፣ አእምሯቸው የታመሙ ሰዎችን ጤናማ የማድረግ ኃይል ከየት እንዳገኘ ማሰቤን ቀጠልኩ።

በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ይህንን ጠንቋይ ለማግኘት ሶስት ቀን ሙሉ ጠበቅን።

ተራችን ደርሶ ሽማግሌውን ለማግኘት ወደ ውስጥ ገባን። ገና እንደገባን ሚስተር ማቲቡላ ሰላውየው ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረበ። ሚስተር ማቲቡላ ከሽማግሌው ጋር እንደ ድሮ ጓደኞች እያወሩና እየሳቁ ስመለከት የቤቱ ደንበኛ እንደሆነ ተረዳሁ። ሽማግሌው ከተቆጣጠረው ፀጉሩ ጋር ሊታይ ጭርጭስ ያለ ይመስላል። በትከሻው ላይ ደግሞ ፀጉሮቹን የምትነካካ ትንሽዬ ጦጣ ተቀምጣለች። ቡናማ ሸሚዝና የተቀደደ ሱሪ የለበሰውን ይህ ሰው አተኩራ ተመለከትኩት። የበሰጠ ኃይል የማግኘት ጉጉቴ አንድ ቀን እንደዚህ አይነት ጠንቋይ ጋ ያደርሰኝ ይሆናል ብዬ ግን አስቤ አላውቅም ነበር። ግን ይኸው ኢንችቶፐ ውስጥ በጣም የሚያስፈራ ሽማግሌ ጠንቋይ ፊት ተቀምጫለሁ።

ዘና ብሎን ወለሉ ላይ እንደተቀመጥን ሽማግሌው ስሜን ጠየቀኝና ከቦርሳው ውስጥ ሶስት የባህር ሼሎች አውጥቶ ምንም ቃል

@Amharicbookstore

ሳይናገር ሶስት ጊዜ ወደላይና ወደታች እየወረወረ ኃይል ሊሰጠኝ እንደሚችል ተናገረ፡፡

ሚስተር ማቲቡላ ሽማግሌው የተናገረውን ሲተረጉምልኝ፣ የሚስተር ማቲቡላ ጓደኛ ላይ የደረሰውን ነገር ስለሰማሁ፣ ቤተሰቦቼ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ያለምንም ማመንታት እዚያው አንድ ፈጣንና አስተውሎት ያለበት ውሳኔ መወሰን አለብኝ ብዬ አሰብኩ፡፡

"የምፈልገው ኃይል ምን አይነት እንደሆነ በኋላ እነግርሀለሁ" አልኩት፡፡ ሽማግሌው ራሴን ለመግለፅ በቂ ጊዜ እንደሚሰጠኝ ለሚስተር ማቲቡላ ነገረው፡፡ ሚስተር ማቲቡላ እየተረጉመልኝ ሳለ ትንሿ ጦጣ መጥታ ትከሻዬ ላይ ተቀመጠችና ሶስት ጊዜ ፊቴ ላይ በጥፊ መታችኝ፡፡

"አይዞህ ፓስተር" አለኝ ሚስተር ማቲቡላ፡፡

የሚናገረው የሚደረገውን ነገር ሁሉ በደንብ እንደተረዳ ሰው ነበር፡፡ ወዲያው ሽማግሌው ስንት ልጆች እንዳሉኝ ጠየቀኝ፡፡ አንዲት ሴት ልጅ ብቻ እንዳለችኝ ነገርኩት፡፡ ወዲያው ሽማግሌው ከተቀመጠበት እመር ብሎ ተነሳና በጣም ልጅ እንደሆንኩና እነዚህ ኃይላት ለትንንሽ ልጆች እንደማይሆኑ ተናግሮ እንድንሄድ ጠየቀን፡፡

እድሜዬ ከዚህ ነገር ጋር ምን እንዳገናኘውና ሽማግሌው በዚህ አይነት እንዲያባርረን ሊደርገን የቻለው ምን እንደሆነ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ከዚያ የሰራሁት ስህተት ይኖር እንደሆነ ወይም የጠጣዋ ሶስት ጥፊ ችግር አምጥቶ እንደሆነ ለማወቅ ሚስተር ማቲቡላን

ጠየቅኩት፡፡ ሚስተር ማቲቡላ ምንም ማብራሪያ ያለው አይመስልም፡፡ ከእኔ በበለጠ ተስፋ የቆረጠ መስሎ ነበር፡፡

ተመልሰን እንግዳ ማረፊያው ውስጥ ከተቀመጥን በኋላ ኦፓል የሚባለው የሽማግሌው የልጅ ልጅ ተመልሶ ሲመጣ ሚስተር ማቲቡላ ለዚህ በአያቱ ስር ላደገውና ስለ አያቱ ብዙ ነገር ለሚያውቀው ወጣት የሆነውን ሁሉ ነገረው፡፡ ኦፓልም አያቱ ይህንን ያደረገበት ምክንያት ካለፈ ተሞክሮው የተነሳ እንደሆነና ለአንድ ወጣት ልጅ ኃይል ከሰጠ ከጥቂት አመታት በኋላ የሆነውን ነገረን፡፡ የዚያ ወጣት ቤተሰቦች ከቤተሰብ አባላት መካከል በየአመቱ ሰዎችን በመግደል እየጨረሰ ስላለው ነገር ግራ በመጋባታቸው ስለጉዳዩ ለመጠየቅ ወደየቤተሰባቸው መንፈሳዊ አባት ሄደው ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ወጣቱ ሀብታም ለመሆን ሲል የሚጠቀምበት ኃይል መኖሩንና ቤተሰቡን ሁሉ እየጨረሰ ያለው ይሄው ኃይል መሆኑን በማወቃቸው የኦፓል አያት ለወጣቱ የሰጠውን ኃይል መልሶ እንዲወስድ ለመጠየቅ ቤተሰቦቹ ሁሉ ወደዚህ መጥተው ነበር፡፡

ሽማግሌው ለወጣቱ ልጅ የሰጠውን ኃይል መልሶ መውሰድ እንደማይችል ነገራቸው፡፡ ቤተሰቡ ግን ሽማግሌው ለወጣቱ ኃይል እንዲቀበል የሰጠውን ጥቁር ቅል መልሶ እንዲወስድ ግድ አሉ፡፡ ይህ ግን መሆን የማይችል ስለነበር ሽማግሌው ጋ ከመጡ ከሳምንት በኋላ የአእምሮ በሽተኛ የሆነውን ልጃቸውን ይዘው መጡ፡፡ የምነግራችሁ ወጣት ውጪ በሰንሰለት ከታሰሩት ሰዎች መሀል የሚገኝ ሲሆን አያቴ እንተም ተመሳሳይ ነገር እንዳታደርግ ፈርቶ ነው፡፡" አለኝ፡፡

@Amharicbookstore

ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብዬ ከቆየሁ በኋላ የቅርብ ቤተሰቦቼ ሊጎዱ ስለሚችሉ ይህ ኃይል በቀላሉ ሊታይ እንደማይገባ ተረድቻለሁ። ኃይል ለማግኘት ብዬ ቤተሰቦቼን እደጋ ላይ አልጥልም። ወዲያው ሀሳቤን ቀይሬ መፍትሄ ፍለጋ ከሩቅ የመጣሁ በመሆኔ በጣም ከባድ ሳይሆን ቀለል ያለ ኃይል ማግኘት እችል እንደሆነ አፓልን ጠየቅኩት። አፓል ግን ከሰአት በኋላውንና ምሽቱን ሙሉ በአያቱ ቅዱስ ስፍራ ስላለው ህይወት የሚነግረንን ስናዳምጥ ቆየን። አፓል ስለ አያቱ በጣም ብዙ መረጃ ስላለው ጥንቃቄ ካላደረገ ጭንቅላቱ ታሞ በሰንሰለት ታስረው ግቢ ውስጥ እንደሚቀመጡ ሰዎች ሊሆን እንደሚችል አሰብኩ።

የአስራ ሁለት አመት እድሜ ያላት ሚስት

ሌላም ያሰገረመኝ አንድ ታሪክ ነበር። አፓል የ85 ዓመት እድሜ ያለው አያቱ፣ የአስራ ሁለት አመት እድሜ ያላት ሚስት እንዳለው ነገረን። ብዙ መናፍስታዊ አሰራር የሚሰሩ ሰዎች ለምን ብዙ የማግባት ዝንባሌ እንደሚኖራቸውና አያቱም እንደዚች አይነት ትንሽ ልጅ ለምን እንዳገባ ጠየቅኩት። አፓልም ከዚህ ነገር ጀርባ ያለውን ታሪክ መተረክ ቀጠለ።

ከአመታት በፊት ሚስቱ ልጅ መውለድ የተቸገረች አንድ ሰው ወደ ሽማግሌው ይመጣል። የዚህ ሰው ሚስት በህክምና መውለድ የማትችል መሆን መሆኗ የተረጋገጠ ነበር። በተጨማሪም ሰውየው የንግድ እድል እንዲኖረው ይፈልግ ነበር። ሽማግሌው የሚፈልጉትን መድኃኒት ሊሰጣቸው ግን ምንም አይነት ገንዘብ እንደማይቀበላቸውና የሰጣቸው ኃይል ራሱ እንዴት ዕዳቸውን መክፈል እንዳለባቸው

እንደሚነግራቸው አሰረዳቸው። ጥንዶቹም የተነገራቸውን ተስፋ አድርገው ሽማግሌውን ተሰናብተው ከሄዱ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሀብታም ሆኑ። በተጨማሪም ሶስት ልጆች አፈሩ።

ይህ ሰው አንድ ምሽት ላይ በህልሙ ከልጆቹ አንደኛዋ ከብዙ አመታት በፊት ሀብትና ልጆች እንዲያገኙ ኃይል የሰጣቸውን ሽማግሌ ጠንቋይ ስታገባ አየ። ሰውየው ህልሙን ለሚስቱ እስኪነግራት ድረስ በየምሽቱ ተደጋግሞ እየመጣበት ያስጨንቀው ነበር። ከዚያ ሁለቱም በአቅራቢያቸው ወዳለ መንፈሳዊ አባት በመሄድ እንዲረዳቸውና ከዚህ ህልም እንዲያነፃቸው ጠየቁት። ያ መንፈሳዊው አባት ግን መጀመሪያ ኃይል ወደተቀበሉበት ቦታ እንዲሄዱ ነበር ያዘዛቸው።

ጥንዶቹ ወደሞዛምቢክ ተመልሰው መሄድ ባለመፈለጋቸው ይህንን እርግማን ለመስበር ሌሎች መንፈሳዊ አባቶችን፣ ቀሳውስትንና ነቢያትን አማከሩ። ከጥቂት አመታት በኋላ በዚህ ህልም ይሰቃይ የነበረው ሰው ሞተ። ሚስቱም ለሞት እስክትደርስ ድረስ ታመመች። አልጋዋ ላይ ሆና ሞቷን እየተጠባበቀች ሶስቱን ልጆቿን ሰበሰበችና እነርሱ ከመወለዳቸው በፊት የሆነውን ነገር ነግራ የሽማግሌውን አድራሻ ሰጠቻቸው። እናትየው ከሞተች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትልቋ ልጅ በህልሟ የእንድ አመት ልጇ ወንዝ ውስጥ ስትሰምጥ አየች። ህልሙ ቀንና ሌሊት እየመጣ ስላስጨነቃት ቤተሰቡን ሰብስባ ወደ ሽማግሌው ሄዳ ለመጠየቅ መወሰኗን ነገረቻቸው።

ሁሉም የእንድ አመቷን ህፃን ጨምሮ ሽማግሌው ወዳለበት መንደር በመጣት ታሪኩን ነገሩት። ሽማግሌው ወላጆቻቸው የመናፍስቱ ብዙ ዕዳ እንዳለባቸውና መናፍስቱን ለማስደሰት የአንድ

@Amharicbookstore

አመቷ ህፃን ከእርሱ ጋር ቆይታ መናፍስቱን ማገልገል እንዳለባት ተናገረ። ቤተሰቡ ያቺ ህፃን በጠንቋዩ ሽማግሌ ቤት እንድታድግ ሰጡ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስክ አሁን ድረስ አስራ ሁለት አመት ሙሉ ቤተሰቦቿ ምንም አይነት መጥፎ ነገር ወይም መጥፎ አድል አጋጥሟቸው አያውቅም። የልጅቷ እናትም ከዚያ ወዲያ ይህንን ህልም አይታ አታውቅም።

ታሪኩ በጣም አሰፈራኝ።

እንደዚህ አይነት ነገሮች ፊልሞች ላይ አይቼ የማውቅ ብሆንም በእውነተኛ ህይወት ሊሆን እንደሚችል አስቤ አንኳን አላውቅም ነበር። ታሪኩን ከሰማሁ በኋላ ወዲያውኑ እንደዚህ አይነት ኃይል እንደማልፈልግ ለሚስተር ማቲቡላ ነገርኩት። ሁሉንም ነገር የሚያውቅ የሚመስለው ሚስተር ማቲቡላ ሽማግሌው ምናልባት የእንስሳ መስዋዕት ብቻ የሚፈልግ ኃይል ሊሰጠኝ ይችል እንደሆነ አፓልን ጠየቀልኝ። አፓልም ወደፊት ከባድ ዋጋ መክፈልን ለማስቀረት እንደዚህ አይነት ቀላል ኃይሎት ማግኘት የሚቻል እንደሆነ ነገረን። ከዚያ ስለዚህ የእንስሳት መስዋዕት ስንነጋገር እኔ ክርስቲያን ጋስተር በመሆኔ ሰዎች ቤተክርስቲያን ውስጥ እንስሳት ስሰዋ ሲያዩ ምን ሊሉ እንደሚችሉ ሚስተር ማቲቡላን ጠየቅኩት።

"አትጨነቅ፣ ሽማግሌው የእንስሳ ደም የሚፈልግ ኃይል የሚሰጥህ ከሆነ፣ ሰድሆችና የተራቡትን በመመገብ ሰበብ እንስሳውን ትሰዋለህ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ኃይማኖቶች ይህንን ሲያደርጉ አይቻለሁ።" አለኝ።

የስርዓቱ ክብረ በዓል

በዚያ ምሽት አፓል ከአያቱ ጋር በጣም ቅርብ ስለሆኑና ለእርሱ ቀኝ እጅ ስለሆነ እንደሚያነጋግርልን ቃል ገባልን። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት አፓል የተኛንበትን ቤት በር አንኳኳና አያቱ የእንስሳ መስዋዕት የሚመገብ መንፈስ ሊያዋርሰን መስማማቱን ነገረን።

ብዙ የመናፍስት አሰራር የሚሰሩ ሰዎች የሚሰጡት ኃይል የማያቋርጥ መስዋዕት ሲሰጠውና ደም ሲፈስለት የበለጠ ጠንካራ እንደሚሆን ይናገራሉ። ከዚያ አፓል ለትልቁ የስርዓቱ አከባበር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ከገበያ እንድገዛ ዝርዝሩን ሰጠኝ። ዝርዝሩ ላይ ነጭ ዶሮ፣ ጥቁር ፍየል፣ ላም፣ የወንድ ጃኬት፣ የእንፈት ከዘራ፣ ቀሰበት፣ ቢላዋ፣ ነጭ ሸሚዝና ነጭ ሱሪ እንድገዛ ይጠይቃል። በተጨማሪም ሁለት ብርድ ልብሶች፣ ስድስት ሳጥን አልኮልና ቀዝቃዛ መጠጥም እንድገዛ ያዛል።

በኋላ እንደሚከፍሉ የተስማሙ ሰዎችን ታሪክ ከአፓል ስለሰማሁ የሽማግሌውን የትኛውንም ኃይል በነፃ ላለመውሰድ መጠንቀቅ ነበረብኝ። ስለዚህ ቢያዝኩት ገንዘብ የተጠየቅኩትን ሁሉ ገዛሁ። ቀኑን ሙሉ ማታ ላይ ለሚደረገው ስነ ሰርዓት ስንዘጋጅ ቆየንና ምሽት ላይ ለመንፃት ወደ ጫካ ተወሰድኩ። ከታጠብኩ በኋላ ቀን እንድገዛ የታዝኩትን ነጭ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ እንድለብስ ታዘዝኩ። ሽማግሌው ከገዛኋቸው ነገሮች ጋር ወደ ሌላኛው ክፍሉ ወሰደኝና ስድስት እጆችና እያንዳንዱ ጣቱ ላይ ቀሰበት ወዳሰበት አንድ ሀውልት ጠቆመኝና አንዱን ቀሰበት እንስቼ በገዛሁት ቀሰበት እንድተካ አዘዘኝ። በነዚያ የሀውልት ጣቶች ላይ ያሉት ቀሰበቶች የሚያማምሩ

@Amharicbookstore

ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ የተሰያዩ ቀለማትና ቅርፅ ያለው ድንጋይ ያለባቸው የብር ቀለበቶች ናቸው። ሌሎቹ ቀለማት ሮዝ፣ ሀምራዊ ቀይና ጥቁር ናቸው። እኔም እንግዳ የሆነ ምልክት ያለበትን የብር ቀለበት መረጥኩ። ቀለበቱን ወስጄ ጣቴ ላይ አደረግኩና ከገበያ የገዛሁትን ቀለበት የሀውልቱ ጣት ላይ ተካሁ። ቀለበቶቹን ስለዋውጥ ልክ ሰርግ እንደሆነ ሁሉ በዚያ የነበሩ ሴቶች ሁሉ በደስታና በእልልታ አደመቁት። ብርድ ልብሶቹን በእድሜ ትልቅ ለሆነችው ለሽማግሌው ሚስት፣ ቢላዋውን፣ ጃኬቱንና ከዘራውን ለሽማግሌው ሰጠሁ። ሽማግሌውም በዚያ ክፍል ውስጥ ከነበሩት የተሰያዩ አይነት ከዘራዎች መካከል አንድ ከዘራ ሰጠኝ።

በመቀጠል ሽማግሌው ሰውነቴን በምላጭ በጣና የተቆረጠውን ቦታ በሁለት ቅሉች ውስጥ በያዘው እንግዳ የሆነ ዘይት ባለበት የአሰማት መድኃኒት ሸፈነው። ሁለቱ ቅሉች ወንድና ሴት ፆታን የሚወክሉ በመሆናቸው አንዱን ለይቶ መውሰድ ችግር እንደሚያመጣ ነገረኝ። የወንድ ጾታ የሚወክለውን ቅል ብቻ ብወስድ፣ መንፈሱ ሰሚስቱ ባል መሆን እንደሚፈልግ፣ የሴት ጾታ የሚወክለውን ብቻ ብወስድ ደግሞ ለመንፈሱ እኔ ባል የመሆን ግዴታ እንዳለብኝ ነገረኝ። ስለዚህ ሁለቱንም በአንድ ላይ እንድወስድ እንደሚሰጠኝና እነዚህ ሀይላት እኔን ለመምራት የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚገልጡ እንደሆኑ ነገረኝ። ፓስተር ስለሆንኩ ይህ ኃይል ብዙ ቅርንጫፎችን በመክፈት ወይም ከስሬ ብዙ ፓስተሮችን ለማፍራት የሚያደርግ መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንዳለብኝ አስረዳኝ። በተጨማሪም የእንስሳ ደምና መስዋዕት ብቻ የሚቀበል ኃይል እንደምፈልግ መስማቱን ጠቀሰልኝና በየሳምንቱ የትኛውን እንስሳ መሰዋት እንደምችል ጠየቀኝ። የምገዛበት

ገንዘብ እስካለኝ ድረስ የትኛውም እንስሳ ቢሆን ፈቃደኛ እንደሆንኩ ነገርኩት። የሚሰጠኝን ነገር በእጆቹ እንደያዘ እንድከተለው ጠራኝና አፓልና እያቱ ነጩን ዶሮ፣ ጥቁሩን ፍየልና ሳሚን ወዳከቀመጡበት ቦታ ሄድን።

ቦታው ላይ ስንደርስ ሽማግሌው የያዘውን ነገር አስቀመጠና ከለምች ጋር እንደሚነጋገር ሁሉ ከሁለቱ ቅሉች ጋር መነጋገር ጀመረ። እነርሱን በማመስገን ጀመረና አማልክቶቹ እኔን ወደዚህ ስላመጡኝ ምስጋና አቀረበ። ከዚያ ቅሉቹን የትኛውን መሰዋዕት እንደሚመርጡ ጠየቀ። ከአስር ደቂቃ በኋላ ፍየሏ እየተራመደች ወደ ቅሉቹ መጣችና ቅሉቹ አጠንብ ስትደርስ ወደቀች። ይህም መናፍስቱ የፍየል ደም ለመምረጣቸው ምልክት ነበር። ሁሉም ነገር አስገራሚ ነበር። እና እንደዚህ አይነት ነገሮች ለምን ሚስጥር እንደሚደረጉ መረዳት ጀመርኩ። አንዳንድ ሰዎች መናፍስቶችን የሚመግቡ መሆናቸውን ባለማወቅ በእንደዚህ አይነት ስርዓት ላይ ይሳተፋሉ። ያደግነው እንደዚህ አይነት የስርዓት አከባበር ላይ በሚሳተፉ ወዳጆችና ቤተሰቦች ዙሪያ ቢሆንም ብዙዎቻችን ከእነዚህ ስርአቶች ጀርባ ያሉትን ምክንያቶችም ሆነ የስርዓቱን ምንጭ አናውቅም።

መናፍስቶችን መሰየም (እሳትና ኃይል)

ሽማግሌው ሁለቱን ቅሉች ከመሬት ላይ አንስቼ ላያቸው ላይ ባለው ረጅም የቆዳ ማንገቻ አንገቴ ላይ እንዳንጠለጥላቸው ነገረኝ። ከዚያ ከመናፍስቱ ጋር አስተዋወቀኝና ስም እንድመርጥላቸው አዘዘኝ። ስም የማውጣበትን ምክንያት ስጠይቅ፣ ፓስተር እንደመሆኔ የቅሉን መናፍስት በቀላሉ በቤተክርስቲያን ስርዓት ላይ ሳይቀር ለመጥራት

@Amharicbookstore

እንዲረዳኝ መሆኑን ሹማግሌው ነገረኝ። መናፍስቱ በጠራኋቸው ቁጥር ምላሽ በመስጠት እንዲያደርጉ የምንግራቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉ አስረዳኝ። እኔም ቤተክርስቲያን ውስጥ በምሰብክበት ጊዜ ሁሉ የምጠቀምበት እንዲሆን በማሰብ መናፍስቶቹን "አሳት" እና "ኃይል" ብዬ ለመጥራት ወሰንኩ።

ሽማግሌው ሳቀና ለምን እነዚህን ስሞች እንደመረጥኩ ጠየቀኝ። "አሳት" እና "ኃይል" በቤተክርስቲያን ስርዓት ውስጥ ለመጥራት ቀላል ስለሆኑ እንደሆነ ነገርኩት። ወዲያው ሽማግሌው የሰው ጭንቅላት የሚመስል ቅርፅ ባለው እንጨት የተዘጋውን የመጀመሪያውን ቅል ከፈተና ቅሉ ውስጥ ምራቁን በመትፋት "አሳት" የሚለውን የመጀመሪያ ስም እንድጠራ ነገረኝ።

የተባልኩትን አደረግኩ።

ከዚያ ሹማግሌው ሰቅሉ "ከዛሬ ጀምሮ 'አሳት' ተብለህ ትጠራለህ" ሲል ነገረው። ለሁለተኛውም ቅል ተመሳሳይ ነገር በማድረግ "ኃይል" ብዬ እንድጠራው ተደረገ። ሁሉም ነገር ካለቀ በኋላ ሽማግሌው ዕቃዎቼን ይዤ ምንም ነገር ሳልናገር እንድሄድ አዘዘኝ። ለቤተሰቦቼ ደህንነት ስል ምንም አይነት የእርሱ እዳ እንዲኖርብኝ ስለማልፈልግ "አሳት" እና "ኃይል" መሰራት ሲጀምሩ ይህንን ላደረገበት ምን ያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለብኝ ለማወቅ ፈልጌ ነበር።

ከሚስተር ማቲቡላ ጋር ምንም በጫካ ውስጥ ብዙ ከሄድን በኋላ ፀሀይ አስክትወጣ ድረስ አንድ ትልቅ ዛፍ ስር ተኛን። በዚያ ማለዳ አንድ የጭነት መኪና ሹፌር ሊፍት ሰጠንና ወደ ማፑቶ

ሄድን። ማፑቶ እንደደረስን ወደ ሀገራችን የሚወስደንን ታክሲ ያዝን። ድንበሩን እያቋረጥን ሳለን ግን ታክሲው ያልተጠበቀ የሞተር ብልሽት ችግር አጋጠመውና ባለታክሲው ስመጠገን እየሞከረ ቆመን ቀረን።

ሚስተር ማቲቡላ ወደኔ ጠጋ አለና "ስመናፍስቱ ወደ አዲሱ ቤታቸው እየወሰድካቸው እንደሆነ ነግረሀቸዋል?" አለኝ።

"ሹማግሌው ምን ማድረግ እንዳለብኝ በዝርዝር እንዳልጠይቀው በቂ ጊዜ ስላልሰጠኝ አልነገርኳቸውም" ብል መለስኩለት።

"አሀ... ታክሲው ችግር የገጠመው ለካ ለዚያ ነው" አለኝ። እኔም ፈጠን ብዬ ቅሎቹን ወዳነቀመጥክብት ሻንጣ ሄድኩና ያለኝን ነገርኳቸውና ለሚስተር ማቲቡላ ማድረጌን በምልክት ነገርኩት። ወዲያው ሚስተር ማቲቡላ ባለታክሲውን ለመጨረሻ ጊዜ ሞተሩን እንዲሞክረው ነገረው። ምንም ማድረግ ባለመቻሉ ዝም ብሎ ቆሞ የነበረው ባለታክሲ ሲሞክረው ሞተሩ ተነሳ፣ ወዲያው ወደታክሲው ገብተን ጉዞ ስንጀምር ሚስተር ማቲቡላ "ነግሬህ ነበር ፓስተር" አለኝ።

ወደ ደቡብ አፍሪካ እየተመለስን በዚያች ኢንችቶፕ በምትባለው ትንሽ መንደር የተከሰተውን ሁሉ በጭንቅላቴ እንደ ፊልም እያየሁት ነበር።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ ስምንት

ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፎ ኮንጎ

ኮንጐ ውስጥ ባለ ደሴት ላይ

በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጐ ውስጥ በምትገኝ ኮንጐላ ተብላ በምትጠራ ትንሽ ደሴት ላይ የሚኖር አንድ ሽማግሌ ሀይለኛ የመናፍስት አሰራር የሚያደርግ ሰው ሲያስተዋውቀኝ ደሴቲቱ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሞሳች እንደነበረ አስታውሳለሁ። ባባ ፍራንሲስ በዚያች ደሴትና በዙሪያዋ ባሉ መንደሮች የታወቀና የተከበረ መናፍስታዊ አሰራር የሚያውቅ ሰው ሲሆን፣ በትንሿ ጐጆው ውስጥ ከተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚመጡ የተለያዩ ዝርያዎች ያሏቸውን ሰዎች በመሉ ያማክራል። የሚኖረው በአቅራቢያው ያሉ ሰዎች በሚኖሩባቸው ተመሳሳይ ባህላዊ ጐጆ ውስጥ በመሆኑ መንፈሳዊ ጉዳዮችና ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች የባባ ፍራንሲስን የአስማት ኃይል

ለማግኘት ከየክፍለ አህጉራቱ መጥተው ምክር የሚቀበሉት እዚያችው ጠባብ ጐጆ ውስጥ ነው።

መንገድ መሪዬና አስተርጓሚዬ የሆነው ፓስተር ጆን ስለዚህ አስማት አሰራር ብዙ ታሪኮችን እየነገረኝ ነበር። ስለ ጥቁር አስማት የሚነገሩት አንዳንድ ታሪኮች በጣም አስፈሪ ቢሆኑም እኔ ግን ተጨማሪ መስማት አጓጉቶኝ ነበር። ለዚያም ነው ባባ ፍራንሲስ የምፈልገውን በእርግጥ ሊሰጠኝ ይችል እንደሆነ የጠየቅኩት። በሞተር ሳይክል ለአምስት ቀናት 3000 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘን የመጣን በመሆኑ ይህ ዝነኛና ኃያል የሆነው ባባ ፍራንሲስ በእርግጥም ስለመኖሩ ማረጋገጫ ፈልጌያለሁ።

ፓስተር ጆን ባለ መናፍስቱ ሲቀበለን ወደሚጠብቀን ትንሽ ጐጆ አመለከተኝና በሁሉም ሙያ ላይ ያሉ ሰዎች ፖለቲከኞች፣ መሪዎች፣ የህክምና ዶክተሮች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ ነገስታት፣ ንግስቶችና የስፖርት ሰዎች ሳይቀሩ ከመላው ዓለም ኃይል ለማግኘት ወደዚች ጐጆ እንደሚመጡ ነገረኝ።

"ኃይል ካልክ እዚያ ኃይል አለ።" አለና ውስጥ ምን እንደሚጠብቀኝ ቡሚያውቅ አይነት ሳቀ።

በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያደግኩና ወጣት በመሆኔ ጥርጣሬዬን በልቤ ይዤ ዝም ብዬ ተመለከትኩት።

@Amharicbookstore

ቤተክርስቲያን ውስጥ ጥንቆላ ማካሄድ

ተጠርተን ወደ ትንሿ ጉጆ እስክንገባ እየጠበቅን ሳለ ፓስተር ጆን ስለገደኛው ነቢይ ዘካርያ አንድ አሳዛኝ ታሪክ ነገረኝ። ነቢይ ዘካርያ ኃይል ያገኘው ከባባ ፍራንሲስ ነበር። ከዚህ በፊት ነቢይ ዘካርያ በአንዲት መንደር ውስጥ የሚኖር ያገሰገሱ ልብሶች በመሸጥ የሚተዳደር ሰው የነበረ ሲሆን ስራው እየቀዘቀዘ ሲመጣ ግን የነቢይነት ኃይል ለማግኘት ወደ ባባ ፍራንሲስ መጣ። ነቢይ ዘካርያ ያዋረሰውን፣ የነቢይነትና የተአምራት ኃይል የሰጠውን ባባ ፍራንሲስን እስኪያገኝ ድረስ ምንም አይነት የነቢይነት ስጦታ ያልነበረው ሰው ነበር። ነቢይ ከሆነ በኋላ ግን ከሞቱ ሰዎች ጋር የመገናኘትና እነርሱን የማነጋገር ችሎታ ሁሉ ነበረው። የእርሱ ቤተክርስቲያን ከውጪ ሲታይ ቤተክርስቲያን ቢመስልም በባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች ተፅዕኖ ያለበት ነበር። የነቢይ ዘካርያስ ቤተ ክርስቲያን በተሳሳተ መንፈሳዊ መሰረት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያኑ መሰረት ክርስቶስ አለመሆኑ ግልፅ ነበር። ሆኖም ግን ብዙ ሰዎች ወደዚያ ይጉርፉ ነበር። ቤተክርስቲያኑ የተመሰረተው በክፉ መናፍስትና ኃይል ላይ ባለ ትንቢት፣ ፈውስና ተአምራት ነበር።

እምነታቸው በትንቢት፣ በፈውስና ተአምራት ላይ የተመሰረተ ሰዎች ትልቅ አደጋ ላይ ናቸው። ምክንያቱም የመዳን ዋና አላማ ፈውስ፣ ትንቢት መንገር ወይም ስለ ተአምራት ሳይሆን ንስሀ ስለመግባትና እንድ ቀን መንግስተ ሰማያት ስለመሄድ ነውና።

አስተርጓሚዬ ፓስተር ጆን የነቢይ ዘካርያን ታሪክ ሲቀጥልልኝ፣ "ነቢይ ዘካርያ የሚሰራበት ኃይል ከውሻና አሞራ

መንፈስ ጋር የተቀላቀለ የሞተ ሰው መንፈስ ነበር።" ሲል ነገረኝ። የሞተ ሰው መንፈስ፣ ውሻና አሞራ እንዴት የእንድን ሰው ያለፈና የወደፊት ነገር ማናገር እንደሚችል ስላልገባኝ መሳው ታሪክ ሰሚት አልሰጥ አለኝ። ነገሩ ጥንቆላ እንደሆነ ሲነግረኝ ነቢይ ዘካርያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጥንቆላ ስራ የሚሰራ መሆኑን ማሰቡ ራሱ አስደነገጠኝ።

ከባባ ፍራንሲስና ከጠንቋዮቹ ጋር መገናኘት

ፓስተር ጆን ጥንቆላው እንዴት እንደሚሰራ እየነገረኝ ሳለ ነጭ ጋዋን የለበሰች ውጣት ሴት ከጉጆው ወጣችና ተራችን እንደደረሰና እንድንገባ ጠራችን። ከተቀመጥንበት ተነስተን ወደ ጉጆው ለመግባት ስንዘጋጅ ፓስተር ጆን ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ እንዳልፈራ በሹክሹክታ ነገረኝ። ለሚሆነው የምፈልገውን እንደሚነግርልኝና ጥያቄዬም ለባባ ፍራንሲስ ግልፅ እንደሚሆን አረጋገጠልኝ። የመጀመሪያውን በር አልፈን እንደገባን ከውጪ እንድንገባ የጠራችን ውጣቷ ሴት ፊታችንን፣ እጆቻችንን፣ ደረታችንንና ጀርባችንን ውሀ ከረጨችን በኋላ ጫማዎቻችንን እንድናወልቅ ነገረችን። የተባልነውን አደረግንና ወደ ማማከሪያው ክፍል ገባን። ክፍሉ ውስጥ እንደገባን ያጋጠመን የተለያዩ ምልክቶች ባሉበት ጥቁር መጋረጃ የተሸፈነ ክፍል ነበር። ምልክቶቹን አተኩሬ እየተመለከትኩ ምን እንደሆኑ ሰማወቅ ስሞክር ፊታችንን አዙረን ወደ መጋረጃው ውስጥ እንድንገባ ታዘዝን። ፊታችንን ከማዞራችን በፊትም ግድግዳውን ሶስት ጊዜ መምታት ነበረብን።

የታዘዝነውን ሁሉ አደረግን።

@Amharicbookstore

በጣም ፈርቼ ልቤ በኃይል እየመታ ነበር። የገባንበት ክፍል ውስጥ ሁለት መሰዊያዎች ስላየሁ አእምሮዬ በአድናቆት ተሞላ። ሁለቱም መሰዊያዎች ክፍሉ ውስጥ ባሉ ሰዎች ተከበዋል። የገባንበት ክፍል ነጭ ቀለም የተቀባና ውስጥ ያሉት ሰዎች በሙሉ ነጭ የለበሱ ናቸው። ልክ ክፍሉ ውስጥ እንደገባን ሁሉም አልልታ ማሰማት ጀመሩ። ከዚያ እንድንቀመጥ ተነገረን። እንደተቀመጥንም ወጣቷ ሴት ሁለት ነጫጭ ልብሶች አመጣችልን። በቤቱ ውስጥ ያሉት ሁሉ ያረጁ ግን ጠንካራ የሚመስሉ ሴቶች ቢሆኑም ለባባ ፍራንሲስ ሁሉንም ነገር የምታቀርበው ግን ወጣት ይህቺ ሴት ናት።

የተሰጠንን ነጭ ልብስ ትከሻችን ላይ ያዝንና በክፍሉ መካከል ያሉትን ሁለቱን አሮጌ መሰዊያዎች የከበቡትን ሰዎች ተቀላቀልን። ባባ ፍራንሲስ ከመሰዊያዎቹ በተቃራኒ ተቀምጦ ነበር። ከመተዋወቃችን በፊት እሱ እንደሆነ አውቂያለሁ። ምክንያቱም ከእኔና ከጆን ሌላ ያለው ወንድ እርሱ ብቻ ነበርና። እንኪን ደህና መጣችሁ ተባልንና ተዋወቅን። በእኔና በሽማግሌው መሀል የሚያስተረጉምልን ፓስተር ጆን ነበር። ባባ ፍራንሲስ በጣም ያረጀና ከሀገሩ ቋንቋ ውጪ ሌላ ቋንቋ የማይችል ነበር። ፓስተር ጆን ባባ ፍራንሲስና ጠንቋዮቹ እንኪን ደህና መጣህ እንዳሉኝ ሲነግረኝ ድንጋጤ ውስጥ ብሆንም ምስጋናዬን አቀረብኩ። በአእምሮዬ ፓስተር ጆን አሮጊቶቹን ጠንቋዮች ብሎ መጥራቱ ግራ አጋብቶኝ ነበር። ምክንያቱም አንድ ሰው ጥንቆላ እንደሚሰራ ቢታወቅም ጠንቋይ ብሎ መጥራት ትክክል አለመሆኑን አውቃለሁ።

የዘፈኑን ግጥም ባልረዳውም ጠንቋዮቹ ከበሮ እየመቱ መዝፈን ጀመሩ። ዘፈኑ ቀስ ባለና ለስላሳ በሆነ ምት ተጀመረ። ወዲያው ከበሮ እየመቱና እያጨበጨቡ ሲዘፍኑ ራሴን የሙዚቃ ምቱን ተከትዬ ሳጨበጭብ አገኘሁት። የዚያን ቀን መመሪያዬ ሮም ውስጥ ከሆንክ ሮማውያን እንደሚያደርጉት ማድረግ አለብህ የሚል ይመስል ነበር። አብዝተው በዘፈኑ መጠን አካባቢው የበለጠ መናፍስታዊ ኃይል ያለው ይሆናል። የዘፈኑ፣ የከበሮውና የጭብጨባው ድምፅ እየጨመረ መጣ። በዚያን ጊዜ ባባ ፍራንሲስ ትንሽ የሬሳ ሳጥን የሚመስል ሳጥን ከፈተና ከዚያ አስፈሪ ሳጥን ውስጥ ነጭ ዱቄት የሚመስል ነገር አወጣ። ያወጣውን ነጭ ዱቄት እጁ ላይ አደረገና በክፍሉ ውስጥ በአንድ አቅጣጫ በትንፋሹ በተነው። ሁለተኛውንም ነጭ ዱቄት አውጥቶ ወደ ሌላኛው አቅጣጫ ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ዱቄቱን በትንፋሹ በበተነ ቁጥር እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ይከታተላል። ባባ ፍራንሲስ ነጩን ዱቄት መሰል ነገር በሁሉም አቅጣጫ፣ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምዕራብና በምስራቅ ከበተነ በኋላ በመጨረሻ በተከፈተው መስኮት ወደ ውጪ ሲበትን ክፍሉ ውስጥ ከፍተኛ ፀጥታ ሰፈነና ሁሉም ወደኔ ይመለከቱ ጀመር።

ለአምስት ደቂቃ ያህል በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ነገሰ።

ባባ ፍራንሲስ አሁንም ትንሹን የሬሳ ሳጥን በሁለት እጆቹ ይዞ እንዳለ ድንገት እንዲት ነጭ ርግብ በመስኮቱ በኩል ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባች።

ሁሉም ነገር ለእኔ እንግዳ ነበር። አይኖቹ ከአርግቧ እንቅስቃሴ ጋር ወዲያ ወዲህ ሲሉ የጠንቋዮች አይኖች ደግሞ እኔ ላይ ነበሩ።

@Amharicbookstore

በመጨረሻ ርግቧ ወለሉ ላይ አረፈችና ወደኔ ተራመደች። ባባ ፍራንሲስ ነጩን ጹቁት ፊቱ ላይ በትንፋሹ በተነና መናፍስቶቹ ታላቅ ሰው መሆኔንና ኮከቤ ብሩህ መሆኑን እንዲረጋገጡለት ነገረኝ። ሁሉንም ነገር የሚነግረኝ በፓስተር ጆን በኩል ነበር። ምክንያቱም የእነርሱ መንደር ተወላጅ በመሆኑ ቋንቋውን የሚረዳው እሱ ነበር። ፓስተር ጆን ለአገልግሎት የተሰያዩ ቦታዎች የሄደ ቢሆንም በአብዛኛው ግን በትንቢት፣ በፈውስና ተአምራት የሚሰራ በመሆኑ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ይጋበዛል።

"እርግቧ አንድ ጊዜ ወዳንተ ከቀረበች መናፍስቶቹና ጠንቋዮቹ ተቀብለውሀል እና የምትፈልገውን ሊሰጡህ ፈቃደኛ ናቸው ማለት ነው።" አለኝ።

አንዳንድ ጊዜ ከሩቅ ሀገር መጥተውም የእርሱ መናፍስቶችና ዝርያዎቹ እነዚያን ሰዎች መርዳት የማይፈልጉበት ጊዜ እንዳለ ባባ ፍራንሲስ ነገረኝ።

ባባ ፍራንሲስ እያታለለኝ ይሆን? አላውቅም፣

የማውቀው ነገር ቢኖር በውስጤ "ራሴን ምን ውስጥ እየከተትኩ ነው? የዚህን ሁሉ ጉዞ ዋጋ መክፈል እችል ይሆን? ውጤቱንስ መሸከም እችል ይሆን?" የሚል ጥያቄ እየጮኸ እንደነበር ብቻ ነው።

ከማምባሙቱ ጋር ቀጠሮ

ባባ ፍራንሲስ በእኩለ ሌሊት ኮንጎላ ደሴት ላይ ወደሚገኘ ወንዝ እንድንሄድ ሲያዘኝ *በዚህ ብርድ ወንዙ ውስጥ እንድታጠብ ይፈልግ ይሆን* ስል አሰብኩ። ነገር ግን ማምባሙቱ ብለው ከሚጠሩት ፍጥረት ጋር እንድገናኝ ፕሮግራም ተይዞልኝ ነበር። ማምባሙቱ ሚስጥራዊ ስም ሲሆን ማንም ሰው ይህንን ስም መጥቀስ ወይም ከዚህ ሚስጥራዊ ፍጥረት ዙሪያ ጋር የሚገናኝ ታሪክ መናገር አይችልም። በዚያች ደሴት ላይ ስልጣኔ ያለው በሙሁራኑ መካከል ብቻ ነው። እዚያ ካሉት ሰዎች መካከል የሰለጠኑ የሚባሉት ባህላዊ ፈዋሽ፣ የመንደሩ አለቃና ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ነበሩ። ተንቀሳቃሽ ስልክ ያላቸው በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ ሰዎች የሚለብሱት ከሚሽነሪዎችና ከቱሪስቶች የሚገኙ ያገለገሉ ልብሶችን ነው። እዚያ ደሴት ላይ ስደርስ ይቺ ትንሽ ደሴት የሆነ ድግምት ወይም ኃይል እንዳለባት አወቅሁ። ምክንያቱም ወደዚች ደሴት የሚመጡ ሰዎች ጭና አየር መንገድ ላይ እያሉ በዚያች ቦታ ስላለ መናፍስታዊ ኃይል ይነገራቸዋልና። ብዙ ቱሪስቶችም ወደዚህ የሚመጡት እነዚህን አደገኛ የመናፍስት ሀይሎች ለማግኘት ነው።

እኔም ማምባሙቱ የሚባለውን ፍጥረት ከመገናኘቴ በፊት ይህንን ኃይል አይቻለሁ።

ከአስፈሪው ምሽት ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ወደዚሁ ወንዝ ተወስጄ ነበር። ከዚህ በፊት ይህንን የሚያክል ትልቅ ወንዝ አይቼ አላውቅም። እኔና አስተርጓሚዬ ሁለታችንም ወንዙ ጋ ወዳለ የተለየ ቦታ ተወሰድን። ያ የተለየው ቦታ ትልቅ ድንጋይ የሚመስል ነገር

@Amharicbookstore

ነበረበት። ይህ ትልቅ ድንጋይ ወይም አለት የሚገኘው ወንዙ ዳር አካባቢ ነበር። ይህ ሽማግሌ ወደ ድንጋዩ አመለከተና በራሱ ቋንቋ ተናገረ።

አስተርጓሚዬ "ይህ የአለም መግቢያ በር ነው።" አያለ እንደሆነ ነገረኝ።

አስተርጓሚዬ ያለውን ሲነግረኝ ፊቱ በአድናቆት በርቶ ስለነበር፣ ስለዚህ ቦታ ብዙ ነገሮችን እንደሚያውቅ ማየት ችያለሁ። ድንጋዩን በቅርበት ስመለከት ወንዝ ወይም ባህር አካባቢ የሚገኙ ድንጋዮች አይነት መሆኑን አየሁ።

አስተርጓሚዬ በጣም ከመደነቁ የተነሳ ከሽማግሌው ጋር በሀገራቸው ቋንቋ መነጋገር ጀመረ። ከንግግራቸው እዚያ ቦታ ላይ ስለተደረጉ ታሪኮች የሚያወሩ ይመስሉ ነበር። ከሚያወሩት ነገር አንዱን ቃል እንኳን መስማት የማልችል ብሆንም ከፊገሃታቸውና ከፊታቸው ተልዕኮዬ በዚህ ሽማግሌና በአስተርጓሚዬ እንደሚሳካ አውቄያለሁ። አንዳንድ ቦታዎች በአካላዊ አይኖች ሲታዩ ተራ ቢመስሉም፣ በመንፈሳዊ አይኖች ሲታዩ ግን በጣም አስደናቂ ናቸው።

አስተርጓሚዬ እጁን ትከሻዬ ላይ አደረገና "ወንድሜ ሽማግሌው እዚህ እንድትመጣ ስላደረገህ በጣም እድለኛ ነህ።" አለኝ። እንደገና ወደኔ ተመለከተና "ዛሬ እዚህ ኃይል እንዳለ ታያለህ።" አለኝና ወደ ድንጋዩ አመልከቶኝ ብዙ ፖለቲከኞች፣ ነጋዴዎች፣ መንፈሳውያን፣ ጳጳሳት፣ የህክምና ዶክተሮችና የአለም መሪዎች

ላይቀሩ በየሙያዎቻቸው ስኬት ማግኘት እንዲችሉ ኃይል ለመጠየቅ እዚህ እንደሚመጡ ነገረኝ።

ከዚያ ሽማግሌው በእጆቹ ይዟት የነበረችን ርግብ ሰጠኝና አሁን የሚከሰተውን መቋቋም እችል እንደሆነ ጠየቀኝ። በሀገሩ ቋንቋ እየተናገረ በእጆቹ ምልክቶችን እያሳየኝ ነበር። አስተርጓሚዬ ሽማግሌው ያለኝን ሲነግረኝ ለማንኛውም ነገር በደንብ የተዘጋጀሁ መሆኔን እንዲነግረው ነገርኩት። ወዲያው ሽማግሌው በወንዙ ውስጥ ገብቶ ወደ አለቱ ሲራመድ እንድከተለው ታዘዝኩ። ከዚህ ቀደም ፖለቲከኞችን፣ የቤተክርስቲያን መሪዎችንና ነጋዴዎችን በዚህ መንገድ የመራውን ሰው ስከተል፣ አያንዳንዱ ርምጃዬ ወደ አዲስ እውነታና ጥለት የሚያደርሰኝ ርምጃ እንደሆነ አውቄያለሁ።

ድንጋዩ አጠገብ ስንደርስ ሽማግሌው ርግቧን ከእጄ ላይ ወሰደና በአርግቧ ሶስት ጊዜ ደረቴን ሲመታኝ ከሰውነቴ የሆነ ነገር የወጣ አይነት ስሜት ተሰምቶኝ ነበር። ከዚያ ርግቧን መልሶ ሰጠኝና ድንጋዩ ጫፍ ላይ እንዳስቀምጣት ነገረኝ። እንደታዘዝኩት ድንጋዩ ላይ ሳስቀምጣት እንዳትበር እየፈራሁ ነበር። ርግቧ ግን በዚህ ሚስጥራዊ ድንጋይ ውስጥ የማግኔት ኃይል ያለ ይመስል ዝም ብላ ተቀመጠች።

ርግቧን በዚህ ለስላሳና የተጠረበ የሚመስል ድንጋይ ላይ ካስቀመጥኩ በኋላ ስመለከታት በሆነ ሲገለፅ በማይችል ኃይል ስር የሆነች ትመስል ነበር። አልተንቀሳቀሰችም።

ወዲያው ግን ድንገት ከአይኖቼ ስር ስትሰወር በመደነቅ ድንጋዩ ላይ አፈጠጥኩ። ርግቧ የለችም። ሽማግሌው ወደኔ

@Amharicbookstore

ተመለከተና እጆቹን በማጨብጨብ ምስጋና ማቅረብ ጀመረ። እኔም የደነገጥኩና ግራ የተጋባሁ ቢሆንም አብሬው ማጨብጨብ ጀመርኩ። በጭንቅላቴ ውስጥ ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ነበሩ።

ወደ ቤት ከተመለስን በኋላ ባባ ፍራንሲስ ማግኘት የምፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር ወረቀት ላይ እንድጽፍ ነገረኝ። ወረቀቱን አጣጥፌ ትራሴ ስር አድርጌ እንድተኛና በሚቀጥለው ቀን ጠዋት እንደተነሳሁ፣ ያንን የተጣጠፈ ወረቀት ዝርዝሩን እንደገና ከተመለከትኩት በኋላ በብርጭቆ በተሞላ ውሃ ውስጥ እንድከትተው ተነገረኝ። የተባልኩትን አደረግኩ። ወረቀቱን ውሃ ውስጥ ከትቼ ሙሉ በሙሉ እስኪረጥብ ጥቂት ደቂቃዎች ጠበቅኩ። ወረቀቲ ሙሉ በሙሉ መርጠቡ ከተረጋገጠ በኋላ እንዳወጣው በተነገረኝ መሰረት ያንን ወረቀት ከውሃው አውጥቼ ስዘረጋው እኔ በጻፍኳቸው ጥያቄዎች ምትክ በራሴ ሀገር ቋንቋ በጣም ቦሚያስገርም አይነት ለጥያቄዎቼ መልስ ለማግኘት የቀጠሮ ቀንና ሰዓት ተጽፎበት በማየቱ እጅግ ደንግጬ ነበር። ባባ ፍራንሲስ እዚህ የመጣ ሁሉ ይህንን እድል እንደማያገኝና መናፍስቱ መልስ ስለሰጡኝ እድለኛ መሆኔን ነገረኝ።

ባባ ፍራንሲስ በተሰጠኝ ቀጠሮ መሰረት አኩለ ሌሊት ላይ ወደ ወንዙ እንድንሄድ አዘዘኝ። ማምባሙቱ ብሰው ከሚጠሩት ግማሽ ሰውና ግማሽ አዞ ከሆነ ፍጥረት ጋር እንድገናኝ የተያዘልኝ ፕሮግራም በመሆኑ በጣም ፈርቼ ነበር።

የቀጠሮው ምሽት ጨረቃ ሙሉ ስለነበረች ሁሉ ነገር ፍንትው ብሎ ይታይ ነበር። ወንዙ ጋ ስንደርስ ባባ ፍራንሲስ ያለማቋረጥ ምንነቱ ባልታወቀ ቋንቋ እያነበነበ ነበር። እኔም በጨረቃው ብርሃን ወደ ወንዙ አተኩሬ እየተመለከትኩ ሳለ ውሃው በሚያስፈራ አይነት እየተንቀሳቀሰ ወደኛ ሲገሰግስ አየሁ። በውስጡ የሆነ ግዙፍ አካል እየዋኘ ይመስላል። በድንጋጤ ውሃው ላይ እንዳፈጠጥኩ ያ እየጋለበ የሚመጣ ውሃ ከጀርባዬ ዞሮ ቆመና የሆነ ግዙፍ አካል ከኋላዬ በእጆቹ ትከሻዎቼን ሲይዘኝ ትንፋሹ በስባዱ እየተሰማኝ ነበር። የያዙኝን እጆች ለማየት ስሞክር ጣቶቹ የሰው እንዳልሆኑ ስላየሁ ድንጋጤዬን ለመቆጣጠር ከመቻሌ በፊት ያ ፍጥረት ሶስት ጊዜ ያህል ውሃው ውስጥ እየዘፈቀ ከጠመቀኝ በኋላ በመጣበት መንገድ ተመልሶ ሄደ።

ተአምራዊ ገንዘብ

ባባ ፍራንሲስ "ገንዘብ የማግኘት ሰርዓት" የሚባለውንና በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተአምራዊ ገንዘብ ተብሎ የሚጠራውን አሳየኝ። ሰይጣን የአማኞች ችግር እላማኝ የሚመስል ነገርን ሁሉ በቀላሉ ማመን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። አንድ ነገር ተአምር ወይም ቅዱስ ከተባለ ሰዎች ከእግዚአብሔር እንደሆነ ስለሚያምኑ አንተ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለህ ብትጠይቅ ልክ አጋንንት እንደሆንክ ይቆጥሩሀና "ነቢያችን የእግዚአብሔር ተአምር ነው ብሎናል።" ይሉሀል።

ባባ ፍራንሲስ ባዶ እንስራ አሳየኝና እንስራውን በነጭ ጨርቅ ሸፍኖ የሆነ ድግምት ደገመ።

@Amharicbookstore

ወዲያው ያ ባዶ እንስራ በገንዘብ ሲሞላ ተመለከትኩ።

ያ የተሸፈነ እንስራ በወረቀት ገንዘቦች ሞልቶ መፍሰስ ጀመረ። ይህ ባህላዊ እንስራ ወደ ገንዘብ መስሪያ ማሽንነት ሲለወጥ እያየሁት ትንግርት ሆኖብኝ ፈዝዣለሁ። መናፍስቶቹ እንስራውን በገንዘብ እየሞሉ ሳለ ሹማምሌው ድግምቱን በማነብነብና የሆኑ እንቅስቃሴዎች በማድረግ ስራ በዝቶበት ነበር። ሲጨርስ ከእንስራው ላይ ነጩን ጨርቅ እንዳነሳ፣ ነገር ግን ገንዘቡን እንዳልነካ ነገረኝ። ገንዘቡን በፍፁም መንካት እንደሌለብኝ እርግጠኛ እንድሆን ደጋግሞ ነገረኝ። ጨርቁን ሳነሳ የተሰያዩ ሀገራትን የወረቀት ገንዘቦች ተመለከትኩ። ይህ ሰው እንደዚህ አይነት ኃይል እያለው እንዴት በዚህች የተሰነጣጠቀ ግድግዳዎች ባሏት ትንሽ ቤት እንደሚኖር አሰብኩ። በእንስራ ውስጥ የተከናወነውን ተአምር ከዚህ ሰው የመኖሪያ አካባቢ ጋር ሳነፃፅር ሁሉም ነገር ትርጉም የማይሰጥ ሆነብኝ።

ኮባ ፍራንሲስ ሪዳቶች አንዷ ገንዘቡ የእውነት ገንዘብ እንደሆነ ነገረችኝ። ከዚያ እንደገና ወደ እንስራው እየተመለከትኩ *ገንዘቡ የእውነት ከሆነ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት ሰዎችስ ሀብታም ለምን አልሆኑም* ስል አሰብኩ። ሹማምሌው የእነርሱ መናፍስት የሀሰት ገንዘብ እንደማይሰሩ ነገረኝና አሁን ጥቂት የገንዘብ ኖቶችን እንስቼ እውነተኛ መሆናቸውን እንዲረጋግጥ ነገረኝ። እጄን ዘረጋሁና እንድ የወረቀት ገንዘብ ወሰድኩ። የራሴን ሀገር ገንዘብም ስላየሁ ያንንም አነሳሁ። የራሴ ሀገር ገንዘብ የእኛን ሀገር የገንዘብ ሚኒስቴር እንኳን በማያውቁ ሰዎች ባህላዊ እንስራ ውስጥ ማግኘቴ የበለጠ ግራ አጋባኝ። ወዲያው ገንዘቡን እንዲሰጡኝና በገንዘቡ ስራ ሰርቼበት

መልሼ እንደማመጣው ነገርኳቸው። ብዙ የንግድ ሀሳቦችንም ተናገርኩ። በጥንቆላ ስራው ላይ ያለውን ማዕረግ የሚያሳይ ቀይ የአምልኮ ልብስ የለበሰው ባባ ፍራንሲስ እንስራው ውስጥ ያለው ገንዘብ የእኔ መሆኑንና የፈለግኩትን ላደርግበት እንደምችል ነገረኝ። ወደ እኔ መጣና እጄን ይዞ ጉተት ሲያደርገኝ ከእኔ በስተቀር ክፍሉ ውስጥ ያሉት ሰዎች በሙሉ ለየት ያለ ቀለበት እንዳላቸው አየሁ። ይህ ቀለበት የዚያ አምልኮ ቡድን አባል የመሆን ምልክት ሲሆን ይህ የአምልኮ ቡድኑ ቀለበት ከዚያ የአምልኮ መንፈስ ጋር የተጋባ መሆንን የሚያሳይ ነው። ቀለበቱ ካገኘኋቸው ብዙ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ጣት ላይ ካየኋቸው ቀለበቶች ጋር ተመሳሳይ ነበር።

ይህንን ገንዘብ ምን እንደምሰራበት ማሰብ ጀመርኩ።

ቤተ ክርስቲያን መስራት ወይም አዲስ መኪናና የሚያማምሩ ነገሮች ስለመግዛት አሰብኩ። አስጨናቂው ነገር ግን በላስቲክ ከረጢት የያዝኩትን ገንዘብ ይዤ እንዴት በአየር መንገድ አልፋለሁ ወይም እንዴት ድንበር ማቋረጥ እችላለሁ የሚለው ነበር። ይህንን ያህል ገንዘብ ይዤ እንዴት ወደ ሀገሬ መግባት እንደምችልና የጉዞ ባለስልጣናት ስለ ገንዘቡ ቢጠይቁኝ ምን እንደምመልስ ሳስብ ፍርሃቴ እየጨመረ መጣ። በተአምር የተገኘ ገንዘብ ነው ብዬ ብነግራቸው በዜና ማሰራጫዎች ሁሉ እንደምቀርብና በምርመራ ስር እንደምሆን አውቃለሁ። አእምሮዬ ይህንን ገንዘብ ወደ ሀገሬ የማስገቢያ መንገድ ለማግኘት ስራ በዝቶበት ሳለ ባባ ፍራንሲስ ጠራኝና፦

"እዚህ የምታየው ገንዘብ ሁሉ ያንተ ቢሆንም ከመጠቀምህ በፊት ልታነፃው ያስፈልጋል።" አለኝ።

@Amharicbookstore

ገንዘቡ ከመገኘቱ በፊት እንድጠቀምበት እንደማይፈቅድልኝ ሲነግረኝ በእኔ አስተሳሰብ ይህንን የተለምር ገንዘብ ማገኘት ማለት መመንዘር መስሎኝ ነበር። ገንዘቡንም እንዴት እንደማነሳው ስጠይቀው ግን ወዲያውኑ የእንሰሳ መስዋዕት ማቅረብ እንዳለብኝ ነገረኝ። ይሁንና ሽማግሌው አስፈላጊውን ነገር ለማድረግ ስላልተዘጋጀሁ ገንዘቡን ማግኘት የምችል እንደማይመስለው ነገረኝ። መስዋዕት ማቅረብ ያለብኝ ምን እንደሆነ ስጠይቅ የብዙ እንስሳት ዝርዝር ነገረኝ። ቦታውን ስለማላውቀው እነዚያን ሁሉ ነገሮች የት እንደማገኝ ስጠይቅ፣ ከአምልኮ ቡድኑ አባላት አንዱ ገንዘቡን ስጠኝና የሚያስፈልገውን ሁሉ ከገበያ ገዝቼልሀ እመጣለሁ አለኝ። ዋጋው በጣም ብዙ ነበር። ጠቅላላ የሚያስፈልገው ገንዘብ በዚያ ሀገር ለአንድ ወር ብቆይ ለሆቴል፣ ለምግብና ለአውሮፕላን ቲኬት ከምከፍለው በላይ ነበር። የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለመግዛት የተወሰነ ገንዘብ ከእንስራው ውስጥ በብድር መልክ ለመውሰድ ብጠይቅም የማይቻል ነበር። ባባ ፍራንሲስ ተለምራዊ ገንዘብ ሚስጥር ቢሆንም ከሩቅ ስለመጣሁ ሊያብራራልኝ እንደሚችል ነገረኝ። ሽማግሌው አንዳንድ ሰዎች ትኩረትህ ወደ ሌላ ነገር እንዲሆን ካደረጉ በኋላ በሚስጥር ሰዎች ቦርሳዎች ውስጥ በመጨመር ተለምራዊ ገንዘብ እንደሆነ የሚያስመስሉ ሰዎች አሉ። "እነዚህ ሰዎች እውነተኛው የተለምራት ገንዘብ ድግምት የሚመጣው በውርጃ ከተገደሉ ያልተወለዱ ህፃናት መንፈስ ነው ብለው ይናገራሉ።" አለኝ።

የዚህ ስራ መንፈሳዊ መሪ ሆኖ ለ40 አመታት ያገለገለው ባባ ፍራንሲስ የነገረኝን ታሪኮች ተጠራጠርኩ።

ከዚያ ይህ የለምልኮ ቡድን መሪ ከተለምራዊ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ሰዎችን ሊያታልል ስለነበረ አንድ ወጣት ሰባኪ ነገረኝ። ይህ ሰባኪ እውነተኛ ተለምራዊ ገንዘብ የመስራት ኃይልን ለማግኘት ወደ እርሱ መጥቶ ነበር። በትንቢትና ተለምር በመስራት በሀገሩ ውስጥ ዝነኛ የሆነው ይህ ሰባኪ በቤተክርስቲያን አገልግሎቱ ላይ ከሌሎች የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ጋር በመሆን የሚሰራ ሲሆን፣ ተለምር ሰሪው ወደ ቤተክርስቲያን ከመግባቱ በፊት፣ አገልጋዮቹ ሰዎቹን ለምልጃ ፀሎት ወደ ፊት ለፊት ይጠሯቸዋል። በዚያ ጊዜ የዚያ ፀሎት መሪ ሁሉም ሰው ክብ ሰርቶ እንዲፀልይ ያዛል።

እነዚያ ሰዎች ክብ ሰርተው በመፀለይ ተጠምደው ሳለ፣ ሌሎች አገልጋዮች ሰዎቹ ወንበሮቻቸው ላይ በተዋቸው ቦርሳዎች ውስጥ ገንዘብ ያስቀምጣሉ። ሁሉም ሰው አይኖቹን ጨፍኖ ጮክ ባለ ድምፅ እየፀለየ በመሆኑ ማንም ምን እንደሚደረግ አያስተውልም። በኋላ ለሚደረገው ተለምር፣ ገንዘብና የከበሩ ድንጋዮች ቦርሳዎች ውስጥ በማስቀመጥ ያዘጋጃሉ። ከዚያ ተለምር ሰሪው መጥቶ ይፀልይና ለቤተክርስቲያኑ አባላት እግዚአብሔር ይህ ምሽት የተቀደሰ ምሽት መሆኑን እንደነገረውና "መልአኩ ሚካኤል መጥቶ ይባርከናል።" ይላል።

የመልአኩ ሚካኤል ጉብኝት በሚባለው ጊዜ ተለምራት ይሰራል፣ አንዳንዶች ፈውስ፣ አንዳንዶች ገንዘብ፣ አንዳንዶች ደግሞ የከበሩ ድንጋዮች ይቀበላሉ። ሰዎቹ ቦርሳዎቻቸውና ኪሶቻቸው ውስጥ እነዚህን አስቀድመው የተቀመጡ ነገሮች ያገኛሉ። ገንዘብና የከበሩ ድንጋዮች ያገኙ ብዙ ሰዎች ስለ ተለምራዊው ገንዘብ ይመሰክራሉ።

@Amharicbookstore

ሰዎች የእውነትም የእግዚአብሔር ስራ እንደሆነ እንዲያምኑ ብዙ ጊዜ ይህ ተአምራዊ ገንዘብ የሚሰጠው በውጪ ሀገር የገንዘብ ኖቶች ነው።

ይህ ሰባኪ እውነተኛውን ገንዘብ የመስሪያ ድግምት ለማግኘት ወደ ባባ ፍራንሲስ ይመጣል። ድግምቱን የሚፈልገው ለሌሎች ለሰዎች እንጂ ለራሱ አለመሆኑን በመናገሩ ትክክለኛው ድግምት ተሰጠው። ከዚያ በሰዎች የባንክ ሂሳብ ውስጥና ኪስ ውስጥ ገንዘብ መገኘት ጀመረ። የዚህ ተአምራዊ ጉዳቱ ይህንን ገንዘብ የተጠቀመ ሰው በወደፊት ህይወቱ የገንዘብ እስራት የሚያጋጥመው መሆኑ ነው።

ይህ የጥንቆላ ገንዘብ እንዴት እንደሚሰራና የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ተአምራዊ ገንዘብ እየተባለ እንዴት እንደሚወራለት ሰሰማ፣ ገንዘብ በመሳራት ዘዴ ሰዎችን ማታለል አደገኛ ጨዋታ እንደሆነ ተረዳሁ። ወዲያው ይህንን ኃይል ለማግኘት የነበረኝን ሀሳብ እርግፍ አድርጌ ተውኩት።

ምዕራፍ ዘጠኝ

እንዴት እንደተጀመረ

ከናይጄሪያ መመለስ

ከኪይ ጀርሚያህ ጋር ከናይጄሪያ ወደ ሀገሬ ስመለስ አሁን ህይወቴንና ውሳኔዎቼን የሚቆጣጠር ሚስጥራዊ ማህበር አባል በመሆኔ በቤተክርስቲያን ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ውሳኔ እንደሆነ እውቀያለሁ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሚስጥራዊ ማህበር ውስጥ ባለ ሚስጥራዊ ኃይል ተይዣለሁ።

ከአምልኮ ስፍራው የተሰጠኝን ልዩ የአስማት መድኃኒት ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ከቀበርኩ ከአንድ ወር በኋላ ከየቤተክርስትያን አባላት መብዛት በተጨማሪ ጥቂት ለውጦች ማየት ጀመርኩ።

@Amharicbookstore

አንድ አሁድ ቀን አገልግሎት ሰመሰጠት ወደ ቤተክርስትያን ከመሄዴ በፊት ከተሰጡኝ የእስማት መድሀኒቶች እንዱ የሆነውን በፐሳስቲክ የታሸገ ሳሙና በመጠቀም መታጠብ ጀመርኩ። ይህን ሳሙና በምጠቀምበት ጊዜ መታጠብ መጀመር ያስብኝ ከላይ ከጭንቅላቴ አንስቶ ሲሆን፣ ቀስ በቀስ እስክ እግሬ ድረስ መውረድ እንዳለበትና ስታጠብም ወደ ቤተክርስትያን ስሄድ ምን እንዲሆንልኝ እንደምፈልግ እየተናገርኩ እንድታጠብ በተሰጠኝ ትእዛዝ መሰረት ነበር እያከናወንኩ የነበረው። በሳሙናው እየታጠብኩ "ሰዎች እንዲወድቁ እፈልጋለሁ፣ ሰዎች እንዲሙሁ እፈልጋለሁ..." እያልኩ ነበር። ይህንን አድርጌ ወደ ቤተክርስትያን በሄድኩበት አንድ አሁድ ቀን ገና መድረሱ ላይ ወጥቼ "ትንቢት እንድናገር ትፈልጋላችሁ?" ብዬ ስጠይቅ ቤተክርስትያኑ በጩኸት ተሞላ። በቅፅበትም ብዙ ሰዎች ራሳቸውን እየሳቱ ይወድቁ ጀመር። እኔም ባየሁት ነገር እጅግ ተደሰትኩ።

ነቢይ ጀርሚያህ የተባለው ወደ ናይጀሪያ የወሰደኝ ሰው ናይጀሪያ ውስጥ የሚገኘው ሚስጥራዊ ማህበር አባላት በሚያደርጉት ሚስጥራዊ ስብሰባ ላይ እንድገኝ ጠራኝ። ይህ ስብሰባ የተዘጋጀው ከእርሱ አጋርትመንቶች በአንዱ ውስጥ ሲሆን፣ የሚካሄደውም ቅዳሜ ምሽት ነበር።

"አሁን ከእኛ እንዱ ስለሆንክ ቤቴክርስቲያንህ ውስጥ መጠቀም መጀመር የሚገባህን አንዳንድ 'ዘዴዎች' አገልፅልሀለሁ። በመጀመሪያ የተሰጠህን የአምልኮ ስም መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው። የአምልኮ ስምህ ከመጠሪያ ስምህ የበለጠ በጣም ታዋቂ እንድትሆን ኃይል ይሰጥሀል። በተጨማሪም ለሌሎች የአምልኮው አባላት በውስጥህ

ያለው ኃይል ምን አይነት እንደሆነና ስለአንተ ደረጃ እንዲያውቁ ያደርጋል።" አለኝ።

የተሰጠኝ ስም ካታካታ የሚል ሲሆን ይህ ስም በሁሉም በምጠቀምባቸው ፖስተሮችና የገፀያ ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል። ተከታዮቼና ህዝቡ ሁሉ እኔን በዚህ ስም ሊጠሩኝ ወይም ሊሰዩኝ ያስፈልጋል። ነቢይ ጀርሚያህ "የቤተክርስቲያንህን ሰዎችና ተከታዮችህን ሁልጊዜ የካታካታን አምላክ እንዲያመሰግኑና እንዲያወድሱ ማስተማር ያስፈልግሀል። ይህ ራሱ ስምህ በሁሉም ሰው አፍ ላይ እንዲሆንና ስምህን የሰማ በሙሉ አንተን ለማግኘት እንዲፈልግ የሚያደርግ ይሆናል።" አለኝ።

በሚቀጥለው ቀን ሁለት ሰዎች ወደ እኔ ቤተክርስቲያን እንደሚልክና አላማቸውም እነዚያ ከሚስጥራዊ ማህበሩ የወሰድኳቸው ኃይሎች በውጤታማነት እየሰሩ መሆናቸውን ማየት እንደሆነ ነገረኝ። በመጀመሪያ ናይጀሪያውያን በእኛ አጥቢያ በሚገኙ ማህበረሰብ ውስጥ ገና ስላላቸው ማንም ሰው ከናይጀሪያውያን ጋር ሚስጥራዊ ጉዳይ እንዳለኝ እንዲያውቅ ስላልፈለግኩ የቤተ ክርስቲያኑ አመራር ይህንን ሁሉ ነገር እንዴት እንደሚቀበለው እንደማደርግ ግራ ገባኝ።

ነቢይ ጀርሚያህ ነገሮች መስወጥ እንዳለባቸውና መንፈሱን ከተቀበልኩ ጀምሮ የራሴን ውሳኔ መሰወን የማልችልና ተጠሪነቱ ናይጀሪያ ውስጥ ላሉት የአምልኮው ካህናት እንደሆነ ነገረኝ።

"ይህ አምልኮ ይመራሀል፣ ያሉብህን ችግሮች ሁሉ ይፈታልሀል።" አለኝ።

@Amharicbookstore

በአእምሮዬ ውስጥ አሁን ደጉ መንፈስ ቅዱስ በአምልኮ ካህናቱ ኃይል ተተክቷል እያልኩ እያሰብኩ ነበር። በመጨረሻም ናይጀሪያ ውስጥ የሚኖሩትና ከተማ ውስጥ የባህል ህክምና ቢሮ ያላቸው የሁለቱ የአምልኮ ቡድን አባላት ሚስጥራዊ ጉብኝት እንዲያደርጉ ተስማማን።

የእሁድ አገልግሎት

ይህ በሁለት ሰዎች የሚደረገው ሚስጥራዊ ማሰልጠን ለአንድ ወር ያህል ቀጠለ። የቤተክርስቲያኗ እድገት ከእያንዳንዱ የእሁድ ፕሮግራም በኋላ ናይጀሪያ መንደር ውስጥ ለሚገኘው የአምልኮ ማህበር ሪፖርት ይደረጋል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአንድ አምልኮ ማህበር አባላት በመሆናችን እርስ በርስ ወንድም ተባብለን እንድንጠራራ ተነገረን። ነቢይ ጀርሚያህ አሁን ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀሁና የሰለጠንኩ በመሆኑ ዋናው መንፈስ ነቢይ ሆኜ እንድሰራ እንደፈቀደልኝ ነገረኝ። ከዚያ የሚከተሉት መመሪያዎች ተሰጡኝ፦

- መጽሀፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ የተማርኩት ሁሉ አይሰራም። ምክንያቱም የመጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስራ ከአምልኮ ማህበሩ ስራ ጋር አንድ አይደለም። የአምልኮ ማህበሩ እንዴት እንደሚሰራ ደረጃ በደረጃ አስተማረኝ። ስራዎቹን ‹ፎረንሲክ ትንበያ፣ ጉግል ትንበያና ትክክለኛ ትንበያ› ብለው ይገልጿቸዋል።
- የጎብኚዎች ካርድ እንዳዘጋጅና በካርዶቹ ላይ ስሞቻቸውን፣ የአባታቸውን ስም፣ የትውልድ ቀናቸውንና የፀሎት ጥያቄዎቻቸውን እንዲጽፉ ማድረግ እንደሚገባኝ አበረታታኝ።

ሁሉም የጎብኚዎች ካርድ እኔ ጋ እንዲቀመጥና በሚቀጥለው ሳምንት ከተማ ውስጥ ባህላዊ ሀኪም ሆኖ የሚሰራውን የአምልኮ ማህበር አባል የሆነውን ዶክተር ያያ የሚባለውን ሰው ማግኘት እንደሚገባኝ ነገረኝ። ይህ ሰው የጎብኚዎችን ካርዶች ወስዶ በእኔ ምትክ ለአምልኮው ካህናት ይሰጣል። የአምልኮው ማህበር ዝርዝሩ ላይ ስላሉት ስለእያንዳንዳቸው ዝርዝር መረጃ ይሰጣል። ከዚያ ወንድም ጀርሚያህን "በብዙ ኪሎሜትር ርቆ ስላለ ሰው የግል መረጃ የሚገኘው እንዴት ነው?" ስል ጠየቅኩት። ወንድም ጀርሚያህ "የርቀት ፈውስ ወይም ትንቢት ብለን የምንጠራው ይህንን ነው። የሚሰራው የሰውየውን ሙሉ ስምና የልደት ቀን ልክ መታወቂያው ወይም ፓስፖርቱ ላይ በተፃፈው አይነት ስታውቅ ብቻ ነው።" አለኝ። የካህናቱ አምልኮ ማህበር ዝርዝሩ ላይ የተፃፉትን ሰዎች የግል መረጃ ያገኛሉ። እኔ ደግሞ በሳምንቱ ውስጥ ሁሉንም እፅፋለሁ።

- በእሁድ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ላይ ትንቢት የምናገረው የካህናቱ አምልኮ ዝርዝር መረጃውን ለሰጠኝ ሰዎች ብቻ ይሆናል።

- እያንዳንዱ የእሁድ የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ላይ ከመሄዴ በፊት የእንስሳ መስዋዕት ማቅረብና ቅርብ ባለው ወንዝ ውስጥ በእንስሳው ደም መታጠብ ይጠበቅብኛል።

@Amharicbookstore

- በቀንድ ውስጥ ተደርጎ ከናይጀሪያ የተሰጠኝን "የአመድ ኃይል" መጠቀም አለብኝ። የጥቁሩን አመድ የአስማት መድሀኒት በምላሴ መላስ አለብኝ። ይህ ሁሉ ሰው የምናገረውን ሁሉ ያለምንም ጥርጣሬና ጥያቄ እንዲያምን የሚያደርግ ሲሆን፣ የሰውን አእምሮ የሚያደነዝዝና ሀሳብ የማስለውጥ ኃይልም አለው። ስለዚህ የምናገረው ሁሉ ያለምንም ተቃውሞ ተቀባይነት ያገኛል።

የመታወቂያ ቁጥርና የመኪና ታርጋ

ነቢይ ጀርሚያህ በብዙ ትንቢታዊ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሆነውን የመታወቂያ ቁጥርና የባንክ ሂሳብ ትንበያ መስራት እፈልግ እንደሆነ ጠየቀኝ። እንደዚያ አይነት ትንበያ ፎረንሲክ ትንበያ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ ብቻዬን ልሰራው እንደማልችልና ለእኔ መረጃ የሚሰጡ ሁለት የአይቲ ሰዎች የሚያስፈልጉ መሆኑን ነገረኝ። በተጨማሪም ይህ ነገር እውነት እንዲመስል ከጀርባ ለሚሰሩት ሰዎች የምከፍለው በቂ ገንዘብ ሊኖረኝ እንደሚገባም አስረዳኝ። በደንብ የታቀደ ትንቢት ነበር።

ከዚያ ከጀርባ ለሚሰሩት ሰዎች የሚሰጥ ሙሉ ስምና የመኪና ታርጋ ቁጥር እንደሚያስፈልግም ነገረኝ። የመጀመሪያው ደረጃ ትንቢት የሚነገርላቸውን ሰዎች የመኪና ታርጋ ከጀርባ ለሚሰሩት መስጠት ሲሆን፣ ሰዎቹ የመኪናውን ባለቤት አድራሻና የመታወቂያ ቁጥር ያገኙታል። የሚገኘው መረጃ ሁሉ ከሚተነበየው ሰው ስም ጋር የሚዛመድ ከሆነ መረጃው በሙሉ ትክክል ነው ማለት ነው።

ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ለሁለተኛው ሰው ትንቢት የሚነገርለትን ሰው የመታወቂያ ቁጥር መስጠት ሲሆን፣ ከጀርባ የሚሰራው ሁለተኛው ሰው ትንቢት የሚነገርለትን ሰው የባንክ ሂሳብ የማወቂያ መንገድ ያገኛል። ከዚያ ስለገንዘብ እንቅስቃሴዎቹና ያለው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣል።

ይህ ሁሉ መረጃ የካህናት አምልኮው ከሳኩው መረጃ ጋር ተደርጎ ለነቢዩ ይሰጣል። ይህ ሁሉ የተሰበሰበ መረጃ የነቢዩና ከጀርባ የሚሰሩት ሰዎች ኢላማ መሆናቸውን በማያውቁት ንፁሀን ላይ ተግባራዊ ይደረጋል።

የተአምራዊ ገንዘብ ክወናዎች

የተአምራዊ ገንዘብ ጉዳይም ልክ መታወቂያ ቁጥሩ በሚሰራበት አይነት የሚሰራ ሲሆን እዚህ ላይ ግን ከጀርባ የሚሰሩት ሰዎች ነቢዩ በሰዎቹ የባንክ ደብተር ላይ በሚፀልይበት ወቅት ወደ ሰዎቹ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ ማስተላለፍ መቻል አለበት። ስራው የቤተክርስቲያኑ አባላት ዝርዝር መረጃ ስላለው ኢንተርኔት ባንኪንግም መጠቀም ይችላል። ተጨማሪ ተአምራዊ ገንዘብ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም በሚካሄድበት ጊዜ ሰዎች ቦርሳዎች ውስጥ በሚስጥር ገንዘብ በመክተት የሚሰራ ነው። ቦርሳዎቹ ውስጥ የሚከተተው ገንዘብ በአብዛኛው የውጪ ሀገር ገንዘብ ሲሆን፣ ስራው የሚሰራውም ለዚሁ ስራ በሰለጠኑ መባ ሰብሳቢዎች ነው። ይህ ስራ የሚሰራው ምዕመናኑ ትኩረታቸው ሌላ ነገር ላይ ሲሆን ወይም አገልጋዮቹ ተያይዘው እንዲፀልዩ ወደ ፊት ሰፊት በሚጠሯቸው ጊዜ ነው። ነቢይ ጀርሚያህ ይህንን የገንዘብ ተአምር የሚሰራው የቤተ ክርስቲያኑ

@Amharicbookstore

ተከታዮችና አባላት ያንን ነቢይ ያሰምንም ጥርጣሬ እንዲያምኑት ለማድረግ እንደሆነ ነገረኝ። ይህንን የገንዘብ ተአምር ከተመለከቱ በኋላ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያኑ አባላት ያንን ነቢይ በደሞዛቸው፣ በጡረታ አበላቸው ወይም በገንዘብ ፍሰታቸው ሁሉ ሊያምኑት ይጀምራሉ።

ጀርሚያህ እንደነገረኝ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ብድር ለመጠቅ ወደ ባንክ ሄደው ይከለከሉና በነቢይ ሲፀለይላቸው የጠየቁት ብድር በጥቂት ወራት ውስጥ ይፈቀድላቸዋል። ነቢዩ ብድር እንዲፈቀድላቸው የሚፈልጉትን ሰዎች ዘር የሚሆን ገንዘብና ሙሉ ስማቸውን ከግል መረጃዎቻቸው ጋር እንዲሰጡ ይጠይቃል። ያ ነቢይ የሚፈልገውን መረጃና ዘር የሚሆነውን ገንዘብ ካገኘ በኋላ ከጀርባ የሚሰሩት ሰዎች ወደ ሰዎቹ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ እንዲያስተላልፉ ያደርጋል።

እነዚህ ተአምራቶች ሌሎች ሰዎች ያንን ነቢይ የበለጠ እንዲያምኑት ያበረታታቸዋል። ምክንያቱም በተአምር የተገኘው ገንዘብ እንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ወቅት ስለሚገለጽ ነው። የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም በሚካሄድበት ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔር ተአምር እንደሆነ እንዲያስቡ በሂሳባቸው ላይ ገንዘብ እንደገላላቸው የሚገልፅ መልዕክት ያገኛሉ። እንደዚህ አይነት ተአምራት ተከታዮቹ ነቢያቶቻቸውን ከየትኛውም ተቃውሞ እንዲከላከሉ የሚጠቅም ሲሆን በተጨማሪም በመጀመሪያ ዘር እንዲሆን ተብሎ የሰጡትን ገንዘብ የመናፍስቱ መሰዊያ ጋር እንዲቀመጥ በማድረግ እነዚያ ሰዎች እጀቻቸው ላይና በባንክ ሂሳቦቻቸው ውስጥ ያላቸውን ገንዘብ እንዲሁም ደሞዛቸውንና የጡረታ አበሎቻቸውን ሳይቀር የመጨረሻዋ ሳንቲም እስክትቀር ድረስ እንዲሰጡ በመናፍስቱ ተፅእኖ ስር

እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። የሀሰተኛ ነቢይ ተከታዮች አንድ ጊዜ በዚህ አይነት ኃይል ከተያዙ በኋላ እነርሱን ንስሀ እንዲገቡ ማሳመን በጣም አስቸጋሪ ነው።

ይህንን አይነት ማታለያ መስበር የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው።

ነቢይ ጀርሚያህ ሲነግረኝ አንዳንድ ጊዜ ነቢያት ታማኝ የቤተክርስቲያን አባላትን ብድር እንዲያገኙ ያምላል። ይህንንም ለማድረግ ከጀርባ የሚሰሩት ሰዎች ለብዙ ወራት ጥሩ የብድር መረጃ ላላቸው ሰዎች ይህንን የተአምራት ገንዘብ ወደ ሂሳባቸው ያስተላልፉላቸዋል። ከዚያ ከሶስት ወራት በኋላ ይህ ነቢይ እነዚህን የተአምራት ገንዘብ የተቀበሉ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብድር እንዲጠይቁ ይነግራቸዋል። ይህ ነቢይ ተከታዮቹ ያለምንም ተቃውሞ ብድር እንዲወስዱ ለማድረግ ማታለያ "እርሱም ሄደሽ ከጉረቤቶችሽ ሁሉ ከሚዛ ባዶ ማድጋዎች ተዋሺ" 2ኛ ነገ. 4፡3 የሚለውን የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ይነግሯቸዋል።

የእዳ ማጣከር ክንውን

ይህ አሰራር የሚከናወነው ከጀርባ በሚሰሩ ሰዎች አማካኝነት ሲሆን እነዚህ ሰዎች የቤተክርስቲያኑ አባላትና ጉባኤዎች የግል መረጃዎች ስላላቸው የነዚህን ሰዎች የብድር መረጃና ዕዳ ማወቅ የሚችሉ ናቸው። የአንዳንድ አባላትን ዕዳ ይከፍሉና አባላት መጥተው እዳቸው በተአምር እንደተከፈለላቸው እንዲመሰክሩ ያደርጋሉ። እንደዚህ አይነት ተአምር የተደረገላቸው ሰዎች የዚህ ነቢይ ቀንደኛ

@Amharicbookstore

ደጋፊ ስለሚሆኑ ነቢዩ ተቃውሞ ሲደርስበት እነዚህን ተአምራት በመናገር ይከላከሉለታል።

የስራ ቃለ መጠይቅ ክንውን

በአባልነት ወይም ጉብኚ ፎርም ላይ የሰዎችን የስራ ሁኔታ የሚገልፅ የጥያቄ ክፍል አለ። ስራ የሌላቸው ሰዎች እንዲፀለይላቸው ይጠሩና ከጥቂት ቀናት በኋላ ለስራ ቃለ መጠይቅ እንዲቀርቡ የሚገልጽ የፅሁፍ መልዕክት በማይሰሩ የስልክ ቁጥሮች በመጠቀም በስልኮቻቸው እንዲደርሳቸው ይደረግና ሰዎቹ ስለ የስራ ቃለ መጠይቁ የፅሁፍ መልዕክት መመስከር ይጀምራሉ። የተአምራት አገልግሎታቸውን ቡቲቪ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ የሚያስተላልፉ አካላት ብዙ ንፁህ ሰዎችን ለመሳብ የሚጠቀሙት እንደዚህ አይነት ምስክርነቶችን ነው።

የፅሁፍ መልዕክት፣ የዘመድ አዝማድ ግንኙነት ዝርዝርና ትንቢቶች

ነቢይ ጀርሚያህ "ይህንን ትንቢት ስትሰራ አገልጋዮችህ መረጃዎችን ለአንተ እንዲሰጡ በጣም የሰለጠኑ መሆናቸውን እርግጠኛ ሁን።" አለኝ። ይህንን ለማድረግ የቤት ለቤት ጉብኝት ጊዜ ወይም የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት አባላቱ ሳያውቁ የእጅ ስልኮቻቸውን በመፈተሽ ነው። ስልኩ ላይ ያሉትን የፅሁፍ መልዕክቶች፣ የሰውየውን የቅርብ ዘመዶችና ጓደኞች ቁጥሮች በሚስጥር ይታያል። የተሰበሰበው መረጃ ሁሉ በኋላ ላልጠረጠረው ተጠቂ ትንቢት ሆኖ ይቀርባል።

የህይወት አጋር የማግኘት ትንቢት

በዚህ ክንዋኔ ውስጥ የቤተ ክርስቲያኑ አባላት የግል መረጃ ዝርዝር ከጀርባ በሚሰሩ ሴላ የሰዎች ቡድን ይሰጣል። ከዚያ እነዚህ ሰዎች የህይወት አጋር ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራሉ። በዚህ ስራ ውስጥ "ሁልጊዜ ዝርዝሩ ላይ የሚኖሩትና ቀላል ኢላማ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ እነዚህን ሴቶች ወደ ጋብቻ እንዲሄዱ የሚያደርገው መሳሪያ ማህበራዊ ሚዲያ ነው።" ሲል ነቢይ ጀርሚያህ ነገረኝ።

ነቢዩ ላጤ ስሆኑትና ባል ማግኘት አጥብቀው ለሚፈልጉ ሴቶች ከፀሰየ በኋላ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ አገልጋዮቹ ከእነዚህ ሴቶች የተቀበሳቸውን የመገኛ መረጃዎች በመጠቀም ከሰዎች ጋር የማገናኘት ስራ ይሰራሉ። ለእንደነዚህ አይነት የተለያዩ ቦታዎች ሳሉ ያላገቡ ሴቶች በተመሰነ ክፍያ ለፀሎት የሚጋበዙበት ልዩ አገልግሎትም አለ።

"አንዳንዶቹ ሴቶችም በመጨረሻ ሆን ብሎ ከተዘጋጀላቸው የህይወት አጋር ጋር የሚጋቡበት ሁኔታም አለ።" ሲል ነቢይ ጀርሚያህ ነገረኝ። ነገር ግን በማታለል ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እንደዚህ አይነት ጋብቻዎች ዘላቂ አይደሉም።

እባቦች፣ አሳና ሌሎች እንግዳ ነገሮችን ማስመለስ

ነቢይ ጀርሚያህ እንደነገረኝ እንደነዚህ አይነት ተአምራት ለመስራት ሁለት ቡድኖች ያስፈልጋሉ። የመጀመሪያው ቡድን ተከፍሏቸው የሀሰት የተቀናበረ ተአምራት የሚሰሩ የመድረክ ሰዎች

@Amharicbookstore

ሲሆኑ፣ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በመረጃ ዴስክ ላይ የሰዎችን የፀሎት ጥያቄዎች የሚመዘግቡ ከአገልጋዮች የተውጣጡ ሰዎች ናቸው። የሆነ ሰው መጥፎ ሀልሞች ስለማለምና በምሽት እንቅልፍ መተኛት እንደተቸገረ ከተናገረ አገልጋዮቹ የሰውየውን ቤት አፈላልገው በሰውየው ግቢ ውስጥ የሆነ ነገር መትከላቸውን እርግጠኛ መሆን አለባቸው። የሆድ ሀመም እንዳለባቸው የሚናገሩ ሰዎች ሲኖሩ ደግሞ ነቢዩ መድረክ ላይ ሲወጣ ይፀልይና "ዛሬ የተለያዩ ነገሮችን የሚያስመልሱ ሰዎች አሉ።" በማለት ይጮሀል። ምክንያቱም የጠጡት ውሀ እንዲያስመልሱ እንደሚያደርጋቸው ስለሚያውቅ የጠጡት ፈሳሽ ሰራውን የሚሰራበትን ጊዜ ይጠብቃል። ከዚያ የሚፀልይላቸው ሰዎች ማስመለስ ይጀምራሉ። የሆድ ሀመም የሌለባቸው ሰዎች ደግሞ ቤታቸው ከደረሱ በኋላ እንዲያስመልሳቸው የሚያደርግ ነገር ይሰጣቸዋል። በሚቀጥለው አሁድ ወደ ቤተክርስቲያን መጥተው ወይም በሳምንቱ ቀናት የምክር አገልግሎት ለማግኘት ይመጡና ስለ ሁኔታው ይመሰክራሉ።

የራዕይ ዘይት

በትንቢታዊ አብያተ ክርስቲያናት በተለምዶ የሚሸጥ ልዩ የራዕይ ዘይትም አለ። አባላት ይህንን ዘይት ሁልጊዜ ማታ ማታ ከመተኛታቸው በፊት ፊታቸውን እንዲቀቡት ይታዘዛሉ። የዘይቱ ሽታ በሰው አእምሮ ላይ መጥፎ ውጤት የሚያሳድር በመሆኑ የተቀባው ሰው መጥፎ ሀልሞችንና ቅዠቶችን ያያል። ከዚያ ወደ ነቢዩ በመምጣት ገንዘብ ከፍሎ እነዚህን ሀልሞች በተመለከተ ምክር ይቀበላል።

ታላቅ ወይም የስታዲየም ስብሰባ ከታላላቅ ስብሰባዎችና ከመሰጠት በፊት መስዘብ ይዘጋጃል

በስታዲየም ወይም በሌሎች ትላልቅ ቦታዎች ላይ በሚደረግ ስብሰባ ላይ ፓስተሮች ብዙ ሰዎችን መሳብና ሰዎችንም ሁለት ጊዜ እንኳን ሳያስቡ ንብረቶቻቸውን፣ የጡረታ አበሎቻቸውን፣ መኪናዎቻቸውንና ሌሎች ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎቻቸውን እንዲሰጡ ማድረግ የሚችሉት እንዴት እንደሆነ ነቢይ ጀርሚያህን ጠየቅኩት። እነዚህ ሰዎች ድሆችን፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸውን፣ ወላጆች የሌሏቸውንና በአጥቢያቸው ያሉትን ፓስተሮች መርዳት የማይፈልጉ፣ ነገር ግን ተጋብዞ ለሚመጣ ነቢይ ተአምር ለማድረግ የሚፈቅዱ መሆናቸውን ጭምር ጠቀሰኩለት። ሳቀና ከዚህ ብዙ ሰዎችና ገንዘብ ከመሰብሰብ ጀርባ ያለውን ኃይል ነገረኝ።

ለምች ገንዘባቸውን፣ መኪናዎቻቸውን፣ ቤቶቻቸውን፣ የእጅ ስልኮቻቸውንና ሌሎች ውድ ንብረቶቻቸውን የሚሰጡት ስብሰባው በሚካሄድበት ቦታ ላይ ከተቀበረው የአስማት መድሀኒት የተነሳ መሆኑን ነቢዩ ነገረኝ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ስብሰባዎች ከመደረጋቸው በፊት፣ በመጀመሪያ የሚመቻቹት በመንፈስ ባሉ አጋንንቶች ነው። አንድ ነቢይ ስብሰባ ማድረግ ከመቻሉ በፊት ከዚያ ቦታ ላይ ብዙ ሰዎች እንዲመጡ ለማድረግ እዚህ ቦታ ላይ ለሚገኙ መናፍስት በግ ወይም ፍየል በማረድ መስዋዕት ያቀርባል። ወዲያው ነቢይ ጀርሚያህ "ራስህን አንድ ጥያቄ ጠይቅ፣ የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ላይ ስትታደም በእግዚአብሔር ተመርተህ ነው ወይስ በዚያ

©Amharicbookstore

ቦታ ላይ በተቀበረ መስዋዕትና መናፍስት ተጐትተህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ። ይህንን አዲስ መረዳት በትኩረት አዳመጥኩ።

አንድ ነቢይ እነዚህ ኃይላት በትልልቅ ስብሰባዎች ወቅት በውጤታማነት እንዲሰሩ ስብሰባው ከመደረጉ ከሰስት ሳምንት በፊት ቦታውን ለመሰለል አገልጋዮቹን ይልካል። ከዚያ ይህ ሰው በዚያ አካባቢ ዙሪያ ያሉ ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናትን ይጐበኛል። የጉብኝቱ አላማም ከእነዚያ በዙሪያው ካሉት አብያተ ክርስቲያናት አፈር ቆንጥሮ ለመውሰድ ነው። በተጨማሪም ይህ ሰው ሰዎች ከሚበዙበት ቦታ ላይም አፈር ይወስዳል። እንዲሁም የሰዎችን ስም በተለይም በዚያ አካባቢ ሀብታም ወይም ብዙ ገንዘብ ያላቸው ክርስቲያኖችን ስሞች ይወስዳል። እነዚያን ስሞችና አፈር በመጠቀም ከስብሰባው በፊት መስህብ ይሰራል።

ነቢይ ጀርሚያህ "እንደዚያ አይነት የሚሰራው መስህብ ሰዎቹ ምንም ሳያስቡ ገንዘባቸውን፣ መኪኖቻቸውንና ቤቶቻቸውን እንዲሰጡ የሚያደርግ ልክ ሩቅ እንዳለ ሪሞት ኮንትሮል ነው። የሚያሳዝነው ነገር እነዚያ ሰዎች ወደራሳቸው ሲመለሱ ያ ነቢይና ቡድኑ ርቀው የሄዱ መሆናቸው ነው።" ሲል ነገረኝ።

እኔም ለምን ክርስቲያኖችን ኢላማ እንደሚያደርግ ስጠይቀው "ክርስቲያኖች ደካሞች ናቸው፣ ተለምራት ስለሚወዱ በቀላሉ ይታለላሉ። የትኛውንም ነገር የማመን ዝንባሌ ስላላቸው አስፈላጊውን ምርመራ ሳያደርጉ በቀላሉ ይሸወዳሉ።" አለኝ። በቀመጠል መስህቡን እንዴት እንደሚያዘጋጁ አብራራልኝ።

"ከስብያተ ክርስቲያናትና እንደ የንግድ ማዕከላት ካሉ ሌሎች የሰዎች መሰብሰቢያ ቦታዎች አፈር ከወሰዱ በኋላ ያንን አፈር ከመናፍስት አምልኮ ቦታ ከተሰጣቸው የእስማት መድኃኒት ጋር ያደባልቁታል። ያንን ድብልቅ በጥቁር የፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ ካደረጉት በኋላ በዚያ የስብሰባ ቦታ መግቢያ ላይ ወይም በዚያ አካባቢ ባለ የትኛውም አራት መንታ መንገድ መግቢያ ላይ ይቀብሩታል። በተጨማሪም ህይወት ያለው ዶሮም ይቀብርና ዶሮው ሞቶ መበስበስ ሲጀምር ያ መስህብ መሰራት ይጀምራል። ከጥቂት ቀናት በኋላ የሞተው ዶሮ በስብሶ ትሎች ማፍራት ሲጀምር ሰዎች በብዛት ወደ ስብሰባው ይመጣሉ። ብዙ ጊዜ ስብሰባው ክለቅም በላይ በመሙላት ይጨናነቃል።" ሲል ነገረኝ። ቀጥሎም ከዶሮው ጋር ስለሚቀበረው በወረቀት ላይ ስለተፃፉት ስሞች ጠየቅኩት። እርሱም "እነዚያ ሰዎች ብዙ መጠን ያለው ገንዘብ፣ መኪናዎች ወይም ቤቶች እንዲሰጡ ወይም የሆነ ትልቅ ነገር እንዲያደርጉ በአጋንንት ተፅዕኖ የተደረገባቸው ናቸው።" አለኝ።

ሁሉም ስጦታ በእግዚአብሔር የተነሳሳ ሰው የሚሰጠው እንዳልሆነ የተረዳሁት የዚያን ጊዜ ነበር።

ስሞቻቸው በነዚያ ወረቀቶች ላይ ከተፃፉት ሰዎች አንዳንዶቹ የሚፀልዩና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ቢሆኑ ኖሮ አጋንንቶች እንደዚህ አይነት ወጥመድ ውስጥ እንዲወድቁ ተፅዕኖ ሊያሳድሩባቸው እንደማይችሉ አምናለሁ። የፀሎት አለመኖር ሰዎችንና ቤተሰቦቻቸውን የአጋንንት ተጠቂ ያደርጋል። ሰዎች ያለማቋረጥ የሚፀልዩ ከሆነ፣ እነዚህ አጋንንቶች በእንደዚህ አይነት ወጥመድ ውስጥ እንዲወድቁ

@Amharicbookstore

ተፅዕኖ ሊያሳድሩባቸው አይችሉም ነበር። ሰዎችንና ቤተሰቦቻቸውን የአጋንንት ተጠቂዎች የሚያደርገው የፀሎት አለመኖር ነው። ሰዎች ያለማቋረጥ የሚፀልዩ ከሆነ በአጋንንቶች ተፅዕኖ ስር ሊሆኑ አይችሉም።

የእንደዚህ አይነት ትላልቅ ስብሰባዎች መደረጋቸው የሚያስከትለው ስቃይ፣ መላውን ማህበረሰብ ሊያንቀጠቅጥ የሚችል ታላቅ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መዘጋት የመጀመራቸው እውነታ ይህ ነው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሚዘጉበት፣ ፓስተሮች መፀለይ የሚቀንሱበት፣ አብያተ ክርስቲያናት የማያድጉበትና የፍቺ ቁጥር የሚጨምርበት ምክንያት በዚያ አካባቢ የመናፍስት አምልኮ ነቢያትን የመቀበልና የአምልኮ መናፍስት የመገኘታቸው ውጤት ነው።

በዚህም ምክንያት ክፍተኛ የሆነ የነፍስ ግድያ፣ ደም ማፍሰስ ወይም አደጋዎች መጠን ይኖራል፣ ብዙ ውጣቶች፣ የፅፀ፣ የዝሙትና የብዙ የተለያየ መጥፎ ነገሮች ሱሰኞች ይሆናሉ። ራስን የማጥፋት ክፍተኛ መጠንም ይኖራል። ሁልጊዜ የሚከፈል ዋጋ ቢኖርም፣ በአብዛኛው ክባዱን ዋጋ የሚከፍሉት ግን ንፁሀን ሰዎች ናቸው።

ቀጥሎ ነቢይ ጀርሚያህ "ከአንድ አካባቢ ውጤታማ የሆነ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲኖር ለማድረግ ሶስት የመስክ ሰራተኞች ሊኖሩህ እንደሚገባ እርግጠኛ መሆን አለብህ። የሶስቱ የመስክ ሰራተኞች መኖር አላማ መንፈሳዊ መነቃቃቱ ወደሚካሄድበት ቦታ በመሄድ በዚያ አካባቢ የተለያዩ ቦታዎች በመከፋፈል መረጃ መሰብሰብ ነው።" ሲል ነገረኝ።

ስለዚህም የሚከተሉትን ተግባራዊ ምሳሌዎች ሰጠኝ።

የመጀመሪያው የመስክ ሰራተኛ (ክርስቲያናዊ አብያተ ክርስቲያናት)

የመጀመሪያው የመስክ ሰራተኛ በመጀመሪያ በአብያተ ክርስቲያናትና በአካባቢው ባሉ ክርስቲያኖች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። የመስክ ሰራተኛው በዚያ አካባቢ በጣም ውጤታማና ፀሎት የሚደረግበትን ቤተ ክርስቲያን ለመለየት በአካባቢው ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ይጉበኛል። ከዚያ ቤተክርስቲያኑን በህንፃው መጠንና በአባላቱ ብዛት ይለካል። የመስክ ሰራተኛው አንድ ጊዜ አብያተ ክርስቲያኑን ከለየ ቡኋላ በነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ያሉትን ፓስተሮች፣ የዋናውን ፓስተር የኋላ ታሪክ፣ ቤተሰቡን፣ የሚያዘውን መኪናና የት እንደሚኖር ያጠናል። በተለምዶ ኢላማ የሚደረጉት ክርስቲያኖች ደግሞ ተአምራትና ቅፅበታዊ ትንቢቶችን የሚወዱ ሲሆኑ ነው። ከእንደዚህ አይነት ክርስቲያኖች አብዛኞቹ የሚለዩት በመኪናዎቻቸው ላይ በሚለጥፏቸው የፓስተሮቻቸው ምስሎች ያሉባቸው ስቲከሮችና የቤተ ክርስቲያናቸው ወይም የነቢይ ስም ባለበት የእጅ አምባሮቻቸው ነው።

የመስክ ሰራተኛው ከነዚህ ክርስቲያናት ጋር በግቢያቸው ውስጥ በሚስጥር የሆነ ነገር መቅበር የሚያስችለውን ወዳጅነት መመስረቱን እርግጠኛ መሆን አለበት። እነዚህ የመስክ ሰራተኞች በተለምዶ እንደ አባብ የመሳሰሉ ነገሮችን፣ አስፈሪ እቃዎችን፣ በውስጣቸው አስፈሪ ነገር ያለባቸው ትናንሽ ብልቃጦችን በስዎቹ ግቢ ውስጥ ይቀብራሉ። በተጨማሪም ይህ የመስክ ሰራተኛ ሰዋናው ነቢይ

© Amharicbookstore

የሚሰጥ የመኪና ታርጋ ቁጥሮችና የቤተሰብ የግል መረጃዎች ይሰበሰባል።

ዋናው ነቢይ ከመስክ ሰራተኞቹ የተገኘውን መረጃ በሚያደርገው ትልቅ ስብሰባ ላይ በትንቢት መልክ ለመናገር ያስቀምጠዋል። ነቢዩ በተጨማሪም እርሱ የሚሰራባቸውን መናፍስትና ሀይላት ምሪት እንዲሰጡት ይጠይቃል። ከእነዚህ መናፍስት ምሪት የመጠየቁ አላማ፣ ስለ ስራው ማረጋገጫ ለማግኘት መሳው አሰራር ውጤታማና ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥና የመስክ ሰራተኞቹ የጉበኟቸው ቤተሰቦች ሁሉ ስብሰባውን የሚታደሙ መሆኑን ለማወቅ ነው። አሰራሩ ውጤታማ እንዲሆን፣ መናፍስቶቹ ሊላማ የተደረጉት ሰዎች ምክር ለማግኘት በርካታ ገንዘብ እንዲከፍሉና እንደ ተቀደሱ ዕቃዎች ሆነው የቀረቡ የአሰማት መድኃኒቶችን እንዲገዙ በትክክል መታለላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

አንድ ጊዜ መናፍስቱ ከተስማሙ፣ ስብሰባው ይቀጥላል። ፖስተሮችና በራሪ ፅሁፎች በመላው አካባቢ ይሰራጫሉ።

በትልቅ ስብሰባዎች ላይ ሰዎች ላይ የሚደረጉ የተለመዱ ማታለያዎች

በትልልቅ የማነቃቂያ ስብሰባዎች ላይ የሚገኙ ነቢያት ስለ ነቢይነት ስጦታዎቻቸውና የእነርሱ ትንቢት ምን ያህል ኃያልና ትክክለኛ እንደሆነ ጉራ ይነዛሉ። ከዚያ ለተሰበሰበው ህዝብ ሰዎችን እንዴት በስማቸውና በቤት ቁጥሮቻቸው እንዲሁም ካለምንም ንግግር ከየቤቶቻቸው መጥራት እንደሚችሉ ይናገራሉ። ለተሰበሰበው ህዝብ ችሎታቸውን ለማሳየት በዚያ አካባቢ ያለውን ታዋቂ ፖስተር ሰም

ይጠቅሳሉ። ስሙን በሚጠሩበት ጊዜም የተሰበሰቡት ሰዎች ያንን ሰም የእግዚአብሔር መንፈስ በድንገት ለነብዩ የነገረው እንደሆነ አድርገው እንዲያምኑ በማድረግ ስሙን አስተካክሰው አሰሙጥራታቸውን አርግጠኛ መሆን አለባቸው። የተሰበሰቡት ሰዎች በጣም በመደነቅ የተጠቀሰውን ፖስተር ሰም አስተካክሰው በመጥራት ነቢዩን ያግዙታል። ምክንያቱም ከፖስተሩ የቤተ ክርስቲያን አባላት አንዳንዶቹ እዚያ ይገኛሉ። ከዚያ ያ ነቢይ የተገረመ በመምሰል የሰውየውን መልክ፣ ቤተክርስቲያኑ የት እንደሚገኝ፣ የእጁ ስልክ ቁጥር ስንት እንደሆነና የመኪናውን ታርጋ ሳይቀር መናገሩን ይቀጥላል። የተሰበሰቡት ሰዎች በዚህ የተቀናበረ ትንቢት ነቢዩን ባመሰገኑበትና በእድናቆት በጮሀበት ቅጽበት ያ ነቢይ የተሰበሰበው ህዝብ ሙሉ በሙሉ ለመታለሉ ጥሩ ምልክት ይሆንለታል።

ከዚያ ነቢዩ ለተሰበሰበው ህዝብ ጌታ እንደገለጠለት በመናገር የታዋቂውን ፖስተር የሞባይል ስልክ ቁጥር ይናገራል። የተሰበሰቡት ሰዎች ያ ነቢይ ሰዎችን በስልክ ቁጥራቸው ሳይቀር የሚተነብይ በመሆኑ ልክ ግማሽ ሰው፣ ግማሽ አምላክ እንደሆነ አድርገው ማየት ይጀምራሉ። ወዲያው ከተሰበሰቡት ሰዎች አንዱን ለፖስተሩ ደውሎ ወደ ስብሰባው ቦታ እንዲመጣ እንዲነግረው ይጠይቃል። ፖስተሩ ሲመጣም፣ ያ ነቢይ ያውቀው እንደሆነ ይጠይቀዋል። ፖስተሩም በድንጋጤና ባለማመን እንደማያውቀው ይናገራል። ከዚያ ያ ነቢይ ለፖስተሩ በእድናቆት "አም" የሚልባቸው በህይወቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን በመጥቀስ እንዲያረጋግጥለት ይጠይቃል። ይህን ጊዜም መላው ህዝብ ተነስቶ እጅግ በበዛ አድናቆት ያጨበጭባል፤ ከዚያ ቀን አንስቶም ስለዚያ ስብሰባ የሚነገረው አድናቆት ልክ እንደ

@Amharicbookstore

ሰደድ እሳት ይዛመትና ብዙ ሰዎች ተአምራትና ትንቢቶችን ለመቀበል ተስፋ በማድረግ ወደዚያ ስብሰባ ይጉርፋሉ።

ሁለተኛው የመስክ ሰራተኛ

ሁለተኛው የመስክ ሰራተኛ ደግሞ መረጃ ለመሰብሰብ በአቅራቢያ ባሉ ሆስፒታሎችና ባህላዊ ሀክምና መስጫዎች የሚሄድ ነው። የመስክ ሰራተኛው ታማኝ ከሆኑ ምንጮች መረጃዎችን ይወስዳል። ሆስፒታል የታመሙ ዘመዶቻቸውን የሚጠይቁ ሰዎችን ስምና አድራሻ የያዙ ናቸው። የመስክ ሰራተኛው ከዚያ ውጪ ቁጭ ብለው ፀሀይ የሚሞቁና የተገለሉ የሚመስሉ ሰዎችን ያነጋግራል። የመስክ ሰራተኛው የነዚህን ታማሚዎች ዘመዶች መረጃ በመጠየቅ እንደሚደውሉላቸውና መጥተው እንደሚጠይቋቸው እንደሚያደርጉ ቃል ይገባል። ቀጥሎ ወደ ባህላዊ የህክምና መስጫዎች በመሄድ በሚስጥር የስራ ግንኙነት ለመፍጠር ይሰማማል። አንዳንድ ባህላዊ ሀኪሞች እነዚህን ታካሚዎቻቸውን ዝርዝር መረጃ አይሰጡም። አንዳንዶቹ ደግሞ ከፍተኛ ገንዘብ በማስከፈል ይሰጣሉ። አንዳንድ ባህላዊ ሀኪሞች ስለታካሚዎቻቸው እጅግ ሚስጥራዊ የሆነ መረጃ ሳይቀር ይሰጣሉ። እንዳንዶቹ ደግሞ በጣም ብዙ ገንዘብ በመቀበል ያ ነቢይ የእነርሱን ህመምተኞች መፈወስ የሚችል ኃይል ያለው መሆኑን መናፍስት እንደነገራቸው አድርገው ይመሰክራሉ። እነዚህ ድርጊቶች የሚፈፀሙት በነቢዩ፣ በነቢዩ ቡድንና በባህላዊ ሀኪሙ መካከል ነው።

ሶስተኛው የመስክ ሰራተኛ

ሶስተኛው የመስክ ሰራተኛ አካባቢው ላይ ባሉ መሸታ ቤቶች፣ የምሽት ክለቦችና ሌሎች ታዋቂ የህዝብ መዝናኛዎች ላይ ትኩረት በማድረግ አስፈላጊ ሰዎችን ፎቶ የሚሰበስብ ነው። ከነዚህ ሰዎች ጥቂቶቹን ወደ ስብሰባው መጥተው ምስክርነት እንዲሰጡ ያግባባል።

ነቢይ ጀርሚያህ እንደ ነቢይ ስኬታማ መሆን የምፈልግ ከሆነ እነዚህን ሁሉ ነገሮች በደንብ ማወቅ እንዳለብኝ ነገረኝ።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ አስር

በዶክተር ያያ አይኝ ወንጌልኝ መሸቀጥ

የገንዘብ ውጥረት

ጋስተር ተብሎ ከመጠራት ነቢይ ተብሎ መጠራትና ራስ ሰራሽ ነቢይ ወደ መሆን የተለወጥኩበት ዋና ምክንያት በቤተክርስቲያን ውስጥ ባጋጠመኝ የገንዘብ ችግርና ጭንቀት ምክንያት ነው።

ነቢይ ጀርሚያህ ብዙ ነገሮች በፍጥነት ይቀየራሉ ሲል ሁኔታዎቹን ግልፅ አድርጉልኝ ነበር። ዛሬ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሰዎች የሚፈልጉት ብልፅግና፣ ሀብት፣ ገንዘብ፣ ተአምራትና ፈውስ በመሆኑ አስተምህሮዎቹና ስብከቶቹ ትኩረት ማድረግ የሚገባቸው በነዚያ ላይ መሆን እንዳለባቸው ነገረኝ።

ነቢይ ጀርሚያህ "ቤተ ክርስቲያን የማህበረሰብ መንቃቃት አነሳሽ ፕሮግራም ከመሆን ርቃ ፓስተሮችና ነቢያት ቅዱስ ዘይትና ቅዱስ ውሀ ብለው የሚጠሯቸውን መንፈሳዊ ዕቃዎች የሚሸጡባት ትንሽ የገበያ ማዕከል ሆናለች። ስለዚህ ፈጣን በሆነ መንገድ ብዙ ገንዘብ መስራት ከፈለግክ የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ መክፈት አለብህ።" አለኝ።

"የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ ምንድነው? እንዴትስ ነው የምከፍተው?" ስል ጠየቅኩት።

የእርሱ መልስ "የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ ማለት ሰዎች ገንዘብ በመክፈል መንፈሳዊ ምክሮች የሚያገኙበት ቦታ ነው። ምክር ለማግኘት ከሚከፈለው ገንዘብና እንደ ቅዱስ ዘይቶች የእጅ እምባሮች፣ ቅዱስ ጨው አይነት መንፈሳዊ ነገሮችንና ሌሎች ነገሮችን በመሸጥ እንዲሁም ገንዘብ በማስከፈል ሌሎች መንፈሳዊ ነገሮችን መስራት በመቻል ገንዘብ ታገኛለህ። ካታኒታ ነግሬሀለሁ ቢሮ ያስፈልግሀል።" አለኝ።

በሚቀጥለው ቀን ነቢይ ጀርሚያህ ናይጀሪያ አባል ከሆንኩበት ሚስጥራዊ ማህበር አባል ከሆነ አንድ ጓደኛው ዘንድ ወሰደኝ። ይህ ሰው በጣም ሰው በሚበዛበት የታክሲ ተራ አካባቢ ቢሮ የከፈተ ሲሆን በስተግው ዙሪያና በታክሲ ተራው አካባቢ በራሪ ወረቀቶችን የሚያሰራጭበትን ስራ የሌላቸውን ደቡብ አፍሪካውያንን ቀጥሮ ያሰራል። በራሪ ወረቀቶቹ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ሙሉ ዝርዝር የያዙ ሲሆን፣ የምዕራብ አፍሪካው ዶክተር ያያ ተብሎ የሚጠራና

@Amharicbookstore

መፈወስና መርዳት የሚችላቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉት የሚናገር ነው።

በዶክተር ያያ የምክር አገልግሎት መስጫ ክፍል ስንደርስ ነቢይ ጀርሚያህ ይህንን በጣም ጥቁር የቆዳ ቀለም ያለውን ዶክተር ያያ የሚባለውን ሰው አስተዋወቀኝ። ነቢይ ጀርሚያህ ከዶክተር ያያ ጋር እየተነጋገረ በነበረበት ወቅት የዶክተር ያያ ስልክ ያለማቋረጥ እየጠራ መሆኑን አስተዋልኩ። ነቢይ ጀርሚያህ ያለማቋረጥ የሚደውሉት የዶክተሩ ደንበኞች መሆናቸውን፣ የሚደውሉትም አገልግሎቱን ፍለጋ እንደሆነና የእርሱ የገበያ ስልትም ጥቅም በሚያገኝበት መንገድ መስራት መሆኑን በሹክሹክታ ነገረኝ። ወዲያው ዶክተር ያያ ስልክ ማውራት ጀመረና በስልኩ "እሺ ፓፓ፣ ጠንካራና ትልቅ ሆኖ እንዲያድግ ማድረግ እችላለሁ።" ሲል ሰማ ስለ ቤተክርስቲያን አድገት እያወራ እንደሆነ አሰብኩ። ዶክተር ያያ ስልክ ማውራቱን ጨረሰና ለጥቂት ሰከንዶች ወደኔ ተመልክቶ ነቢይ ጀርሚያህን በቋንቋቸው አነጋገረውና ከት ብሎው ሳቁ። ነቢይ ጀርሚያህ የሳቁበት ምክንያት ዶክተር ያያ የወንዶችን ችግር በመቅረፍ ታዋቂ መሆኑንና ብዙ የደቡብ አፍሪካ ወንዶች የመራቢያ አካላቸው እንዲያድግላቸው ምክር ፍለጋ እንደሚመጡ ስለነገረው መሆኑን አብራራልኝ።

የዶክተር ያያ ስልክ ላይ ያለማቋረጥ እንደሚደወል ስመለከት ይህ ሰው በጣም ብቃት ካላቸው በእኛ አካባቢ ካሉ የህክምና ዶክተሮች በላይ ስራ እንደሚበዛበት አሰብኩ። ዶክተር ያያ ስልኩን ደቡብ አፍሪካዊት ለሆነችው ፀሀፊው ሰጣት። ዶክተር ያያ ደቡብ

አፍሪካውያንን የሚቀጥርበት ምክንያት አብዛኞቹ ደንበኞቹ ትምህርታቸውን ያቋረጡና የሀገራቸውን ቋንቋ ብቻ የሚናገሩ በመሆናቸው በትርጉም እንዳይቸገር ነበር።

የመጣንበትን ጉዳይ መጀመር ከመቻላችን በፊት፣ ነቢይ ጀርሚያህ ለዶክተር ያያ ተመሳሳይ የሚስጥር ማህበር አባላት እንደሆንን ለማሳየት በግራ እጁ ላይ ያለውን በምላጭ የመቁጣት ምልክት እንዳሳየው ባዘዘኝ መሰረት የሸሚዜን እጅ ሰበሰብኩና እጁ ላይ ያለውን ምልክት አሳየሁት። ዶክተር ያያም የራሱን ሲያሳየኝ ምልክቶቹ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ አንድ አይነት መሆናቸውን ተመለከትኩ። ወዲያው አምልኮው በሚያዘው መሰረት የግራ እጆቻችንን በመጠቀም ሰላምታ ተለዋወጥን። ሀገሩ ላይ በሚገኝ በጣም ኃያል የሚስጥር ማህበረሰብ የተዋረሰ ደቡብ አፍሪካዊ ፓስተር ማግኘቱ ጥሩ እንደሆነ ነገረኝ። በዚህ ሀገር የሚገኙ አብዛኞቹ ነቢያት ኃይል ለመቀበልና ለምኞን በስምና በስልክ ቁጥሮች መጥራትና የደበቋቸውን ክባባድ ሚስጥራት የማውጣት ትክክለኛ ትንበያዎችንና ተአምራት ለመስራት ወደዚህ ሚስጥራዊ ማህበር እንደሚመጡ ነገረኝ።

"ይህ ማለት ሚስጥራዊ ማህበረሰባችን በዚህ ሀገር ውስጥ ቀላልና ፈጣን በሆነ ሁኔታ ያድጋል ማለት ነው።" አለኝ።

ወዲያው ነቢይ ጀርሚያህ በአቅራቢያዬ ስኬታማና ውጤታማ የምክር መስጫ ቢሮ እንዴት መክፈት እንደምችል እንዲነግረኝ ዶክተር ያያን ጠየቀው።

@Amharicbookstore

ዶክተር ያያ ወደኔ ተመለከተና በአምልኮው የተሰጠኝን ካታ-ካታ የሚለውን ስም በሁሉም ፖስተሮችና ህትመቶች ላይ መጠቀም እንደሚገባኝ ነገረኝ። ከተዋርሶ ክብረ በዓሉ በኋላ በሚስጥራዊ ማህበረሰቡ የተሰጠኝን ስም በመጠቀም ክቢይ ካታ-ካታ ተብዬ እንድጠራ ነገረኝ። በተጨማሪም የዚህ ማህበረሰብ መለያ የሆኑት ቀይ፣ ሰማያዊና ነጭ የአምልኮ ማህበረሰቡን ቀለማት እንድጠቀም አዘዘኝ።

ዶክተር ያያ "ፖስተር በመሆንህ ገንዘብ ወደመስራት ስትመጣ በጣም ብልጥ መሆን አለብህ። እንደ ፖስተርነትህ ምንም ክፍያ መጠየቅ አይገባህም። ነገር ግን ገንዘብ ለማግኘት ለደንበኞችህ አንዳንድ ነገሮችን መሸጥ መቻልህን ማረጋገጥ እንደሚገባህ አስታውስ።" አለኝ። ይህ ዘዴ በጣም የሚያጓጓ እንደሆነ ስለተሰማኝ ወደ መቀመጫው ጠርዝ ጠጋ ብዬ ማዳመጥ ጀመርኩ። ማንም ምንም ነገር ሳይጠረጥር ወንጌልን እንዴት መሸቀጥ እንደሚቻል በደንብ ማወቅ ፈልጌያለሁ።

ዶክተር ያያ እየሰራ ያለው እንደ ባህላዊ ሀኪም በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማማክር ስራ እንዴት መስራት እንደሚቻል ያለውን ተሞክሮ ጠየቅኩት። "ነቢይ ካታ-ካታ በደንብ አዳምጠኝ የአንድ 'ቤተሰብ' አባላት በመሆናችን እውቀቱን አሰጥሀለሁ፣ ልምዴንም አካፍልሀለሁ።" አለኝ። ቀጥሎም "ብዙ ሰዎችን ወደ የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮህ የሚሰብ ፖስተር ማዘጋጀትና ሰዎችን መርዳት የምትችልባቸውን ችግሮችን ዝርዝር መጥቀስ አለብህ። ብዙ ደቡብ አፍሪካውያን የሚወዷቸውን ሰዎች መልሶ

ማምጣት፣ የመራቢያ አካላቸውን ማሳደግ፣ ሱተሪ የማሽነፍ እድል ማግኘት፣ በፍጥነት ሀብታም መሆን፣ ሥራ መቀጠርና ቃሰ መጠይቅ ማለፍ፣ ቢዝነስን ማሳደግና መስፋፋል እንዲሁም ተአምራዊ ገንዘብ መቀበል በሚባሉ ነገሮች ይለባሉ። ይህ የበራሪ ወረቀቶች ዘሃሴ ሰዎችን ወደ ምክር አገልግሎትህ ይስብልሃል።" አለኝ።

ቀጥሎም ዶክተር ያያ "ፖስተር እንደመሆንህ ሰወንዶች የመራቢያ አካል እንዲሁም ስትጫርና ስፍቅር ችግሮች ስመፀለይ የምታውልበት ልዩ አገልግሎት በማዘጋጀት መጀመር ትችላለህ። እንደዚህ አይነት አገልግሎቶች ዝነኛ ያደርጉሀል። ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ያደርጋል። ምክንያቱም አብዛኞቹ ደቡብ አፍሪካውያን ደንበኞቼ የመራቢያ አካልን በተመለከተ ጉዳይ ያሳቸው ወንዶችና የትጫር ውስጥ ችግር ወይም ፍቅረኛቸው የጠፉባቸው ሴቶች ናቸው።" ሲል ነገረኝ። እነዚህን መረጃዎችና ዘዴዎች ስመፃፍ ወረቀት እንዲሰጠኝ ስጠይቀው "ወንድሜ ለማስታወቂያ ካሰራኋቸው የራሴ ፖስተሮች አንድ ቅጅ ስለምሰጥህ ምንም ነገር መፃፍ አያስፈልግህም። ዶክተር ያያ በሚለው ቦታ ላይ የአንተን ከአምልኮው የተሰጠህን ስምና የቤተክርስቲያንህን ስም በመተካት ልትጠቀምበት ትችላለህ። ነገር ግን ክስር የኢየሱስ ጋይል የሚል ፅሁፍ መጨመርህን እርግጠኛ ሁን።" አለኝና የብልጠት ፈገግታ አሳየኝ። "ደንበኞችህን የምታስተናግድበት የተቀደሰ ቦታ ብለን የምንጠራው አይነት ልዩ ቢሮ ሊኖርህ ይገባል። እንዴት መደረግ እንደሚገባው እኔ እግዝሀለሁ። ና ምን ማለቴ እንደሆነ ሳሳይህ" አለኝና እንድከተሰው አዘዘኝ።

@Amharicbookstore

ከፊት ቀድሞኝ ከአንግዳ መቀበያው ጏላ ወዳለው አንድ ጨለማ ክፍል ገባ። ተከትየው እንደገባሁ "ብዙ ገንዘብ የምሰራው እዚህ ነው።" አለ ዶክተር ያያ። "በእንደዚህ አይነት ጨለማ ክፍል ውስጥ ብዙ ገንዘብ እሰራለሁ ማለት ምን ማለት ነው?" ስል ጠየቅኩት።

መብራቱን ሲያበራው ክፍሉ እንግዳና አስፈሪ በሚመስሉ ስዕሎችና ክፍሉ ጥግ በተቀመጡ ጣያቶች ተሞልቷል።

"ደንበኞቼ ብዙ ገንዘብ እንዲከፍሉ የሚያሟቸውና የሚያነጋግሯቸው መናፍስት እነዚህ ናቸው።" አለኝ።

"እንዴት?" ስል ጠየቅኩት።

ዶክተር ያያ "አንድ ደንበኛ መጥቶ እንደ ህመም ወይም ብልቱን ማሳደግ በተመለከተ ምክር ሲጠይቅ፣ ችግሩን ወይም ትኩረቱን ወደሌላ አቅጣጫ እንዲያዞር እደርጋለሁ። አብዛኛውን ጊዜ የችግራቸው ዋና ምክንያት ከዘር ማንዘሮቻቸው መንፈስ ጋር የተገናኘ እንደሆነ በመንገር ደንበኞቼን አታልላቸዋለሁ። ከዘር ማንዘሮቻቸው ጋር እንዲገናኙ ማድረግ የሚያስችል ከምዕራብ አፍሪካ የመጣ ልዩ ኃይል እንዳለ አሳምናቸውና በምክር አገልግሎቱ ወቅት ደንበኞቼ ከዘር ማንዘሮቻቸው ጋር መነጋገር ወይም መገናኘት መቻላቸውን እረጋግጣለሁ። ደንበኞቼ ሳይጠራጠሩ በቀላሉ መታለላቸውን ለማረጋገጥ መላውን ሂደት ለመጀመር ደንበኛው ወደሚነባበት ሰርዓት እንዲገባና በእኔ የአስማት መድኃኒት እንዲታጠብ እጠይቃለሁ። ይህ የአስማት መድሀኒት ወደ መንፃቱ ለመግባት የተስማማው የትኛውም

ሰው ላይ ወዲያውኑ ከባድ ድግምት ይልካል። ወንድሜ ካታሕታ በእኔ የአስማት መድሀኒት ታጥቦ የምለውን ሁሉ የማያደርግ ሰው የለም። የማዘዝ መንፈስ ብለን የምንጠራው ያንን ነው። ወንድሜ ብዙ የደቡብ አፍሪካ ጋስተሮች ይህንን መንፈስ ሲጠቀሙ በቴሌቭዥን አይቻለሁ።

"ይህ አጥበት ደንበኛው ለተጨማሪ ትዕዛዝና ምሪት ወደኔ የምክር አገልግሎት እንደገና እንደሚመጣ የሚያረጋግጥ በተጨማሪም ወደኔ መጥቶ ምክር እንዲፈልግ ያደረገውን ዋናውን ምክንያት እንዲረሳ የሚያደርግ ነው። ከዚያ ያ ሰው ሙሉ በሙሉ በመታለል ውስጥ በመውደቅ አዲሱን ከዘር ማንዘር የተላከ መንፈስ ጨዋታ ይቀጥላል። በተጨማሪም ደንበኞቼን በተከታታይ የምክር አገልግሎት ወቅት ኮሚቆዩበት ስፍራ ላይ ጥቂት አፈር ቆንጥረው እንዲያመጡ አጠይቃቸዋለሁ። ካታሕታ በመጀመሪያው ግንኙነታችሁ ወቅት ከደንበኞችህ ብዙ መረጃዎችን ማግኘት መቻል እንዳለብህ አስታውስ። ያገኘኸውን መረጃ ለደንበኛህ ትንቢት ስትናገር ወይም ዘር ማንዘሩ መናፍስት በሚያናግሩት ጊዜ መጠቀም አለብህ።" አለ ዶክተር ያያ።

ቀጥሎም "የደንበኛው ስምና የአባት ስም የዘር ማንዘሮቹ መናፍስት ሊመጡ የትኛው ቋንቋ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ይነግርሀል።" አለ። "ምን ማለትህ ነው ዶክተር ያያ?" ስል ጠየቅኩት። ወደሌላ ክፍል ወሰደኝና ከምድር በታች የተቀበረ ቧንቧ አሳየኝ። ቧንቧው ከሌላ ክፍል ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ ከዘር ማንዘር መናፍስት ጋር መገናኘት የሚባለውን ማታለያን ለማሳካት በሚስጥርና በስልት የተቀመጠ ነው። ዶክተር ያያ ቀጠለና "ወደ ጥቁር አስማት አለም

@Amharicbookstore

እንኪን ደህና መጣህ ካታ-ካታ፣ በጠረጴዛዬ ላይ ምግብ እንዲኖር የሚያስችለኝና በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ምርጥ በተባለው ቦታ የምኖረውን ህይወት እንድችል ያደረገኝ ይሄ ዘዴ ነው።" አለኝ።

በመቀጠልም "ደንበኛህ ከዘር ማንዘሮቹ መናፍስት ጋር እንዲነጋገር ቀጠሮ ከያዝክ የዚያን ሰው ቋንቋ በደንብ የሚናገር ሰው መፈለግ ይኖርብሃል። ለእኔ የሚያስፈልጉትን በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚነገሩትን ቋንቋዎች በደንብ የሚናገሩ ሰዎችን በማምጣት የምትረዳኝ ፀሀፊዬ ነች።" አለኝ።

በተጨማሪም "የእናንተን ቋንቋ የሚናገሩ አሮጊት ሴቶችንም በክፍያ ታመጣልኛለች። እኔም ለአሮጊቶች በሚያገለግሉበት ወቅት በቂ ክፍያ አሰጣለሁ። ደንበኛው ከዘር ማንዘሮቹ መናፍስት ጋር ለመገናኘት ብዙ ገንዘብ እንዲከፍል ለማድረግ ይህ ድርጊት በትክክልና በጥንቃቄ መደረጉን እናረጋግጣለን። ወንድሜ፣ ይህ ድርጊት ብዙ ሰዎች የጡረታ አበላቸው እንዲበዛላቸውና በሚሊየን የሚቆጠር ገንዘብ የማግኘት የውሸት ተስፋ ያለጊዜያቸው ስራ እንዲያቆሙ አድርጓቸዋል።" ሲል ነገረኝ።

ዶክተር ያያ ስለ ሁለተኛው ማታለያ ዘዴ ሲያብራራልኝ በጣአታት ከተሞላች ትንሽ ክፍል ጋር የተያያዘች ትንሽ የሚስጥር በር አሳየኝና "በዚህች የሚስጥር በር የምፈልገውን ተአምር መስራት እችላለሁ። በተለምዶ የሚሆነው ነገር እንዲናገር የሚጠራው የደንበኛው የዘር ማንዘር መንፈስ ደንበኛው የእንስሳ መስዋዕት እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል። ደንበኛው የታዘዘውን እንስሳ ይሰዋና ከስጋው የተወሰነ ክፍል ለመንፈሱ ይዞ ይመጣል። ደንበኛውም

ያመጣውን የመስዋዕት ሥጋ በዚህ ክፍል ውስጥ አስቀምጦ እንደወጣ ከሚሰሩልኝ ሰዎች አንዱ ቦሚስጥር በሩ በኩል ገብቶ ስጋውን ይበላና አጥንቱን እዚያው እንዲተወው ይደረጋል። የአግር ጻና እንዲታይም ነጭ ዱቄት መሬቱ ላይ በመነስነስ የእግሩን ምልክት ይተዋል። ከዚያ ደንበኛው ወደ ክፍሉ እንዲመለስ አዘዋለሁ። ሰውየው ወደ ክፍሉ ውስጥ ሲገባ ስጋው ተብልቶ አጥንቱ ብቻ እንደቀረ ሲመለከት የዘር ማንዘሮቹ መንፈስ መስዋዕቱን እንደተቀበለና አጥንቱን የተወውም መደሰቱን ለማሳየት እንደሆነ እነግረዋለሁ።" አለኝ።

"ሶስተኛው ደረጃ የዘር ማንዘሩ መንፈስ ለሰውየው የሚሰጠውን ገንዘብ አባዝቶ እንዲሰጠው የሚፈልግ መሆኑን ሲነግረው ነው። ለደንበኛው የዘር ማንዘሩ መናፍስት በሎተሪ ቁጥሮች በኩል ሀይላቸውን ማረጋገጥ እንደሚፈልጉ እነግረዋለሁ። ባዶ የሎተሪ ቲኬት አሰጠውና መናፍስቱ ሰሰውየው የእድል ቁጥሮቹን እንደጠራለትና ደንበኛው ቁጥሮቹ ላይ ምልክት እንዲያደርግ አደርጋለሁ። ደንበኛው ምልክት ያደረገበትን ቲኬት ፖስታ ውስጥ ከትቶ እንዲያሸገውና ብቻውን እንዳይከፍተው ይታዘዛል።

ደንበኛው ያንን ፖስታ ቤቱ ይዞ ይሄድና በዚያ ሳምንት የሚወጣ የሎተሪ ቁጥር ይመለከታል። ነገር ግን ሁልጊዜ ደንበኛው በመናፍስቱ የተነገረውን ቁጥር እንዲረሳ ድግምት እናደርጋለን። ደንበኛው በዚያ ሳምንት የነበረውን የሎተሪ ዕጣ አሸናፊ ቁጥር በወረቀት ላይ እንዲፅፍ ባዘዝኩት መሰረት ደንበኛው ተመልሶ ሲመጣ የታሸገውን ፖስታ በወረቀት ላይ የፃፈውን የአሸናፊውን የሎተሪ ቁጥር ይዞ ይመጣል። ይዞ የመጣውን የታሸገ ፖስታ የአሸናፊ

@Amharicbookstore

እንኳን ደህና መጣህ ካታ-ካታ፣ በጠረጴዛዬ ላይ ምግብ እንዲኖር የሚያስችለኝና በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ምርጥ በተባለው ቦታ የምኖረውን ህይወት እንድችል ያደረገኝ ይሄ ዘይ ነው።" አለኝ።

በመቀጠልም "ደንበኛህ ከዘር ማንዘሮቹ መናፍስት ጋር እንዲነጋገር ቀጠሮ ከያዝክ የዚያን ሰው ቋንቋ በደንብ የሚናገር ሰው መፈለግ ይኖርብሃል። ለእኔ የሚያስፈልጉትን በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚነገሩትን ቋንቋዎች በደንብ የሚናገሩ ሰዎችን በማምጣት የምትረዳኝ ፀሀፊዬ ነች።" አለኝ።

በተጨማሪም "የእናንተን ቋንቋ የሚናገሩ አሮጊት ሴቶችንም በክፍያ ታመጣልኛለች። እኔም ለአሮጊቶች በሚያገለግሉበት ወቅት በቂ ክፍያ እሰጣለሁ። ደንበኛው ከዘር ማንዘሮቹ መናፍስት ጋር ለመገናኘት ብዙ ገንዘብ እንዲከፍል ለማድረግ ይህ ድርጊት በትክክልና በጥንቃቄ መደረጉን እናረጋግጣለን። ወንድሜ፣ ይህ ድርጊት ብዙ ሰዎች የሙታን አበላቸው እንዲበላቸውና በሚሊየን የሚቆጠር ገንዘብ የማግኘት የውሸት ተስፋ ያለጊዜያቸው ስራ እንዲያቆሙ አድርጓቸዋል።" ሲል ነገረኝ።

ዶክተር ያያ ስለ ሁለተኛው ማታለያ ዘዴ ሲያብራራልኝ በጣአታት ከተሞች ትንሽ ክፍል ጋር የተያያዘች ትንሽ የሚስጥር በር አሳየኝና "በዚህች የሚስጥር በር የምፈልገውን ተአምር መስራት እችላለሁ። በተለምዶ የሚሆነው ነገር እንዲናገር የሚጠራው የደንበኛው የዘር ማንዘር መንፈስ ደንበኛው የእንስሳ መስዋዕት እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል። ደንበኛው የታዘዘውን እንስሳ ይሰዋና ከሰጋው የተወሰነ ክፍል ለመንፈሱ ይዞ ይመጣል። ደንበኛውም

ያመጣውን የመስዋዕት ሥጋ በዚህ ክፍል ውስጥ አስቀምጦ እንደወጣ ከሚሰሩልኝ ሰዎች አንዱ በሚስጥር በሩ በኩል ገብቶ ስጋውን ይበላና አጥንቱን እዚያው እንዲተወው ይደረጋል። የእግር ዳና እንዲታይም ነጭ 'ዱቄት መሬቱ ላይ በመነስነስ የእግሩን ምልክት ይተዋል። ከዚያ ደንበኛው ወደ ክፍሉ እንዲመለስ አዘዋለሁ። ሰውየው ወደ ክፍሉ ውስጥ ሲገባ ስጋው ተበልቶ አጥንቱ ብቻ እንደቀረ ሲመለከት የዘር ማንዘሮቹ መንፈስ መስዋዕቱን እንደተቀበለና አጥንቱን የተወውም መደሰቱን ለማሳየት እንደሆነ እነግረዋለሁ።" አለኝ።

"ሶስተኛው ደረጃ የዘር ማንዘሩ መንፈስ ለሰውየው የሚሰጠውን ገንዘብ አባዝቶ እንዲሰጠው የሚፈልግ መሆኑን ሲነግረው ነው። ሰደንበኛው የዘር ማንዘሩ መናፍስት በሎተሪ ቁጥሮች በኩል ሀይላቸውን ማረጋገጥ እንደሚፈልጉ እነግረዋለሁ። ባዶ የሎተሪ ቲኬት እሰጠውና መናፍስቱ ለሰውየው የእድል ቁጥሮቹን እንደጠራለትና ደንበኛው ቁጥሮቹ ላይ ምልክት እንዲያደርግ አደርጋለሁ። ደንበኛው ምልክት ያደረገበትን ቲኬት ፖስታ ውስጥ ከትቶ እንዲያሸገውና ብቻውን እንዳይከፍተው ይታዘዛል።

ደንበኛው ያንን ፖስታ ቤቱ ይዞ ይሄድና በዚያ ሳምንት የሚወጣ የሎተሪ ቁጥር ይመለከታል። ነገር ግን ሁልጊዜ ደንበኛው በመናፍስቱ የተነገረውን ቁጥር እንዲረሳ ድግምት እናደርጋለን። ደንበኛው በዚያ ሳምንት የነበረውን የሎተሪ ዕጣ አሸናፊ ቁጥር በወረቀት ላይ እንዲፅፍ ባዘዝኩት መሰረት ደንበኛው ተመልሶ ሲመጣ የታሸገውን ፖስታ በወረቀት ላይ የፃፈውን የአሸናፊውን የሎተሪ ቁጥር ይዞ ይመጣል። ይዞ የመጣውን የታሸገ ፖስታ የአሸናፊ

@Amharicbookstore

የሎተሪ ቁጥር ምልክት የተደረገበት የሎተሪ ቲኬት ባለበት ሌላ ፖስታ በሚስጥር እተካዋለሁ። ደንበኛው ፖስታውን ከፍቶ ፅፎ ካመጣው አሸናፊ ቁጥር ጋር እንዲያነፃፅር እነግረዋለሁ። ሰውየው ፖስታ ውስጥ ያለው ቁጥር ከተፃፈው ጋር እንደሚመሳሰል ሲመለከት በእርግጥም የዘር ማንዘሩ መናፍስት ኃይል እንዳላቸውና ሀብት መስጠት እንደሚችሉ ስለሚያምን መናፍስቱ የሚያዙትን ሁሉ ለማድረግ ወደኋላ አይልም። የሎተሪው ዘዴ ዋና አላማ ደንበኛው የዘር ማንዘሮቹን መንፈስ በሁሉም ነገር እንዲያምናቸው ለማድረግ ነው። ስለዚህ ካታ-ካታ አሁን አንተ ነቢይ ስለሆንክ ለደንበኞችህ ከሞቱ ዘመዶቻቸው ጋር ሊገናኙ የሚችሉበት ኃይል እንዳለህ መናገር ይገባሀል።" ሲል ዶክተር ያያ አብራራልኝ።

የራዕይ ውሀ

"የቤተ ክርስቲያን ፓስተር በመሆንህ በመጀመሪያ ክርስቲያኖችን ማሳመን ያስፈልግሀል። ምክንያቱም ክርስቲያኖች ተአምራት ይወዳሉ። ስለዚህ እኔ የራዕይ ውሀ ብዬ የምጠራውን ፊላሽ አዘጋጅልሀለሁ። እንዴት እንደሚዘጋጅም አስተምርሀለሁ። ይህ የራዕይ ውሀ ፒቱተሪ ግላንድ ብለን የምንጠራውን ዕጢ እንዲነቃቃ በማድረግ ሰዎች በዙሪያቸው ያሉትን መንፈሳዊ ነገሮች እንዲያዩ ያደርጋል።" አለ ዶክተር ያያ።

"ይህ የራዕይ ውሀ ሰዎች የሌሉ ነገሮችን እንዲያዩ ወይም እንዲሰክሩ ያደርጋል ማለትህ ነው?" ስል ዶክተር ያያን ጠየቅኩት።

"አይደለም ይህ ውሀ በሰዎች ውስጥ ያለውን ሶስተኛ አይን የሚባለውን ንቁ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። የራዕይ ውሀ የጠጣ ሰው ንቁ ባልሆነው የአእምሮው ክፍል ውስጥ የተቀመጡትን ማየት ይችላል ማለት ነው። እኔ ይህንን ውሀ በመጠቀም ሰዎች በመስተዋት ወይም በውሀ ውስጥ ጠላቶቻቸውን እንዲያዩ አደርጋለሁ።" አሉ።

እንደዚህ አይነት ነገሮች ያሉት ፊልሞች ላይ ብቻ ይመስለኝ ስለነበር የነገረኝ ነገር ከአእምሮዬ በላይ ነበር። "መስተዋት ወይም ውሀ ለሰዎች የተደበቁ መንፈሳዊ ነገሮችን ያሳያሉ ማለት ነው?" አልኩት። "አይደለም፤ ለሰዎች መናፍስቶችን የሚያሳይ ምንም መስተዋት ወይም ውሀ የለም። ሁሉም ነገር የሚከናወነው በሰውየው አእምሮ ውስጥ ነው። ይህ የራዕይ ውሀ የሚገኘው ለዘር ማንዘር መንፈሳዊ ኩበራ-በዓል የሚውለውን የአፍሪካ ድንች በመቀቀል ነው። የአፍሪካ ድንች ከተቀቀለ በኋላ የተቀቀሰበት ውሀ ሰሰው ይሰጣል። ይህ ውሀ የሰዎችን ፒቱተሪ ዕጢ በማነቃቃት ሰዎች በአይናቸው ስር ልክ እንደ ፊልም የሆኑ ነገሮች እንዲታዩዋቸው ያደርጋል። ይህ የማየት ነገር ለሰአታት የሚቀጥል በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች የሚያስፈሩ ነገሮችን ጭምር ሊያዩ ይችላሉ፤ ስለዚህ ይህንን ሂደት እንዲቆም ከፈለግክ ጠንካራ ቡና ማዘጋጀትህን እርግጠኛ መሆን ይኖርብሀል። ምክንያቱም ቡና እየሰራ ያለውን ፒቱታሪ ዕጢ እንዲረጋጋ ያደርጋል።" ሲል ዶክተር ያያ ነገረኝ።

ቀጥሎም "በእኛ ሀገር አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በረጅም የፆምና የፀሎት ፕሮግራሞች ላይ ይህንን ውሀ በሚስጥር ይጠቀማሉ። ሰዎቹ በራዕይ ውሀው ገንፎ እንዲዘጋጅ ያደርጉና ያንን

@Amharicbookstore

የሎተሪ ቁጥር ምልክት የተደረገበት የሎተሪ ቲኬት ባለበት ሴላ ፖስታ በሚስጥር አተካዋለሁ። ደንበኛው ፖስታውን ከፍቶ ፅፎ ካመጣው አሸናፊ ቁጥር ጋር እንዲያነፃፅር እነግረዋለሁ። ሰውየው ፖስታ ውስጥ ያለው ቁጥር ከተፃፈው ጋር እንደሚመሳሰል ሲመለከት በእርግጥም የዘር ማንዘሩ መናፍስት ኃይል እንዳላቸውና ሀብት መስጠት እንደሚችሉ ስለሚያምን መናፍስቱ የሚያዙትን ሁሉ ለማድረግ ወደኋላ አይልም። የሎተሪው ዘዴ ዋና አላማ ደንበኛው የዘር ማንዘሮቹን መንፈስ በሁሉም ነገር እንዲያምናቸው ለማድረግ ነው። ስለዚህ ካታ-ካታ አሁን አንተ ነቢይ ስለሆንክ ለደንበኞችህ ከሞቱ ዘመዶቻቸው ጋር ሊገናኙ የሚችሉበት ኃይል እንዳለህ መናገር ይገባሀል።" ሲል ዶክተር ያያ አብራራልኝ።

የራዕይ ውሀ

"የቤተ ክርስቲያን ፓስተር በመሆንህ በመጀመሪያ ክርስቲያኖችን ማሳመን ያስፈልግሀል። ምክንያቱም ክርስቲያኖች ተአምራት ይወዳሉ። ስለዚህ እኔ የራዕይ ውሀ ብዙ የምጠራውን ፊላሽ አዘጋጅልሀለሁ። እንዴት እንደሚዘጋጅም አስተምርሀለሁ። ይህ የራዕይ ውሀ ፒቱተሪ ግላንድ ብለን የምንጠራውን ዕጢ እንዲነቃቃ በማድረግ ሰዎች በዙሪያቸው ያሉትን መንፈሳዊ ነገሮች እንዲያዩ ያደርጋል።" አለ ዶክተር ያያ።

"ይህ የራዕይ ውሀ ሰዎች የሌሉ ነገሮችን እንዲያዩ ወይም እንዲሰክሩ ያደርጋል ማለትህ ነው?" ስል ዶክተር ያያን ጠየቅኩት።

"አይደለም ይህ ውሀ በሰዎች ውስጥ ያለውን ሰከተኛ አይን የሚባለውን ንቁ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። የራዕይ ውሀ የጠፋ ሰው ንቁ ባልሆነው የአእምሮው ክፍል ውስጥ የተቀመጡትን ማየት ይችላል ማለት ነው። እኔ ይህንን ውሀ በመጠቀም ሰዎች በመስተዋት ወይም በውሀ ውስጥ ጠለቶቻቸውን እንዲያዩ አደርጋለሁ።" አሰ።

እንደዚህ አይነት ነገሮች ያሉት ፊልሞች ላይ ብቻ ይመስለኝ ስለነበር የነገረኝ ነገር ከአእምሮዬ በላይ ነበር። "መስተዋት ወይም ውሀ ለሰዎች የተደበቁ መንፈሳዊ ነገሮችን ያሳያሉ ማለት ነው?" አልኩት። "አይደለም፤ ለሰዎች መናፍስቶችን የሚያሳይ ምንም መስተዋት ወይም ውሀ የለም። ሁሉም ነገር የሚከናወነው በሰውየው አእምሮ ውስጥ ነው። ይህ የራዕይ ውሀ የሚገኘው ለዘር ማንዘር መንፈሳዊ ክብረ-በዓል የሚውለውን የአፍሪካ ድንች በመቀቀል ነው። የአፍሪካ ድንች ከተቀቀለ በኋላ የተቀቀለበት ውሀ ለሰው ይሰጣል። ይህ ውሀ የሰዎችን ፒቱተሪ ዕጢ በማነቃቃት ሰዎች በአይናቸው ስር ልክ እንደ ፊልም የሆኑ ነገሮች እንዲታዩዋቸው ያደርጋል። ይህ የማየት ነገር ለሰአታት የሚቀጥል በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች የሚያስፈሩ ነገሮችን ሞምር ሊያዩ ይችላሉ፤ ስለዚህ ይህንን ሂደት እንዲቆም ከፈለግክ ጠንካራ ቡና ማዘጋጀትህን እርግጠኛ መሆን ይኖርብሀል። ምክንያቱም ቡና እየሰራ ያለውን ፒቱታሪ ዕጢ እንዲረጋጋ ያደርጋል።" ሲል ዶክተር ያያ ነገረኝ።

ቀጥሎም ግብኛ ሀገር አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በረጅም የፆምና የፀሎት ፕሮግራሞች ላይ ይህንን ውሀ በሚስጥር ይጠቀማሉ። ሰዎቹ በራዕይ ውሀው ገንፎ እንዲዘጋጅ ያደርጉና ያንን

@Amharicbookstore

ገንፎ የበሉ ሁሉ የሞቱ ዘመዶቻቸው ሲያነጋግሯቸው ማየት ይጀምራሉ። ይህ ነገር በድራማ መልክ የተሰራ ሳይሆን የእውነት በመሆኑ ለዚያ ቤተክርስቲያን በሺህዎች የሚቆጠሩ ተከታዮችን ይስባል። ሌሎች ነቢያት ደግሞ ደንቆሮቻቸው ከእነርሱ የሰረቃቸውን ሰው ወይም በህይወታቸው ችግር የፈጠረባቸውን ሰው ማወቅ ሲፈልጉ ይህንን የራዕይ ውሀ እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ። እነዚያ ሰዎች ወንጀለኞቹን ካዩ በኋላ ነቢዩ ነገሮችን የመግሰጥ ኃይል አንዳለው በማመን ያመሰግኑታል። ምክንያቱም ያ ኃይል የተገኘው ከእፍረት ድንች መሆኑን አያውቁም። ተመልከት ነቢይ ካታ-ካታ ከፍተኛ ኃይል ያለው የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ በአካባቢህ እንድትከፍት እናግዝሀለን።" አለኝ ዶክተር ያያ።

የመስዋዕት ቅል

ቀጥሎም ዶክተር ያያ "ልክ እንደኔ አይነት ልዩ አስማት የመስሪያ ዕቃዎች ማግኘት ይናርብህል። ይህኛው የመስዋዕቶ ቅል ይባላል። በዚህ ቅል ውስጥ የመስዋዕቱን ስጋ የሚያደርቅ በጣም ጠንካራ የባትሪ አሲድ እጨምርበታለሁ። ደንበኛው በትንንሹ የተቆራረጡ የመስዋዕቱን እንስላ ጉበት በቅሉ ውስጥ እንዲያስቀምጥ ይታዘዛል። ከዚያ እኔ ከባትሪ አሲድ ጋር የተቀላቀለ ጥቁር የአስማት መድኃኒት አስጠዋለሁ። ደንበኛው የተሰጠውን ፈሳሽ የእንስላውን ጉበት በያዘው ቅል ውስጥ ጨምሮ ቅሉን በመሸፈን ደብቆ እንዲያስቀምጠው ይደረጋል። ከዚያ በፈሳሹ ውስጥ የሚገኘው የባትሪ አሲድ የእንስላውን ጉበት እንደሚበላውና እንደሚያደርቀው ስለማውቅ ሰውየውን በሚቀጥለው ጠዋት ቅሉን ከፍቶ እንዲመለከት

አዝዘዋለሁ። ሰውየው ስጋው ቅሉ ውስጥ እንደሌለ ሲነግረኝ መናፍስቱ ሌሊት መጥተው መስዋዕቱን እንደበሉት በመናገር ደንበኛውን አሳምነዋለሁ።" ሲል ዶክተር ያያ ነገረኝ። በዚያ የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ ውስጥ የሚደረገውን ማታለል ለመረዳት የሚከብድ ነበር።

"ይኼኛው ደግሞ ባህላዊ የአርግብ መጥበሻ ብለን የምንጠራው ነው። ልክ ትላልቅ አስማተኞች በሚጠቀሙበት የአስማት የአርግብ መጥበሻ አይነት የተሰራ ሲሆን ልዩነቱ ይኼኛው በሳባዎች የተሸፈነና የእንስላ ደም የነካው መሆኑ ነው።" አሰኝ ዶክተር ያያ። አንድ ትንሽ መርፌ መሰል ነገር አሳየኝና "ይህንን መርፌ ስጫነው የመጥበሻው ሁለተኛው ድራቢ ይከፈታል።" ሲል ነገረኝ።

"በመጀመሪያው ተደራቢ ላይ ደንበኛው እንቁላል ሰብሮ እንዲያደርግበትና በላዩ ላይ ነጭ ዱቄት ነስንሶ እንዲዘጋውና በጥቁር ጨርቅ እንዲሸፍነው እጠይቃለሁ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እኔ በሚስጥር ይህችን ትንሽ መርፌ መሰል ነገር እጫንና ሰውየው ጥቁሩን ጨርቅ አንስቶ የመጥበሻውን ክዳን እንዲከፍት አዘዋለሁ። ደንበኛው ክዳኑን ሲከፍት በሁለተኛው ተደራቢ ላይ የተቀመጠውን በነጭ ዱቄት የተሸፈነ ትንሽ እርግብ ያገኛል። እርግቢ ከመጥበሻው ውስጥ ስትወጣ ስትታይ ሁሉም ነገር እንደ ተአምር ይቆጠርና ደንበኛው እኔ እውነተኛ ተአምር ሰሪ እንደሆንኩ ያምናል።" አለኝ።

እርሱንና መጥበሻውን በድንጋጤ እየተመለከትኩ ጥቁር አስማት የሚለው ቃል ከየት እንደመጣ ተረዳሁ። ወዲያው ሀሰተኛ

@Amharicbookstore

ነቢያት ከተከታዮቻቸው ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የሚሄዱባቸውን የማታለል ርቀት ማወቅ ጀመርኩ።

የሚናገር ክፉ መንፈስ

ዶክተር ያያ እንዲት ትንሽ ሰሀን የምትመስል ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አንስቶ ትንሽ ቀዳዳ ያላት አነስተኛ ቧንቧ መሰል ነገር አስገባበትና አንዱን ጫፍ በግራ አፍንጫው ቀዳዳ ውስጥ ከተተ። ወዲያው ለየት ያለ የአተነፋፈስ ዘዴ ሲጠቀም ለየት ያለ ድምፅ መውጣት ጀመረ። ዶክተር ያያ ያቺን ቧንቧ መሰል ነገር በመጠቀም መናገር ሲጀምር የሚወጣው ድምፅ በጣም የሚገርም አይነት ነበር። ዶክተር ያያ ተገልጋዮቹን ከመናፍስት ጋር እንደሚነጋገሩ አስመስሎ ለማታለል የሚጠቀመው ይህንን ዘዴ ነበር። "ይህ ከሀሎትና ዘዴም በጣም ዝነኛ ያደርግሀል፤ ምክንያቱም ይህ ያልተለመደ ድምፅ ከጣእት ወይም ከክፉ መንፈስ ቶኮሉሺ የሚመጣ እንዲመስል ስለምታደርገው ነው። እነዚህ ሁሉ ዘዴዎች ከተገልጋዮችህ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚጠቅሙህ ሲሆኑ፣ ገንዘቡን የሚጠይቁት ስውር መናፍስቱና የዘር ማንዘሮቻቸው መናፍስት እንደሆኑ ስለሚታመን ማንም ሰው በማታለል ተጠያቂ ሊያደርግህ አይችልም። ማንም በፍፁም ወንጌልን በመሸቀጥ ሊከሰህ አይችልም።" ሲል ዶክተር ያያ አስረዳኝ።

የሀሰት ገንዘብ ኃይል

"ተገልጋዮች በርካታ ገንዘብ እንዲያመጡ በማዝበት ጊዜ ገንዘቡን ፈጽሞ በእጄቼ አለመንካቴን አረጋግጥላቸዋለሁ። ለተገልጋዮቹ ትልቅ ቦርሳ አሰጣቸውና ያላቸውን ገንዘብ በሙሉ እዚያ ቦርሳ ውስጥ እንዲከቱ እነግራቸዋለሁ። ከዚያ ያንን ቦርሳ ውስጥ ያለ

ገንዘብ በሚስጥር በር በኩል የሀሰት ገንዘብ በያዘ ተመሳሳይ ቦርሳ አለውጥና ተገልጋዩ ያንን በሀሰት ገንዘብ የተሞላ ቦርሳ ይዞ እንዲሄድ እነግረዋለሁ። በመቀጠል ወደ ተገልጋዩ ቤት በመሄድ የሀሰት ገንዘቡን በያዘው ቦርሳ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎ እንዲያቃጥለው እደርጋለሁ። ቦርሳው ከነገንዘቡ ተቃጥሎ አመድ ሲሆን ተገልጋዮቹ ያላቸው ገንዘብ በሙሉ እንደተቃጠለ እንጂ በሀሰት ገንዘብ እንደተሰወጠ አያውቁም። ቦርሳው ሙሉ በሙሉ ተቃጥሎ ሲልቅ አመዱ በተገልጋዩ ግቢ ውስጥ እንዲቀበር ይደረጋል። ተገልጋዩ መናፍስቱ መጥተው ገንዘቡን እጥፍ አድርገው እስኪያበዙት እንዲጠብቅ ይነገረዋል። የገንዘቡ መብዛት ሲዘገይ ተገልጋዩ ገንዘብ ተበድሮ ወይም ንብረቱን ሸጦ ተጨማሪ ገንዘብ ለዘር ማንዘሩ መናፍስት እንዲሰጥ ይታዘዛል። ተገልጋዩ የባንክ ሂሳቡ ውስጥ ያለው ገንዘብ በሙሉ ተሟጦ እስኪያልቅ ድረስ ይህ ማታለል ይቀጥላል። ያ ተገልጋይ ገንዘቤን አምጡ ብሎ ማስፈራራት ከጀመረ እኔም እርሱና ቤተሰቡ ላይ እርግማን እንደምልክበት በመንገር አስፈራራዋለሁ።" አለ ዶክተር ያያ።

የፈውስ ትምህርት ቤት (ሂሊንግ ስኩል)

"ፓስተር በመሆንህ የፈውስ ትምህርት ቤት መክፈት አለብህ።" ሲል ዶክተር ያያ ነገረኝ። "የፈውስ ትምህርት ቤት ምንድነው?" ስል ጠየቅኩት። "የፈውስ ትምህርት ቤት የታመሙ ሰዎችን በአንተ እንክብካቤና ቅርበት ውስጥ ማስቀመጥ ነው። እነዚህ የታመሙ ሰዎች ሙሉውን ጊዜ ከአንተ ጋር የሚቆዩ ሲሆኑ፣ ከቤተሰቦቻቸው ገንዘብ ለመሰብሰብ ትጠቀምባቸዋለህ። እዚህ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ብዙ ሰዎች የታመሙባቸውን የቤተሰብ አባላት የፅኑ

@Amharicbookstore

ሀሙማን መንከባከቢያ ማዕከላት ውስጥ ያስገቧቸዋል። ስለዚህ የአንተ የፈውስ ትምህርት ቤት እነዚያን የሀሙማን መንከባከቢያ ቤቶች የሚተካ ይሆናል ማለት ነው። ይህ የፈውስ ትምህርት ቤት በቤተክርስቲያንህ ግቢ ውስጥ ከሆነ ደግሞ ብዙ ትኩረት ይስባል። በፈውስ ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተአምራት ምክንያትም ከተለያዩ ቦታዎች ሰዎች እንዲመጡ ያደርጋል። በፈውስ ትምህርት ቤቱ ውስጥ የተቀናበሩ በተአምራትና ፈውሶች ማድረግ ስለምትችል ብዙ ሰዎችን ማታለልና መቆጣጠር ትችላለህ። ሰዎች በፈውስ ትምህርት ቤቱ ውስጥ እንዴት እንደተፈወሱ የሀሰት ምስክርነቶች ይሰጣሉ። ሰዎቹ ሙሉ ጊዜ ከአንተ ጋር የሚቆዩ በመሆናቸውም ከመንግስትና ከግለሰቦች ድጋፍ መጠየቅም ትችላለህ።

መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሂሳብ በመክፈት የእኖ ልጆች ሀጋዊ ያልሆኑ ገንዘቦችን እንደ ሀጋዊና ንፁህ ገንዘብ አድርገው እንዲያስተላልፉና ያንን የሂሳብ ቁጥር ሀጋዊ ያልሆነ የገንዘብ ልውውጥ ለማድረግ የምንጠቀምበት ይሆናል። በሰዎች እይታ የፈውስ ትምህርት ቤት ቢሆንም ከጀርባ ግን ሀጋዊ ያልሆኑ የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን የምናደርግበት እንደሆነ እናውቃለን። አሁድ በመጣ ቁጥር ታማሚዎቹን ለአደባባይ ምስክርነት ትጠቀምባቸዋለህ። እና አንዳንዶቹን ደግሞ እንዲናገሩ የምትፈልጋቸውን ነገሮች እንዲናገሩ የምታደርግበት ይሆናል። እመነኝ በውጤቱ አንተ የየቤቱ ነቢይ የምትሆንበት ይሆናል። ቴሌቭዥን በሚያየውና በሚሰማው የሚሳብ በመሆኑ የፈውስ ትምህርት ቤቱ ቴሌ ኢቫንጀሊዝምን ያጠናክርልሀል። አንድ ጊዜ የፈውስ ትምህርት ቤት አንዲኖርህ ከሆንክ በሚገፋ ተሽከርካሪ ወንበር የመጡ ሰዎች አንተ ከፀለይክላቸው

በኋላ እግሮቻቸው እንዲራመዱ የማድረግ፣ ሌሎች የታመሙና በሜካፕ አርቲስቶች በጥንቃቄ የተሰሩ ቁስሎችና ጠባሳዎች ያሉባቸው ሊፈወሱ የማሳየት የተቀናበረ ፈውስ ታያለህ። ለዚህም በምትፈልገው መንገድ መቅረፅ የሚችሉ የሰለጠኑ የቴሌቭዥን ካሜራ ባለሙያዎችን ትጠቀማለህ። ተገልጋዮችህ አንተ የምትሰጣቸውን ውሀና ዘይት ሲጠቀሙ በቲቪ ከታዩ በኋላ የካሜራ ባለሙያው ቀድሞ የነበረና የአሁን ምስሎችን በማሳየት ሀገሩ በሙሉ ስለዚህ የፈውስ ቦታ እንዲያውቁ እንዲያደርግ ይደረጋል። በተጨማሪም ይህ የፈውስ ትምህርት ቤት ታማሚዎችህ ሁሉ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ያስችልሀል። በቤተክርስቲያን ፕሮግራም ጊዜ የራዕይ ውሀ ጠጥተው መናፍስት እንዲያዩ በማድረግ ሰዎች በአንተ ኃይል እንዲያምኑ ታደርጋለህ። ታማሚዎችህ ምን እንደሚሰሩና የሚሰሩትም በአንተ ትዕዛዝ መሆኑን ልትነግራቸው ትችላለህ። ይህ የፈውስ ትምህርት ቤት የታማሚዎች መጠጊያ ተብሎ ይጠራል።" ሲል ዶክተር ያያ አብራራልኝ።

የሁሉም ሰዎች የተአምራት ማዕከል

"ካታካታ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ፈላጊ ያለው ተአምር የሚለው ቃል በመሆኑ የቤተክርስቲያንህን ስያሜ ወደ ተአምራት ማዕከል ለውጠው። ደቡብ አፍሪካውያን ተአምራት ይወዳሉ። እና የአንተን ቤተክርስቲያን የሁሉም ዘር የተአምራት ማዕከል ካልከው ገበያህ ከሁሉም ዝርያ ያሉ ሰዎች የሚመጡበት ይሆናል። አሁን ግን ገና ከናይጀሪያ መመለስህ በመሆኑ የቤተክርስቲያንህን ስም መለወጥ ብዙ ጥርጣሬዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ ቀላል አይሆንም። መቀየሩ ግን ብዙ የውጪ ሀገር ሰዎችን ይስብልሀል። አስብበት ነቢይ ካታካታ

@Amharicbookstore

አኖም በአንተ ስር ሆነን እንደ ጠባቂና ረዳት ፓስተር በመሆን እናገለግላለን።" አለኝ ዶክተር ያያ።

የጋዜጠኝነትና መረጃ ሰጪነት ኃይል

"ነቢይ ካታ-ካታ የምመክርህ ገንዘብ ፈልገህ የተለምራት አገልግሎትህን የምታስተላልፍበት የአየር ሰዓት ከብሔራዊ ቴሌቭዥን እንድትገዛ ነው። ለመጪረሻ ጊዜ በጠየቅኩበት ወቅት የአየር ሰአት መግዛት ውድ እንደነበረ አስታውሳለሁ። ነገር ግን የቴሌቭዥን ፕሮግራም ካለህ አንተና ቤተክርስቲያንህ በጣም እንዲያድግና በሁሉም ቦታ ታዋቂ እንዲሆን ያደርጋል። የቴሌቭዥን አገልግሎት ሲኖርህ ብሔራዊና አለማቀፋዊ ብለን የምንጠራቸውን ትንቢቶች እንድትናገር እንረዳሀለን። ይህ አይነት ትንቢት የፖለቲካ ሰዎችንና የተከበሩ ሰዎችን ወደ አገልግሎትህ ይስብልሀል።" ሲል ዶክተር ያያ ማዘዙን ቀጠለ።

"ያ እንዴት ይቻላል?" ስል ጠየቅኩት።

ይህንን ለማድረግ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ጋዜጠኞች ከአንዱ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ሊኖረኝ እንደሚያስፈልግ ነገረኝ። የዚህ ግንኙነት አላማ በቤተክርስቲያን ትንቢት ለመናገር የምጠቀምባትን መረጃ አስቀድሞ እንዲሰጠኝ ለማድረግ ነው። ጋዜጦች በሳምንቱ ውስጥ ርዕስ የሚሆኑ ታሪኮች በዜና ስምሪት ስብሰባዎቻቸው ላይ አስቀድመው ፕሮግራም ስለሚያሲዙ ያ ጋዜጠኛ የእነዚያን ታሪኮች መረጃ አስቀድሞ ይነግረኝና እኔም ከጋዜጠኛው ያገኘሁትን መረጃ የካሜራ ቀረጻ ባለበት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ትንቢት እናገረዋለሁ። ከዚያ ዜናው በሚዲያ ሲለቀቅ የቴሌቭዥኑ ጣቢያ

አዘጋጆች ለዚያ ትንቢት ማረጋገጫ እንደሆነ ሁሉ ያንን ታሪክ ያስተላልፉታል።

"እነዚህ ጋዜጠኞች በተጨማሪ የሌላ ሀገራት ለበር ዜናዎችን ከሚዘግቡ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ጋር ያስተዋውቁና ዜናዎቹ በጋዜጣ፣ በቲቪ ወይም በራዲዮ ከመሰራጨታቸው በፊት ስለ ዜናዎቹ የምትተነብየው አንተ ትሆናለህ። ይህ ጉዳይ በአንተ ትውልድ ውስጥ ያለ ብቸኛው እውነተኛ ነቢይ ያደርግሀል። ይህ መረጃ ሰጪ ትንቢት እግዚአብሔር ያለው ባይሆንም ከጋዜጠኞች በተገኘ ሾልኮ የወጣ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው።" አለ ዶክተር ያያ።

"በተጨማሪም ቤተክርስቲያንህ ባለበት አካባቢ መረጃ ሰጪዎች ሊኖሩህ ይገባል። ከወንበዴዎች ቡድን እቅድ እስከ በአካባቢው ያሉ ፖለቲከኞች ሚስጥራዊ እቅዶች ማወቅ መቻል ያስፈልግሀል። በብሄራዊ ቲቪ ፕሮግራምህ ላይ የምትጠቀምባትን መረጃ ከሚሰጡህ በአካባቢህ ካሉ ባህላዊ ሀኪሞች ጋር በቅርበት መስራት ይኖርብሀል። መኪና ተሰርቆ ከሆነ ጉዳና ላይ ካሉ ሰዎች በኩል መኪናው የት እንዳለ ማወቅ ይኖርብሀል። በሌሎች ሀገራት እንዳንድ ነቢያት የታላላቅ ፖለቲከኞችና ወንበዴዎችን ስልኮች በማስለጠፍ የሚያገኙትን መረጃዎች እንደ ትንቢት ይጠቀሙበታል። እዚህ ላሉ ሰዎች ሁሉ የሚሆን ከፍተኛ የተለምራትና የትንቢት ማዕከል እንድታቋቁም ልንረዳህ እንችላለን። ሁሉም በታዎች ላይ ሰዎች ስላሉን በእንድ ምሽት ታዋቂ ትሆናለህ። ይህ በጣም ውሀ የሚቋጥር ስብሰባ ነው ወንድሜ።" ኦለ ዶክተር ያያ።

@Amharicbookstore

ምዕራፍ አስራ አንድ

የኤች አይቪ ፈውስ ማታከያ

የገበያ ፕሮግራሞች

ስብሰባዎችና የማነቃቂያ ፕሮግራሞች ሱሳዊ እነዚህን ስብሰባዎች ገንዘብ ለመሰራት ክርስቲያኖችንና ክርስቲያን ያልሆኑትንም ለመሳብ እርግጠኛ መሆን አለብኝ። የስብሰባዎቼን ለገበያ የሚሆኑ ፖስተሮችና ማስታወቂያ ፅሁፎች "ለተአምራት አገልግሎት፣ ለፈውስና ለመዳን፣ ለገንዘብና ፅዳ ጥሰቶች ወደኛ ይምጡ። ከነቢይ ካታካታ ጋር የአንድ ለአንድ የምክር አገልግሎትና ምሽቱን ሙሉ ለሚደረግ ፀሎት ወደ እኛ ኑ።" የሚሉ አይነቶች ናቸው። አንድ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ በማስከፈል መፍትሄ ለመስጠት የሰዎችን ችግሮች በማጻምጥበት የአንድ-ለአንድ የምክር አገልግሎት ላይ አንዲት ወጣት ሴት ከእናቷ ጋር መምጣቷን አስታውሳለሁ። ወጣቷ ሴት ቆዳዋ በጣም የገረጣና ሰውነቷ ቦጫ ቀጭን ስለነበረ

በጣም እንደታመመች ያስታውቃል። በመጀመሪያዊ የምክር አገልግሎት ወቅት ስለ ሁለቱ ሴቶች የተናገርኩት ትንቢት ትክክል የነበረ በመሆኑ እናትየው በትንቢቱ ትክክለኛነት ከመደንገጧም በላይ ሰለ አንድ ግለሰብ ህይወት እንዲህ አይነት ጥልቅ ነገሮችን መግለጥ መቻሌን ማመን አልቻለችም።

ከዚያ እናትየው ቤተሰቦቿ የልጅቷ ሁሙም አውነተኛ ምክንያት የልጅቷ አባት ከተወለደች ጀምሮ ስለተዋትና እናትየው ከወለደች በኋላ መክፈል ያለበት የጉዳት ካሳና መደረግ ያለበት ስርዓት ባለመደረጉ መሆኑን ነገረችኝ። ቀጥሎም አሁን የወጣቷ ልጅ አባት ስርዓቱን ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆነ ወደኔ የመጡበት ምክንያት በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል ሰላማዊና ስኬታማ ክብረ በዓል እንዲኖር ለመጠየቅ እንደሆነ ነገረችኝ። እናትየው በአባትና በልጅ መካከል የሚኖረው እንደገና መገናኘት ልጂን ወደ ፈውስ እንደሚያመጣት ታምናለች። እናትየውንና ወጣቷን ልጅ ለማስደሰት ፀለይኩላቸውና ሄዱ። ከጥቂት ወራት በኋላ በአንድ የገበያ ማዕከል ውስጥ ከዚያች ወጣት ልጅ ጋር ድንገት ተገናኘን። በጣም ጤናማ ትመስላለች። አሁን ኤች አይ ቪ ኔጌቲቭ እንደሆነች ነገረችኝ።

ስለምትሉው ነገር እርግጠኛ መሆኗን ስጠይቃት ቅርብ ካሰ መድሀኒ ቤት የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ፕዘተን ሁኔታውን እንድናረጋግጥ ግድ አለችኝ። መመርመሪያውን ገዝንና መኪና ውስጥ ቁጭ ብለን ምርመራውን አደረገች። ውጤቱ ከኤች አይ ቪ መፈወሷን የሚያረጋግጥ ነበር። "ምን ተፈጠረ?" ስል ይህቺን ከወራት በፊት ካየኋት እጅግ የተለየች የሆነችብኝን ወጣት ጠየቅኳት። እሷም እናቷ ከወላጅ አባቷ ቤተሰቦች ጋር እንደገና እንድትገናኝ ለማድረግ ካዘጋጀችው ክብረ በዓል በኋላ ሁኔታዋ ተባብሶ ሆስፒታል ገብታ

@Amharicbookstore

እንደነበር ነገረችኝ። እናቷ እርሷን ለመጠየቅ ወደ ሆስፒታል በመጣችበት ጊዜ ሁልጊዜ ሆስፒታል በር ላይ ቆሞ ኤች አይ ቪን ለማዳን የሚችል ተአምራዊ ሻይ እንዳለ ለአንዳንድ ህመምተኞች እየነገረ የነበረ አንድ ሰው እንደተገናኘች ነገረችኝ። ቀጥላም ልጅቷ "እናቴ ኤች ኤይ ቪ ፖዘቲቭ እንደሆንኩ ብታውቅም ያለሁበትን ሁኔታ እውነታ መቀበል አትፈልግም ነበርና በአካባቢያችን ካሉት ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት የአንዱ ካህን ወደሆነው ወደዚህ ሰው ቀረበች። ከዚያ ተአምራዊ ሻዩን ለማግኘት ካህኑ ጋር ቀጠሮ ያዘች።" አለችኝ።

"ካህኑ በመጀመሪያ ተአምራዊውን ሻይ እንድጠቀምና የምከፍለው ውጤት ካየሁ በኋላ እንደሆነ ስለነገረን ምንም ገንዘብ አልከፈልንም ነበር። የሰጠንን ሁለት ባለ አምስት ሊትር ፈሳሽ ይዘን መድኃኒቱን ለመሞከር ወደቤት ሄድን። እንዳዘዘኝ ለአንድ ወር አንዱን ባለ አምስት ሊትር ፈሳሽ እንደተጠቀምኩ ወሩ ከማለቁ በፊት ውጤቶች ማየት ቻልኩ። ህክምናውን በሙሉ ከጨረስኩ በኋላ በአካባቢዬ ባለው ክሊኒክ ስመረመር ኤች አይ ቪ ኔጌቲቭ በመሆኔ በጣም ተገረምኩ። ውጤቱን ስመለከት የተሰማኝ የተደበላለቀ ስሜት ነበር። እና ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎችም አሉኝ። ነቢይ ካታሓታ" ስትል ወጣቷ ልጅ ነገረችኝ።

የነገረችን ታሪክ እውነት ቢሆንም በጣም ጥሩ የሆነና ለማመን የሚከብድ ነበር። ሁኔታዋ በጣም ስሜታዊ ስለሆነ እንኳን ደስ ያለሽ ልላት አልፈለግኩም፣ የፈለግኩት ይህንን ቁስ አግኝቼ የራሴን ምርመራ ማካሄድ ብቻ ነበር።

"ያንቺን ጉዳይ በተመለከተ በአሰቸኳይ ላገኘው ስለምፈልግ ወደዚህ ካህን ልትወስጂኝ ትችያለሽ?" አልኳት። ስለተስማማች ወዲያውኑ በመኪና ወደ አካባቢው ደርሰን በግራ በኩል የቤተክርስቲያኑ ምልክት ያለበት ጥቁር መስመር ያለው ጂኬት የለበሰውን የአካባቢውን ካህን አገኘሁት። ቁሱ እንኳን ደህና መጣችሁ አለንና ሌሎች ህመምተኞች ተራ እየጠበቁ ወደነበረበት ሄደን ተቀመጥን። ተራችን ደርሶ ይህንን የአካባቢው ፈዋሽ የማነጋገር እድል አገኘንና ማን እንደሆንኩና ነቢይ መሆኔን ገለፅኩለት። ተመሳሳይ ነገር የምንሰራ መሆኑን ስለተረዳ፣ መናፍስት የኤች አይ ቪ ፈውስ እንደገለፁለት ነገረኝ። እኔም ይህንን ነገር ወደ ጤና ጥበቃ መስሪያ ቤት ለተጨማሪ ፍተሻ ቢወስደው ታላቅ ግኝት ስለሆነ ብዙ ሰዎች ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ነገርኩት። መናፍስቱ እንዳልፈቀዱ ነገረኝ። "እዚህ የምታያቸው አብዛኞቹ ሰዎች አስተማሪዎች፣ ፖሊሶች፣ ነርሶች ናቸው። ሁሉም የመጡት ይህንን ፈዋሽ ሻይ ለመግዛት ነው። ይህንን ሻይ የተጠቀሙ ሰዎች ሁሉ በውጤቱ ረክተዋል።" አለኝ። የእርሱና የዚያች ወጣት ቃላት በዚያ ሻይ ውስጥ ያለውን ግኝት እንዳምንና እንዳረጋግጥ አደረጉኝ።

ለተገልጋዮቼ ጥቂት ጠርሙስ ሻይ ወሰድኩና ተገልጋዮቼ ተመሳሳይ ውጤቶች ካገኙ ደንበኛው እንደምሆን ነገርኩት። ያስገረመኝ ነገር ይህ ካህን ተገልጋዮቼ ይህንን ሻይ ቢወስዱም ህክምናቸውን ማቋረጥ እንደሌለባቸው መናገሩ ነበር። ተገልጋዮቹ ተአምራዊውን ሻይ ተጠቅመው ኤች አይ ቪ ኔጋቲቭ ቢሆኑም እንኳን በሆስፒታል የሚደረግላቸውን ህክምና መውሰዳቸውን እንዲቀጥሉ ይበረታታሉ። ሀሰተኛ ነቢይ ሆኜ እገለግልበት በነበረበት ዘመን ይህ ሻይ በጣም ዝነኛ ስላደረገኝ ከሌሎቱና ከቦትስዋና ሳይቀር ተአምራዊውን ሻይ ለመግዛት

@Amharicbookstore

ብዙ ሰዎች ወደኔ ይመጡ ነበር። ተአምራዊውን ሻይ ለአንድ ወር ከተጠቀሙ በኋላ ተመርምረው ኤች አይ ቪ ኔጌቲቭ መሆናቸውን ይነግሩኛል።

ጥቂት ጊዜ እንዳለፈ ያ ቂስ ሌላ ግኝት ስለማግኘቱ ሊነግረኝ ደወለልኝ። መናፍስቱ ከተአምራዊው ሻይ የበለጠ ኃይል ያለው በኪኒን መልክ የተዘጋጀ ሌላ ቅመማ እንደሰጡት ነገረኝ። እነዚያን ኪኒኖች እንዲልክልኝ ጠየቅኩትና ላከልኝ። ኪኒኖቹን እኔ ጋ ሰምክር አገልግሎት መምጣት ለምታዘወትር ሆዷ ልክ እንደ ነፍሰ ጡር ሴት በየጊዜው መጠኑ እየጨመረ ለሚመጣባት ሴት ሰጠኋት። ያቺ ሴት መድኃኒቱን መውሰድ በጀመረች በሶስት ቀናት ውስጥ ያበጠው ሆዷ ወደ ቦታው ተመለሰ። ይህ ተአምራዊ መድኃኒት የፈውስ እውነተኛ ማስረጃ ያለው በመሆኑ ሰዎች ወደኔ የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ መጉረፍ ጀመሩ።

ከዚያ እነዚያን መድኃኒቶች በብዛት በማከማቸት ወደኔ ለሚመጡት ሰዎች ተአምሩን ካያችሁ በኋላ ትከፍላላችሁ እያልኩ መሰጠት ጀመርኩ። በማህበረሰባችን ሬዲዮ ጣቢያ ብዙ ምስክርነቶች መሰማት በመጀመራቸው ነቢይ ካታካታ የሚባል ሰው አለ የሚለው ዜና ልክ እንደ ሰደድ እሳት ተሰራጨ። በሺዎች የሚቆጠሩ በራሪ ወረቀቶችን አሳተምን። በተጨማሪም የእያንዳንዱን ሰው ትኩረት ለመሳብ በእኔ የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮ የሚካሄዱትን ፈውሶች የሚያስተዋውቅ በነፃ የሚሰጥ የራሴ ጋዜጣ ማሳተም ጀመርኩ። አንድ ቀን ያ ቂስ ያለበት ቤተክርስቲያን የሚፈውስበትን መንገድ ስላልወደዱትና ሰዎች ቤቱ መጥተው በክፍያ የሚገለገሉ በመሆኑ እንዳባረሩት ነገረኝ። ስለዚህ ወደ አሱ በምመጣበት ጊዜ አስቀድሜ

እንድደውልለትና ቤቱ ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ ሌላ ቦታ ቦሚስጥር እንደምንገናኝ ነገረኝ። በእርግጥም በሚስጥር ተገናኘን።

መድኃኒቶችን በተገልጋዮቼ ላይ ከሞከረኩ በኋላ የእርሱ ኪኒኖችም ሆኑ ሻዩ፣ ቫይረሱም ሆነ ሌላ በሽታ በማሽንም ሆነ በመመርመሪያዎቹ እንዳይታዩ የሚደብቁ እንጂ የሚያድኑ እንዳልሆኑ ተረዳሁ። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ላፋጥጠው ወስኜ እንኑሁትና እንዳታለለኝና ውሸት እየሸጠ መሆኑን ነገርኩት።

አሁን ላይ ሆኜ ወደ ኋላ ስመለከት እውር እውርን የመምራት አይነት ነገር እንደነበረ እረዳለሁ። ምክንያቱም ሁለታችንም ጨለማ ውስጥ የነበርንና በማታለል የምንገፋ ነበርን። እርሱም ከተአምራዊው ሻይ ጀርባ ያለውን ማታለል በማመንና በመናዘዝ ጥርጣሬዬን አረጋገጠልኝ። ብዙ ተገልጋዮች በፍጥነት የማገግማቸው ሚስጥር ቂሱ በሆስፒታል ወይም በክሊኒክ የሚሰጣቸውን ህክምና ሁሉ በእግባቡ እንዲከታተሉ፣ ዶክተሮቻቸው ያሳቸውን እንዲያደርጉና ከሚሰጣቸው ተአምራዊ ሻይና መድኃኒት ጋር ጤናማ ምግብ እንዲመገቡ ያዛቸው ስለነበር መሆኑን ተረዳሁ። የእርሱ መድኃኒቶች የኤች አይ ቪ ቫይረስን እንደማያጠፉ ወይም እንደማይፈውሱ ከነገረኝ በኋላ ከመንግስት ወይም ከጤና ሚኒስቴር ጋር ችግር ውስጥ መግባት ስላልፈለግኩ መድኃኒቶቹን ሁሉ ሰማስወገድ ወሰንኩ።

© Amharicbookstore

ምዕራፍ አስራ ሁለት

የመናፍስት አምልኮ ያሉባቸውና አብያተ ክርስቲያናትና መለየት

የምስጋና አምልኮ ሀሰተኛ መንገድ

ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚሸጡና ጥቅም ላይ በሚውሉ ቅዳሴ ውሀ፣ ዘይትና ሌሎች ነገሮች የተነሳ ፎረንሲክ ትንበያ፣ ተአምራትና ምስክርነቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ የተለያዩ ስሞች ያሏቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ይህ አዲስ የተከሰተ የነቢያት እንቅስቃሴ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ፈጣን በሆነ ሁኔታ እንዲያድጉ እያደረገና ብዙ ሰዎች ጥሰትና ፈውስ ማግኘታቸውን እንዲመሰክሩ እያደረገ በመሆኑ አሁን አሁን ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን እያስነሳ ነው።

እነዚህ አዳዲስ ሰባኪያንና ነቢያት መዝሙሮችን የሚዘምሩና በጌታ ስም የሚፀልዩ ቢሆኑም በሚሰጥር ተክታዮቻቸው ባለማወቅ በክፉ መንፈስ እንዲያዙ የሚያደርግ የክፉ መናፍስት አሰራር ያፈፅማሉ።

በመናፍስቱ አለምና በአውነተኛው የእግዚአብሔር ወንጌል የሁለቱም ተሞክሮ ስላለኝ ከግል ተሞክሮዬ በመነሳት የመናፍስት አሰራር ያለበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ምልክቶች መለየት የሚያስችሉትን ጥቂት ቁልፍ ሁኔታዎች አብራራለሁ።

በሀገራችን የሚታየው የአብያተ ክርስቲያናት ፈጣን እድገት

ብዙ ሰዎች የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው የአነርሱን መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንደማያሟሉ ሲሰማቸው የራሳቸውን አብያተ ክርስቲያናት ወይም አገልግሎቶች ሲከፍቱ አይቻለሁ። እኔ የማውቃቸው አንዳንድ ቤተክርስቲያን መስራቾች እውቅና በሌላቸው የመጽሀፍ ቅዱስ ኦሌሜር ኮርሶችን በሚሰጡ ትምህርት ቤቶች የተማሩ፣ የፓስተርነት ሰርተፍኬት የነበሩና አንዳንዶች ደግሞ የዶክተርነት የብቃት ማሰረጃ በሀሰት ያሰሩ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ትርፍ አግበስባሽ ከሆኑ የመጽሀፍ ቅዱስ ኮሌጆችና መንፈሳዊ ድርጅቶች ፓስተር፣ ነቢይ፣ ሀዋርያና ቢሾፕ የሚሉ የቅስና ስሞች ያገኙ ናቸው።

እንደዚህ አይነት አብያተ ክርስቲያናት እውነተኛውን የእግዚአብሔር ወንጌል በሚያስተምር የመጽሀፍ ቅዱስ መሰረት ላይ ያልታነፁ ሲሆኑ፣ በጠቅላላ የመጽሀፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ስምችን

@Amharicbookstore

ወደ ጌታ የሚመሩም አይደሉም። እነዚህ አዳዲስ የሚመሰረቱ አብያተ ክርስቲያናት በየቀኑ ቁጥራቸው በፈጣን ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል። አንድ ሰው በአንድ ቤክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነት ያገኘና ያለው ስጦታ ያልታወቀለት ሲመስለው ለትርፍ ያልቆመ ድርጅት ሆኖ ይመዘገብና ህንፃ ተከራይቶ ወይም ድንኳንና የሙዚቃ መሳሪያዎችን ሰብስቦ እንዴት በራሱ የሚተዳደር የፓስተርነት ወይም የነብይነት ሙያ እንደሚከተል አይቻለሁ። እነዚህ በራሳቸው የተቋቋሙ ነቢያት፣ የነቢያትና የተአምራት ማዕከላትን የሚወዱ ናቸው። እነዚህ የተአምራት ማዕከላት ዛሬ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሀብረት አለመኖርና መከፋፈልን አምጥተዋል።

የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት

የመናፍስት አምልኮ ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት በጥንቆላ አሰራር ኃይል ተፅእኖ ስር ያሉ በመሆናቸው እንደኛው ኃይል ከሌላኛው የበለጠ ጠንካራ እንደሆነ ስለሚታመን እርስ በርሳቸው ይጣላሉ። ስለሆነም የነዚህ የመናፍስት አሰራር ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ፓስተሮች በእነሱ ቤተክርስቲያን አባላትና በሌላ ቤተክርስቲያን አባላት መካከል መከፋፈልን ያስተምራሉ።

ከዚያ ይህ መንፈሳዊ ጠብ "በተቀነባበረ ሁኔታ በአጋንንት እንደተያዙ ሆነው በቀረቡ ሰዎች ሊያጠፉ የፈለጉትን ፓስተር ወይም ነቢይ ስም በመጥራት ስለዚያ ሰው መጥፎ ነገር እንዲናገሩ ወደማድረግ ደረጃ ይደርሳል። እንደዚህ አይነት ነገሮች የመናፍስት አምልኮ ባለባቸው አብያተ ክርስቲያናት የተለመዱ ሲሆን፣ አጋንንት እንዳለበት ሆኖ የሚናገረው ሰው አሁን እነርሱ ጋ ያለውን ነቢይ

ብቸኛ፣ ሀያሉና እውነተኛው የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆነ ማረጋገጫ ይሰጣል። በተጨማሪም ይህ አጋንንት እንዳለበት ሆኖ የሚናገረው ሰው አሁን በስራ ላይ ያለውን ነቢይ ኃይል ለማጥፋት ከሌላ ቤተክርስቲያን በሰው አምሳል ተልኮ የመጣ አጋንንት እንደሆነ ይናገራል። ለሰዎች ሁልጊዜ በአብያተ ክርስቲያናትና በቲቪ የሚታዩትን እነዚህን የአጋንንት መገለጦች ማመን [illegible]ሊለባቸው የምንነግረው ለዚህ ነው። በእንደዚህ አይነት በቅንብር የተሰሩ መገለጦች አብዛኞቹ እውነት አይደሉም። ከነዚህ ነቢያት አንዳንዶቹ አጀንዳቸውን በተቀናበረ የአጋንንት መገለጦች፣ ምስክርነቶችና ትንቢቶች በኩል ያሳካሉ።

የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት ስለዚህ መስበክ የሚገባት ንስሀ፣ የሀጥያት ይቅርታ፣ ፍቅርና አንድነት ነው። ክርስቶስ ራስ ነው፣ እኛ ደግሞ የዚህ አካል አባላት ነን። የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት መፈወስ፣ ተአምራት መስራት፣ ትንቢት መናገር ስለሚችሉ የእነርሱ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው የበለጠ እንደሆነ ያምናሉ። በተጨማሪም ለተከታዮቻቸው የእነርሱ መባረክና ጥበቃ ሊገኝ የሚችለው በእነርሱ የመናፍስት አምልኮ ቤተክርስቲያን ብቻ እንደሆነ የሚገልፅ የሀሰት ትምህርት ያስተምራሉ።

የቤተክርስቲያን ስሞች

እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የክርስቶስ እንጂ ድርጅት ወይም ቤተሰብ አለመሆኗን መረዳት ያስፈልገናል። ሁላችንም በጌታ የወይን እርሻ ውስጥ ሠራተኞች ነን። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንግዳ የሆኑ ስሞች አሏቸው። ምክንያቱም አብዛኞቹ የመናፍስት

© Amharicbookstore

አምልኮ ማህበራት ሚስጥራዊ ማህበራቱ ከቆሙለት ዓላማ ጋር የሚስማማ እንዲሆን ስለሚፈልጉ ነው። ምክንያቱም ማህበሩ አንድ ቤተክርስቲያን ብዙ ሰዎችን የሚሰበው በስሙ ጭምር እንደሆነ ስለሚናገሩ ነው። አንዳንድ የመናፍስት አምልኮ ማህበራት ደግሞ የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን ሎጎ ላይ የማህበሩን ምልክቶችና ቀለማት እንዲጠቀሙ ያዛሉ። ለቤተክርስቲያን ስያሜ የመስጠት መመሪያ የለም። ግን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በክርስቲያን አስተምህሮ ላይ የተመሰረተች በመሆኗ ስሟም ከመጽሀፍ ቅዱስ ትክክለኛ አስተምህሮ ጋር የሚስማማ መሆን ይገባዋል። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ተአምራት ፈላጊዎችን፣ የታመሙ ሰዎችንና ከነዚይ ጋር የሰንድ ለሰንድ የምክር አገልግሎት ፈላጊዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችላቸው ፊውስ፣ ተአምራትና ትንቢት የሚሉትን ቃላት ይጠቀማሉ። የእንደዚህ አይነት አብያተ ክርስቲያናት መሰረታቸው ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ተአምራት፣ ፊውስና ትንቢቶች ናቸው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለምእመናኑ ተአምራት እንደሚደረግላቸው ቃል ስለሚገቡ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግስት ሳይሆን እነዚህን ተአምራት በመፈለግ ወደ አነርሱ ይጉርፋሉ።

በቤተክርስቲያን አባላት ላይ ያለ ሙሉ የመቆጣጠር ኃይል

በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ የመናፍስት አምልኮ ሰራ የሚለይበት ሌላኛው መንገድ መንፈሳዊ መሪዎች በተከታዮቻቸውና በጉባኤው ላይ ያላቸው አእምሮን የመቆጣጠር ኃይልና መንፈሳዊ

ሚታለያዎች ነው። እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባላቱ በመጽሀፍ ቅዱስ መመሪያዎች ላይ እንዲተክሉ ሲያዝ የመናፍስት አምልኮ ያለበት ቤተክርስቲያን ደግሞ የቤተክርስቲያኒቷ አባላት የመሪዎቹ ባሪያዎች እንዲሆኑ ለማስር አንዳንድ የመጽሀፍ ቅዱስ ጽሁፎችን ያጣምማሉ። የመናፍስት አምልኮ ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት የሚያስተምሩት ከክርስቶስ አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ የስሚ ስሚ ትምህርቶችን ነው።

ብዙ የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት ንፁህን ተከታዮቻቸው የፀረ-ክርስቶስ አስተምህሮ እየተከተሉ መሆናቸውን ሳያውቁ ወደ ፀረ-ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያንነት ተቀይረዋል። ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ መሪዋን ቃል ከእግዚአብሔር ቃል በላይ እንደሆነ አድርጋ መቁጠር ከጀመረች ያ ፀረ-ክርስቶስ የመሆን ድርጊት ነው። እነዚህ ፀረ-ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ለጉባኤያቸው የመንፈሳዊ መሪያቸው ስልጣንና ትዕዛዝ ላይ ምንም ጥያቄ እንዳያነሱ ያዛሉ። እነዚህ የመናፍስታዊ አምልኮ መሪዎች ያለ ትክክለኛ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ስልጠና መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም ጉባኤዎቻቸውን በአእምሮና በመንፈስ ባሪያ ያደርጋሉ። በተጨማሪ የቤተክርስቲያን አባላቱን ከእግዚአብሔር ይልቅ ለመሪዎቻቸው ያላቸውን ታማኝነት ለማረጋገጥ ህይወታቸውን አደጋ ላይ የሚጥሉ ድርጊቶችን እንዲፈፅሙ ሳይቀር ይገፋፏቸዋል። የቤተክርስቲያን አባላት አንድ ጊዜ ለፀረ-ክርስቶስ ስራ ከታጩ፣ ለመንፈሳዊ መሪው እጅግ ታማኝ ስለሚሆኑ መሪው በሌሎች ጥቃት ቢደርስበት ወይም ሌሎች ስዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የመናፍስት አለራር ለማሳየት ቢሞክሩ ይከላከሉለታል።

@Amharicbookstore

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የመጐብኘት አደጋ

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ቀን መንግስተ ሰማያት ስለመሄድ የሚናገሩ ቢሆንም የተከፋፈሉ ናቸው። የመናፍስት አምልኮ ያለባቸው ቤተክርስቲያን አባላት መንፈሳዊ አባታቸው ከሚያስተምራቸው ትምህርቶች ጋር የማይገጥም ቤተክርስቲያኖችን ከመጐብኘት ወይም በሌሎች የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ከማመን እንዲታቀቡ ይነገራቸዋል። የመናፍስታዊ አምልኮ ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠረው አንድ ሰው ሲሆን፣ በአብዛኛው ያ ሰው ዋና እገልጋይ፣ ዋና ነቢይ፣ መንፈሳዊ አባት ወይም ቢሾፕ የሚል ማዕረግ የተሰጠው ሰው ነው። በጋብቻ፣ ስራ፣ ጤንነት፣ ንግድ ወይም የፍርድ ቤት ጉዳዮች ያሉ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚወሰኑት ንፁሀን ጉባኤውን ወክሎ በሚወሰነው ዋና ነቢይ ነው። ብቸኛው እውነተኛ ምክር የሚመጣው በብቸኝነት ከሚያዳምጠውና በጌታ ከተመረጠው መንፈሳዊ መሪ ነው ብለው ስለሚያምኑ በጉባኤው ውስጥ ያሉ የተማሩ ሰዎች የሚቆጠሩ አይደሉም። የቤተክርስቲያን አባላት በአንዳንድ ትክክል ያልሆኑ አስተምህሮዎች ላይ ግልፅ እንዲሆኑላቸው የሚፈልጓቸውን ነገሮች በሚያነሱበት ጊዜ፣ የቤተክርስቲያኒቱን መንፈስ መጠየቅ አይገባም ብሎ በመንገር ፀጥ ያሰኟቸዋል። የመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት አባላት የሚገዙት ባለማወቅና በጨለማ ነው። ጉባኤው አብዝቶ በመናፍስት አምልኮው ፓስተር ላይ በተማመነ መጠን የለበጠ በጨለማ የሚንዝ ይሆናል። ምክንያቱም ህይወታቸው የሚሸከረከረው እንደ ጣዖት በሚቆጠረው በመሪው ዙሪያ ብቻ ነው።

የቤተክርስቲያን አባላት ወደሌሎች አብያተክርስቲያናት መሄድ በፈለጉ ጊዜ ሁሉ፣ በነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ስለሚገኙ ክፉ መናፍስት ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ማስጠንቀቂያውም ከሌላ አብያተ ክርስቲያናት የመጣ በሚል የተቀናበረ የአጋንንቶች መገለጥ፣ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አባላት የሆኑ ሰዎች እንዴት መንፈሳዊ ትግል እንደሚገጥማቸው በሚነገር የተቀናበረ ምስክርነት የተደገፈ ነው። የመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን በእግዚአብሔር ማረጋገጫ የተሰጠው ብቸኛ ቤተክርስቲያን አድርገው ይሰራሉ። ነቢያቸውም መላዕክትን ወደ ቤተክርስቲያን መጋበዝ የሚችል ኃይል ያለው አምላካዊ ምስል ይሰጡታል። የቤተክርስቲያን መሪዎች ብዙ የተደበቀ ስራ እያላቸው አባላቶቻቸውን ግን ሁልጊዜ እንደ ሲጋት በመቁጠር እንደ ተጠራጣሪ፣ ክሳሽ፣ የማያምኑ፣ ኃጢአተኞችና ሌሎች መጥፎ ሰሞች በመስጠት የቤተክርስቲያን አባላትን ይቆጣጠራሉ።

ከነቢዩ ጋር አንድ ለአንድ

የቤተክርስቲያኑ ፓስተር ወይም መሪ ዋና ተልዕኮ ለእግዚአብሔር ሀዝብ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ፣ መፀለይና ያለምንም የተቆረጠ ክፍያ ለአባላት የምክር አገልግሎት መስጠት ነው። ፓስተር ደግሞ በእግዚአብሔር ለሀዝብ የተመረጠ እረኛ ነው። የመናፍስት እምልኮ መሪዎቹ ግን በተለያዩ መንገዶች ንፁሃን የቤተክርስቲያን አባላትን ይበዘብዛሉ። ከነዚህ መንገዶች መሀከል የተለመደው እንደኛው አሰራር ከነቢዩ ጋር የሚደረግ የአንድ ለአንድ የምክር አገልግሎት አሰጣጥ ነው። ይህ የመንፈሳዊ የምክር

@Amharicbookstore

አገልግሎት አሰራር የሚመጣው ከዋጋ ጋር ሲሆን አባላቱ ህመምተኞች ወይም ተገልጋዮች ተብለው የሚጠሩና በፓስተሩ ወይም በነቢዩ ትዕዛዝ መሰረት የሚኖሩ ናቸው። አንዳንድ ነቢያት እንዲያውም አባላቶቻቸውን እንግዳ በሆነ አስተምህሮ ለማነሳሳትና በተወሰነ ክፍያ ዘይትና ውሀ ለመሸጥ ወርክሾፕና ስልጠናዎች እስኮማዘጋጀት ድረስ ይሄዳሉ።

እነዚህ ነቢያት የሚሰጧቸው ትእዛዛት ከአንድ ህመምተኛ ወደሌላው የሚለያይ ሲሆን፣ የትኛው ላጤ ማግባት እንዳለበት፣ የትኛው መኪና መንዳት እንደሚገባው፣ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚሰጥና ባልና ሚስት እንዴት መቀራረብ እንዳለባቸው ሳይቀር ይታዘዛል። ሰዎች የተነገራቸውን የማድረጋቸውን ሪፖርት ለመንገር የክትትል ትዕዛዛትን ለመቀበል ነቢዩ በሚያዘው መሰረት በመክፈል ከነቢዩ ጋር ወደሚደረግ ወደዚህ የአንድ ለአንድ የምክር አገልግሎት በብዛት ይመጣሉ። አባላት በሁሉም ነገር እምነታቸውን በዚያ ነቢይ ላይ እንዲጥሉ ይደረጋሉ። አብዛኞቹ አባላት በነዚህ በዝፍያ በሚደረጉ የምክር አገልግሎቶች በኩልና በመሰዋዕቶች ወይም ስርዓቶች ነፍሳቸውን መንፈሳዊ መሪ ለሚባለው ወይም ለነቢዩ መሸጣቸውን እንኳን አያውቁም።

ከቤተክርስቲያን የመልቀቅ እደጋ

መንፈሳዊ መሪው በአባላቱ ገንዘብ፣ አእምሮና መንፈሳዊ ህይወት ላይ ሙሉ ቁጥጥር ስላለው አባላቱ ከዚህ ቤተክርስቲያን እንዲርቁ በሚወጿቸው ሰዎች ቢመከሩም እንኳን ለእነርሱ ከዚህ ቤተክርስቲያን መላቀቅ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። አብዛኞቹ አባላት

በጣም ሚስጥራዊ ጉዳዮቻቸውን ሳይቀር ለዚያ ሰው የተናገሩ በመሆኑ ያ ነቢይ ከእንደዚያ አይነት ቤተክርስቲያን ሰቆ መውጣት የሚፈልገውን ማንኛውንም ሰው እንዳይወጣ ለማድረግ የዚያን ሰው ሚስጥር በመጠቀም ያስፈራራዋል።

ይህ የማስፈራራት ተግባር በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውለው ብዙ ገንዘብ ላላቸውና አብዝተው ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የሚሰጡ ሰዎች ላይ ሲሆን በአንዳንድ የምክር አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ውስጥ ዋናው ነቢይ ድብቅ ካሜራ በማስቀመጥ ተገልጋዩ የሚናገራቸውን ሚስጥራትና ወንጀሎች ሳይቀር ቀርፀው ያስቀምጣሉ። እነዚህ የተቀዱ ንግግሮች ያ ሰው ቤተክርስቲያን ለቆ እንዳይሄድና ለዚያ ነቢይ ገንዘብ መስጠቱን እንዲቀጥል ለማድረግ ማስፈራሪያ በመሆን ያገለግላሉ። አንዳንዶች እንዲያውም በአባላቶቻቸው ላይ አካላዊና መንፈሳዊ ጥቃት ወይም እርግማን እንደሚያደርሱ አድርገው ሳይቀር ያስፈራራሉ። ይህ መናፍስታዊ አምልኮ ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁልጊዜ በሰው ተሞልተው ከሚታዩባቸው ምክንያቶች አንዱ ነው። ነገር ግን ይህ መፅሀፍ በሚነበብበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ነፃ ወጥተው ወደ ጌታ ለመመለስና ከነዚያ ሰዎች ለማምለጥ ድፍረት እንደሚያገኙ አምናለሁ።

ሚስጥራዊነት

ግልፅ የሆነ ፖሊሲ ለጉባኤው መኖር ለአንድ ቤተክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። መናፍስታዊ አምልኮ ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ግን የቤተክርስቲያን አባላት በተለያዩ ስሞችና ፕሮጀክቶች የተለያዩ መስዋዕቶች እንዲሰጡና ፀሎታቸው እንዲሰማ ለማድረግ

@Amharicbookstore

ሌሎች መንፈሳዊ ዕቃዎች እንዲገዙ በማድረግ አብያተ ክርስቲያናቱን ወደ ሱቅነት ይለውጧቸዋል። ነገር ግን ከመስዋዕት ወይም ከእቃዎች ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ግልፅ አያደርጉም። የቤተ ክርስቲያኑ መሪ ህዝቡ ወይም ሌሎች ጉባኤዎች "መናፍስቱ" ለአንድ በአንድ የምክር አገልግሎት ሰዎች በንስ እንዲሰጡ እንዳዘዙ እንዲያውቁ አይፈልግም። ይህ አይነቱ ሚስጥራዊ ስጦታ በአንዳንድ ሁለተኛ ነቢያት የይስሀቅ መስዋዕት ተብሎ ይጠራል። መንፈሳዊ መሪው ይህንን "የይስሀቅ መስዋዕት" ተብሎ የሚጠራውን ሚስጥራዊ ገንዘብ የሚደግፍለትን ሀሳብ የሚያገኘው አንዳንድ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማጣመም ወይም በተሳሳተ መንገድ በመጥቀስ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ሚስጥራዊ አሰራሮች በበዙ መጠን አንድ ሰው የበለጠ መጠንቀቅ አለበት።

የቤተ ክርስቲያን አባላት እጩዎች እየመለመሉ ይሰለጥናሉ

የመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት በፈጣን ሁኔታ ካሚያድጉበት የተለመዱ መንገዶች አንዱ እጩዎችን መመልመል ነው። እጩዎችን መመልመል ብዙ በምጠራው ዘዴ የቤተሰቡ አንድ አባል መላውን መንደር ማምጣት ይችላል። አባላት ወደ እነዚህ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ ከተደረጉ በኋላ መንፈሳዊ አባታቸው በተለይ በፎረንሲክ ትንበያ ምን ያህል ስጦታ እንዳለው መጥተው እንዲያዩ ሌሎች የቤተሰብ አባላትን ይጋብዛሉ። አዲሶቹ የቤተሰብ አባላት ወደ ቤተክርስቲያኑ መጥተው ጉባኤው ስለዚያ መንፈሳዊ አባት ሲዘምሩና እንዳንዶቹ ደግሞ ከዚያ ነቢይ ወይም ፓስተር

በተደረገላቸው ልዩ ፀሎት ስላገኙት ልዩ ኃይል በግልፅ ሲመሰክሩ ይሰማሉ፣ ያያሉ። አዳዲሶቹ ሰዎች ቀስ በቀስ ከነዚህ መናፍስታዊ አታላይ ኃይላት ጋር ይተዋወቃሉ። ቀጥሎም የቤተክርስቲያኑ አባላትን የአለባበስ ሁኔታ፣ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚሸጡትን ነገሮች፣ ነቢዩ ወደ መድረክ ሲወጣ ያለውን የአድናቆት ጩኸትና ነቢዩም ሰዎችን በሰምና በክልክ ቁጥር ሲጠራ በትኩረት ይመለከታሉ።

ነቢዩ ሁልጊዜ አዳዲስ የመጡ ሰዎች እንዲቆሙ ይጠይቅና በነዚያ ሰዎች ላይ ትንቢት ይናገራል። የመናፍስት አምልኮ ነቢያት ትንቢት ለመናገር የባህር መንፈስ የሆነችውን እኒታን የሚጠቀሙ ሲሆን፣ አብዛኞቹ ትንቢቶች በትክክል ንፁህን ነፍሶችን የሚያታልሉ ናቸው። ከፕሮግራሙ በኋላ ትንቢት የተነገረላቸው ሰዎች የምክር አገልግሎት ለማግኘትና ለክትትል ነቢዩን ማግኘት እንደሚያስፈልጋቸው ይነገራቸዋል። ይህ የክትትል የምክር አገልግሎት የአዳዲስ ሰዎችን ሀሳብ ለማሰለወጥና ለክትትል የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሰው እንዲመጡ ለመጋበዝ መልካም አጋጣሚ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሰው ሲመጡ ይህንን ተአምራት እንዲያዩ ሌሎች ሰዎችን ይዘው ይመጣሉ። ሰዎች ትክክለኛ ትንቢት እንዲያታልላቸው መፍቀድ የለባቸውም። ምክንያቱም ከነዚህ ትንቢቶች አንዳንዶቹ በጣም በተወሳሰበ መንገድ የሚገለፁ በመሆኑ ትንቢቱ ለሚነገርበት ሰው ግልጽ የሆነ ነገር ከማምጣት ይልቅ ተጠቂው ግራ እንዲጋባ በማድረግ ከነቢዩ ጋር የክትትል የምክር አገልግሎት እንዲያደርግ የሚያደርግ ነው።

@Amharicbookstore

በመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም ላይ የሚውሉ አደገኛ መናፍስታዊ ዕቃዎች መናፍስታዊ ቀለበቶች

መናፍስታዊ ቀለበቶች በብዙ ክርስቲያን ፓስተሮች፣ ነቢያትና ቢሾፖች ጣት ላይ የሚደረጉ ልዩ ቀለበቶች ተብለው የሚጠሩ ናቸው። ከነዚህ ቀለበቶች አብዛኞቹ የተለዩና ውድ ዋጋ ያላቸው የሚመስሉ ናቸው። እነዚህ ቀለበቶች ያ ነቢይ ወይም ፓስተር በቤተክርስቲያኑ አባላት ላይ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ ስልጣን እንዲኖረው የሚያደርግ የመናፍስት ኃይል ያላቸው ናቸው። እነዚህ ቀለበቶች ፓስተሩ በቤተክርስቲያን ውስጥ ፕሮግራም ላይ ወይም በቴሌቭዥን በሚታይበት ጊዜ የሚያዩት ሁሉ እንዲያምኑት የሚያደርግ ነው። አጅግ አስደናቂ ተአምራት የሚደረጉት በነዚህ ቀለበቶች ላይ ባለ ኃይል በኩል ነው።

ይህ ቀለበት ከብረት የሚሰራ ሲሆን መስራት የሚጀምረው በሰውየው ጣት ላይ ሲደረግ የሰውየውን አካል ሲነካ ነው። ቀለበቱ ኃይል የሚኖረው በዚያ ቀለበት አናት ላይ በሚገኝ ምስል፣ ምልክት ወይም የተለየ ድንጋይ ነው። እነዚህ ሀይላት ቀለበቱን የሚያደርገውን ሰው አካል የሚጠቀሙ አጋንንቶች ሲሆኑ፣ ቀለበቱን ባደረገ ቁጥር በሰውየው ውስጥ የሚሰሩ ናቸው። ከአብዛኞቹ ተአምራት፣ ፈውስና ትንቢቶች ጀርባ የሚሰራው ኃይል አጋንንቶቹ ናቸው። ነቢዩ ቀለበቱን አድርጎ የሚፀለይላቸው ወይም ትንቢት የሚነገርላቸው ሰዎች ያ ነቢይ ሲፀልይ ቀለበቱ ላይ ያለው አጋንንት ራሱን በማባዛት ያንን ትንቢት በሚቀበሉ ነፍሳት ውስጥና እጅ ተጭኖ በሚፀልይላቸው

ሰዎች ውስጥ ይሰራጫል። አጋንንቱ ራሱን የሚያባዛበት ዘዴ ተአምራትና ፈውስ በማሳየትና ትንቢቱን በመሚሳት ሲሆን፣ ይህንን ሲያደርግም በየቀኑ፣ በየሰምንቱና በየአመቱ ንፁህን ነፍሳት በመንፈስም ሆነ በንዝብ ደረቅና ባዶ እስኪሆኑ ድረስ ይመገባል። ይህ አጋንንት በዚያ ነፍስ ውስጥ ባለው ቆይታ በመደሰት ያድግና የዚያን ንፁህ ነፍስ ህይወት ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል።

ነጭ መሀረብና ፎጣ

ይህ የመናፍስት ነጭ መሀረብ ወይም ደረቅ ፎጣ የመናፍስት አምልኮ ሰባኪዎች በስብከት፣ በጸሎትና ትንቢት በሚናገሩ ጊዜ የሚጠቀሙበት ነው። ሰባኪው በሚሰብክበት ጊዜ በአንድ እጁ ነጭ መሀረብ ወይም ፎጣ መያዙን እርግጠኛ መሆን አለበት። አንዳንዶቹ ደግሞ ለንፁህን ነፍሶች በሚፀልዩበት ወቅት ይህንን መሀረብ ይጠቀማሉ። በዚህ ጊዜ እነዚያ የሚጸለይላቸው ሰዎች ይፈዛሉ፣ በመጨረሻም ይወድቃሉ። እነዚህ መሀረቦችና ፎጣዎች ተአምራት ለመስራት ልዩ ኃይል የሚያስከትሉ ናቸው። ይህንን ስል ግን ሁሉም መሀረቦች፣ ፎጣዎችና ሻርፖች የመናፍስት ናቸው ማለቴ አይደለም።

ነጩ መሀረብ

ይህ ጨርቅ የሰዎችን መንፈሳዊ ህይወት ለመቆጣጠር ልዩ የአስማት መድኃኒት ተደርጎበት አንድ ጥግ ላይ ይታሰራል። የመናፍስቱ ነቢይ በነጩ መሀረብ ራቱን ከጠረገ በኋላ ሰዎች ገንዘብ እንዲሰጡ ያላል። በዚህ ጊዜ ድንገት ሁሉም ሰው ገንዘብ ሲሰጥና ለመስጠት ቃል ሲገባ ታስተውላለህ። የመናፍስቱ ነቢይ በአንድ እጁ

@Amharicbookstore

ይህንን ነጭ መሀረብ ይዞ ሲሰብክ የሚናገረው አሉባልታ ቢሆንም እንኳ ሁሉም እንዲያዳምጠው ያደርጋል። ሰባኪው እነዚያን መናፍስት አንዲገሰጡ ለማድረግ አሁንም አሁንም ፊቱን በመሀረቡ ይጠርጋል። በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እነዚህ የተለምራት ነጭ መሀረቦች ለቢዝነስና ለፍቅር ግንኙነት ለሚፈልጉ አባላት ይሸጣሉ።

የተለምር ውሀ

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውሀን ለፈውስ ይጠቀማሉ። ውሀ ለሰውነታችን እጅግ አስፈላጊ በመሆኑና ብዙ ነገሮችን የማጸን ኃይልም ስላለው የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ጠቃሚነቱን ከግምት በማስገባት ውሀው ውስጥ መናፍስት እንዲኖሩ በማድረግ ውሀን ለፈውስ ይጠቀማሉ። እነዚህ መናፍስት የውሀ መናፍስት ወይም የባህር መናፍስት የሚባሉት ናቸው። ይህንን ውሀ ለፈውስ ወይም ትንቢት ለመናገር የሚጠቀሙ የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ተለምራት፣ ፈውስ፣ ትንቢት ለመናገርና በቤተክርስቲያናቸው ብዙ ህዝብ ለመሳብ የሚጠቀሙበት የባህር መናፍስቶችን ኃይል ነው። እግዚአብሔር ያለምንም ውሀ ይፈውሳል። ከሰዎች የሚፈልገው በእርሱ እምነት እንዲኖራቸው ብቻ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህንን "ተለምራዊ ውሀ" መጠቀም ሲጀምሩ እንግዳ የሆኑ ራዕዮችንና ህልሞችን ማየት ይጀምራሉ። ራዕዮቹ በአብዛኛው በጥልቁ አለም ዙሪያ የሆኑ ሲሆኑ፣ ይህንን ውሀ የሚጠቀሙ ሰዎች በጥልቁ ውስጥ ሆነው መናፍስት ባሉችና መናፍስት ሚስቶች ሲያገቡ ራሳቸውን ያዩታል። ይህ ተሞክሮ የሚመጣው በዚህ ተለምራዊ ውሀ በኩል የባህር መናፍስት ስለሚቀሰቀሱ ነው።

ቅዱስ ዘይት

በመጀመሪያ መጽሀፍ ቅዱስ በክህናት የሚዘጋጅ ቅዱስ ዘይት ስለመጠቀም የሚናገር መሆኑን መረዳት ያስፈልገናል። ይህ ዘይት የሚገኘው ከወይራ ዛፍ ሲሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ካህናት እውነተኛውን ቅዱስ ዘይት ለማዘጋጀት የወይራ ፍሬዎችን ይጠቀሙ ነበር። ዛሬም የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት የወይራ ዛፍን ጨምሮ የፈለጉትን የራሳቸውን ዘይቶች ይጠቀማሉ። የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ለተለያዩ ችግሮች የተለያዩ ዘይቶች የሚጠቀሙበት ምክንያት በዘይቶች ውስጥ ካሉት ንጥረ ነገሮች የተነሳ ነው። አብያተ ክርስቲያናቱ ከእንስሳት ስብ የተሰራ ዘይትን ለስልጣንና ለጠንቋይ ማንነት ይጠቀሙበታል። በተለይ እንደ አንበሳ፣ አቦሸማኔ፣ ንስር አሞራና እባብ ያሉ እንስሳት ስብ ወደ ፈሳሽ ዘይት ይለወጥና ዘይቱ ሲያዩት ደስ የሚል እንዲሆንና መልካም ሽታ እንዲኖረው ተደርጎ ጥቅም ላይ ይውላል። አንዳንድ ነቢያት እነዚህን ዘይቶች በሚያምሩ ጠርሙሶች ውስጥ ያሽጓቸዋል። የፈውስ ዘይት በአብዛኛው ከዘንዶና እባብ ስብ የሚሰራ ነው። ምክንያቱም እባብ ራሱን በራሱ የመፈወስ ተፈጥሮ ያለው በመሆኑ ነው። እነዚህ ቅዱስ ተብለው የሚጠሩ ዘይቶች በፍፁም ቅዱስ አይደሉም። እነዚህን ዘይቶች የሚጠቀሙ ሰዎች አብዝተው በተጠቀሙ መጠን ከዘይቶቹ ጀርባ ያሉት መናፍስት የሰዎቹን ነፍስ የሚያሰቃዩ በመሆኑ ህይወታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል።

@Amharicbookstore

ልብስ፣ ፎቶና ዶክመንቶችን ወደ ነቢያት ማምጣት

ብዙ ሰዎች ልብሶችን፣ ፎቶዎችን፣ ዶክመንቶችንና ሌሎች የግል ዕቃዎችን ወደ ነቢይ ወይም መናፍስታዊ ስራ ወደሚሰራ ሰው ሲያመጡ አይቻለሁ። ሰዎች እውነተኛ ፀሎት ርቀት እንደማይገድበው ይረሱታል። ፀሎት በየትኛውም ጊዜ የሚያስፈልግበት ቦታ ይደርሳል። ፎቶዎችንና ልብሶችን ወደ መናፍስታዊ ነቢይ ማምጣት ያ ነቢይ ያንን ፎቶ ላይ ያለ ሰው ወይም የልብሱን ባለቤት እንዲቆጣጠረው ያደርጋል። በተጨማሪም ንፁሀን ነፍሶችን ለማጥመድ እንደ ቅዱስ ዘይትና ውሀ ካሉት ነገሮች ጋር ልዩ መስሀብም ጥቅም ላይ ይውላል። የተለየዋቸውን ፍቅረኞችን መልሶ ለማምጣት፣ የፍርድ ቤት ጉዳይና ጨረታ ለማሸነፍና ለሌሎች ምክንያቶች ደግሞ የጥንቆላ ድርጊት ይፈፀማል። የዚህ አሰራር መዘዙ ተጠቂውን በከባድ ክፉ መናፍስት እንዲታሰር ማድረግ ነው።

ቁሳዊነትን መስበክ

በመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ዲያብሎስ ብዙ ቁሳዊ ነገሮችን ለማግኘት ወደ አብያተ ክርስቲያናት እንዲመጡ ተከታዮቹን ያነሳሳል፣ ያስተምራል። ጠላት የእግዚአብሔር ሰዎች ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ ፍቅራቸውንና መተማመናቸውን እንደ ገንዘብ፣ ቤቶች ወይም መኪኖች ባሉ ጊዜያዊ ነገሮች ላይ እንዲያደርጉ ይፈልጋል። አንድ ጊዜ የሆነ ፓስተር ወደኔ መጥቶ ቤተክርስቲያኑ ሙሉ እንዲሆን የቤተክርስቲያን አባላት ሀብታም እንዲሆኑ የሚደረግ ነገር እንድሰጠው ጠይቆኝ ነበር።

በእኛ ጊዜ ያለው እውነታ ይህ ነው። ሰዎች "የሞቱ አብያተ ክርስቲያናት" ብለው ከሚጠሯቸው ውጥተው ተአምራት ይሰራሉ ብለው ወደሚያምኗቸው አብያተ ክርስቲያናት ይሄዳሉ። ዛሬ ዛሬ ለጥሪያቸው እውነተኛ ታማኝና ንፁሕ የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ገንዘብ አፍቃሪና በቤተክርስቲያን ተአምራት የሚሰሩና ትንቢት የሚናገሩ ለመሆን ምንም ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ የሚሆኑ ሆነዋል። የዚህ ጉዳይ እውነታ ዲያብሎስ የብልፅግና ወንጌል እያሰራጨ መሆኑ ነው። ይህ ወንጌል ደግሞ የደህንነት ወንጌል አይደለም። ከእግዚአብሔር የበለጠ ለማግኘት በማሰብ ያላቸውን ንብረት በሙሉ ጥሰው የደኸዩ፣ እንዳሰቡት ሳይሆንላቸው የቀሩና ተስፋ የቆረጡ ሰዎችን አይቻለሁ። እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን እንዴት መውደድ እንዳለብህ የሚያስተምር ነው። እግዚአብሔርን መውደድ ያለብን እግዚአብሔር ስለሆነ እንጂ ለእኛ የሆነ ነገር ስለሚያደርግልን አይደለም። በአታላዩ ወጥመድ በመያዝ በቤተክርስቲያን ውስጥ ቁሳዊ ነገሮችን ከመፈለግ ይልቅ እግዚአብሔርን በይበልጥ ለማወቅ ጥማት ይኑርህ። አሁን አሁን የሚሰቀሉ ቢልቦርዶችና ፖስተሮች ቤተክርስቲያን ወይም ፓስተር ለስጋዊ ፍላጐታችሁ ሊያደርጉልህ ስለሚችሏቸው ቁሳዊ ነገሮች አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። ስራ ወይም ልጅ እንዲኖርህ እየፈለግክ ይሆናል። ቢሆንም ግን በአታላዩ ወጥመድ ውስጥ አትውደቅ። ጠላትም ያንተን ፍላጐት የሚያውቅ በመሆኑ በሳልና ጠንቃቃ ካልሆንክ ያታልልሀል። ተስፋ መቁረጥ አንድን ሰው ቀጥታ ወደ ለይጣን ካምፕ ይመራል።

@Amharicbookstore

ፈዋሾች በቤተክርስቲያን

አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያኖቻችን በፈዋሾች የተሞሉ በመሆናቸው በአለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች እነዚህን ፈዋሾች ለማግኘት እንዴት እንደሚመጡ አንሰማለን፣ እናያለን። አንዳንዶች ፈዋሾች የሚፈውሱት የእግዚአብሔርን ኃይል በመጠቀም እንደሆነ ቢናገሩም መጽሀፍ ቅዱስን እንኳን አያውቁም። መንፈሳዊ ፈዋሾች ወይም የእምነት ፈዋሾች ተብለው ከሚጠሩ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ አውቃለሁ። ብዙዎቹ የሚሰሩት በራሳቸው የማማከር አገልግሎት መሸጫ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰሩ ናቸው። ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን ለክርስቶስ ሳይሰጡ ፈዋሹ አንዳንድ መንፈሳዊ ድርጊቶችን ሲሰራ ስማየትና ፈውስ ሰመቀበል ብቻ ወደ ቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች ሲመጡ ማየት እጅግ አሳዛኝ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ፈዋሾችን በአለባበሳቸው እንለያቸዋለን። ምክንያቱም በፈዋሾች የሚለበሱት አንዳንድ የተለዩ ልብሶች የታመሙ ሰዎችን ለመፈወስ የሚያግዙ አጋንንታዊ ኃይል ያላቸው ናቸውና።

የመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የታመሙ ሰዎችን ለመፈወስ እንዴት አይነት አቋቋምና የእጅ እንቅስቃሴዎች እንደሚጠቀሙ እናያለን። አብዛኞቹ ፈዋሾች የአቋቋም አይነቶችና እንግዳ የእጅ እንቅስቃሴዎች በመሰረታዊነት ብመናፍስታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚማሯቸው ናቸው። ፈዋሹ ፈውስ በሚያከናውንበት ጊዜ እንግዳ የሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርገው ፈዋሹ ከመናፍስቱ አምልኮ የሚመጡት ፈዋሽ መናፍስት በሰውነቱ ውስጥ በነፃነት እንዲያልፉ ለመፍቀድ ነው። አጋንንታዊ መንፈሱ ወደ ፈዋሹ ሰውነት ውስጥ

በመግባትና ያንን አካል እንደ መተላለፊያ በመጠቀም ፈውስ፣ ነፃ መውጣትና ትንቢት የሚያከናውነው በዚያ ጊዜ ነው።

አጋንንታዊ መንፈሱ በአጋንንቱ የተያዘውን ሰው ምን እንደሚያደርግ ይመራዋል። በዚያን ጊዜ ፈዋሹ በእጁ የሆነ አጋንንታዊ ምልክት ያሳያል። በአብዛኛው ጊዜ የፈዋሹ አንድ እጅ ወደ ላይ ይነሳና ሌላኛው እጁ ደግሞ በውስጡ ባለው አካል ትዕዛዝ መሰረት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፣ ሌሎች አካላት ደግሞ የተሰቡ ድምፆችን ማሰማት ይመርጣሉ። ከነዚህ የመናፍስት አምልኮ ፈዋሾች ጥቂቶቹ እንግዳ የሆነ ድምፅ ማሰማቱን ይወዱታል። ልክ እነዚህ ድምፆች ሲሰሙ፣ በታው ወይም ክፍሉ በመንፈስ ስለሚነካ ሰዎች መውደቅና ልክ እንደ አውራ አይነት ባህርይ ማሳየትና መሪሀ ይጀምራሉ። ብዚህ ሂደት ውስጥ እየተፀለየላቸው ያሉት ሰዎች ሁሉ በተለያዩ አጋንንቶች ቁጥጥር ስር ይሆናሉ። እነዚህ አጋንንቶች ደግሞ ፈዋሹን ከያዘው በጭካራ አካል ትዕዛዛትን የሚቀበሉ ናቸው።

ፈዋሹ ለታማሚው የሚነግረውን ትእዛዛት ሁሉ አጋንንቶቹ ይታዘዙለታል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በፈዋሹና ታማሚውን በያዙት አጋንንቶች መካከል ጥልቅ መንፈሳዊ የንግግር ልውውጦችን ልትሰማ ትችላለህ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ክርስቲያን መሆን ስለ መዳን እንጂ ከአጋንንታዊ አስተምህሮና እምነት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ነግሯቸዋል። ይህ ማለት አንድ ክቢይ ወይም የመናፍስት አምልኮ መሪ አጋንንቶችን ማውጣት ስለቻለ ያ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ስመሆኑ ማረጋገጫ አይደለም ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈዋሽ በመሆኑ ዛሬም በቃሉ ይፈውሳል።

© Amharicbookstore

ፈዋሾች በቤተክርስቲያን

አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናቶችን በፈዋሾች የተሞሉ በመሆናቸው በአለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች እነዚህን ፈዋሾች ለማግኘት እንዴት እንደሚመጡ እንሰማለን፣ እናያለን። አንዳንዶች ፈዋሾች የሚፈውሱት የእግዚአብሔርን ኃይል በመጠቀም እንደሆነ ቢናገሩም መጽሀፍ ቅዱስን እንኳን አያውቁም። መንፈሳዊ ፈዋሾች ወይም የእምነት ፈዋሾች ተብለው ከሚጠሩ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ አውቃለሁ። ብዙዎቹ የሚሰሩት በራሳቸው የማማከር አገልግሎት መሸጫ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰሩ ናቸው። ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን ለክርስቶስ ሳይሰጡ ፈዋሹ አንዳንድ መንፈሳዊ ድርጊቶችን ሲሰራ ለማየትና ፈውስ ለመቀበል ብቻ ወደ ቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች ሲመጡ ማየት እጅግ አሳዛኝ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ፈዋሾችን ዘለለባለሳቸው እንለያቸዋለን። ምክንያቱም በፈዋሾች የሚለበሱት አንዳንድ የተለዩ ልብሶች የታመመ ሰዎችን ለመፈወስ የሚያግዙ አጋንንታዊ ኃይል ያላቸው ናቸውና።

የመናፍስታዊ አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የታመሙ ሰዎችን ለመፈወስ እንዴት አይነት አቋቋምና የእጅ እንቅስቃሴዎች እንደሚጠቀሙ እናያለን። አብዛኞቹ ፈዋሾች የአቋቋም አይነቶችና አንግዳ የእጅ እንቅስቃሴዎች በመሰረታዊነት ከመናፍስታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚማሯቸው ናቸው። ፈዋሹ ፈውስ በሚያከናውንበት ጊዜ እንግዳ የሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርገው ፈዋሹ ከመናፍስቱ አምልኮ የሚመጡት ፈዋሽ መናፍስት በሰውነቱ ውስጥ በነፃነት እንዲያልፉ ለመፍቀድ ነው። አጋንንታዊ መንፈሱ ወደ ፈዋሹ ሰውነት ውስጥ

በመግባትና ያንን አካል እንደ መተላለፊያ በመጠቀም ፈውስ፣ ነፃ መውጣትና ትንቢት የሚያከናውነው በዚያ ጊዜ ነው።

አጋንንታዊ መንፈሱ በአጋንንቱ የተያዘውን ሰው ምን እንደሚያደርግ ይመራዋል። በዚያን ጊዜ ፈዋሹ በእጁ የሆነ አጋንንታዊ ምልክት ያሳያል። በአብዛኛው ጊዜ የፈዋሹ አንድ እጅ ወደ ላይ ይነሳና ሌላኛው እጁ ደግሞ በውስጡ ባለው አካል ትዕዛዝ መሰረት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፣ ሌሎች አካላት ደግሞ የተለዩ ድምፆችን ማሰማት ይመርጣሉ። ከነዚህ የመናፍስት አምልኮ ፈዋሾች ጥቂቶቹ እንግዳ የሆነ ድምፅ ማሰማቱን ይወዳታል። ልክ እነዚህ ድምፆች ሲሰሙ፣ ቦታው ወይም ክፍሉ በመንፈስ ስለሚነካ ሰዎች መውደቅና ልክ እንደ አውሬ አይነት ባህርይ ማሳየትና መጮህ ይጀምራሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ እየተፀለየላቸው ያሉት ሰዎች ሁሉ በተለያዩ አጋንንቶች ቁጥጥር ስር ይሆናሉ። እነዚህ አጋንንቶች ደግሞ ፈዋሹን ከያዘው ጠንካራ አካል ትዕዛዛትን የሚቀበሉ ናቸው።

ፈዋሹ ለታማሚው የሚነግረውን ትእዛዝት ሁሉ አጋንንቶቹ ይታዘዙለታል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በፈዋሹና ታማሚውን በያዙት አጋንንቶች መካከል ጥልቅ መንፈሳዊ የንግግር ልውውጦችን ልትሰማ ትችላለህ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ክርስቲያን መሆን ስለ መዳን እንጂ ከአጋንንታዊ አስተምህሮና እምነት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ነግሯቸዋል። ይህ ማለት አንድ ነቢይ ወይም የመናፍስት አምልኮ መሪ አጋንንቶችን ማውጣት ስለቻለ ያ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ስለመሆኑ ማረጋገጫ አይደለም ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈዋሽ በመሆኑ ዛሬም በቃሉ ይፈውሳል።

@Amharicbookstore

መንፈሳዊ ማታለያ

መንፈሳዊ ማታለያ አንድ ቤተክርስቲያን ወይም የቤተክርስቲያን መሪ በመንፈሳዊ ቁጥጥር ስር መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን የመናፍስታዊ አምልኮ እንቅስቃሴ አካል በነበርኩበት ጊዜ የቤተክርስቲያን ተከታዮቻችንን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ለተከታዮቻችን መንፈሳዊ ማግኔቶች እንድንሰጥ ይነገረን እንደነበረ አስታውሳለሁ። እነዚህ መንፈሳዊ ማግኔቶች በተለያየ ቅርፅና አይነት የሚመጡ ቢሆኑም ዋና አላማቸው መንፈሳዊ ማታለያ መሆን ነው። በመናፍስታዊ አምልኮ ቡድን ያሉ ብዙ ፓስተሮች ፎታቸው ያለበት የቤተክርስቲያን ቀን መቁጠሪያ ካላንደር፣ ፎታቸው ያሰበት የቤተክርስቲያን ቲ-ሸርትና የቤተክርስቲያን የእጅ አምባሮችን ይጠቀማሉ። ከአካላዊ አይታ አንፃር እነዚህ ነገሮች ንፁህ መስለው ቢታዩም ሀሰተኛ ነቢያት ተከታዮቻቸውን የእጅ አምባሮቹ መንፈሳዊ ቁጥጥር ማድረጊያ እንደሆነ በመንገር ያታልሏቸዋል። እኔ በገሌ የቤተክርስቲያኑ መሪ ምስል ያለባቸው ስቲከሮች ተሰጥተዋቸው የፓስተሩ ፊት አጋንንቶችን እንደሚያባርርና እነርሱንም ከየትኛውም አይነት ጉዳት እንደሚከላከልላቸው የተናገራቸውን አማኞች አይቻለሁ።

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የትኛውም ቦታ ላይ አጋንንት ሚች የሆነ ሰው እንደሚፈሩ አልተነገረንም። የማንም ፊት አጋንንትን ማስፈራራት አይችልም። በቤተክርስቲያን ስም ጥቅም ላይ የሚውሉ ውሀ፣ ዘይትና ሌሎች ፊሳሾችም የሚጠቀሟቸው ሰዎች መንፈሳዊ

መሪውን ከእግዚአብሔር የበለጠ እንዲፈሩት ለማድረግና በመሪው ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ በማስፈራራት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው።

የመናፍስት አምልኮ ተከታዮች መንፈሳዊ መሪያቸውን ከራሳቸው አብልጠው የሚወዱት ለምን እንደሆነ አስባችሁ ታውቃላችሁ? በቤተክርስቲያን በሚሰጡ ወይም በሚሸጡ የተአምርና መንፈሳዊ ዕቃዎች በሚመጡ መናፍስት ምክንያት ነው።

ሶስተኛው አይን በመናፍስታዊ አምልኮ

ሀሰተኛ ነቢይ ሆኜ እሰራ በነበረበት ጊዜ የጸሎት ቤተክርስቲያን ወይም በዚያ አካባቢ ያለ የፀሎት ሰው ፍለጋ መላውን መንደር ወይም አካባቢ አስስ ነበር። ለመናፍስቱ አሰራር እንቅፋት የሆኑ ቦታዎችን ከለየን በኋላ የእነዚያን እንቅፋቶች ስሞች እንፈልጋለን። ያ እንቅፋት የሆነ ቦታ ወይም ሰው ከተገኘ በኋላ ያ እንቅፋት ካለበት ቦታ አፈር ዘግነን ማምጣታችንን እርግጠኛ መሆን ይኖርብናል።

ቀጥሎ እነዚያ የተገኙት ስሞች በመናፍስት አምልኮ ቡድኑ ድግምት እንዲዘጋጅላቸው ወደ ቡድኑ ይላካሉ። ይህ ድግምት የሚዘጋጀውና የሚሰራጨው በ12 የመናፍስት አምልኮ አባላት ነው። በእኛ የመናፍስት አምልኮ ቡድን ውስጥ ሰተለያዩ ግለሰቦች የተመደቡ የተለያዩ ደረጃዎች አሉን። በተጨማሪም የምንታወቅባቸው የሚስጥር ስሞችም አሉን። እኔም ካታ-ካታ የሚል ስም ተሰጥቶኝ ነበር። ድግምት የመስራት ሀላፊነት የአስራሁለቱ ዋና ዋና የመናፍስት አምልኮ አባላት ብቻ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። 12ቱ ዋና ዋና

@Amharicbookstore

አባላት ሙሉውን የመናፍስት አምልኮ ኡደት የያዙ ናቸው። በመናፍስታዊው፣ በአስማታዊውና በእምልኪዊው አሰም 12 ቁጥር ከሂሳብ ቁጥር በላይ ነው። ሙሉ ኡደቱ የሚሟላበት መንፈሳዊ ምልክትም ነው። ለአታችን ሙሉ ኡደት ያሰው 12 ቁጥሮች ይሟል። የቀን መቁጠሪያችን 12 ቀናት አሉት። አንድ ሙሉ ቀን 12 ሰዓት ቀንና 12 ሰዓት ምሽት አሉት። ስለዚህ ድግምት መስራት የአሰራ ሁሰቱ ዋና ዋና የመናፍስቱ አምልኮ አባላት ድርሻ ነው። ፀሎት በሚደረግበት ቤተክርስቲያንና ፀሎት በሚያደርግ ክርስቲያን ላይ ከምናስደግማናቸው ድግምቶች ዋነኛው መንፈሳዊ አይኖቻቸው እንዲዘጉ ማድረግ ነበር።

በመናፍስታዊው አምልኮ አለም መንፈሳዊ አይን የሚጠራው ሶስተኛው አይን በመባል ሲሆን የሚገኝውም በሰው ግንባር ላይ በሁሰቱ አይኖቹ መካከል እንደሆነ ይታመናል። አንድ ነቢይ "አይኖቼ ሲዘጉ አያለሁ፣ አይኖቹ ሲከፈቱም አያለሁ" ሲል ስትሰማ የሚናገረው ስለዚህ ሶስተኛው አይን እንደሆነ ማወቅ አሰብህ።

በመሆኑም አብዛኞቹ የመናፍስት አምልኮ አብያተ ክርስቲያናት ሎጐዎችና ምልክቶች ሩቅና ቅርብ የሚያየው ይህ አይን ያላቸው ናቸው። በዘመናዊው አለም ሶስተኛ አይን የተከፈተን ሰው ለመግለጽ በጣም የሰለጠነ፣ "ብርሃን የበራለት" የሚል ቃል እንጠቀማለን። እንደ ቤተክርስቲያን ወይም ክርስቲያን እንደመሆናችን እግዚአብሔር መንፈሳዊ አይኖች ሰጥቶናል። እኔ መንፈሳዊ ንግግሮችንና ሴሚናሮችን ሳደርግ፣ ሁልጊዜ እግዚአብሔር ለልጆቹ የዲያብሎስን ማታለያዎች እንዲሰዙና መሰኮታዊ የሆነውን ማየት እንዲችሉ

መንፈሳዊ አይኖቻቸውን እንዴት እንደሚከፍትና እንዲጠቀሙ እንደሚያደርግ አስተምራለሁ።

በመናፍስታዊ አምልኮ ሰዎች ሶስተኛ አይን ብለው የሚጠሩትን ሲጠቀሙ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ደግሞ እምነት እንጠቀማለን፣ ሁለቱ ግን ተመሳሳይ አይደሉም። የሚፀልይ ሰው ወይም ቤተክርስቲያን ማወቅና ማግኘት አስፈላጊ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ አንድ ቤተክርስቲያን የሚፀልይ ከሆነ፣ በዚያ መንደር ወይም አካባቢ የመንግስተ ሰማያት ውክልና ያለው ይሆናል ማለት ነው። ያ ቤተክርስቲያን ትልቅ ወይም ብዙ ተከታዮች ያሉት ባይሆንም እንኳን የሚፀልይ በመሆኑ በመንፈሳዊው አለም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሊሆን ይችላል። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊው አለም ተፅዕኖ ፈጣሪ ከመሆን ይልቅ የሚያስቡት ስለ አብያተ ክርስቲያናቱ በብዙ ሰዎች መሞላትና ታላቅ ጉባኤ ማድረግ ነው። ዲያብሎስ የሚፈራው ፅኑ፣ የሚፀልይ ቤተክርስቲያንና እምነት ያሰው ሰው እንጂ ብዙ ቁጥር አይደለም።

ብዙ ሰዎች በቤተክርስቲያን የነበረኝን ተሞክሮ ሲሰሙ የልብወለድ ፊልም እንደሚመስል ይነግሩኛል። እኔም ሁልጊዜ የዳንኩት በእግዚአብሔር ፀጋ እንደሆነ እነግራቸዋለሁ። የሰዎች መንፈሳዊ አይኖች የሚከፈቱት በፀሎት እንደሆነ ስለሚያውቁ፣ የመናፍስት አምልኮ መሪዎች ለነዚህ የሚፀልዩ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ለሚፀልዩ ሰዎች መንፈሳዊ እውርነት ብለን የምንጠራውን እርግማን መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃሉ።

@Amharicbookstore

መንፈሳዊ እውርነት የጨለማው መንግስት በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚጠቀምበት መሳሪያ ነው። በመንፈሳዊ እውር መሆን፣ የሚፀልዩ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸውን ማየት እንዲሳናቸው በማድረግ የፀሎታቸውንም ምላሽ በአይን በሚታይ ተአምራትና ፈውስ መልክ ብቻ ለማየት እንዲጠብቁ ያደርጋል። በህይወታቸው የትኛውን አቅጣጫ መያዝ እንዳለባቸው እንዳያዩ እንዲሁም ትክክለኛ የህይወት አጋራቸው ማን እንደሆነ ማየት እንዳይችሉ ማድረግን ያጠቃልላል።

የዚህ መንፈሳዊ እውርነት እርግማን በጣም አስፈሳጊ ምክንያት ክርስቲያናች በቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች ወይም በሌሎች ሀይማኖታዊ ስብሰባዎች ላይ የሚደረጉትን የመናፍስታዊ አሰራር ምልክቶች እንዳያዩ ለማድረግ ነው። ይህ መንፈሳዊ እውርነት እርግማን የሚሰራው ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ ነው። ምክንያቱም በጥንቃቄ ከተደረገ ማንም ሰው በዚያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰራውን እውነተኛ አጋንንታዊ መንፈስ ማየት ወይም ማወቅ በማይችልበት ሁኔታ መናፍስታዊ አሰራርን በመጠቀም ተአምራት፣ ፈውስ፣ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን መስራት ስለሚያስችል ነው።

ብዙ የመናፍስት አምልኮ ተከታዮች በቤተክርስቲያን ውስጥ በአይኖቻቸው ፊት የሚደረጉ መንፈሳዊ አደጋዎችን ማየት ወይም መስማት የማይችሉት በነዚህ አጋንንታዊ ድግምቶች ኃይል ምክንያት ነው። አንዳንዶቹ የሚሰሙት በእነርሱ ላይ መንፈሳዊ እውርነት የሳከውን ሰው ድምጽ ብቻ እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል አይደለም። መንፈሳዊ እውርነት ከሚሰሪባቸው ምክንያቶች አንዱ ድግምቱን ለመስራት ጥቅም ላይ ከሚውለው ንጥረ ነገር የተነሳ ነው።

በሚስጥራዊ ማህበሩ ውስጥ ይህንን ድግምት ለመስራት የጉጉትና የሴቲት ወፍ አይኖችን ይጠቀማሉ። እነዚህ አይኖች አመድ እስኪሆኑ ድረስ ይቃጠሉና የሚፀልየው ሰው ወይም ቤተክርስቲያን ስም የተላፊበት ወረቀት ከተቃጠለበት አመድ ጋር ይቀላቀላል። ከዚያ ቀጥሎ ይህ የተቀላቀለ አመድ ከአፈር ጋር በመደባለቅ ይዘጋጃል።

ይህ መንፈሳዊ እውርነትን እንዲያመጣ የተሰራው ጹቁት ከተዘጋጀ በኋላ 12ቱ ዋና ዋና የመናፍስት አምልኮው አባላት ኢላማ የሆነውን የሚፀልይ ቤተክርስቲያን ወይም ክርስቲያኖች ስም በመጥቀስ የሃራሳቸውን ኃይል ይለቃሉ። ይህ አይነት ድግምት የሚሰራው በቀን ነው። ምክንያቱም እነዚህ ወፎች የሚተኙት በቀን በመሆኑ ነው። ይህ ማለት ቀን ሲሆን አይናቸው ሰለማያይ የእነርሱን አይኖች በመጠቀም የሚሰራው ድግምት ኢላማ የተደረጉትን ሰዎች ወይም አብያተክርስቲያናት መንፈሳዊ እንቅልፍ ውስጥ እንዲወድቁ ያደርጋል።

መንፈሳዊ እውርነት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሰፀሎት የሞቱ ያደርጋቸዋል። ድግምቱ ከተዘጋጀ በኋላ አመጻ ይወሰድና በአራቱም አቅጣጫ ይበተናል። ይህ የእርግማን ጹቁት በአራት አቅጣጫዎች የሚበተነው ዩኒቨርስ አራት መግቢያዎች ስላሉት ነው። እነዚህ መግቢያዎች ደግሞ መንፈሳዊ ሀይላት ወደ አለም እንዲገቡ የሚያደርጉ አመላላሾች ናቸው። መንፈሳዊ ብርሃን ያላቸው ሰዎች በምድር ላይና በሰውነታችን ውስጥ አራት ነገሮች ያሉት ለምን እንደሆነ ይረዳሉ። ጥንቆላ ወይም መናፍስታዊ ማታለል የሚሰሩ ሰዎች እነዚህ አራት ነገሮች ማለትም እሳት፣ ውሀ፣ ነፋስና አፈር (መሬት) እንድን እርግማን በዚህ አለም ውስጥ የትኛውም ቦታ መሄድ እንዲችል ማጓጓዝ እንደሚችሉ ያውቃሉ። አብዛኞቹ የመናፍስት

@Amharicbookstore

አምልኮ ነቢያት ሰለእነዚህ አራት ነገሮች አፅንኦት ሰጥተው ይሰብካሉ። ይህ የሚደረገው ደግሞ ውሀን ለማመልከት የመናፍስት አምልኮ ውሀ ይሸጣሉ፣ እሳትን ለማመልከት አንዳንድ ጊዜ ሻማ የማብራት ስርዓት ያካሂዳሉ፣ አየርን ለማመልከት አዋጆችንና ትዕዛዛትን በመጮህ ይናገራሉ፣ መሬትን ለማመልከት ደግሞ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ነቢያት ለምኞን ከቤታቸው አፈር እንዲያመጡ ይጠይቃሉ። እነዚህን አራት ነገሮች ከሚጠቀሙ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ከሆንክ እነዚህ አራት ነገሮች በመናፍስታዊ አምልኮ ቡድን ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆናቸውን ማስታወስ ይኖርብሀል።

ምዕራፍ አስራ ሶስት

ከማዕበል በኋላ የመመለስ ሂደት

በቁጥጥር ስር መዋል

2012 የነቢይ ካታካታን ስራ ሙሉ በሙሉ የሰወጠ አመት ነበር። ብቻዬን የገነባሁት የነቢይ ካታካታ ግዛት ልክ ሙሉ በሙሉ በሰደድ እሳት እንደተቃጠለ መስክ ሁሉ ነገር በድንገት ከሰመ።

በማህበረሰባችን ውስጥ በተፈጠረ የአክል ማጉደል ቅሌት ተጠርጥሬ በቁጥጥር ስር ዋልኩ።

በቁጥጥር ስር የመዋሌ ዜና በአካባቢውና በቤተክርስቲያን ሲሰራጭ ዜናው በሚያውቁኝም፣ በማያውቁኝም ዘንድ የቀን ተቀን ወሬና አሉባልታ ሆነ። በቁጥጥር ስር በዋልኩበት ቀን ሁሉም ነገር ልክ እንደሌሎቹ ቀናት በታቀደው መንገድ እየሄደ ይመስል ነበር።

@Amharicbookstore

ተገልጋዮቼ ወረፋ ለመያዝ የመጡት ጠዋት 10:00 ጀምሮ ነበር። ሌሎች ደግሞ ተአምራት ለመቀበል ከሌሎች ግዛቶችና ከጉረቤት ሀገራት ተጉዘው መጥተው ነበር። ሰራው በአካባቢው የሚኖሩ ሙዚቀኞችን፣ ባለስልጣናትን፣ ፖለቲከኞችን፣ ባህላዊ መሪዎችንና ቤተክርስቲያናት መሰራቾችን ሳይቀር ዕለት ተዕለት የሚሰብ ነበር። የግል ረዳቶቼ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጡና የክትትልና የምክር አገልግሎት ፊላጊ ተገልጋዮችን ብዛት አስታወቁኝ። ለመንፈሳዊ አላማ የሚሆነውን በተሰየ ሁኔታ የተሰራ ቀይ ባህላዊ የክብር ልብስ ሰብሼ ነበር። ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ኃይላት የተከማቹበትና ማንም እንዲገባ ወደማይፈቀድለት መሰዊያ ክፍል ገባሁ።

ስምንት ገደማ የሚሆኑ መሰዊያዎች ያሉኝ ሲሆን ከተለያዩ ቦታዎች ተጉዘው መንፈሳዊ እርዳታ ለማግኘት ወደ ቢሮዬ ለሚመጡ ሰዎች ልዩ የትንቢትና ፈውስ ኃይል ለመጠየቅ ለእያንዳንዱ አማልክት በመሰዊያው ፊት በየግለሰቡ መንበርከክ አለብኝ። ሰዓቱ ለመናፍስታዊ ኃይላት ፀሎት የማደርግበት ጊዜ በመሆኑ ከአማልክቱ ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። ቀደም ካለው ቀን የተሰበሰበው ገንዘብ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በዚሁ ክፍል ውስጥ ከመሰዊያዎቹ አጠገብ መቀመጥ አለበት። ምክንያቱም ሁሉም ገንዘብ የተገልጋዩን እድል የያዘ እንደሆነና ስጪው ሁልጊዜ እንዲሰጥ ወይም እንደ ራስ ምታት እይነት ቀላል ነገሮች ሲያጋጥሙት እንኳ ሁልጊዜ ወደ ምክር አገልግሎት መስጫ እንዲመጣ የሚያደርገው ገንዘቡ ውስጥ ያለው እድል እንደሆነ ተምሬያለሁ።

ብዙ ረዳቶቼ ማንም አያውቅም ብለው በማሰብ ገንዘብ ሲሰርቁ ይሞክራሉ። ነገር ግን ከረዳቶቼ አንዱ ከነዚህ መሰዊያዎች ገንዘብ ቢሰርቅ መናፍስቱ ገንዘባቸውን የሰረቀው ማን እንደሆነ ይገልጣሉ። ወንጀለኛው ቀኑ ከማለቁ በፊት መናዘዝ እምቢ ካለ፣ የፈፀመውን እምነት የጉደለው ድርጊት እስኪናዘዝ ድረስ የሆነ መጥፎ ነገር ይከሰትበታል።

በዚያ ቀን ሶስት የአካባቢው የፖሊስ አባላት መጡና አሁን የሁሉም ቤተሰብ መለያ የሆነውን ስም በመጥራት ነቢይ ካታሓታን ለማየት ጠየቁ። ፖሊሶቹ የምክር አገልግሎት ወደሚሰራበት ክፍል ሲገቡና አይኖቼ ከአይኖቻቸው ጋር ሲገናኙ በእነርሱ መምጣት መጥፎ ስሜት ተሰማኝ። ነገር ግን በአማልክቶቼ ስለምተማመንና በየቀኑ በእነርሱ ጥበቃ ስር እንደሆንኩ ስለማውቅ ምንም እንደማልሆን ገብቶኛል። ፖሊሶቹ ራሳቸውን ካስተዋወቁ በኋላ ሙሉ ስሜን እንድናገር ሲጠይቁኝ ነቢይ ካታሓታ መሆኔን ነገርኳቸው። እንደኛው ፖሊስ የሚፈልጉት መታወቂያዬ ላይ የተፃፈውን እውነተኛ ስሜን እንደሆነ ሲነግረኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ውጪ ወረፋ እየጠበቀ እንዳሉት ሰዎች ተራ ሰው መሆኔ ተከለተልኝ። ሙሉ ስሜን ነገርኳቸው። ከዚያ በአካል መጉደል ወንጀል ተጠርጣሪ እንደሆንኩና ባህላዊውን የክብር ልብስ እንድቀይር ነገሩኝ። ኃይል ወዳለበት ክፍል ገብቼ ስምንቱን መሰዊያዎች ስመለከት አይኖቼ በእምባ ተሞልተው ያሳለፍኩትን ወደኋላ መቃኘት ጀመርኩ።

በዚህ መናፍስታዊ አሰራር ውስጥ ከገባሁ ጊዜ ጀምሮ ወደ ቤተክርስትያን የምሄደው ብቻዬን እንጂ ከቤተሰቤ ጋር አልነበረም።

@Amharicbookstore

ምክንያቱም ከመሄዴ በፊት እኩሰ ሴሊት ላይ በአቅራቢያዬ ባለው ወንዝ ውስጥ በተሰጠኝ ሳሙና መታጠብ፣ 'አሼ' የሚባለውን የአሰማት መድሀኒት ምላስ ላይ መቀባት፣ በመስዊያዎቼ ላይ የእንሰላ መስዋዕት ማቅረብ ይጠበቅብኛል። ይህንን ሁሉ ለማድረግ ደግሞ በአብዛኛው ቤት ውስጥ ብቻዬን መሆን ስለሚናርብኝ ባለቤቴ ከሄደች በኋላ ዘግይቼ ለመሄድ እገደድ ነበር። የምዘገይበት ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ፀሎትና አምልኮ በሚደረግበት ጊዜ ጉባኤው የሚፀልይበት መንፈስና እኔ ላይ ያለው መንፈስ ተቃራኒ በመሆናቸው ወደ ቤተክርስትያን መግባት የምፈልገው ጸሎትና አምልኮ ካለቀ በኋላ ነበር።

ክፉ መናፍስት አብዝቶ መስዋዕት በቀረበላቸው ጊዜ የበለጠ ኃይል እንደሚያገኙ ስለተነገረኝ በቀን ቢያንስ ሶስት ጊዜ መስዋዕት አቀርብ ነበር። መስዋዕት ሳቀርብላቸውና ስለግድላቸው የነበሩት መናፍስት አሁን እኔን መስዋዕት እያደረጉኝ ነው። የፖሊስ ካቴና እጄ ላይ ሲገባ ነው። መናፍስቱ ግን ምንም እያደረጉ አይደለም። ያመንኳቸው፣ ያገለገልኳቸው መናፍስት ከፖሊስ አይን ሲሰውሩኝ አልቻሉም። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ስሜ ጠፍቶ ልዋረድ ነው። መናፍስቱ እንዴት የእኔ የአገልጋያቸውን መዋረድ ዝም ብለው እንደሚያዩት ሊገባኝ አልቻለም። ስሜ በፖሊሶቹ ሲጠራ ሰምን በራሴ ላይ ይህ እንዲሆን እንደፈቀድኩ ራሴን እየጠየቅኩ እጄ ላይ ካቴና ሲገባ አንገቴን ልደፋ ወደ መስዋዕቱ አመራሁ።

ልብሴን ቀይሬ እንደጨረስኩ ፖሊስ ቦክቴና አሰረኝና በቁጥጥር ስር እንደዋልኩ ነገረኝ። ከቤት ወጥቼ በአገልጋዮቼ ረድም ስልፍ

አልፌ ስሄድ እጆቼ ወደኋላ ታስረው ከተገልጋዮቼና ከሰራተኞቼ ጋር ስጋፈጥ ፊቴ በሀፍረት ተሞልቶ ነበር። እንደ እድል ሆኖ ይህ ነገር ሊከሰት ሚስቴ ሰራ ነበረች። በፖሊስ መኪና ውስጥ ንብቼ እንደሄድኩ አንድ ክርስቲያን ነቢይ አካል በማጉደል በቁጥጥር ስር ዋለ የሚለውን ዜና በፍጥነት በመሰራጨቱ ፖሊስ ጣቢያ ስንደርስ ብዙ ሰዎች ይህ በአካል ማጉደል ወንጀል የተከሰሰው ነቢይ ማን ነው ብለው ለማየት ተሰብስበው ነበር። ወደ ማረፊያ ቤት አስገብተውኝ የብረት በሩ ሲቆለፍ ሰሰማ አሁን ህይወቴ በሁኔታዎች የተዘጋ እንደሆነ አወቅኩ። ወዲያው ጉዳዩ ብሄራዊ ፍላጎት ያሳደረ ሆነና የዜና ማሰራጫዎችን ትኩረት በመያዙ በባቡር፣ በአውቶቡሶች፣ በስብከት ቦታዎች፣ በገበያ ማእከላት፣ በቀብር ቦታዎች፣ በሰርጎችና በየትኛውም ሰው በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ሁሉ መነጋገሪያ ሆነ።

ከዚያ ወደ ሌላ ማረሚያ ቤት እንድዛወር ተደርጌ አሁንም አሁንም ወደ ፍርድ ቤት መመላለስ ጀምርኩ። በፖሊስ መኪና ተጭኜ ወደ ፍርድ ቤት በሄድኩ ቁጥር ነፍሰ ጡር ሚስቴንና ልጀን ወደተውኩበት አካባቢ ስደርስ በመኪናው መስኮት አሻግሬ እመለከት ነበር። በእውነታው እንደተያዝኩ አውቄያለሁ። ከነቢይነትና መናፍስታዊ ስሞችና ማዕረጎች ጀርባ የነበረው ሰው አሁን "ማንም" አይደለም።

በተከሰስኩበት ጥፋት ወንጀለኛ እንዳልሆንኩ ባውቅም በሰው አይን ግን ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት እንኳን ጥፋተኛ ነበርኩ። ብዙ ሰዎች ክሱ የእውነት መሆኑን በማመናቸው ራሳቸውን ከእኔ ስላራቁ፣ ድጋፍና ጥንካሬ ይሰጡኝ የነበሩት የቅርብ ቤተሰቦቼ ብቻ ነበሩ። ይህ

@Amharicbookstore

በህይወቴ ከነበሩት ሁሉ እጅግ አስደንጋጩ ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ እጅግ ትደግፈኝ የነበረችው በንብይነት ስራ ምክንያት ችላ ብያት የነበረችው ባለቤቴ ብቻ ነበረች። ሻንጣዎቿን ሰብስባ ወደ ቤተሰቦቿ ለመመለስ በቂ ምክንያት የነበራት ቢሆንም፣ እሷ ግን በህይወቴ ዝቅተኛው ነጥብ ላይ በነበርኩበት ጊዜ ሳይቀር ደገፈችኝ።

ማረሚያ ቤት

በማረሚያ ቤት በነበርኩበት ወቅት ብራ ስፔንዘር ከሚባል ሰው ጋር ተወዳጀሁ። ይህ ሰው በታሰረበት ጉዳይ ምክንያት በሌሎች ታራሚዎች የሚፈራ ነበር። ምክንያቱም ታራሚዎች ሌሎች ታራሚዎችን የሚፈሩት በጉዳያቸው ክብደት መሰረት ነው። ብራ ስፔንዘር ራሱን አስተዋውቆኝና በደረቱና በክንዶቹ ላይ ያሉትን ንቅሳቶች እያሳየኝ ራሴን እንዳስተዋውቅ ጠየቀኝ። ፓስተር እንደሆንኩና በአካባቢያችን በተከሰተ አካል ማጉደል ተጠርጣሪ ሆኜ እንደታሰርኩ ነገርኩት። ወዲያው ብራ ስፔንዘር ህይወቴን ሙሉ የማልረሳው አንድ ጥያቄ ጠየቀኝ።

"ፓስተር ቤተክርስቲያን ውስጥ ሆኖ የጌታን ወንጌል ማሰራጨት ሲገባው አንተ ማረሚያ ቤት ውስጥ ምን ትፈልጋለህ?" ነበር ያለኝ።

ሁልጊዜ የተሳሳተ ቦታ ላይ እንደሆንኩና በእንደዚህ አይነት አካባቢ መኖር እንደማልችል ደጋግሞ ይነግረኝ ነበር። ማረሚያ ቤት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የማሳልፈው በማሰብና እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ ለመጠየቅ በመፀለይ ነበር። ማታ እንቅልፍ ለመተኛት

እንዴት እንደምታገልና ሌሊቱን ሙሉ እግዚአብሔር እንዲጠብቀኝ ስፀልይ አሳልፍ እንደነበር አስታውሳለሁ። ለራሴ ጠንካራ መሆን እንዳለብኝ አውቂያለሁ። ብዙ ታራሚዎች ፓስተር መሆኔን ስሳወቁ ስለግል ህይወታቸው ለእኔ ለመንገር ቀላል ሆኖላቸው ነበር። እኔም የፓስተርነት ክህሎቴን በመጠቀም እመክርና ለሌሎች እፀልይ ነበር። ማረሚያ ቤት ውስጥ ምንም አይነት የሀሰት ቅዱስ ዘይት ወይም ውሀ ሳልጠቀም ለሌሎች ታራሚዎች ተስፋና መመሰል ስመሰጠት ከጌታ ያገኘሁትን የማበረታቻ ቃላት አጠቀም ነበር። ለጥቂት ወንጀለኞች እንዴት በየቀኑ መፀለይ እንዳለባቸውና በህይወታቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መናገር እንዳለባቸው አስተማርኩ። በነቢይ ማታለያ ዘዴ ሳይሆን በየምሽቱ በማረሚያ ቤት ክፍሎቻችን በአንድ ላይ በምናነብው መጽሀፍ ቅዱስ በማመናቸው ምክንያት አንዳንድ ታራሚዎች ከክሶቻቸው ነፃ ሆኑ። እሁድ እሁድ እርስ በርስ የምንበረታታበትና የእግዚአብሔርን ቃል የምንማማርበት የራሳችን ፕሮግራም ነበረን።

ማረሚያ ቤት የቆየሁበት ጊዜ አጭር ቢሆንም የማረሚያ ቤት ህይወት በጣም ቀስ ያለና ጭንቀት ያለበት በመሆኑ ለረጅም ጊዜ እዚያ የቆየሁ አይነት ስሜት ይሰማኝ ነበር። በማረሚያ ቤት የነበረኝ አጭር ጊዜ ዝነኛ ከመሆንና ሚች በሆኑ ሰዎች ዘንድ ኃያል ሆኖ ከመታየት በላይ የሆነ ህይወት እንዳለ አስተምሮኛል። ብራ ስፔንዘር "ሁልጊዜም ወደ እስር ቤት ቡሮች መግባት ቀላል ነው፣ መውጣት ግን አመታት ሊወስድ ይችላል።" ብሎ ነገረኝ። እነዚህ ቃላት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝን ቅርበት እንዳስታውስና ጣልቃ የሚገባ መሆኑን መተማመኔን እንድቀጥል አደረገኝ።

@Amharicbookstore

ማጠቃለያ

ከተከሰስኩበት ወንጀል ነፃ ብተለቀቅኩበት ቀን ሁለተኛ ልጃችንን ነፍሰጡር የነበረችው ባለቤቴ የዚያን ጊዜ ጥሩር ብሎ አገልፀው ከነበረው ሰው ጋር በመሆን መጣች። ሚስቱ ዝርጥታና ከስታ ነበር። በወደቀብኝ ቅሌትና ሀፍረት ድካምና ጭንቀት ተፈጥሮባት እንደሆነ አውቂያለሁ።

ባለቤቴ እንግዳ የሆኑ ባህርያትን ማሳየት ስጀምርና ብቻዬን የምጠቀምበት የመናፍስቱ መገልገያ ክፍል ሳዘጋጅ እንዲሁም የመንፈስ ኃይል ለመቀበል አፍሪካን ስዞር በትክክል እያደረግኩ ያለሁትን ነገር ባታውቅም ከፍተኛ ጥርጣሬ ስለነበራት አብዝታ በመምከር ወደ ትክክለኛው መሰመር እንድመሰሰ ታግላ ነበር። ከእኔ በእንቢታ መፅናት በኋላ ግን *መጋደላችን ከሲጋና ከደም ጋር* አይደለም ብላ ይመስለኛል በራሷ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ግንኙነት በማጥበቅ በፀሎት መትጋቷን ቀጥላ ነበር። ሌላ ሴት ብትሆን እርግጠኛ ነኝ ጥላኝ ትሄድ ነበር እንጂ ይዟን ሁሉ ጉድ ተሸክማ አትቆይም ነበር። እሷ ግን በትክክለኛው መንገድ እግዚአብሔርን ለማገልገል መጠራቱን በሙሉ ልቧ ታምን ስለነበር አንድ ቀን እንደምመለስ እርግጠኛ ነበረች። ይሁንና በዚህ አይነት ሀፍረት ውስጥ በሚኸት መንገድ ይሆናል ብላ ግን የምትጠብቅ አይመስለኝም። ስሜ ጠፍቶ ስአስር መዳረጌ ቅስሟን ሰብሮ እንዲህ እንድትገረጣ ቢያደርጋት አይደንቅም።

እንዲህ አይነት ነገር ሲከሰት አብዛኞቹ የቤተክርስቲያን አባላት ቤተክርስቲያኑን ይለቃሉ። አንዳንዶቹ ሌሎች ተአምራትን የሚሰሩ

ነቢያትን የሚከተሉ ሲሆን ጥቂቶች ደግሞ እስክሞራሹ ቤተክርስቲያን መሄድ ያቆማሉ። ሰዎች አንድ በአንድ ራሳቸውን ከእኔ ማራቅ ሲጀምሩ፣ ያስኝ ቤተሰቤ ብቻ እንደሆነ አወቅኩ። ነቢይ ብነበርኩበት ወቅት ያፈራኋቸው ጓደኞቼ ሁሉ ጠፉ። ጥቂት የቤተክርስቲያን አባላት ለጥቂት ጊዜ ከእኛ ጋር የቆዩ ቢሆንም በመጨረሻ ብዙዎቹ ሄደው የራሳቸውን ኑሮ በመቀጠላቸው ስለአብዛኞቹ ቁራሽ ሰምቼ አላውቅም። ነቢይ ካታካታ ሆኜ እሰራ ብነበርበት ጊዜ ለቤተሰቤ በተለይ ለባለቤቴ ጊዜ አልነበረኝም። ሁልጊዜም የምነር አገልግሎት በመስጠት በስብሰባ ወይም በቤት ለቤት ጉብኝት ስራ ይበዛብኝ ስለነበር ቤተሰቤ ትንሽ ፀትንሽ ከሀይውቱ እየጠፋ ነበር። በወቅቱ ብዙ ተጨማሪ ሚስጥራዊ ኃይላትን ለማግኘትና የራሴን ዝና በመገንባት ላይ ተጠምጄ ነበር።

ከስልኮቻቸውና ከማህበራዊ ገፆቻቸው ላይ የሰረዙኝ እነርሱን ለማስገረም ጊዜዬን የሰዋሁባቸው ሰዎች ነበሩ። ሌሎች ደግሞ በመንገድ ላይ ወይም በገበያ ማዕከላት ሰንገናኝ ሲጨብጡኝ እንኳን አይፊልጉም ነበር። በአንድ ወቅት እንደ ጀግና ሲያዩኝ በነበሩት ሰዎች የተገለልኩ ሆንኩ።

አንድ ቀን አንድ በአድሜ የገፋ ጋስተር ደውሎልኝ ከጭንቅላቴ በላይ በጣም ትልቅ የሆነ ጥቁር ደመና ሲከተለኝ ራዕይ እንዳየና ያንን ጥቁር ደመና ለማስገወድ አመታት ሊፈጅ እንደሚችል እንደተሰማው የነገረኝን አስታውሳለሁ። ደመናው ለዘላለም በእኔ ላይ እንደሚሆን ገምቶ ነበር።

@Amharicbookstore

ከማረሚያ ቤት የተለቀቅኩ ቢሆንም ግን አሁንም በሰዎች አእምሮ ውስጥ በተሰይም በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ እንደተቀስፈብኝ ነበር። አዲስ ጅማሬ እንደሚያስፈልገኝ ያወቅኩ በመሆኑ እንደ አዲስ ለመጀመር ብዙጋጅም ማንም ሰው በህይወት ሁለተኛ እድል ሊሰጠኝ የፈለገ አይመስልም። ከማረሚያ ፍርድ ቤት ካገኘሁት ተሞክሮ በኋላ ከመደሰትና የተለባበረ ህይወቴን ከመጠገን ይልቅ አስከፊ ድብርትና እንቅልፍ ማጣት ውስጥ በመውደቄ ራሴን የማጥፋት ሀሳብ ሳይቀር አድሮብኝ ነበር። የመገለል ስቃይ ሰብሮኝና ብቸኛ አድርጉኝ ነበር። አንድ ቀን ባለቤቴን ቤተክርስቲያን እንኪን የሌለኝ ሆኜ ሳለ ሰምን ፓስተር ብላ እንደምትጠራኝ ስጠይቃት እግዚአብሔር ሰፓስተርነት እንደጠራኝ እርግጠኛ እንደሆነች ያንን ምንም ነገር እንደማይቀይረው ነገረችኝ። ድብርት ውስጥ በነበርኩበት በዚያን ጊዜ ብቻዬን መሆን እፈልግ ስለነበር ከባለቤቴና ከልጄ ጋር ጊዜ ማሳለፍ እንኪን አልቻልኩም። አብዛኛውን ጊዜዬን የማሳልፈው ውጪ ወይም መኪናዬ ውስጥ በመተኛት ነበር። ጥቅም እንደሌለኝና የተሰበርኩ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር። ድብርት ውስጥ በመሆኔ ምክንያት ለልጆቼ ፍቅር ለማሳየትና ወደ እነርሱ ለመቅረብ አታገል ነበር።

አይኔ እያየ ህይወቴ ሲበላሽ የማየቴ ስቃይ ወደ ማንጫያ በመሄድ እርዳታ ማግኘት አሰብኝ ብዙ እንድወስን አደረገኝ። መንገዱ ተስፋ የሌለው ቢመስልም በውስጤ ያለ የሆነ ነገር እርዳታ እንድፈልግ ጥንካሬ ሰጠኝ። ለባለቤቴና ለልጆቼ ስል ህይወቴን እንደገና የመገንባት ጠንካራ ፍላጎት አደረብኝ። በደጉ ጊዜ ለሌሎች ፓስተሮች ሁላችንም ሰዎች እንደሆንንና ፓስተርም ወደሌሎች ሰዎች ሄዶ

እርዳታ መጠየቅ መፍራት የሌለበት ጊዜ እንደሚመጣና ፓስተሮች አብያተ ክርስቲያናትን እንዲመሩ የተጠሩ ቢሆኑም አሁንም በእግዚአብሔር ሊጠገን የሚያስፈልገው ድክመት ያለባቸው ሰዎች ናቸው እያልኩ እንግራቸው ነበር።

የአካባቢ መቀየር

ወላጅ አባቴ ደውሎ ወደ እነርሱ ሄጄ ከእነርሱ ጋር ትንሽ ጊዜ እንዳሳልፍ የጠራኝ በዚህ ጥልቅ ድብርት ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ነበር። ምንም አይነት የገቢ ምንጭ፣ ቤተክርስቲያን ወይም የፓስተርነት ስራ የሌለኝ መሆኔ በራሱ ሰብሮኝ ነበር። ለቤተሰቤም ሆነ ለራሴ ሙሉ በሙሉ የወደቅኩ እንደሆነ ተሰምቶኝ ነበር። ወዲያው ወደ ወላጆቼ ቤት ለመሄድ ሻንጣዬን ይዤ ሚስቴንና ልጆቼን ተሰናብቼ ስወጣ አምባዬን እያፈሰስኩ ነበር። ሲምፖፖ ወደሚገኘው ወላጆቼ ቤት ስንገሽ የመፈወስ ጉዞዬ አንዱ ክፍል እንደሆነ እየተሰማኝ ነበር።

ትንሽ ልጅ ሆኜ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ኃይል ወዳገኘሁበትና ወደተለማመድኩበት ቦታ መመለስ ነበረብኝ። በሊጋነት አድሜዬ ቀላል ወንጌል ወደተማርኩበት ቦታ መመለስ ነበረብኝ። ከሚስቴና ከልጆቼ ጋር አየኖርኩ ያለሁበት ቦታ ለእኔና ለቤተሰቤ አመቺ አልሆነም። በአካል ከእነርሱ ጋር ብሆንም መንፈሴ ግን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበር። ብቻዬን መሆን እፈልግ ነበር። አስፈሪ ፍጡር ወደመሆን ተለውጬ ነበር። ያ ከተማ ውድቀቴንና ስህተቶቼን የሚያስታውስኝ በመሆኑ ጥንካሬዬን መልሼ ለማግኘትና ራሴን ለመሰብሰብ አካባቢ መቀየር ነበረብኝ።

@Amharicbookstore

ወላጆቼ ከማረሚያ ቤት ከወጣሁ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኙኝ ሁለቱም በደስታና በፍቅር ተቀበሉኝ። አቅም እንዳጣ ሰው ሳይሆን አሁንም በእግዚአብሔር እንደተመረጠና እንደተጠራ ውጣት ተመለከቱኝ። እኔም ለማልቀስ ትከሻ የሚፈልግ ትንሹ ልጃቸው እንደሆንኩ ተሰማኝ። ለእኔና ለቤተሰቤ የሚያደርጉት ድጋፍ ራሴን የማይበትን መንገድ ለወጠውና ፀሎቶች ላይ በመገኘት ይፀልያልኝ ጀመር። የአባቴ ቤተክርስቲያን አባላትም ፓስተራቸው እንደሆንኩ አድርገው ይጠሩኝ ስለነበር ያ ነገር ቀስ በቀስ በራስ መተማመኔን እየመለሰልኝ መጣ። ቤተክርስቲያን ለእኔና ለቤተሰቤ የማያቋርጥ ፀሎት፣ የገንዘብና መንፈሳዊ ድጋፍ አደረጉልን። እንኖርበት በነበረበት ከተማ ከነበረው ከባድ ሁኔታ ወጥቼ ወደ ቤት በመመለስ የፓስተሩ ልጅ ነቢይ ካታ-ካታ ተብሎ ከሚጠራበት አሮጌ የአኗኗር ዘይቤ ተለውጦ ንስሀ በመግባት አሁን በአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ አባቱን እየረዳ ነው የሚል ዜና ተሰራጨ። በልጅነታችን በአንድ አካባቢ ያደግን በመሆናችን ባለቤቴ ልጅም እያሰን ሁልጊዜ ሀይወቱ የህዝብ አይን የሚስብ እንደሆነ ትቀልድብኝ ነበር። ያለፈውን አስቸጋሪ ሀይወት የሚያስታውሱኝን ግንኙነቶችና ማህበራት መቁረጥ እንዳለብኝ የወሰንኩት በዚህ ወቅት ነበር። በማረሚያ ቤት የነበረኝ ተሞክሮ አሳፋሪና ድብርትና ኪሳራ ውስጥ የከተተኝ ቢሆንም ንስሀ ገብቼ ሀይወቴን እንደ አዲስ ለመጀመር የወሰንኩት እዚያው ማረሚያ ቤት ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በመሆኑ ያ ተሞክሮ ወደ እግዚአብሔር እንድመለስ መርቶኛል። የወደፊቱ አስቸጋሪ ቢመስልም፣ እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ጸጋ የጨለማው መንግስት ሚስጥራዊ ኃይላት ከተያዝኩበት ሀይወት ስላወጣኝ ሁልጊዜ አመሰግናለሁ።

በመዳን፣ በማገገምና መመለስ ሂደቶች ውስጥ ማለፍ ነበረብኝ። እግዚአብሔር እኔን መልሶ ስለመጠገን በመጀመሪያ ሊሰብረኝና ሊከረክመኝ ያስፈልግ ነበር።

ከማዕበል በኋላ ሀይወት

መመለስ በአንድ ምሽትና ወዲያውኑ የሚከሰት ነገር አይደለም። ጨለማ ሀይወት የነበረኝ ቢሆንም በእግዚአብሔር የምወደድና የተለወጥኩ ሰው መሆኔን እየነገርኩ በየቀኑ ራሴን ማሳመን ነበረብኝ። ሳላቋርጥ መፀለይና በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብ ፕሮግራም መከተል ጀመርኩ። በየቀኑ መንፈስ ቅዱስ መሪዬ፣ ፈዋሼና መካሪዬ እንዲሆን እጠይቃለሁ። በጌታ ፊት ጊዜ ሳሳልፍ መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ያለፉ ስህተቶቼን ይገልጥልኛል። እኔም በእንደዚያ አይነት ወጥመድ ውስጥ ዳግመኛ ላለመውደቅ ለራሴ ቃል ገባሁ። ደቡብ አፍሪካ በሚገኘው አፖስቶሊክ ፌዝ ሚሽን የሙሉ ጊዜ ፓስተር ሆኜ ለማገልገል እንደገና ያመለከትኩት በዚያ ጊዜ ነበር። ነገር ግን በቀድሞ ሀይወቱ አይን እያዩኝ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ስለነበሩና ይህንን ሀያወቴን የምገነባበትን አድል ሊዘጉ እየሞከሩ ስለነበር ማመልከቻዬ ተቀባይነት ለማግኘት ብዙ ጊዜ ወስዶ ነበር። ወደዚህ ቤተክርስቲያን ለመመለስ የወሰንኩበት ምክንያት ከልጅነቴ ጀምሮ አባቴ ሲያገለግልበት የነበረ ቤተክርስቲያን ስለሆነና እውነተኛውን ወንጌል የተማርኩበት፣ የስነ መለኮት ስልጠና የወሰድኩበትና የራሴን ቤተክርስቲያን ከፍቼ የመናፍስት አምልኮ ስራ ከመክፈቴ በፊት የፓስተርነት ብቃቴን ያገኘሁበት ቤተክርስቲያን ስለነበረ ነበር።

@Amharicbookstore

የቀድሞ የመጽሀፍ ቅዱስ ኮሌጅ አስተማሪዬ ከነበረው ፓስተር ዶክተር ቲጂ ስኮሳና ጋር የተገናኘሁትም በዚህ ጊዜ ነበር። ይህ ሰውና የእርሱ ቤተክርስቲያን ለእኔና ለቤተሰቤ ያሳዩን ፍቅርና እምነት ከዚህ አለም አልነበረም። እኔና ቤተሰቤ ክክርስቶስ አካል ጋር መልሰን እንድንገናኝ ረድተውናል። ባለፈው ስህተቴ ሳይፈርዱብኝ ክንዶቻቸውን ክፍተው በደስታ ተቀብለውኛል። ቤተክርስቲያኗ ብዙ ወታደሮች የነበሩባት ስለሆነች እነርሱም ልክ እንደ ወታደር በጥንካሬ እንድቆም ድፍረት ሰጥተውኛል። የኃያሉ እግዚአብሔርን ፍቅርና ፀጋ ማየት የጀመርኩትም በዚህን ጊዜ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር። ጌታ እንደ ንስር መምጠቅ የምችልበት ቦታ ላይ ስላስቀመጠኝ ጥንካሬዬን መልሼ እንዳገኝና ለእውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እውነተኛ ፓስተር የመሆን ጥሪዬን ለመቀጠል እንድችል ስላደረገኝ ማመስገን የምችልበት በቂ ቃል የለኝም። ይህ የእገልግሎቴ አዲስ ወቅት ነበር። ከነበርኩበት የመናፍስታዊ አምልኮ ኃይሉት የዳንኩት፣ የተፈወስኩትና በብዙ ሰዎች የሚደርስብኝን መገለል መቋቋም የቻልኩት በዚህ ጊዜ ነበር።

ሀይወቴ እየተሻሻለ ሲመጣ፣ ሀሰተኛ ነቢይ ሆኜ እሰራ በነበረበት ወቅት ስላሳሳትኳቸውና ስላታለልኳቸው ንፁሀን ሀይወቶች ማሰብ ጀመርኩ። ወዲያው ፓስተር ወደሆነ የድሮ ጓደኛዬ ሄድኩና እርሱ ከአመታት በፊት ኮማሪሚያ ቤት ሲለቀቅ እንዳደረገው እኔም ሁሉንም ነገር በሬዲዮ መናገር እንደምፈልግ ነገርኩት። ከዚያ ይህ ፓስተር ናርዝ ዌስት ከሚባለው የሬዲዮ ጣቢያ ጋር አገናኝኖና በዝነኛ ዲጄያቸው ቃለ መጠይቅ ተደረገልኝ። በዚያ የአሁድ ምሽት የሬዲዮ ፕሮግራም ላይ የተደረገው ቃለ ምልልስ በአንድ ምሽት ሀይወቴን ለወጠው። በዚያ አንድ ሬዲዮ ፕሮግራም አማካይነት ብዙ ደጋፊዎች

አገኘሁ። ብዙ ድርጅቶች፣ የሬዲዮ ጣቢያዎችና አብያተ ክርስቲያናት ህዝቡን ለማንቃት ምስክርነቴን እንዳካፍልና መጽሀፍ እንድጽፍ ጠየቁኝ። ምስክርነቴን ለብዙ ሬዲዮ ጣቢያዎች ማካፈል ቻልኩ። ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በብዙዎች በሚታየው SABC ቴሌቭዥን ጣቢያ ሳይቀር ዴይሲ ቴታ በሚለው ቶክሾው ላይ ፓናሊስት ሆኜ ተጋበዝኩ። ፕሮግራሙን የተከታተሉ ብዙ አድማጮችና ተመልካቾች መጽሐፍ እንድጽፍ አበረታቱኝ።

ዴይሲ ሰን በሚባለው በሀገሪቱ ውስጥ በስፋት በሚነበብ ጋዜጣ ላይ ሳይቀር በፊት ገፅ ላይ ወጣሁ። በዚያ ጋዜጣ ላይ ሀሰተኛ ነቢያትን የመከተልን አደጋ አጋለጥኩ። በተጨማሪም ሀሰተኛ ነቢይ ሆኜ በምሰራበት ወቅት የሰራኋቸውን ነገሮች ሁሉ በመናዘዝ ቤተክርስቲያንን በይፋ ይቅርታ ጠየቅኩ። ዜናው እንደሰደድ እሳት ተሰራጨ፣ ለእኔ የመፈወስ ጉዞዬ አንድ ከፍል ስለነበር በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሳፈርኳቸው ሰዎች መሀል ስሜን ማፅዳት ፈልጌ ነበር። ሰው ሁሉ አሰባልታ የሚያወራበት ጉዳይ አሁን ስለተገለጠና የአደባባይ እውቀት ስለሆነ፣ ከዚህ በኋላ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ እኔን ለመቃወም የሚችሉበት ምንም አይነት የተደበቀ ሚስጥር አይኖርም።

የዲያብሎስን ስራዎች በምናጋልጥ ጊዜ ዲያብሎስ እኛን የሚያሳፍርበትና ተስፋ የሚያስቆርጥበትን ኃይል ያጣል። ታሪኬ በዴይሲ ሰን ጋዜጣ የፊት ገፅ ላይ በወጣበት ቀን ከምኖርበት ከተማና ሀሰተኛ ነቢይ በነበርኩበት ጊዜ ከማውቃቸው ሰዎች ብዙ የስልክ ጥሪዎች ተቀበልኩ።

@Amharicbookstore

ሀይውቱን ሰዘላለም የሰወጠው ግን አንድ ለየት ያለ የስልክ ጥሪ ነበር። የደወለልኝ አንድ በእድሜ የገፋ ፓስተር ሲሆን "በህዝብ አይናች ውስጥ ምንም ያህል ስምህን ለማፅዳት ልትሞክር ትችላለህ፣ ነገር ግን ስምህን ሊያፀዳልህ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አስታውስ። ስለዚህ ወጣቱ እባክህ ሁሉንም ነገር በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ አስቀምጥ። ይህንን ጦርነት እርሱ ይዋጋልህል። ሰዎች ባለፈው ድርጊቶችህና ስህተቶችህ ሊጠሉህና ሊያስፈራሩህ ሲሞክሩ ኃጢአታችን ሁሉ ይቅር የተባለበትን የቀራንዮ መስቀል አሳያቸው።" አለኝ። የዚያ ፓስተር ቃላት፣ ታላቅ ተሰፋና አለምን ካለፍርሀት፣ እፍረት ወይም ሀፍረት የመጋፈጥ ድፍረት ሰጡኝ።

አሁን መጋፈጥ የሚኖሩብኝ ጥቃቶች፣ ችግሮችና ተቃውሞዎች ቢኖሩም ጌታ ከእኔ ጋር መሆኑን እርግጠኛ ስለሆንኩ የእርሱ ቃላት የጥፋተኝነት አስተሳሰቤን አፀዳልኝ። በሀገራችንም ሆነ በሌሎች አፍሪካ ሀገራት የሚካሄዱ እንግዳ የሀይማኖት ትምህርቶችና ትንቢቶችን ሳነብና ስመለከት በአንድ ወቅት እኖረው የነበረውን የማታለል ህይወት ሰለሚያስታውሰኝ በሀዘን መሞላት እጀምራለሁ። ስለዚህ ክስተቱ ወደ ክተማ በመዘዋወር ሰዎችን ከብዙ አብያተ ክርስቲያናት ጀርባ ስላሉት ሚስጥራዊና የተደበቁ መናፍስታዊ ሀይላት ማስተማርና ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በቤተክርስቲን ውስጥ ንባሌው ወይም ህዝቡ ሳያውቅ እንዴት መናፍስታዊ አሰራር እንደሚጠቀሙ ለመናገር ወሰንኩ። የመናፍስታዊ አሰራር አንዱ ሚስጥር የመናፍስት አምልኮ ቤተክርስቲያን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚሸጧቸውን ዕቃዎች ብቻ በመጠቀም መናፍስቱን ምዕመናኑ ላይ ማስገባት የሚችሉ መሆኑ ነው። ይህንን ለማያውቁ አገልጋዮች ወይም ለአንድ ሰው እነዚህ ተከታዮች እየተታተሉና ውሸት

እየተሸጠላቸው መሆኑን ማሳመን ቀላል ስራ አይደለም። የሚቻለውም በእግዚአብሔር ኃይልና ፀጋ ብቻ ነው። እግዚአብሔር እኔን በእስር ቤት በሮች ውስጥ ብመቆለፍ አስገድዶ ከመናፍስታዊ አሰራር ስላወጣኝ አድለኛ ነኝ። ጌታ በጥልቀት የገባሁበትን አጋንንታዊ ስራ ለማጥፋት እጅግ በጣም ተሰፋ አስቆራጭ የሆነ ተሞክሮ በመጠቀሙ አመሰግነዋለሁ። ብዙ ሰዎች ቅዱስ ዘይት፣ ቅዱስ ውሀ፣ ቅዱስ ጨው፣ የእጅ አምባሮች፣ የመኪና ስቲከሮችና ጥቅሶች ላይ የሚሰጡ የተደበቁ ክፉ መናፍስትን ይዘው ይሀራሉ። በየቀኑም ይጠቀሙባቸዋል። ፀሎቴ ይህ መፅሀፍ በእነዚህ ክፉ ሚስጥራዊ መናፍስት ወደተያዙ ሰዎች እንዲደርስና ልክ እንደኔ እነርሱም የተሟላ መዳንና መመለስ እንዲሆንላቸው ነው።

@Amharicbookstore

ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በእምነትና ፀሎት መቀዝቀዝ ምክንያት ከጨለማው መንግስት ጋር ባለው መንፈሳዊ ጦርነት እየተሸነፈች ይመስላል። በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ልጅ ነህ ማለት ነገሮች ወዲያው ወይም በአንድ ምሽት ይለወጣሉ ማለት አይደለም። እውነተኛ ተአምራት የሚወለደው ሳያቋርጡ በመፀለያና በእግዚአብሔር መገኘት ነው። አንተ በቀን አንድ ጊዜ የምትፀልይ ከሆነና የመናፍስትና የዲያብሎስ አምላኪዎች ለጣኦቶቻቸው በቀን ሶስት ጊዜ መስዋዕት የሚያቀርቡ ከሆነ የፀሎት ህይወትህን ማስተካከል ይኖርብሀል ማለት ነው።

የምክር አገልግሎት ለማግኘት ወደኔ ለሚመጡ ሰዎች እንዴት ህይወት ያላቸው ዶሮና ፍየሎች በመስዋዕትነት አቀርብ እንደነበር አስታውሳለሁ። አብዝቼ የእንስሳት መስዋዕት ባቀረብኩ ቁጥር የበለጠ ለውጥ እመለከት ነበር። ትንቢት ከተናገርኩ በኋላ በተገልጋዮቼ ምትክ መስዋዕት አቀርብ ነበርና መስዋዕቱ እነርሱ ባይኖሩም ይሰራ ነበር። ፊውስ ከሩቅ አጠራም ነበር። ነገር ግን የመናፍስቱን አለም ህይወት ከተለማመድኩ በኋላም ሰው ሰራሽ ከሆኑ ጣያታዊ ኃይላት ይልቅ እኛ የምናገለግለው እግዚአብሔር በጣም ኃያል መሆኑን አውቅ ነበር።

ወደ መንፈሳዊው አለም ለመግባት የእግዚአብሔር ልጆች ለእግዚአብሔር የተሰጡ መሆን ያስፈልጋቸዋል። አሁን የክርስቶስን አካልና እውነተኛውን ወንጌል የማስተማሪያ ጊዜ ነው። አታላዩ ዲያብሎስ አሁድ አሁድ አስራት፣ መስዋዕትና የምክር አገልግሎት

ገንዘብ ለሀሰተኛ ነቢያትና ፓስተሮች በሚሰጡ ክርስቲያኖች ተክዶ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ መሀል ላይ በመቆም የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን አያታለለ መሆኑን እያሳየን ነው። የጨለማውን መንግስት በገዛ ንብረታችን መደገፍ አይገባም።

አስታውሳለሁ ብዙ ጊዜ 'አሜ' የሚባለውን የአሰማት መድሀኒት ምላሴ ላይ አሸት አድርጌ በመሄድ ሰዎች ገንዘብ እንዲሰጡ በምናገርበት ጊዜ ብዙዎች እንዲት ለመስጠት እንደሚጋፉ፣ ብዙዎች የማራምደውን የጨለማ መንግስት ገንዘባቸውን አንጠፍጥፈው እስኪሰጡ ድረስ ሲደግፉ ነበር። አሁንም በክፉ መናፍስት ቁጥጥር ስር የሆኑ አብያተ ክርስትያናት እንዲት ምዕመናኑን እንደሚዘርፉት በግልፅ የሚታይ ነው። እነሱ የተገደላቀቀ ኑሮ ይኖራሉ፣ ምዕመናኑ ግን የሚሌሱ የሚቀምሱት አጥተው ከእግዚአብሔር ጋር ይጣላሉ። ዲያቢሎስ እየሰራ ያለው ይሄንን ነው።

ከነዚህ መናፍስታዊ ኃይላት አንደዳነ ሰው፣ ለፓስተሮችና መንፈሳዊ መሪዎች ሰዎችን ለግልና ለገንዘብ ትርፍ ሳይሆን ሰእውነት ማገልገል እንደሚያስፈልገን ልነግራችሁ እወዳለሁ። እግዚአብሔር የተሰያዩ ስጦታዎችንና ጥሪዎችን የሰጠን መሆኑ እውነት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በውስጥህ ያስቀመጠውን ለመግለጥ፣ ህይወትህን ለመጠበቅና አገልግሎትህ ላይ ለመቆየት ሌሎች ኃይላትን ላትጠቀም ስጦታህ ብቻውን በቂ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ትእዛዝ ሰጥቶናል። ያም በጎቹን እንድንመግብ ነው። ስለዚህ እነዚህን መናፍስታዊ አሰራሮች ትተን የጠራንን ጌታ እናገልግል። የሚሰሩራዊ

@Amharicbookstore

ሀይላትን ፕሮፖጋንዳና ማታለል በማቆም በንፁህ የእግዚአብሔር ወንጌል ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን።

በነሰም ዙሪያ ያሉ የቤተክርስቲያን ማፊያ የሆኑ ሀሰተኛ ነቢያትንና መንፈሳዊ መሪዎች ፍላጎታቸውም ንሁሀንና ያልጠረጠሩ ተጠቂዎች ለፍተው ያገኙትን ገንዘብ ጥርግ አድርገው በመውሰድ የእነዚያን ሰዎች ህይወትና ቤተሰቦቻቸውን ከሚያሰቃዩ መናፍስቶችና አጋንንቶች ጋር እንዲኖሩ ማድረግ ነው። እነዚህን የማፊያ ቡድኖች ለይተን እንድናውቅ ነው ይሄንን መፅሐፍ መፃፌ። የመናፍስት አገልጋይ አብያተ ክርስትያናት በአፍሪካ በሁሉም ቦታ አሉ። ልምምዶቻቸው ይለያይ እንጂ ሁሉም ከጥልቁ መንፈስ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ትክክለኛ የሆኑትን፣ ወንጌልን የማይሸቅጡትን፣ ክርስቶስ ኢየሱስን የሚያከብሩትንና ለጥሪያቸው ታማኝ የሆኑትን መለየት አለብን።

ተፈፀመ

@Amharicbookstore